# የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት

# የሶስት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ሪፖርት

# (2013-2015)

የአማራ ክልል ፕላንና ልማት ቢሮ

ሰኔ 2016 ዓ/ም

ባህር ዳር

# ማዉጫ


ክፍል አንድ፡-የ10 ዓመቱ መሪ ዕቅድ መነሻዎች፣የዕቅዱ የትኩረት አቅጣጫዎች፣የልማት ዕቅድ የትኩረት መስኮች ........ - 1 -

1.1. የ10 ዓመቱ መሪ ዕቅድ መነሻዎች ........ - 1 -

1.1.1. አገራዊ የረጅም ጊዜ ርዕይ ........ - 1 -

1.1.2. አገራዊ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ማዕቀፎች ........ - 1 -

1.1.3. የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈፃፀም ........ - 2 -

1.1.4. የሕዝባችን አዳዲስ ፍላጎቶች እና ጥያቄዎች ........ - 2 -

1.1.5. የፌደራል የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ ........ - 2 -

1.1.6. የድህረ 2015 ዘላቂ የልማት ግቦች እና አጀንዳ አፍሪካ 2063 ........ - 3 -

1.1.7. ክልላዊ ርዕይ ........ - 3 -

1.2. የልማት መሪ ዕቅዱ የትኩረት አቅጣጫዎች ........ - 3 -

1.2.1. ጥራት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ማረጋገጥ ........ - 3 -

1.2.2. የማስፈፀምና የመፈፀም አቅም በመገንባት፣ የህዝቡንተሳትፎ በማጎልበት ፍትህንና መልካም አስተዳደርን ማስፈን ........ - 4 -

1.3. የ10 ዓመቱ መሪ የልማት ዕቅድ የትኩረት መስኮች ........ - 5 -

1.3.1.ብዝሀ ዘርፍ የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጮች ልማት ላይ ማተኮር ........ - 5 -

1.3.2. የዘመናዊ ግብርና ልማት ........ - 6 -

1.3.3. የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ........ - 6 -

1.3.4. የማዕድን ሀብት ልማት ........ - 8 -

1.3.5. የቱሪዝም ልማት ........ - 9 -

1.3.6. የኢንፎርሜሽን፣ ኮሚዩኒኬሽን እና ቴክኖሎጂ ልማት ........ - 10 -

1.3.7. ዘላቂ የከተማ ልማት ........ - 10 -

1.3.8. መሠረተ ልማት ........ - 11 -

1.3.9. የሰው ኃብት ልማት እና የሥነ-ህዝብ ትሩፋት ........ - 12 -

1.3.10. ዘላቂ የልማት ፋይናንስ ማረጋገጥ ........ - 14 -

1.3.11. ተቋማዊ አቅምመገንባት ........ - 14 -

ክፍል ሁለት፡- የሶስት አመቱ እቅድ አፈጻጸም ዓላማ፣ አስፈላጊነትና የግምገማው ሂደት.....- 15 -
2.1. የግምገማው ዓላማ ..... - 15 -
2.2. የእቅድ አፈጻጸም ግምገማው አስፈላጊነት ..... - 15 -
2.3. በግምገማው ሂደት የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ..... - 16 -
ክፍል ሶስት፡- የክልሉ የሶስት ዓመታት (2013-2015) የልማትና መልካም አስተዳደር አፈጻጸም ትንተና ..... - 17 -
3.1. የኢኮኖሚ ልማት ዘርፍ አፈጻጸም ..... - 17 -
3.1.1. የግብርና ልማት ዘርፍ አፈጻጸም ..... - 18 -
3.1.2. ውሃና ኢነርጅ ልማት አፈጻጸም ..... - 26 -
3.1.3. የመንገድ ዕቅድ አፈጻጸም ..... - 28 -
3.1. 4. የማዕድን ሀብት ልማት አፈፃፀም ..... - 31 -
3.1.5.መስኖና ቆላማ አካባቢዎች ተግባራት አፈጻጸም ..... - 39 -
3.1.6. የአካባቢና ደን ጥበቃ ዘርፍ ልማት አፈጻጸም ..... - 43 -
3.1.7. ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ልማት አፈጻጸም ..... - 50 -
3.2. የከተማ ዘርፍ አፈጻጸም ..... - 55 -
3.2.1. ከተማና መሰረተ-ልማት አፈጻጸም ..... - 55 -
3.2.2. የመሬት ዘርፍ ልማት አፈጻጸም ..... - 62 -
3.2.3. ባህልና ቱሪዝም ልማት አፈጻጸም ..... - 67 -
3.2.4. የገቢዎች ስራዎች አፈጻጸም ..... - 71 -
3.2.5. ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ልማት አፈጻጸም ..... - 72 -
3.2.6. የንግድ እና ገቢያ ልማት ዘርፍ ዕቅድ አፈፃፀም ..... - 82 -
3.2.7. ሥራና ሥልጠና ልማት አፈጻጸም ..... - 87 -
3.3. የማህበራዊ ልማት ዘርፍ አፈጻጸም ..... - 96 -
3.3.1. የትምህርት ዘርፍ አፈጻጸም ..... - 96 -
3.3.2. የጤና ልማት ዘርፍ አፈጻጸም ..... 131
3.3.3. የሴቶች፣ህጻናት እና ማህበራዊ ልማት አፈጻጸም ..... 141
3.3.4. ወጣቶና ስፖርት ልማት አፈጻጸም ..... 146
3.3.5. የሲቪል ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ተግባራት አፈጻጸም ..... 154
3.3.6. ትራንስፖርትና ሎጂሰቲክ ልማት አፈጻጸም ..... 156
3.4. የፍትህና አስተዳደር ዘርፍ አፈጻጸም ..... 161

3.4.1.የፍትህ ዘርፍ አፈጻጸም ....... 161
3.4.2. የሥነ-ምግባር እና ጸረ-ሙስና አፈጻጸም ....... 166
3.5. የመንግስት ኮሙኒኬሽን ዘርፍ አፈጻጸም ....... 168
3.6. ዘላቂ የልማት ፋይናንስ ማረጋገጥ ....... 174
ክፍል አራት፡- የእቅድ አፈጻጸሙ ጠንካራ ጎኖችና ክፍተቶች ....... 174
4.1. የእቅድ አፈጻጸሙ ጠንካራ ጎኖችና እና ክፍተቶች ማጠቃለያ ....... 174
ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎች ....... 178

## List of graph

ግራፍ-1፡የሶስት ተከታታይ ምርት ዘመን የለማ መሬት፤የተገኘ ምርት እና ምርታማነት....- 19 -
ግራፍ-2፡ የ3 ዓመት የመደበኛ ኮምፖስት ዝግጅትና አጠቃቀም ............................- 20 -
ግራፍ-3፡ የ3 ጊዜ ምርት ዘመን ሰ3ብልን በመስመር መዝራት አፈጻጸም .................- 21 -
ግራፍ-4፡በመደበኛ በጀት የክልል ጠጠር መንገድ ግንባታ አፈጻጸም ........................- 29 -
ግራፍ-5፡ክረምት ከበጋ የሚያስተናግዱ መንገዶች ዕቅድ አፈጻጸም...........................- 29 -
ግራፍ-6፡ከማዕድን ዘርፍ የተገኘ ገቢ.........................................................- 37 -
ግራፍ-7፡ የልማት ፕሮጀክቶች የይሁንታ ፈቃድና ዕድሳት .......................................- 45 -
ግራፍ-8፡-የከተሞችን ፕላን ዝግጅት አፈጻጸም...........................................- 57 -
ግራፍ-9፡-የመኖሪያ ቤት ግንባታ አፈጻጸም..................................................- 60 -
ግራፍ-10፡-የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ አፈጻጸም ...........................................- 63 -
ግራፍ-11፡-የቀበሌ ማእከላት አዲስ ፕላን ማዘጋጀት.........................................- 66 -
ግራፍ-12፡ ጥገና የተደረገላቸው ተቋማት......................................................- 68 -
ግራፍ-13 የገቢ አሰባሰብ ተግባራት...........................................................- 71 -
ግራፍ-14፡ በክልሉ ዉስጥ የሚገኙ ነባር አምራች ኢንዱስትሪዎች ያሉበት ሁኔታ.....- 74 -
ግራፍ-15፡ በኢንዱስትሪ መንደር ዉስጥ የገቡ ባለሀብቶች ያሉበት ሁኔታ................- 77 -
ግራፍ-16፡ የንግድ ፈቃድ ዕድሳትና ፈቃድ መስጠት.........................................- 83 -
ግራፍ-17፡- ከእንስሳት ሀብት የተገኘ የውጭ ምንዛሬ .......................................- 85 -
ግራፍ-18፡የስራ እድል ፈጠራ ስራ በዋና ዋና ዘርፎች የከተማ ና ገጠር ንፅፅር .........- 88 -
ግራፍ-19- በየደረጃው የተማሪዎች ጥቅል ተሳትፎ..........................................- 102 -
ግራፍ-20.በየደረጃው የተማሪዎች ንጥር ተሳትፎ...................................... …………- 103 -
ግራፍ-21-የሴት ርዕሰ መምህራን ድርሻ .......................................................111
ግራፍ-26- በ8ኛና 12ኛ ክፍል ፈተና ከ50› ያመጡ ተማሪዎች በመቶኛ .......................120
ግራፍ-23-ደረጃ 3 የደረሱ ትምህርት ቤቶች ...................................................128
ግራፍ-24፡- የቅድመ ወሊድ 4 ጊዜ ክትትል ያደረጉ እናቶች.......................................133
ግራፍ-25፡-በሰለጠነ ባለሙያ የወሊድ አገልግሎት ያገኙ እናቶች ..................................134
ግራፍ-26፡- ሜዳ ላይ ከመጸዳዳት ነጻ የሆነ ቀበሌ ሽፋን ..........................................139
ግራፍ-27፡- ማህበረብ አቀፍ የጤና መድህን አባል ማፍራት ስራ አፈጻጸም ...................140

## List of table

ሠንጠረዥ-1፡ የሥነ-ምድር ጥናት ዕቅድ መረጃ ........ - 33 -
ሠንጠረዥ-2፡ የማዕድን ፍለጋ፣ ክምችትና የስራ ዕድል ፈጠራ መረጃ ........ - 34 -
ሠንጠረዥ-3፡- ወደ ግንባታ የገቡ የመስኖ ፕሮጀክቶች ዕቅድ ........ - 41 -
ሠንጠረዥ-4፡- በለሙ አፕልኬሽኖች ተጠቃሚ የሆኑ የመንግስት ተቋማት ........ - 53 -
ሰንጠረዥ-5- የመሰረተ ልማት አፈጻጸም ........ Error! Bookmark not defined.
ሰንጠረዥ-6፡- የይዞታ ማረገገጫ ደብተርን የብድር ዋስትና ማድረግ ........ - 63 -
ሰንጠረዥ-7 ፡-የመሬት አጠቃቀም እቅድ ........ - 65 -
ሠንጠረ--8፡ ለባለሀብቶች የተሠጠ የኢንቨስትመት ፈቃድ ........ - 72 -
ሠንጠ-ዥ-9፡ የኢንዱስትሪ ክላስተር አደረጃጀትን ማጠናከር ........ - 75 -
ሠንጠ-ዥ-10፡ የአምራች ኢንዱስትሪዎች የደረጃ ሽግግር ማድረግ ........ - 78 -
ሠንጠ-ዥ-11፡ የተኪ ምርት መጠንና የዳነ ዉጭ ምንዛሬ ........ - 80 -
ሠንጠ-ዥ-12፡ አዳዲስ ኢንዱስትሪዎች ማቋቋም እና ወደ ምርት ማስገባት ........ - 81 -
ሠንጠረ-13፡ የከግብርና አስገዳጅ ምርቶች የተገኘ የውጭ ምንዛሬ ገቢ ........ - 84 -
ሠንጠ-ዥ-14 በሦስት ዓመት ዉስጥ የተሠራጨ እና የተመለሰ የብድር መጠን ........ - 93 -
ሠንጠ-ዥ-15:በየደረጃው የተማሪዎች ጾታዊ ምጥጥን ........ 110
ሠንጠ-ዥ-16 በየደረጃው የተማሪዎች ማቋረጥ ምጣኔ ........ 113
ሰንጠ-ዥ-17. የስፖርት ሃብትን ማሳደግ ........ 149
ሰንጠረ-18. የስፖርት ማዘዉተሪያ ስፍራዎችና ስልጠና ማዕከላት ማስፋፋትና ማሳደግ . 150
ሰንጠ-ዥ-19. የታዳጊና የባለሙያ ስልጠና በመስጠት ዉጤታማ ስፖርተኛ ማፍራት .... 152
ሰንጠ-ዥ-20፡ የስፖርታዊ ዉድድር መድረኮችን በማሳደግ የህ/ቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ........ 153
ሠንጠረዥ-21፡ የትራንስፖርት መንኸሪያዎችን ማሳደግ ........ 157
ሠንጠረዥ-22፡- የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ተደራሽነትን ማሳደግ ........ 159

## መግቢያ

የሶስት አመታት እቅድ አፈጻጸም ግምገማ ሪፖርት ዓላማ በ10 ዓመቱ ዕቅድ የተቀመጡ የትኩረት መስኮችን፣መሠረታዊ አቅጣጫዎችንና ግቦችን አፈፃፀም የተሟሉና ትክክለኛ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ በዕቅዱ ማጠናቀቂያ ዓመት ይደረስባቸዋል ተብሎ ከተቀመጡ ኢላማዎች አንፃር በሶስት ዓመታት የተመዘገቡ ውጤቶችን እና ያልተሳኩትን ማስቀመጥ፣ በአፈፃፀም ሂደት ያጋጠሙ ዋና ዋና ተግዳሮቶችን በግልፅ በመለየት ለቀጣይ ጊዜ ትምህርት ለመውሰድ፣ ከዚህም በመነሳት ለቀጣይ የፖሊሲ ውሳኔዎች ግብዓት የሚሆኑ የፖሊሲ ምክረ-ሀሳቦችን በግልፅ ያስቀመጠ የአፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት በማዘጋጀት ለክልሉ መንግስት ማቅረብ ነው፡፡

ይህ የሶስት ዓመታት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት የ10 ዓመቱ ዕቅድ ዋና ሰነድና የፖሊሲ ማትሪክስ፣የፌደራል መንግስት የሶስት ዓመታት እቅድ አፈጻጸም ግምገማ ሪፖርት፣ ከክልል መንግስት አስፈፃሚ አካላት ለክልሉ ፕላንና ልማት ቢሮ የቀረቡ የዘርፍ ዕቅድ ዓመታዊ የአፈፃፀም መረጃዎችን መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ ነው፡፡ሆኖም የአፈፃፀም ሪፖርቱ በመስክ መረጃዎች ያልተደገፈና በተለያዩ ደረጃዎች ባለድርሻ አካላት ያልተወያዩበትና አስተያየቶቻቸው ያልተካተቱበት በመሆኑ ውስንነቶች እንደሚኖሩት መገመት ይቻላል ፡፡

የሪፖርቱ በአራት ክፍሎች የተከፋፈለ ሆኖ የመጀመሪያው ክፍል የ10 ዓመቱ እቅድ መነሻዎች፣የትኩረት መስኮች፣ዓላማዎች እና መሰረታዊ አቅጣዎች የሚተነተኑበት ክፍል ነው፡፡

የሁለተኛው ክፍል የሶስት አመቱ የእቅድ አፈጻጸም ግምገማ ዓላማዎች፣አስፈላጊነትና የአፈጻጸም ግምገማው የተካሄደበት ሁኔታን የሚቀመጥበት ክፍል ነው፡፡ ሶስተኛው ክፍል ደግሞ የዘርፎች የልማት እና መልካም አስተዳደር ዕቅድ አፈፃፀም ትንተና በማዕቀፍ የተተነተነበት ክፍል ነው፣ የመጨረሻው ክፍል የዋና ዋና ውጤቶች ማጠቃለያ፣ ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎች፣ ተሞክሮዎች እና በቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ቀርበዋል፡፡

# ክፍል አንድ፡-የ10 ዓመቱ መሪ ዕቅድ መነሻዎች፣የዕቅዱ የትኩረት አቅጣጫዎች፣የልማት ዕቅድ የትኩረት መስኮች

## 1.1. የ10 ዓመቱ መሪ ዕቅድ መነሻዎች

የ10 ዓመቱን መሪ የዕቅድ ዝግጅት ዋና ዋና መነሻዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 1.1.1. አገራዊ የረጅም ጊዜ ርዕይ

በኢኮኖሚው መስክ በ2017 በጀት ዓመት ኢትዮጵያን የመካከለኛ ገቢ ደረጃ ካላቸው አገሮች ተርታ የማሠለፉ ርእይ ተቀርጾ ሰፊ መግባባት ከተደረሰበት በኋላ ለተግባራዊነቱ ርብርብ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ ይህ የመካከለኛ ገቢ የመድረስ ርዕይ የበለፀገ ህብረተሰብ የመገንባት የረጅም ጊዜ ርዕይ መንደርደሪያ ተደርጐ የሚታይ ነው፡፡ ለዚህ ርዕይ መሳካት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተነድፎ ሲተገበር የቆየ ሲሆን በተለይ የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈጻጸም በርካታ ተግዳሮቶች ገጥመውት ነበር፡፡ በዕቅዱ መገባደጃ ዘመን ከአለፉት መልካም ተሞክሮዎችና ክፍተቶች ትምህርት በመውሰድ አገራችንን እና ክልላችንን ወደ ተሻለ ብልፅግና የሚያሸጋግር አዲስ ርዕይ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በአገር ደረጃ ኢትዮጵያን አፍሪካዊት የብልፅግና ተምሳሌት የማድረግ ርዕይ ተነድፎ የቀጣይ 10 ዓመት አገራዊ መሪ ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡ ስለሆነም የአገራችን የረጅም ጊዜ ርዕይን ለ10 ዓመቱ መሪ ዕቅድ ዝግጅት በመነሻነት መውሰድ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ይህንን አገራዊ ርዕይ ዕውን በማድረግ ሂደት የክልሉን ነባራዊ ሁኔታ መሠረት ያደረገ በቀጣይ 10 ዓመታት ተግባራዊ የሚሆን ዕቅድ ማዘጋጀት ተገቢ ይሆናል፡፡ ስለዚህም በቀጣዩ 10 ዓመት የዕቅድ ዘመን ባለው ጊዜ ውስጥ የሚከናወኑ የልማት ተግባራት እንደ አገር የተቀመጠውን ርዕይ ማሳካት የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይጠይቃል፡፡

### 1.1.2. አገራዊ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ማዕቀፎች

የመደመር ዕሳቤ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ማዕቀፎች ረጅም ዘመናትን ተሻጋሪ የመሆን ባህሪ ያላቸው ቢሆንም ወደ ተግባር የሚመነዘሩት በየዓመቱ እና በየአምስት ዓመቱ በሚነደፉ መርሃ ግብሮች እና ይህን ተከትሎ በሚዘጋጁ ዕቅዶች አማካይነት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ የቀጣዩ 10 ዓመታት፣ አምስት ዓመታት እና የአንድ ዓመት ዕቅድ ሲዘጋጅም የመሠረታዊ

አቅጣጫዎች እና በእነዚህ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በመመራት የመጣውን ለውጥ ለዕቅድ ዝግጅቱ መነሻ ማድረግ የማይታለፍ ጉዳይ ነው፡፡

ስለሆነም ፖሊሲዎቹንና ስትራቴጂዎቹን ለዕቅድ ዝግጅቱ መነሻ አድርጐ መውሰድ በአንድ በኩል በፖሊሲዎቹ አማካይነት የመጣውን ለውጥ በአግባቡ ለመመዘንም ሆነ ከዚሁ ጋር አያይዞ ፖሊሲዎቹንና ስትራቴጂዎቹን በጥልቀት ለመገንዘብ የሚያግዝ ይሆናል፡፡

### 1.1.3. የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈፃፀም

የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ሲዘጋጅ መሠረታዊ መነሻዎች ተቀምጠው የነበሩ ግቦችና ግቦቹን ለማሳካት በተደረገው ርብርብ የተገኙ ውጤቶች፣ ዕቅዱን በመተግበር ሂደት የነበሩ ጥንካሬዎችና ድክመቶች በተለይም ለቀጣዩ መርሃ ግብር ዕቅድ ዝግጅት ካላቸው ፋይዳ አንፃር ታይቶ በዝርዝር መገምገምና ውጤቱን ለቀጣይ ዕቅድ ዝግጅት በመነሻነት መጠቀም የግድ ይላል፡፡ ስለሆነም የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈፃፀም አጠቃላይ ግምገማ በማካሄድ በግምገማው ላይ ከሁሉም የሚመለከታቸው ወገኖች ጋር መግባባት መፍጠር፣ ለመጪው ዘመን ዕቅድ ዝግጅት ወሣኝ መነሻ ተደርጎ ተወስዷል፡፡ በአጠቃላይ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የዕቅድ ትግበራ ዘመን በዘርፍ እና በንዑስ ዘርፍ የታዩ ጉልህ ተሞክሮዎችና ክፍተቶች ለ10 ዓመቱ ዕቅድ ዝግጅትም እንደ መነሻ ተወስደዋል፡፡

### 1.1.4. የሕዝባችን አዳዲስ ፍላጐቶች እና ጥያቄዎች

የክልላችን ህዝብ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ እና በመልካም አስተዳደር ዘርፍ በየጊዜው አዳዲስ ፍላጎቶችና ጥያቄዎችን ያነሳል፡፡ በመሆኑም የቀጣዩ የ10 ዓመት መሪ ዕቅድ ዝግጅት እነዚህን አዳዲስ የሕዝብ ፍላጐቶች እና ጥያቄዎችን ለመመለስና ሕዝብን በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ ለማድረግ በመነሻነት መውሰድ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በዚህ ረገድ እያንዳንዱ ሴክተር ከዘርፉ አንፃር በቀጣይ የመርሃ ግብር ዓመታት የህዝቡን ተሳትፎ ባረጋገጠ መንገድ በዕቅድ ሊመለሱ የሚገቡ የልማትና መልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን ከወዲሁ መለየት እና በዕቅድ መመለስ እንዲቻል ተገቢው ትኩረት መስጠት ይኖርበታል፡፡

### 1.1.5. የፌደራል የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ

በአገር ደረጃ የተቀመጠውን የረጅም ጊዜ ርዕይን ለማሳካት ከፌደራል እስከ ክልል ባሉ የሴክተር አደረጃጀቶች የተናበበ ዕቅድ ማዘጋጀት ይጠይቃል፡፡ ስለሆነም የሴክተሮችን አገራዊ ዕቅድ

ከክልል ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር በመቃኘት የመነሻ ዕቅድ ማድረግ ይገባል፡፡ በዚህ ደረጃ ያልተናበበ ዕቅድ ማዘጋጀት የተቀመጡ አገራዊ አጃንዳዎችን ማሳካት ስለማያስችል በዝግጅቱ ሂደት ይህንን ሁኔታ ከግምት ውስጥ ማስገባት ተገቢ ይሆናል፡፡

### 1.1.6. የድህረ 2015 ዘላቂ የልማት ግቦች እና አጀንዳ አፍሪካ 2063

እ.ኤ.አ. ከ2013-2063 ለ50 ዓመታት የሚዘልቅና የአህጉሪቱ መሪዎችና አገራት የተስማሙበት አጀንዳ 2063 ተቀርጾ እየተተገበረ ይገኛል፡፡ በአጀንዳው ከተቀመጡ አቅጣጫዎች መካከል በአህጉሪቱ መልካም አስተደደር፣ ዴሞክራሲ፣ የሰብዓዊ መብት መከበር፣ ፍትህና የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ፣ ጠንካራ ባህል እና የጋራ ዕሴትን መገንባት፣ በህዝብ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ በተለይም ሴቶችንና ወጣቶችን ያሳተፈና በማደግ ላይ ያሉ ህጻናትን ፍላጎት ታሳቢ ያደረገ ልማትን ዕውን ማድረግ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ይህን በዕቅድ አካቶ መተግበር አስፈላጊ በመሆኑ እንደመነሻ ተወስዷል፡፡

### 1.1.7. ክልላዊ ርዕይ

**የክልሉ ርዕይ፡-** ክልሉ ከነበረበት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ሁኔታ እና የመልማት አቅም እንዲሁም ወደፊት ሊደርስበት ከሚገባው የዕድገት ደረጃና በአገር ግንባታ ሊኖረው ከሚገባው ሚና አንፃር በመገምገም "ሠላምና አንድነቱ የተጠበቀ፣ የህዝብ ተጠቃሚነትና አካታችነት ባረጋገጠ መልኩ ጠንካራና የዳበረ ኢኮኖሚ የገነባ፣ ድህነትን ትርጉም ባለው ሁኔታ የቀነሰ፣ ከአቻ ክልሎች ጋር በጠንካራ ትብብር፣ በመደጋገፍና በወንድማማችነት መንፈስ የሚኖር እንዲሁም ለአገራዊ አንድነትና ብልፅግና በማበርከት ረገድ ወሳኝ ሚና ያለው ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ላይ የደረሰ ክልል መፍጠር" የሚል ርዕይ ተቀምጧል፡፡

## 1.2. የልማት መሪ ዕቅዱ የትኩረት አቅጣጫዎች

### 1.2.1. ጥራት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ማረጋገጥ

በክልሉ ከፍተኛ የሆነ የኑሮ ውድነት እና የሥራ አጥነት ችግሮች ይስተዋላሉ፡፡ ከዚህም በላይ የአምራች ዘርፎች በተሟላ መልኩ በሙሉ አቅም ተግባሮቻቸውን እንዳይፈፅሙ የውጭ ምንዛሪ እና የብድር አቅርቦት ማነቆ ሆኖ ይገኛል፡፡ ለዚህም መሠረታዊ ችግር የሆነው የምርታማነት

ችግር እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም ምርታማነትን ማረጋገጥ በመሪ ዕቅዱ ወሳኝ ጉዳይ ተደርጎ ተወስዷል፡፡ ለዚህም አቅርቦትን ወደሚያሳድጉ አምራች ዘርፎች በመሸጋገር በትኩረት ይሠራል፡፡ የኢኮኖሚ ዕድገት ጥራቱ በፍትሐዊነቱ /የሀብት ክፍፍል/፣ በቀጣይነቱ፣ በምርታማነቱ፣ በአጠቃላይ በመዋቅራዊ ለውጥ አረጋጋጭነቱ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሠራ ይሆናል፡፡ በክልሉ በቀጣይ የሚመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል በማሳተፍ ፍትሐዊ ተጠቃሚነትንና ደህንነታቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ የኢኮኖሚ ዕድገቱ አቅርቦትን የሚያበረታታ እንዲሆን ይሠራል፡፡ በዚህም የዋጋ ንረትንና ሥራ አጥነትን የሚቀንስ፣ የክልሉን ህብረተሰብ የኑሮ ደረጃ በተጨባጭ እንዲሻሻል በማድረግ ድህነትን በሁሉም መገለጫ ለመቀነስ በትኩረት ይሠራል፡፡ ለዘመናዊ ግብርና፣ አምራች ኢንዱስትሪ፣ ቱሪዝም፣ ማዕድንና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘርፎች ትኩረት ይሰጣል፡፡ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት ለዕድገት ምንጭ ዘርፎች ትኩረት በመስጠት የሚሠራ ይሆናል፡፡

ምርታማነትን በማሳደግ ላይ ያተኮሩ አምራች ዘርፎችን ከማስፋፋትና ከማሳደግ አኳያ የዕድገታችን ፍጥነት የሚለካው በማምረት አቅማችን ሲሆን ብዙ ማምረትና በማያቋርጥ ሁኔታ ሀብት መፍጠር ከቻልን ዕድገታችን የተፋጠነ ይሆናል፡፡ የክልላችንን ዋና ዋና አምራች ዘርፎችን ወስደን ብንመለከት የማምረት አቅማችን ገና ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለ ነው፡፡ በግብርናው ዘርፍ የሰብል ምርታማነትን መድረስ ይገባው ከነበረው የምርታማነት ድንበር የማድረስ ሥራ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡ በተለይም ለኤክስፖርት የሚሆኑ የሰብልና የጥራጥሬ ምርታማነትን ለማሳደግ ይሠራል፡፡ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማትን፣ የአበባ ልማትን፣ የመካናይዝድ እርሻን እንዲሁም የመስኖ ልማትን ለማዘመን ትኩረት ይሠጣል፡፡ የእንስሳትን ምርታማነት የሚያሳድጉ የመኖ ልማት፣ የዝርያ ማሻሻል እና የጤና ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡ በግብርናው ዘርፍ የግል ኢንቨስትመንትን የማሳደግ ሥራ የትኩረት አቅጣጫ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

### 1.2.2. የማስፈፀምና የመፈፀም አቅም በመገንባት፣ የህዝቡንተሳትፎ በማጐልበት ፍትህንና መልካም አስተዳደርን ማስፈን

የአንድን መንግስት ውጤታማነት ከሚወስኑ ጉዳዮች መካከል አንዱ ተልዕኮውን በአግባቡ የሚፈፅም ተቋም የመኖር ወይም ያለመኖር ጉዳይ ነው፡፡ ውጤታማ ተቋም እንፍጠር ሲባል የመጀመሪያው ጉዳይ ለተቋማቱ ብቁ መሪ መፍጠር ነው፡፡ ብቁ መሪ ያለው ተቋም ውጤታማነቱ ከፍተኛ በመሆኑ በክልሉ ተቋም የመገንባት ጉዳይ ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ

ተደርጎ ተወስዷል፡፡ ሌላው ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ለማምጣትና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን በሁሉም ደረጃ የሚገኘውን የማስፈፀም አቅምን ማሳደግ ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ሲሆን በክልሉ የማስፈፀም አቅም በዕውቀት፣ በክህሎትና በአመለካከት የበቃ የሰው ኃይል እንዲፈጠር ማድረግ፣ በዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን የሚሰጡ አገልግሎቶች ደረጃቸውን የጠበቁ፣ ስታንዳርድ የወጣላቸው እና ለአካባቢው ነዋሪ ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ ትኩረት የሚሰጣቸው ነጥቦች ናቸው፡፡ ለውጡ የአገልግሎት ቅልጥፍናን፣ የሥራ ውጤታማነትን፣ ተጠያቂነትንና ግልፅኘነትን ባጣመረ አኳኋን እንዲፈፀም ለማድረግ ይሠራል፡፡ ከዚህም አኳያ በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ የተሠማራውን የሰው ኃይል ለማብቃት ልዩ ትኩረት ይሠጣል፡፡ የህግ የበላይነትን ለማስፈን የህግ አስከባሪ ተቋማትን በአመለካከት፣ በቁሳቁስና በሠለጠነ የሰው ኃይል የማጠናከርና የፍትህ አስተዳደር ሥርዓቱን የፍትህ አገልግሎት ቅልጥፍናን ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ ማጠናከር ተገቢ ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ የመንግስት ጉድለትን የሚሞላ ሥርዓት መዘርጋት፣ኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገትን ሊያረጋግጡ የሚችሉ ስትራቴጂዎች፣ የህግ ማዕቀፎች እንዲዘጋጁ ማድረግና ዘላቂነት ያለው የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት የሚሉት በትኩረት የሚሠሩ ይሆናል፡፡

## 1.3. የ10 ዓመቱ መሪ የልማት ዕቅድ የትኩረት መስኮች

ለክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገት ኢኮኖሚያዊ መዋቅራዊ ሽግግር መረጋገጥ እንዲሁም ተወዳዳሪ ኢኮኖሚ ከመገንባት አንፃር ያላቸውን የጎላ ድርሻ መሠረት በማድረግ በአሥር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ልዩ ትኩረት የሚደረግባቸው መስኮች ተለይተው እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 1.3.1.ብዝሀ ዘርፍ የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጮች ልማት ላይ ማተኮር

እስከ አሁን ከነበረው በተለየ መልኩ በአንድ ዘርፍ እና የዕድገት ምንጭ ከማተኮር ይልቅ ወደ ብዝሀ ዘርፍ እና ብዝሀ የገቢና የዕድገት ምንጭ ላይ ማተኮር የሚፈለገውን የኢኮኖሚ ዕድገትና መዋቅራዊ ሽግግር ከማምጣት አንፃር እንደ ወሳኝ ጉዳይ ታይቷል፡፡ እነዚህም ግብርናውን ማዘመን፣ ለአምራች ኢንዱስትሪው ትኩረት ሰጥቶ መሥራት፣ ማዕድን፣ ቱሪዝም እና የከተማን ዕድገት መሠረት ያደረገ የአይሲቲ (ICT) ዘርፍ እንደ ተጨማሪ የዕድገት እና የሥራ ዕድል ምንጮች ተደርገው ተለይተዋል፡፡

### 1.3.2. የዘመናዊ ግብርና ልማት

የግብርና ዘርፍ በክልሉ በአብዛኛው በአነስተኛ አርሶ አደሮች የሚካሄድ ሲሆንከክልሉ ህዝብ ከ75 በመቶ በላይ የሚገመተው መተዳደሪያው የሆነና ከክልሉ ዓመታዊ ጠቅላላ ምርት ውስጥ 53 በመቶ ድርሻ ያለው ሲሆን ዘርፉ በዋናነት ከፍተኛ ድርሻው በሰብል ልማት የተያዘ ሲሆን ምርታማነቱን ሲታይ 24.1 ኩንታል በሄክታር ሲሆን ይህም ዝቅተኛ በሚባል ደረጃ ላይ የሚገኝ በመሆኑ የአርሶ አደሩን ገቢ በማሳደግ ረገድ እና የምግብ ዋስትናን በክልሉ ለማረጋገጥ የነበረው ፋይዳ እንዲሁም ለክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገት እያበረከተ ያለው አስተዋጽዖ በጣም አናሳ ነው፡፡ ከዚህ ዘርፍ የሚጠበቅ ሚና ሲታይ በምግብ እህል አቅርቦት በራስ አቅም ከማሟላት ባለፈ ኢኮኖሚውን የማሳደግ፣ ለኢንዱስትሪው በግብዓትነት ጥሬ ዕቃዎችን የማቅረብ፣ ገበያ የመፍጠር እና የውጭ ምንዛሬ የማስገኘት፣ የሥራ ዕድል የመፍጠር የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ግብርናን በተመለከተ ባለ ሁለት ፍኖት አቅጣጫ መከተል በተለይም የአነስተኛ ባለይዞታ ግብርና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚደረገውን ጥረት ከማስቀጠል ጎን ለጎን ለዘርፉ መዘመን የሚያግዙ ሜካናይዝድ መሣሪያዎችን እና ግብዓቶችን የመጠቀም፣ የግል ባለሀብቶችን ያሳተፈ የግብርና ሥርዓት የማበረታታት ተግባራት በትኩረት የሚከናወኑ ይሆናል፡፡

በመሆኑም ዘርፉ በልማት መሪ ዕቅዱ ዘመን ማነቆዎቹ ተፈተውለት ወደ ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ እንዲሸጋገር ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ለዚህም አርሶ አደሩ ፈጣን የሆነ የምርትና ምርታማነት ዕድገት በማምጣት የዘርፉ ዋና የዕድገት መሠረት ሆኖ እንዲቀጥል ማስቻል፣ የተማሩ ወጣቶችን በማደራጀት በዘርፉ እንዲሰማሩ ማድረግ፣ የመስኖ ልማትን ማስፋፋት፣ የአገር ውስጥ እና የውጭ ባለሀብቶች በግብርና ኢንቨስትመንት እንዲሰማሩ ማበረታታት እና መሳብ፣ እንዲሁም ለሁሉም ተዋናዮች አስፈላጊ የሆኑ የግብርና ግብዓቶችን እና ቴክኖሎጂዎችን በማምረትና በማቅረብ የግብርናውን ዘርፍ መደገፍ በመሪ ዕቅዱ ትኩረት የሚደረግባቸው ዋነኞቹ የየትኩረት መስኮች ናቸው፡፡

### 1.3.3. የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት

ከአምራች ኢንዱስትሪ ልማት አንፃር የኢኮኖሚ ሽግግር እና ኢንዱስትሪያላዊነት ያለዘመናዊ የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት የማይታሰብ ሲሆን በተለይም እያደገ የመጣውን ህብረተሰብ የኢንዱስትሪ ምርት ፍላጎት ለመሸፈን፣ የሥራ ዕድል ለመፍጠር፣ ግብርናን ለማዘመንና

በቴክኖሎጂ ተወዳዳሪ ለመሆን አዳጋች ያደርገዋል፡፡ በዚህ ወቅት ለአምራች ኢንዱስትሪዎች መሬቱን አልምቶ ለማስተላለፍ እና ሌሎችንም የድጋፍ ሥርዓቶች ተግባራዊነት ለማሳደግ ጥረት እየተደረገ ቢሆንም ተግባራትን ለመፈጸም ከላይ እስከታች ያለው ፈጻሚ የአቅም ክፍተት እንዳለበት ይስተዋላል፡፡ በሌላ በኩል የግብዓት፣ የመሠረተ ልማት እና የፋይናንስ አቅርቦት ችግሮች እንዲሁም የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፎች እጥረት በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮች ናቸው፡፡ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የትግበራ ዘመን የአነስተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ሁለንተናዊ ችግሮች በጥናት ለመለየት ጥረት የተደረገ ሲሆን የተለዩ ችግሮችም የግብዓት፣ የመሠረተ ልማት፣ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ እና የፋናንስ አቅርቦት ችግሮች ነበሩ፡፡ ምንም እንኳን አፈጻጸሙ ዝቅተኛ ቢሆንም በጥናት የተለዩ ችግሮችን ከመፍታት አንፃር ጥረቶች ተደርገዋል፡፡

የአምራች ኢንዱስትሪዎችና የሌሎች ፕሮጀክቶችን የመሠረተ ልማት አቅርቦት በማሳደግ በኩል የተደረገው ጥረትሲታይ በቂ መሬት በማዘጋጀት እንዲሁም በኢንቨስትመንት መሬቶች በቂ መሠረተ ልማቶችን በማቅረብ በኩል ችግሩ ሰፊ በመሆኑ ባለው ኢንቨስትመንት ፍሰት ልክ መሬት ማዘጋጀትና መሠረተ ልማት ማሟላት ያልተቻለበት ሁኔታ በመኖሩ በመሪ ዕቅዱ ዘመን እነዚህን እና መሰል ችግሮች እንዲቀረፉ በትኩረት መሥራት ተገቢ ይሆናል፡፡

የዘርፉ ምርታማነት ማነስ አንዱ ምክንያት በክልሉ ያሉ የነባር ኢንዱስትሪዎች ቴክኖሎጂ በዝቅተኛ የማምረት አቅም ላይ የሚገኝ ከመሆኑም ባሻገር ኢንዱስትሪዎቹ በማምረት አቅማቸው ልክ እያመረቱ አለመሆኑ የሚጠቀስ ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪውን ዕድገት በመወሰን ረገድ የቴክኖሎጂ አቅምን ማሳደግ እና ኢንዱስትሪዎቹ በሙሉ አቅማቸው ሊያመርቱ የሚችሉበትን ሁኔታ የማመቻቸት ሥራ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡ ፡ እንዲሁም የተቋማቸውን የሙያ አቅም ለማሳደግ እንዲነሳሱ የሚያበረታቱ የኢንዱስትሪ የህግ ማዕቀፎች ተቀርጸው እንዲተገበሩ ይደረጋል፡፡

ለማኑፋክቸሪንግ የኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚቀርበው የሰው ኃይል ከብዛት በተጨማሪ ጥራትን መሠረት ያደረገ እንዲሆን የተጀመሩ የኢንዱስትሪ እና የትምህርት ተቋማት ትስስር እየተካሄዱ ባሉ የአቅርቦት-ፍላጎት ጥናቶች ግኝት መሠረት እንዲጠናከሩ ይደረጋል፡፡ ምርታማነትን፣ ጥራትንና የቴክኖሎጂ አቅም ግንባታን አስመልክቶ ፕሮጀክቶች ተዘጋጅተው በዕቅድ ዘመኑ የሚተገበሩ ይሆናል፡፡ ነባር የአገር ውስጥ ባለሀብቶች ያለባቸውን ችግሮች ለይቶ በመፍታት እና አቅማቸውን በማጠናከር፣ ሀብቱ ቢኖራቸውም የንግድና አገልግሎት እንዲሁም የኮንስትራክሽን

የሥራ መስክን መልቀቅ የማይፈልጉትን በማስተማርና ከዚህ ጎን ለጎን የኪራይ ሰብሳቢነት በሩንም በማጥበብ ለውጥ እንዲያመጡ ማነሳሳት፣ ፕሮጀክት የመቅረጽ የብቃት ችግራቸውንም ግምት ውስጥ በማስገባት አትራፊ የሆኑትን ኢንዱስትሪዎች በመለየትና የአዋጭነት ጥናት በማካሄድ ኢንዱስትሪውን እንዲቀላቀሉ የማድረግ ሥራ ተጠናክሮ ይተገበራል፡፡

ነባር ኢንዱስትሪዎችን ማሻሻልና የማምረት አቅማቸውን ማሳደግ፣ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ አዳዲስለውጥ እንዲያመጡ ማነሳሳት፣ ፕሮጀክት የመቅረጽ የብቃት ችግራቸውንም ግምት ውስጥ በማስገባት አትራፊ የሆኑትን ኢንዱስትሪዎች በመለየትና የአዋጭነት ጥናት በማካሄድ ኢንዱስትሪውን እንዲቀላቀሉ የማድረግ ሥራ ተጠናክሮ ይተገበራል፡፡

ነባር ኢንዱስትሪዎችን ማሻሻልና የማምረት አቅማቸውን ማሳደግ፣ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ አዳዲስ ኢንዱስትሪዎችንና የምርት ዓይነቶችን ማስፋፋት፣ የውጭና የአገር ውስጥ ኢንቨስትመንቶችን በብዛትና በጥራት መሳብ፣ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ማስፋፋትና ክላስተሮች እንዲፈጠሩ ማድረግ፣ በውጭና በአገር ውስጥ ኢንቨስትመንቶች መካከል የገበያ፣ የቴክኖሎጂ እና የማኔጅመንት ዕውቀት ሽግግር መፍጠር የሚያስችል ትስስርን ለመፍጠር ይሠራል፡፡

በተጨማሪም ስትራቴጂክ የሆኑና የገበያ ክፍተቶች የሚታይባቸውን የሥራ መስኮች በመለየት የመንግስትን ጣልቃ ገብነት በጋራ ልማትና በተናጠል ማመቻቸት፣ የግብርና እና የኢንዱስትሪን፣ የባለድርሻ አካላትን፣ የመንግሥትንና የግሉን ዘርፍ፣ የሠራተኛንና የባለሀብት ቅንጅትን በላቀ ደረጃ ማሳደግ፣ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ዕድገት የሁሉንም ህብረተሰብ በተለይም የወጣቶችና ሴቶችን ፍትሐዊ ተጠቃሚነት (equitable & inclusive growth) ማረጋገጥ፣ ነፃ ውድድር የሚያሰፍን፣ ማህበራዊ ልማትን የሚደግፍ፣ የአካባቢ ተጽዕኖ የማያስከትል አረንጓዴ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪን ዕድገት ማረጋገጥ ተገቢ ይሆናል፡፡

### 1.3.4. የማዕድን ሀብት ልማት

የግብርና ዝመና፣ የአምራች ኢንዱስትሪ ልማትና የኮንስትራክሽን ዘርፍ ልማት ያለ መሠረታዊ የማዕድን ግብዓቶች የሚገኘው ውጤት አመርቂ አይሆንም፡፡ ከዚህ አንፃር ማዕድናትን ወደ ውጭ ሸጦ ከሚገኝ የውጭ ምንዛሬ በላይ በአገር ውስጥ ታንጸው ለብዝሀ ዘርፍ ልማት ቢውሉ የተሻለ አቅም የሚፈጥሩ ይሆናል፡፡የማዕድን ልማት ዘርፍ ምንም እንኳን በበርካታ ፈተናዎች የታጠረ ቢሆንም በቀጣይ የልማት መሪ ዕቅዱ ዓመታት በሚደረግ ሰፊ ሥራና ልዩ ትኩረት የክልሉ መንግሥት ላቅ ያለ ምጣኔ ሀብታዊ ፋይዳ ከዘርፉ ይጠብቃል፡፡ የማዕድን ዘርፍ

ከሌሎች ዘርፎች አንፃር ለአምራች ኢንዱስትሪዎች ጥሬ ዕቃ በማቅረብና በውጭ ገበያ ላይ በመቅረብ ተወዳዳሪ መሆን የሚያስችል ቢሆንም ይሰጠው የነበረው ትኩረት አናሳ በመሆኑ ከዘርፉ ሊገኝ የሚችለውን የላቀ ጥቅም ሳያስገኝ ቀርቷል፡፡ የማዕድን ልማት ዘርፍ ሌሎች የልማት ሥራዎችን የሚያነቃቃ ይሆናል፡፡ የማዕድን ዘርፉ የማኅበረ-ፖለቲካዊ ልማት እና የመሠረተ-ልማት ግንባታዎችን እንዲያፋጥን ለማድረግ በአገር ደረጃ በአለፉት ዓመታት የማዕድን አምራች ኩባንያዎችን ለማነቃቃት የታክስ ቅናሽ የተደረገ ቢሆንም በክልላችን በዘርፉ ያለው እንቅስቃሴ ውስንነት ያለበት ነው፡፡

ስለሆነም በቀጣይ በክልሉ በኢንዱስትሪ ማዕድናት ላይ ትኩረት ይደረጋል፡፡ ወርቅ፣ ብረት፣ ኦፓል፣ የኮንስትራክሽን ማዕድናት ወዘተ የመሳሰሉ ማዕድናት አሉን፡፡ ሌላው ከፍተኛ የመሠረተ-ልማት ግንባታ በማካሔድ ላይ እንገኛለን፡፡ የግንባታው ዘርፍ ከማዕድን ልማት ግብዓት እየፈለገ ነው፡፡ ስለዚህ ይኸም ትኩረት የምናደርግበት ሌላው ሥራ ነው፡ ፡ ደካማው መሠረተ-ልማት፣ የሠለጠነ የሰው ኃይል እጦት፣ እና በፈቃድ አሰጣጥ ዙሪያ ግልፅነት አለመኖሩ የዘርፉን እንቅስቃሴ ጎድተውታል፡፡ ስለሆነም እነዚህን ችግሮች በመፍታት አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን በመሳብና ነባር ኢንቨስትመንቶችን በማጎልበት ለአገር ውስጥ እና ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ማዕድናትን በዓይነት፣ በጥራትና በመጠን በማሳደግ የምንዛሪ ግኝትና የሥራ ዕድል ፈጠራን ማሳደግ የቀጣይ የትኩረት መስክ ነው፡፡

### 1.3.5. የቱሪዝም ልማት

የቱሪዝም ሀብት ለውጭ ምንዛሬ ግኝት፣ ለአገልግሎት ዘርፎች በተለይም ለሆቴል ኢንዱስትሪ እና ለትራንስፖርት አገልግሎቶች ልማት አስተዋጽያው በጣም ከፍተኛ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም ለሥራ ዕድል ፈጠራ ብሎም ድህነትንለመቀነስ የሚጫወተው ሚና የጎላ ነው፡፡ የአማራ ክልል ዓይነተ ብዙ የታሪክ፣ የባህልና የተፈጥሮ መዳረሻዎች (የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ሀብቶች) ያሉት ነው፡፡ ምንም እንኳን ክልላችን በርካታ የቱሪዝም ሀብቶች ቢኖሩትም ከዘርፉ የሚፈለገውን ያህል ጥቅም እያገኘ አይደለም፡፡ ይህ ዘርፍ ድህነትን ለማስወገድ እና ለልማት ቀጥተኛ አስተዋጽዖ የሚያበረክት ኢንዱስትሪ በመሆኑ ጥቅም ላይ በማዋል ተጨባጭ የሆነ ለውጥ ማምጣትና በዓለም አቀፍ የቱሪዝም ገበያ ተወዳዳሪ ሆኖ እንዲገኝ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ስለሆነም በዘርፉ በሥነ ምግባር፣ በዕውቀት፣ በክህሎት እና በአደረጃጀት የተቃኘ አገልግሎት መስጠት ይገባል፡፡ የክልሉን ባህላዊ፣ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ ሀብቶች የሚወድ፣ የሚጠብቅ፣

የሚያበለፅግና ወደ ልማት ኃይልነት የሚቀይር ትውልድ በመፍጠር፣ ባህልና ኪነ-ጥበብን ዋነኛ የልማት ኃይል በማድረግ እና የቱሪስት መስህቦችን በማስተዋወቅ የክልሉን ህብረተሰብ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ይሠራል፡፡ እንዲሁም ቅርሶችን በመጠበቅ፣ በማጥናትና በመመዝገብ ለቅርሶች ክትትል፣ ጥበቃና እንክብካቤ ማድረግ፣ ሙዚየሞችን ማደራጀት መምራትና አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም የክልሉን ዕምቅ የቱሪዝም ሀብት በአገርና በዓለም አቀፍ ደረጃ ጥራቱን በጠበቀና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ማስተዋወቅና ገበያ መፍጠር፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የቱሪስት መረጃ ማዕከል እንዲኖር ማድረግ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡

### 1.3.6. የኢንፎርሜሽን፣ ኮሚዩኒኬሽን እና ቴክኖሎጂ ልማት

የክልላችን ኢኮኖሚ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ለኢንፎርሜሽን፣ ኮሚዩኒኬሽን ና ቴክኖሎጂ እየተሰጠ ያለው ትኩረት አናሳ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህ ዘርፍ የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ባለማደጉ ለኢንፎርሜሽንና ቴክኖሎጂ እንዲሁም ለፈጠራ ሥራዎች መንግስት ከፍተኛውን ድርሻ ሊወስድ ይገባል፡፡ ከዚህም አንፃር አስፈላጊ የመሠረተ ልማት ዓይነቶችን በአግባቡ በመለየት፣ ያሉትንና የተጀመሩትን ተቋማት የማጠናከርና የማስፋፋት እንዲሁም በቀጣይ አስፈላጊ የሆኑ ተቋማትን የመገንባት ሥራ የሚከናወን ይሆናል፡፡ በአገርም ሆነበክልል ደረጃ ዕውቀት መር ኢኮኖሚን ለመገንባት በተያዘው አቅጣጫ መሠረት ለዕውቀት፣ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ልማት ልዩ የማበረታቻና ማትጊያ ሥልቶችበመቀየስ የግሉ ዘርፍ ከመንግስት ጋር በመተባበር የሚሠራበት ሁኔታ እንዲኖር ይደረጋል፡፡ እንዲሁም በመንግስት በኩል ለጥናትና ምርምር ዘርፍ ልዩ ትኩረት በመስጠት የምርምር ተቋማት በቴክኖሎጂ ማላመድና ፈጠራ ላይ አተኩረው እንዲሠሩ አቅማቸውን ለማሳደግ ይሠራል፡፡ በዚህም የጥናትና ምርምር ሥራው በክልሉ እንዲመጣ የሚፈለገውን የኢኮኖሚመዋቅራዊ ለውጥ በሚደግፍና በሚያፋጥን መልኩ በተመረጡ የምርምር ሥራዎች፣ የቴክኖሎጂ መረጣ፣ መቅዳት፣ ማላመድና ሥርፀት ላይ ትኩረት ተሰጥቶት እንዲሠራ ደረጋል፡፡

### 1.3.7. ዘላቂ የከተማ ልማት

በክልሉ የሥነ ህዝብ ትንበያ መሠረት የክልሉ የህዝብ ብዛት እየጨመረ የሚገኝ እንደሆነ መረጃው ያመላክታል፡፡ በቀጣይ የመሪ ዕቅዱ ዓመታት በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚጨምርም ይገመታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከገጠር ወደ ከተማ ያለው ፍልሰት በየዓመቱ እየጨመረ

የሚገኝ ሲሆን ከተሞችን በሥርዓት ለመምራትና ህዝቡን ከከተማው ክፍለ ኢኮኖሚ ተጠቃሚ ለማድረግ በማያስችል መልኩ የሥነ-ህዝብ ሁኔታው እየተቀየረ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ለመኖሪያ እና ለሥራ ምቹ የሆኑ ዘላቂ ከተሞችን በዕቅድ መምራት ለነገ የማይባል ጉዳይ በመሆኑ የከተማ ልማት አንዱ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ዘርፍ ይሆናል፡፡ ሚዛናዊ የሆነ የከተማ-ገጠር ትስስርም እንዲኖር በትኩረት ይሠራል ፡፡

በክልሉ የከተሞች ስሪት እና የአከታተም ሁኔታ በሥርዓት ያልተመራና በዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው፡፡ ስለሆነም ከተሞች ለአምራች ዘርፎች ዕድገት፣ ለኢንቨስትመንት መስፋፋት፣ ለሥራ ሥምሪትና ለነዋሪዎች ምቹ እንዲሆኑ በዘመናዊ የከተማ ዕቅድ የሚመራ የከተሞች አስተዳደር ሥርዓት ያስፈልጋል፡፡ በተለያዩ ገፊና ሳቢ ምክንያቶች የአምራች ዘርፍ እንቅስቃሴ ከታላላቅ ከተሞች ወደ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ፣ አነስተኛ ከተሞችና መንደሮችእየተስፋፋ መሄዱን ያለፉት ዓመታት አፈጻጸም ያሳያል፡፡ ከከተሜነት መስፋፋት፣ ከአምራች ዘርፉ ሚና ማደግ እና የኢኮኖሚ መዋቀር ለውጥ ጋር ተያይዞ ከተሞች የቤቶችና ሌሎች መሠረተ ልማት አቅርቦቶችን ለማሟላት ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በመሆኑም በከተሞች ፈጣንና ፍትሐዊ ልማትን ለማረጋገጥ ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት ያላቸውን ሚና ያገናዘበ መሠረተ ልማቶች እንዲስፋፉ ማድረግ፣ በከተሞች የሚገነቡ መሠረተ ልማቶች ሰፊ የሥራ ዕድልና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን በሚፈጥር መልኩ ተፈፃሚ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ በመሪ የልማት ዕቅዱ ዘመን የከተማ አስተዳደር በዘመናዊ የመሬት አጠቃቀም ፕላንና ጠንካራ የመሬት ግብይት ሥርዓት እየተመራ ቀልጣፋና ውጤታማ የከተማ ልማት እንደሚያረጋግጥ ይጠበቃል፡፡

### 1.3.8. መሠረተ ልማት

በክልሉ በመሠረተ ልማት መስፋፋት ዙሪያ ያጋጠሙ ችግሮችን በመቅረፍ በዘርፉ የሚከናወኑ ኢንቨስትመንቶችን በከፍተኛ መጠን መጨመር፣ የክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገት እንዲፋጠን በተለይ የኢንዱስትሪውን ክፍለ ኢኮኖሚ በአግባቡ ለመምራት የተሟላ መሠረተ ልማት እንዲኖር ማድረግ በትኩረት ይሠራል፡፡ ለዚህም መሠረተ ልማቶችን በማስፋፋት የትራንስፖርት፣ የመገናኛና የኃይል አቅርቦትን በጥራትና በተወዳዳሪ ዋጋ ማቅረብ እንዲሁም ለመንገድ፣ ለኢነርጂ፣ ለመስኖ፣ ለመጠጥ ውኃ፣ ለኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና ለማህበራዊ መሠረተ ልማቶች ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል፡፡ በክልሉ በተለይ በመንገድ መሠረተ ልማት ዙሪያ የገጠር ቀበሌዎችን ደረጃቸውን በጠበቁና ክረምት ከበጋ በሚያገለግሉ መንገዶች ከዋና መንገድ ጋር

የማገናኘት ሥራ አንዱ የትኩረት መስክ ነው፡፡ የክልሉን የኢነርጂ ፍላጎት ለማሟላት ንፁህና አየርን የማይበክል የታዳሽ ኃይል ምንጮችን ማስፋፋት ማለትም ከውኃ ኃይል የመስኖ ግድቦችን በመጠቀምና የፀሐይ ኃይል አማራጮች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡

በክልሉ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት መሠረተ ልማቶች በጥራት ባለመስፋፋታቸው በርካታ ችግሮች ይስተዋሉበታል፡፡ የትራንስፖርት አገልግሎቱን ተደራሽ ከማድረግ አንፃርና ከአመቺነት አኳያ ሲታይ በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ሌላው በመንግስትም ሆነ በግል የትራንስፖርት መጓጓዣ አቅርቦትና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ በገጠርም ሆነ በከተሞች ደካማ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በክልል ደረጃ ያለውን የትራንስፖርት አቅርቦት የማሻሻልና አገልግሎቱን በጥራት ለተጠቃሚው ህብረተሰብ ለማድረስ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓቶችን በመዘርጋት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

### 1.3.9. የሰው ኃብት ልማት እና የሥነ-ህዝብ ትሩፋት

እንደ ክልል ጥራት ያለው ትምህርት፣ አመለካከትና ክህሎት መኖር ለክልሉ የሰው ኃብት ልማት ዕድገት የሚኖረው አስተዋጽዖ በእጅጉ የጎላ ነው፡፡ ከጤና አኳያም ጥራት ያለው የጤና ሥርዓትን መገንባት ለሰው ኃብት ልማቱ ያለው ድርሻ ከፍተኛ እንደሆነ አያጠያይቅም፡፡

በመሆኑም በሰው ኃብት ልማት ዘርፍ በክልላችን የተሄደባቸው ስኬታማ ርቀቶች ለቀጣይ የመሪ ዕቅዱ ትልሞች እንደ ወረት ሊወሰዱ የሚችሉ ናቸው፡፡ ኢኮኖሚው በሚፈልገው ደረጃ ብቁ፣ ተወዳዳሪ እና አምራች ዜጋ ከማበመሆኑም በሰው ኃብት ልማት ዘርፍ በክልላችን የተሄደባቸው ስኬታማ ርቀቶች ለቀጣይ የመሪ ዕቅዱ ትልሞች እንደ ወረት ሊወሰዱ የሚችሉ ናቸው፡፡ ኢኮኖሚው በሚፈልገው ደረጃ ብቁ፣ ተወዳዳሪ እና አምራች ዜጋ ከማፍራት አንፃር በሰው ኃይል ልማት ረገድ እየተደረገ ያለው ርብርብ በቀጣይም ተጠናክሮ ይከናወናል፡፡ በአሁኑ ወቅት የክልሉ የትምህርት ሽፋን እያደገ ያለ ቢሆንም አሁንም በትምህርት ዕድሜ ክልል ከሚገኙ ህጻናት የተወሰኑት በትምህርት ገበታ ላይ አይደሉም፡፡ በዚህ መሠረት ሁሉም በመዋዕለ ሕፃናት ደረጃና በ1ኛ ደረጃ ትምህርት የዕድሜ ክልል የሚገኙ ህፃናት ትምህርት ቤት እንዲገቡ በማድረግ የትምህርት ሽፋንን የማሣደግ እንዲሁም ተገቢነትንና ፍትሐዊነትን የማስጠበቅ ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

በዕቅድ ዘመኑ ለትምህርት ጥራት ልዩ ትኩረት ይሰጣል፡፡ በመሆኑም የትምህርት ተቋማትን የማስፋፋት፣ ለደረጃው የሚመጥኑ በቂ መምህራንን የማሟላት እንዲሁም የሴት ተማሪዎችን

ተሳትፎ የሚቀንሱ ችግሮችን የማቃለል ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ በቴክኒክና ሙያ ትምህርት የሚማሩ ተማሪዎች የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ለማስፋፋትና ለማጠናከር በሚያስችላቸው አግባብ እንዲሰለጥኑ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም በአሁኑ ወቅት በገጠር በምርት ተግባር ከተሰማራው የሰው ኃይል አመዛኙ ማንበብና መፃፍ የማይችል እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ስለሆነም ይህ ኃይል ቴክኖሎጂ በቀላሉ በመቀበል ምርታማነትን እንዲያሳድግ ከማድረግ አንፃር ሚናውን እንዲወጣ እንዲሁም በማህበራዊና ሌሎች መስኮች ንቁ ተሳትፎ ማድረግ እንዲችል ለተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ትኩረትበሌላ በኩልም የመሠረታዊ ጤና አገልግሎትን የማስፋፋትና የአገልግሎት ጥራትን የማስጠበቅ ሥራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የንፁህ መጠጥ ውኃና ሳኒቴሽን እንዲሁም ሥርዓተ-ምግብ የቀጣይ ዓመታት የትኩረት መስኮች ናቸው፡፡ ማህበራዊ ተቋማትን ከማስፋፋት አንፃር ሁሉም የልማት ኃይሎች ከመንግስት ጋር በተቀናጀ አግባብ ርብርብ እንደሚያደርጉ ይጠበቃል፡፡ በማህበራዊ ልማት ዘርፍ ድንቅ ሥራዎች የተከናወኑበት የጤናው መስክ ነው፡፡ የጤና ፖሊሲያችን በዋናነት በሽታን በመከላከል ላይ የሚያተኮር ቢሆንም ከዚሁ ጐን ለጐን መሠረታዊ የጤና አገልግሎትን የማስፋፋቱም ጉዳይ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡ ይሁን እንጂ በጤናው መስክ ለህብረተሰቡ የተሟላ የጤና አገልግሎት በመስጠት በኩል አሁንም በርካታ ተግዳሮቶች አሉ፡፡

በመሆኑም መሠረታዊ የህክምና አገልግሎት የሚሰጡና ጣቢያዎችን በሁሉም የክልላችን አካባቢዎች ማስፋፋት፣ የጤና ተቋማቱን አገልግሎት የማሻሻልና ግብአቶችን የማሟላት ሥራም ትኩረት ተሰጥቶት የሚከናወን ይሆናል፡፡ የጤና ኤክስቴንሽን መርሃ ግብር የመሠረታዊ የጤና አገልግሎት ተደራሽነት መሻሻልና በሽታን በመከላከሉ ሥራ ላይየህብረተሰቡን ተሳትፎ ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ በትኩረት ይሠራል፡፡ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በጤናው ዘርፍ የህብረተሰቡን ባለቤትነት በማሳደግ ጤናማና አምራች ዜጐችን ለመፍጠር ቁልፍ ሚና እንዲጫወቱ ይደረጋል፡ ፡ መሠረታዊ የጤና አገልግሎትን ከማስፋፋት ጎን ለጎን የሆስፒታል አገልግሎትን ለማሻሻልም የክልላችን አቅም በፈቀደ መጠን ትኩረት ተሰጥቶ የሚከናወን ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ የክልሉ የሰው ኃይል ልማት የኢኮኖሚ ልማቱ ከሚጠይቀው አንፃር በጥራትም ሆነ በመጠን በማቅረብ በኩል ችግሮች ተስተውለውበታል፡፡

ስለሆነም በቀጣይ የመሪ ዕቅዱ ዓመታት የሰው ኃይል ልማት በወሳኝነት የሥራ ኃይሉ ጤናማ፣ የተማረና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም የሚችል እንዲሆን በማድረግ ይበልጥ

ምርታማ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የትምህርት አገልግሎት ተደራሽነትን ማሳደግ ብቻ ሳይሆን ጥራቱን ማሳደግ፣ ከመካከለኛ የክልሉ የትምህርት ተቋማት ሰልጥነው የሚመረቁ ወጣቶች የገበያውን ፍላጎት መመለስ የሚያስችላቸው አቅም እንዲኖራቸው ለማድረግ ሥልጠናው ለጥራት ትኩረት ይሰጣል፡፡ በአጠቃላይ የትምህርትና ሥልጠና ሥራዎቻችን ከሀገራችን የትምህርት ግቦችጋር የሚጣጣሙ እና ኢኮኖሚው የሚፈልገውን የሰው ኃይል በጥራት በማምረት በኩል ትኩረት ተሰጥቶት በየደረጃው እንዲፈፀም ይደረጋል፡፡ ጤናው የተጠበቀ የሰው ኃይል እንዲኖር ማድረግ ለኢኮኖሚ ዕድገቱ ያለውን ትልቅ አስተዋጽዖ ከግምት ያስገባ የጤና አገልግሎት ተደራሽነትና ጥራት የማሳደግ ሥራ የትኩረት መስክ ሆኖ ይሠራል፡፡

ከሥነ-ህዝብ ልማት አኳያም የአንድ አገር መሠረታዊ የሥነ-ህዝብ ባህሪያት በአጠቃላይ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች እና በዜጎች ሁለንተናዊ የኑሮ ገፅታ ላይ ጉልህ ተፅእኖ አላቸው፡፡ በመሆኑም በመሪ የልማት ዕቅዱ ዘመን በክልሉ የህዝብ ዕድገት ምጣኔን ከኢኮኖሚ ዕድገት ጋር በማጣጣም ከረጅም ጊዜ አኳያ የክልሉን ህዝብ የኑሮ ደረጃና አጠቃላይ ደህንነት ለማሻሻል ይከናወናል፡፡ የሥነሕዝብን መሠረታዊ ባህሪያት ከኢኮኖሚው አቅም ጋር ለማጣጣምና የባህሪያቱን ተለዋዋጭነት መሠረት የሚጠበቀውን የዲሞግራፊ ትርፍ (Demographic Dividend) እንደቀጣይ የዕድገት ምንጭ ለማዋል የሚቻልበትን አግባብ አሁን ካለው የክልሉ የሥነ- ህዝብ ሁኔታና ቀጣይ ምልከታ አኳያ መወሰድ የሚገባቸው የፖሊሲ ርምጃዎች ተለይተው እንዲቀመጡ ለማድረግ የትኩረት መስክ ሆኖ ተወስዷል፡፡

### 1.3.10. ዘላቂ የልማት ፋይናንስ ማረጋገጥ

በክልሉ የልማት ፋይናንስ ማመንጨትና ዘላቂነቱን ማረጋገጥ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ በአለፉት ዓመታት የክልሉን ገቢ በማሳደግ ረገድ አበረታች ሥራዎች የተከናወኑ ቢሆንም ክልሉ ለልማት ከሚያስፈልገው ወጪ እንዲሁም ከሚያመነጨው ሀብት አንፃር ሲመዘን የገቢ አሰባሰቡ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ስለሆነም በቀጣይ የዕቅዱ ዓመታት በክልሉ የሚሰበሰብ ገቢን በእጅጉ የማሳደግ እና በራስ ገቢ ወጪን የመሸፈን አቅምን ማጎልበት ትኩረት የሚሠጠው ይሆናል፡፡

### 1.3.11. ተቋማዊ አቅምመገንባት

ከዚህ አኳያ በክልሉ ይስተዋሉ የነበሩ የተለያዩ ችግሮችን በመቅረፍ ክልላዊ የልሂቃን ሥምምነትና አገራዊ መግባባት፣ የጋራ ርዕይ መኖር እና የመንግስት ቅቡልነትን የሚያረጋግጡ

የዴሞክራሲያዊና የፍትሕ ተቋማት እንዲኖሩ ጥረት የሚደረግ ሲሆን ከግሉ ዘርፍ ጋር የሚተባበር በተወዳዳሪነት መርህ ላይ የተመሠረተ ቢሮክራሲ እንዲኖር ይሠራል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የትምህርት ተቋሞቻችን የመልካም ዜጋ ማፍለቂያ እንዲሆኑ ከቤተሰብ፣ ማህበረሰብና መምህራን ጋር የተቀናጀ ጥረት እንደሚደረግና ቤተሰብን፣ የማህበረሰብና የዕምነት መሪዎችን በማስተባበር የዕምነት ተቋሞቻችንና አስተምህሮቶቻቸው ድህነትን ለመቀነስ አዎንታዊ አስተዋጽዖ እንዲኖራቸው መሥራት ትኩረት የሚሰጠው ሲሆን ብልፅግናን ለማረጋገጥ የሚረዱ ተገቢ የፖሊሲ፣ የስትራቴጂ እና የህግ ማዕቀፎችየሚዘጋጁ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት፡- የሶስት አመቱ እቅድ አፈጻጸም ዓላማ፣ አስፈላጊነትና የግምገማው ሂደት

### 2.1. የግምገማው ዓላማ

የክልሉን የ10 ዓመት እቅድ አፈጻጸም የባለፉት ሶስት ዓመታት ትግበራን በመተንተን የልማትና መልካም አስተዳደር አቅድ አፈጻጸሙ ምን ደረጃ ላይ እንዳለ እና በአፈጻጸሙ የነበሩ መልካም አፈጻጸሞችንና የነበሩትን ክፍተቶች በመለየት በቀጣይ የእቅድ ዘመናት አካቶ ለመፈጸም የሚያስችል ሰነድ ለማዘጋጀት ነው፡፡

### 2.2. የእቅድ አፈጻጸም ግምገማው አስፈላጊነት

በአጠቃላይ በአለፉት 3 ዓመታት የነበሩ ነባራዊ ሁኔታዎችን በተገኙ መረጃዎች ላይ ተመስርቶ በመተንተንና ያላሳካናቸውን እና ወደኋላ ያስቀሩን ጉዳዮችን በመለየት በቀጣይ 5 ዓመታት ለማካካስና ከዚያ በላይ ውጤት ማስመዝገብን ታሳቢ ያደረገ የዕቅድ ክለሳ ለማከናወን በመረጃነት የሚገለግል ሰነድ በማስፈለጉ የእቅድ አፈጻጸም ግምገማው ተከናውኗል፡፡ በመሆኑም በሚከተሉት ዋና ዋና ምክንያቶች የግምገማው አስፈላጊነት ተቀጧል፡፡ በታቀደው የአስር ዓመት መሪ ዕቅድ መሠረት በተከናወኑ ተግባራት የተመዘገቡትን ውጤት በማየት የቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎችን ለማቀመጥ፣የታቀደው መሪ ዕቅድ በታቀደለት የጊዜ ርዝማኔ መሠረት ሊፈጸም መቻልና አለመቻሉን በመገመት የማስተካከያ እርምጃዎችን ለመውሰድ፣መሪ ዕቅዱን ለመፈጸም ያጋጠሙ ችግሮች እና ስጋቶች ካሉ የመፍትሄ እርምጃዎችን በማስቀመጥ በተያዘለት ጊዜ እንዲፈጸም ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር፣ የክልል ተቋማት በሦስት ዓመት ውስጥ ያስመዘገቡትን ውጤት በማየት የተሻለ የፈጸሙትን ለማነሳሳት እና ዝቅተኛ አፈጻጸም ያላቸውን ተቋማት

ከድክመታቸው እንዲነሱ ለማድረግ እንዲሁም በሦስት ዓመት ውስጥ ታቅደው ያልተፈጸሙ ዕቅዶችን ወደ በቀጣይ 5 ዓመት በማካተትና የማካካሻ እርምጃ በመውሰድ በሚፈለገው ደረጃ የሚፈጸሙበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ግምገማው አስፈላጊ ነው፡፡

## 2.3. በግምገማው ሂደት የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

### 2.3.1. በቅድመ ዝግጅት ምዕራፍ የተከናወኑ ተግባራት

በዚህ ረገድ የመረጃ መሰብሰቢያ ፎርማቶችን ማዘጋጀትና ለሚመለከታቸው አካላት ማድረስ፣የክልል ተቋማትን የሦስት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ማሰባሰብ፣ የ10 ዓመቱን መሪ ዕቅዱን ማደራጀት፣የክልሉን የ2016 በጀት አመት እቅድ እና ፖሊሲ ማትሪክስ መውሰድ፣ የክልሉ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ አፈጻጸም ሰነዶችን ማደራጀት፣ የፌደራል የሶስት ዓመታት እቅድ አፈጻጸም ሰነድን መቀበል፣ በግምገማው ላይ ተሳታፊ ሙያተኞች የሚገመግሟቸውን ዘርፎች ተከፋፍሎ መውሰድ ፣ስለቀጣይ ስራዎች በቂ ውይይትና ኦሬንቴሽን በማካሄድ ግልጽነት መፍጠር እንዲሁም ለግምገማው አስፈላጊ ቁሳቁሶችንና የክፍል አደረጃጀቶችን በማሟላት የትንትና ስራው በአግባቡ እንዲከናወን ለማድረግ የተሻለ የቅድም ዝግጅት ስራ ተስርቷል፡፡

### 2.3.2. በግምገማው ወቅት የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

በሶስት አመቱ የእቅድ አፈጻጸም ትንታኔን ከበቂ ዝግጅት በኋላ የተጀመረ ሲሆን የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶችን መረጃ በትግበራ ዘመን በመለየትና በማጠናከር፣ በ10 ዓመት መሪ ዕቅዱ ላይ የታቀደውን የሶስት ዓመት ዒላማ መለየት፣ የሦስት ዓመቱን ዕቅድ ከአፈጻጸሙ ጋር ማነጻጸር፣ የተሰበሰበውን ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት መረጃ ማጠቃለል፣ የተሰበሰበውን አጠቃላይ ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ማደራጀት፣ መተንተን እና የማጠቃለል ስራ መስራት፣ ሂደቱን በጋራ በመቀመጥ መገምገምና አቅጣጫዎችን የጋራ ማድረግ እንዲሁም የሦስት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም የማጠቃለያ የግምገማና የትንተና ሪፖርት ማዘጋጀት ተችሏል፡፡

የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማው ዝግጅት መረጃዎች ጥራታቸውን የጠበቁ፣ ታዓማኒና ወቅታዊ ሪፖርቶችና ከአስተዳደራዊ መረጃዎች የተወሰዱ ናቸው። ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎች ከተለያየ ምንጭ ታይተው ታዓማኒነታቸው ከተረጋገጠ በኋላ እንደ አስፈላጊነቱ በማሚያነት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፡፡ የልማት ዕቅዱ የአፈጻጸም ግምገማ ሪፖርቱ በልማት

ዕቅድ ዘመኑ የተያዙ ሁሉንም ዒላማዎች የአፈፃፀም ደረጃ በማሳየት እና የአፈጻጸም ውጤቶችን በበቂ ትንተና የተደገፉ ሆነው ይዘታቸው አህዛዊ እና ገላጭ መረጃዎችን በተገቢው ሁኔታ አመጣጥነዉ እንዲተነተኑ ተደርጓል፡፡

የየዘርፎችን የሶስት አመታት የልማት ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማው ከዕቅዱ ግቦችና ኢላማዎች ጋር በማነፃፀርና በመቶኛ በመግለፅ የዕቅድ አፈፃፀሙ የደረሰበትን ደረጃ በሚገባ በመተንተን የአፈፃፀም አዝማሚያውን በግልፅ በማሳየት፣ የታቀደውን ግብ ለመምታት አፈፃፀሙ ያለበትን ደረጃ እና ምን መሰራት እንዳለበት በማመላከት ይህም የዘርፉን ዓላማ ከማሳካት ግልፅ በሆነ ትንተና ተቀምጧል፡፡ በተጨማሪም የየዘርፉ ዕቅድ አፈፃፀም ከተቀመጠው ግብ/ኢላማ ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ ወይም ከፍተኛ ሲሆን አሳማኝና ተቀባይነት ባላቸው ምክንያቶች መደገፍና ዋና ዋና ምክንያቶችን ውሳኔ ሰጪዎችን በሚያሳምን መልኩ ተንትኖ የቀረበ ሲሆን በጉድለት የታዩ አፈፃፀሞችን ለማካካስ ወደፊት ሊወሰዱ የሚችሉ የመፍትሔ እርምጃዎችን ማመላከት ረገድ ብዙ ርቀት ተሂዶ የተዘጋጀ የግምገማ ሪፖርት ነው፡፡

**በማጠቃለያ ምዕራፍ የተከናወኑ ተግባራት**

የተዘጋጀውን የሦስት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማዊ የትንተና ሪፖርት ለቢሮው ሃላፊዎች  እንዲደርስ ማድረግ፣ የግምገማና ትንተና ሪፖርቱን የሚመለከታቸው አካላት አስተያየት እንዲሰጡበት ማድረግ፣ በተገኘው ግኝት መሠረት የቀጣይ አምስት አመት እቅድ ላይ በመረጃነት እንዲያገለግል ማድረግ ለወደፊት እንዴት መፈጸም እንዳለባቸው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ምክክር በማካሄድ ጥቅም ላይ እንዲውል ይጠበቃል፡፡

**ፈጻሚ አካላት**

ይህ ተግባር የተፈጸመው ሰባት አባላት ባሉት በፕላንና ልማት ቢሮ የፕላን ትግበራ ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት ባለሙያዎች ያላሰለሰ ጥረት ነው፡፡

## ክፍል ሶስት፡- የክልሉ የሶስት ዓመታት (2013-2015) የልማትና መልካም አስተዳደር አፈጻጸም ትንተና

### 3.1. የኢኮኖሚ ልማት ዘርፍ አፈጻጸም

### 3.1.1. የግብርና ልማት ዘርፍ አፈጻጸም


የ10 ዓመት መሪ ዕቅድ ዘመን ግብርናው የክልሉ ኢኮኖሚ የዕድገት ዋነኛ ምንጭ ሆኖ እንዲቀጥል በማድረግ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ እና ገበያን መሠረት ያደረገ የግብርና ምርቶችን በማምረት የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ የመሪነቱን ሚና እንዲጫወት የግብርና ልማት ስትራቴጅ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ቁልፍ አቅጣጫ ሆኖ ተቀምጧል፡፡ግብርናው ፈጣን ዕድገትና መዋቅራዊ ለውጥን በማረጋገጥ የግብርና ልማቱ በግብርና በራሱ እና በአጠቃላይ ኢኮኖሚው ላይ ትራንስፎርሜሽን እንዲያመጣ የሚጠበቅ ነው፡፡ በግብርና ልማቱ በሁሉም ዘርፎች የሴቶችንና የወጣቶችን ተሳትፎ የበለጠ በማጠናከር ተጠቃሚነታቸው እንዲረጋገጥ ከማድረግ አኳያ በተለይ በገጠር ወጣቶች ግብርና ነክ በሆኑና ከግብርና ጋር ተያያዥነት ባላቸው ሌሎች ተግባራትም ወደ ሥራ ተሰማርተው ግብርናውን በማዘመን በኩል ሚና እንዲኖራቸው ትኩረት የተሰጠው አቅጣጫ ነው፡፡

በ10 ዓመቱ መሪ ዕቅድ በግብርናው ዘርፍ ከተቀመጡ ዓላማዎች መካከል በዘርፉ ፈጣንና ዘላቂነት ያለው ዕድገት በማስመዝገብ የህዝቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣ ገበያን መሠረት ያደረገ የሰብል እና የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ዋነኛዎች ናቸው፡፡ እነዚህን ዓላማዎች ለማሳካት የሚያስችሉ ግቦች ተቀምጠው ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ተገብቷል፡፡ በመሆኑም ያለፉት ሶስት ዓመታት (2013-2015) የግብርናው ዘርፍ ዕቅድ አፈፃፀም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሰብል ልማትና ጥበቃ በሚመለከት በዋና ዋና የእህል ሰብሎች በመኸር 4.86 ሄክታር መሬት በማልማት 155 ሚሊዩን ኩንታል ለማድረስ ታቅዶ 5.12 ሚሊዩን ሄ/ር በማልማት 145 ሚ/ኩንታል ከመሬት (የዕቅዱን 105%) እንዲሁም ምርት የዕቅዱን 93% ማምረት ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ የዋና ዋና የመኸር ሰብሎችን ጥቅል ምርታማነት በመነሻ ዓመት /2012/ ከተደረሰበት 24.1 ኩንታል በሄክታር ወደ 32 ለማድረስ ታቅዶ 28.38 (የዕቅዱን 88.68%) ኩንታል በሄክታር ማድረስ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል 2015/16 የመሬት ዕድገቱ 87,000 ሄ/ር ወይም 4.9 % ጭማሪ ቢኖረዉም በ2014/15 ምርት ዘመን ከተዘራዉ ተመሳሳይ ሄ/ር የምርት ዕድገት ጋር ሲነጻጸር 2.87 በመቶ የቀነሰ መሆኑን ያሳያል፡፡

በዚህ በኩል የተመዘገበው አፈፃፀም በምርት እና በምርታማነት 2012 ከተደረሰበት አፈጻጸም አንፃር ሲታይ በምርት 35 ሚሊየን ኩንታል ወይም 33% እንዲሁም በምርታማነት 4.92 ኩንታል በሄክታር ወይም የ16% ጭማሪ አሳይቷል፡፡ 2015/16 የመሬት ጭማሪ ቢያሳይም

ከተገኘዉ የመሬት ጭማሪ አንጻር የተገኘዉ የምርት ዕድገት መጨመር ሲገባዉ የቀነሰበት አዝማሚያ መኖሩን አሳይቷል፡፡





**ግራፍ-1፡የሶስት ተከታታይ ምርት ዘመን የለማ መሬት፤የተገኘ ምርት እና ምርታማነት**

ባለፉት ዓመታት የበልግ ምርትን በዕቅዱ መነሻ ዓመት (2012) ከተደረሰበት 185,600 በበልግ የሚለማ ወደ 201,000 ሄ/ር የእርሻ መሬት በማልማት እንዲሁም ከ2.75 ሚ/ኩንታል ምርትን ወደ 3.51 ኩንታል ምርት ለማሳደግ ታቅዶ 230,300 ሄ/ር (የዕቅዱን 114%) መሬት በማልማት 3.70 ሚ/ኩንታል (የዕቅዱን 105%) ምርት የተገኘ መሆኑን ያሳያል፡፡ ከምርታማነት አኳያ ሲታይ በዕቅዱ መነሻ ዓመት (2012) ከተደረሰበት 14.8 ኩንታል በሄ/ር በሶስት ዓመታት ዉስጥ በአማካይ ወደ 17.80 ኩንታል በሄ/ር ለማሳደግ ታቅዶ 16 ኩንታል በሄ/ር በማድረስ የዕቅዱን 89.89% ማከናወን ተችሏል፡፡

በክልሉ የግብርና ሜካናይዜሽን አፈፃፀም በተለይም በትራክተር እና በኮምባይነር አቅርቦትና አጠቃቀም በመነሻው ዓመት /2012/ ከተደረሰበት የ60 ኮምባይነር በሶስት አመታት ዉስጥ ወደ 102 ታቅዶ 37 (የዕቅዱን 36.27%) ተከናዉኗል፡፡በዚህም ከ3 ዓመቱ ዕቅድ አንጻር 36.27% የተከናወነ ሲሆን ከ10 ዓመቱ ዕቅድ አንጻር 2.07 % ብቻ ተከናዉኗል፡፡ በተመሳሳይ የመዉቂያ መሳሪያ አቅርቦት በተመለከተ ባለፉት ሶስት አመታት የዕቅድ ዘመን132 ለማድረስ እንዲሁም በ10 ዓመቱ መሪ ዕቅድ 2022 በጀት ዓመት መጨረሻ 725 ለማድረስ በዕቅድ ተይዞ ከሶስት ዓመቱ አንጻር 92 (69.70%) ተከናዉኗል እንዲሁም ከ10 ዓመቱ (12.69%) ብቻ ተከናዉኗል፡


በሌላ በኩል ባለፉት ተከታታይ ሶስት አመታት የሚጠበቀውን የምርት እድገት ማስመዝገብ እንዲቻል የአፈር ማዳበሪያ አጠቃቀምን ማሻሻል የሚገባ መሆኑ ታምኖበት ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ መገባቱ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ጥቅም ላይ የዋለ የሰው ሠራሽ ማዳበሪያ በ2012/13 ምርት ዘመን ከተደረሰበት 5.04 ሚሊየን ኩንታል በዕቅዱ መጨረሻ ምርት ዘመን ወደ 9.99 ሚሊዮን ኩንታል ለማድረስ ታቅዶ እንዲሁም ባለፉት ሶስት ዓመታት 7.40 ሚሊየን ኩንታል ለማድረስ ታቅዶ በሶስት አመት ዉስጥ 5.47 ሚሊዩን ኩንታል (የዕቅዱን 73.9%) ማድረስ የተቻለ ሲሆን ከ10 ዓመቱ ጋር ሲነጻጸር 54.75% ተከናዉኗል፡፡




**ግራፍ-2፡ የ3 ዓመት የመደበኛ ኮም1ፖስት ዝግጅትና አጠቃቀም**

በመሆኑም የኮምፖስት ዝግጅት አፈፃፀም እድገት ያሳየበት ምክንያት ባለፉት ሁለት ዓመታት የሰዉ ሰራሽ ማዳበሪያ አቅርቦት ዉስንነት ሊኖር እንደሚችል በየደረጃዉ ለሚገኑ አካላት ግንዛቤ በመፈጠሩና አርሶ አደሩም የችግሩን አሳሳቢነት በመረዳት በስፋት ኮምፖስት ማዘጋጀትና መጠቀም በመቻላቸዉ መሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡

በመስመር መዝራት ባለፉት ተከታታይ ሶስት ዓመታት ዉስጥ አፈፃፀም ሲታይ በአማካይ 2.623.003 ሄ/ር የእርሻ ማሣ በመስመር ለመዝራት ታቅዶ 1,764,867 ሄ/ር (የዕቅዱን 67.3%) መዝራት ተችሏል፡፡




**ግራፍ-3፡ የ3 ጊዜ ምርት ዘመን ሰ2ብልን በመስመር መዝራት አፈጻጸም**

በዚህ በኩል አፈጻጸሙ በየዓመቱ ዕድገት እያሳየ ቢመጣም ከታቀደዉ አንጻር ዕቅዱን ያላሳካ መሆኑ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ለዚህ አፈጻጸም አለመሳካት ተጠቃሽ ከሆኑ ምክንያቶች መካከል ለአርሶአደሩ ጉልበት ቆጣቢ የሆነ የመስመር መዝርያ ቴክኖሎጂዎች አለመቅረባቸው፣ አርሶአደሩ ተግባሩን አድካሚ አድርጎ የማየት ዝንባሌ እያደገ መምጣቱ፣ ባለሙያው በግብርና ኤክስቴንሽን ምክረ-ሃሳብ መሠረት ለአርሶ አደሩ ተገቢውን ድጋፍና ክትትል አለማድረጉ ለአብነት ይጠቀሳሉ፡፡

**የአትክልትና ፍራፍሬ መስኖ ዉሀ አጠቃቀም አፈጻጸም**

ባለፉት ሶስት ዓመታት በመስኖ ልማቱ በ2012 ከተደረሰበት በመስኖ የለማውን 220.500 ሄ/ር መሬት እና የተገኘውን 27.67 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ወደ 250.400 ሄ/ር በመስኖ ለማልማትና ምርቱን ወደ 34.83 ሚሊዮን ኩንታል ለማሳደግ ታቅዶ ባለፉት 3 የዕቅድ ዓመታት በመስኖ የለማው የመሬት 280.060 (111%) እንዲሁም በምርት 33.20 ሚሊየን ኩንታል (95%) ማድረስ ተችሏል፡፡ እንዲሁም በመስኖ የሚለሙ ሰብሎች አጠቃላይ ምርታማነት በተመለከተ በ2012 ዓ.ም ከተመዘገበው 140.6 ኩንታል በሄ/ር ባለፉት ሶስት ዓመታት የዕቅድ ዘመን በአማካይ ወደ 139.50 ኩንታል በሄ/ር ለማድረስ ታቅዶ ምርታማነቱን 118 ኩንታል በሄ/ር (የዕቅዱን 84%) ማድረሰ የተቻለ ሲሆን ምርታማነቱ 2012 ከተደረሰበት የ16% ቅናሽ አሳይቷል፡፡

ስንዴን በመስኖ ማልማትን በሚመለከት የስንዴ ፍላጎትን ለማሟላትና ከዉጭ የሚገባዉን ለመተካት በተደረገዉ ርብርብ ባለፉት ተከታታይ ሶስት ዓመታት በትኩረት ተይዞ እየተሰራ

ይገኛል፡፡ በመሆኑም ባለፉት ሶስት ዓመታት ዉስጥ 214.064 ሄ/ር መሬት በማልማት 8.497.260 ኩ/ል ለማምረት ታቅዶ 189.432 ሄ/ር (የዕቅዱን 88.49%) እንዲሁም 6.239.710 ሚ/ኩ ኩ/ል (የዕቅዱን 73%) ተከናዉኗል፡፡ በዚህ በኩል አፈጻጸሙ ሲታይ በጥንካሬ የሚወሰድ ቢሆንም ክልሉ ካለዉ የመስኖ አቅም አንጻር ከዚህ በላይ ሰፋ አድረጎ በማቀድና በትኩረት ይዞ መሰራት እንዳለበት ያመላክታል፡፡

ቡናና ፍራፍሬ ልማትን በተለከተ ባለፉት ሶስት ዓመታት ቡና 22.805.259 ሚሊየን ፤የቆላ ፍራፍሬ 21.487.000 እንዲሁም የደጋ ፍራፍሬ 2.235.553 ችግኝ ለማዘጋጀት ታቅዶ ቡና 18.855.338 (የዕቅዱን 83%) ፤ የቆላ ፍራፍሬ 17.369.137 (የዕቅዱን 80%) እንዲሁም የደጋ ፍራፍሬ 1.276.952 (የዕቅዱን 57%) ለማከናወን ተችለዋል፡፡

በእንስሳት ሀብት ዘርፍ የእንስሳትንና አሳ ሀብት ልማት ምርትና ምርታማነትን ማሳደግና ከዘርፉ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጥቅሞች በላቀ ደረጃ ከፍ ለማድረግ የሚስችሉ ግቦች በዕቅዱ ውስጥ ተካተው ሲተገበሩ መቆየታቸው ይታወቃል፡፡ በመሆኑም በሶስት ዓመታት ዉስጥ የተከናወኑ ተግባራት አፈፃፀም እና የተመዘገቡ ውጤቶች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ 2012 ሪፖርት መሠረት በክልሉ ከአካባቢ ዝርያ ላሞች 1.197 ሊትር ወተት በቀን የሚመረት ሲሆን ከተሻሻሉ ላሞች 10 ሊትር በቀን እንደሚገኝ መረጃው ያሳያል፡፡ በክልሉ ከሚመረተው የወተት ምርት በአብዛኛው ከዳልጋ ከብት ሲሆን ከአገረሰብ ዝርያዎች የሚገኘው የወተት ምርት 97% ይሸፍናል፡፡ቀሪው 3% የሚሆነው ከክልስ ላሞች የሚገኝ ነው፡፡ የክልሉ የነፍስ ወከፍ ዓመታዊ የወተት ፍጆታ ደግሞ ከ19 ሊትር አይበልጥም፡፡ ይህ መረጃ ከአደጉት ሀገራት አማካይ 217 ሊትር እና ከአፍሪካ ሀገራት 25 ሊትር ዓመታዊ ፍጆታ ጋር ሲነፃፀር በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ይህንን ሁኔታ ለመቀየር እና ለማሻሻል በዕቅድ ተይዞ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ባለፉት ሶስት ዓመታት የወተት ምርትን በ2012 ከተደረሰበት 1.2 ሚ/ን ቶን ሊተር ወደ 1.52 ሚ/ን ቶን ሊትር ለማሳደግ ታቅዶ 1.65 ቶን ሊተር ወተት (የዕቅዱን 108%) ማምረት ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ ከ10 ዓመቱ መጨረሻ ይደረስበታል ተብሎ ከተያዘዉ ዕቅድ ጋር ሲነጻጸር (የዕቅዱን 53%) ቶን ሊተር ወተት ማምረት ተችሏል፡፡

በዕቅድ ዘመኑ ለታየው የወተት ምርት ዕድገት አስተዋፅኦ ካደረጉት ምክንያቶች መካከል በወተት ኮሞዲቲ ወጣቶችን ማደራጀት እና ዘመናዊ የወተት ከብቶች አያያዝን እንዲከተሉ መደረጉ፣ በወተት ሀብት ልማት ገበያ ተኮር የኤክስቴንሽን አገልግሎት በስፋት እየተሰጠ

መሆኑ፣ በወተት ሀብት ልማት የግል ባለሀብቶች ተሳትፎ እንዲጨምር በየደረጃው ምቹ ሁኔታዎች መፈጠራቸው፣ የተለያዩ የዝርያ ማሻሻል ስልቶች ተግባራዊ መደረጋቸው፤ የወተት ኅብረት ሥራ ማህበራትና ማሰባሰቢያ ማዕከላትን የማጠናከርና የማቋቋም ሥራዎች መከናወናቸው፣ የወተት ምርት በስፋት በሚመረትባቸው አካባቢዎች የወተት ማቀነባበሪያዎች እንዲቋቋሙ መደረጉ፣ የእንስሳት መኖ ልማት እና የእንስሳት ጤና ስራዎች ከፍተኛ እገዛ ማድረጋቸው እና ባህላዊ የወተት ከብት እርባታን ወደ ተሻሻለ የቤተሰብ ከብት እርባታ እንዲሁም አነስተኛ ስፔሻላይዝድ የወተት ከብት እርባታ ወደ መካከለኛ ስፔሻላይዝድ የወተት ከብት እርባታ እንዲሸጋገሩ ከፍተኛ ጥረት መደረጉ ተጠቃሾች ናቸው፡፡

የሥጋ ምርትን በተመለከተ ባለፉት ሶስት ዓመታት በ2012 ከተደረሰበት 0.27 ሚ/ቶን በአማከይ ወደ 0.5179 ሚሊየን ቶን ለማሳደግ ታቅዶ 0.47 ሚሊየን ቶን (የዕቅዱን 89%) ሥጋ ምርት ማምረት ተችሏል፡፡ በዚህ በኩል የተመዘገበው አፈፃፀም በተመሳሳይ የሶስት ዓመቱ አፈፃፀም ከመነሻው ዓመት 2012 ጋር ሲነፃፀር በ0.2 ሚ/ቶን ሥጋ ወይም በ74% እድገት አሳይቷል፡፡

በሥጋ ሀብት ልማት የተያዘውን ዕቅድ ከማሳካት አኳያ በዕቅድ ዘመኑ ከታዩ ማነቆዋች መካከል የሥጋ ምርታማነትን በማሳደግ ዙሪያ የዝርያ ማሻሻል ስራው ዝቅተኛ መሆኑ፤ በእንስሳት ማድለብ ለተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች እና ባለሀብቶች ያለባቸውን የገበያ ችግር በዘላቂነት መፍታት የሚያስችሉ የሥጋ ፋብሪካ እና ማቀነባበሪያ ተቋማት በክልላችን አለመኖራቸው፤ በሥጋ ማምረት ተግባር ለሚሰማሩ አምራቾች የመሬት አቅርቦት አለመኖር፣ የብድር አቅርቦት ውስንነት እና የሥጋ ምርትን የበለጠ ለማዘመን የተደረገው የሙያ ድጋፍና ክትትል አናሳ መሆን ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ባለፉት ሶስት ዓመታት የሚመረተዉ የእንቁላል ምርት በ2012 ከነበረበት 523 ሚሊየን እንቁላል ወደ 564 ሚሊየን እንቁላል ለማድረስ ታቅዶ 772 ሚሊየን (የዕቅዱን 136%) የእንቁላል ምርት ማምረት ተችሏል፡፡ በዚህ በኩል የተመዘገበው አፈፃፀም በሶስት ዓመት ዉስጥ ይደረስበታል ተብሎ ከተያዘው ዕቅድ አኳያ ከ100% በላይ የተከናወነ ቢሆንም ለክልላችን ህዝብ በነፍስ ወከፍ የሚደርሰዉ በዓመት 24 እንቁላል መሆኑ መረጃዉ ያመላክታል፡፡ በመሆኑም ክልሉ ለደሮ እርባታ ካለዉ ምቹ ሁኔታና ተጠቃሚ አንጻር ብዙ ያልተሰራበት ተግባር መሆኑን ያሳያል፡፡

ክልሉ ለንብ ሀብት ልማት ካለው ምቹ የሆነ የሥነ-ምህዳር ቀጣናዎች ጋር ተያይዞ የንብ ሀብት ልማትን ለማዘመን የዕቅድ ዘመን በትኩረት ከሚከናወኑት ተግባር አንዱ ነው፡፡ በመሆኑም

ባለፉት ተከታታይ ሶስት ዓመታት የማር ምርትን በ2012 ከተደረሰበት18,300 ቶን የማር ምርት ባለፉት ሶስት ዓመታት ወደ 20.10 ቶን ለማድረስ ታቅዶ 29.30 ቶን ማር (የዕቅዱን 145% ) ማምረት ተችሏል፡፡

የተመዘገበው አፈፃፀም ባለፉት ሶስት ዓመታት የተመረተው የማር ምርት ከመነሻው ዓመት (2012) 18.300 ቶን ጋር ሲነፃፀር በ11 ቶን ወይም በ60% በማሳደግ የተከናወነ መሆኑ ሪፖርቱ ያመላክታል፡፡ በሌላ በኩል 2022 መጨረሻ ይደረስበታል ተብሎ ከተያዘዉ ዕቅድ (26.31) ቶን ሲነጻጸር (111%) ተከናዉኗል፡፡ ይህ አፈጻጸም የሚያሳየዉ በሶስት ዓመት ዉስጥ የ10 ዓመቱ ዕቅድ ቀድሞ እንደተፈጸመ መሆኑን ያሳያል፡፡

በክልሉ ዓሣ ሊመረትባቸው የሚችሉ በርካታ የውኃ አካላት የሚገኙበትና በዓመት እስከ 30ሺህ ቶን ዓሣ የማምርት እምቅ ያለው መሆኑ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም ባለፉት ሶስት ዓመታት የዓሣ ስጋ ምርትን በ2012 ከተደረሰበት 0.008 ሚሊየን ቶን ወደ 0.0115 ሚሊየን ቶን ለማድረስ ታቅዶ ማድረስ የተቻለዉ 0.01 ሚሊየን ቶን ወይም የዕቅዱን 78% መሆኑን ያመላክታል፡፡

የቆዳና ሌጦ ምርትን በ2012 ከተደረሰበት 7.32 ሚሊየን 2022 መጨረሻ ወደ 12.10 ሚሊየን እንዲሁም ባለፉት ተከታታይ ሶስት ዓመታት በአማካይ 8.1 ሚሊየን ቆዳና ሌጦ በማምረት ለማዕከላዊ ገበያ ለማቅርብ ታቅዶ 7.6 ሚሊየን ቶን የተከናወነ ሲሆን ከ10 ዓመቱ ዕቅድ አንጻር (የዕቅዱን 63%) ማድረስ የተቻለ እና ባለፉት 3 ዓመታት በአማካይ 7.6 ሚሊየን (የዕቅዱን 93.8%) የቆዳና ሌጦ ምርት ለማዕከላዊ ገበያ ማቅርብ ተችሏል፡፡ በዚህ በኩል የተመዘገበው አፈፃፀም ከዕቅዱ አንጻር የተሸለ አፈጻጸም ቢያሳይም ለዘርፉ ትኩረት ባለመስጠቱ ለኢኮኖሚዉ ዕድገት የሚያበረክተዉ አስተዋጾ አንጻር በጣም ዝቅተኛ መሆኑ ለዘርፉ በቂ ትኩረት ሰጥቶ እየተሰራ አለመሆኑን ያመላክታል፡፡ በዚህ በኩል በቀጣይ የዕቅድ ዘመን ፖሊሲ ከማሻሻል ጀምሮ የሚታዩ ችግሮችን በመፍታት በትኩረት ተይዞ መሰራት እንዳለበት ያሳያል፡፡ በዘርፉ የሚታዩ ችግሮች ለአብነት ደረጃውን የጠበቀ ቄራ በክልሉ አለመቋቋሙ፣ በየከተሞቹ የዕርድ ቦታ አለመዘጋጀቱ፣ በክልሉ የነበሩ የቆዳና ሌጦ ኢንዱስትሪዎች መዘጋታቸው፣ የቆዳና ሌጦ ምርት የዋጋ አወሳሰን ለተወሰኑ የግል ባለሀብቶች እንዲወስኑ የተደረገ በመሆኑ የመግዣ ዋጋው ባልተጠበቀ ሁኔታ መውደቅ እና ይህን ተከትሎ ምርቱ በከፍተኛ ደረጃ እየባከነ መሆኑ እና በባለቤትነት የቆዳና ሌጦን የምርት ግብይት የሚመራ ተቋም አለመኖር ተጠቃሾች ናቸው፡፡

ስለሆነም በዚህ በኩል በቀጣይ የዕቅድ ዘመን ፖሊሲ ከማሻሻል ጀምሮ የሚታዩ ችግሮችን በመፍታት በትኩረት ተይዞ መሰራት እንዳለበት ያሳያል፡፡

አጠቃላይ የእንስሳትና አሳ ሀብት ልማት ምርትና ምርታማነትን ስንመለከት ከዕቅዱ አንጻር የተገኘዉ አፈጻጸም ከ100% በላይ መፈጸማቸዉ በጥንካሬ ሊወሰድ ሚችል ሲሆን በሌላ በኩል ክልሉ ካለዉ የእንስሳትና አሳ ሀብት የመልማት አቅም ሲታይ ብዙም ያልተሰራበት እንደሆነ መረጃዉ ያመላክታል ፡፡ በመሆኑም በመጣዉ አፈጻጸም ሳንዘናጋ የዕቅድ ችግር መሆኑን ተገንዝቦ በቀጣይ ቀሪ የዕቅድ ዓመታት የመልማት አቅምን መሰረት ያደረገ ዕቅድ በማቀድና በመተግበር ልማቱን ማሳደግ ይገባል፡፡

የግብርና ምርምር ሥራዎች አፈጻጸም በሚመለከት የግብርና ልማትን ምርታማነትን ለማሳደግ እና ዘላቂነቱን ለማረጋገጥ ለተለያዩ ሥነምህዳሮች ተስማሚ የሆኑ፣ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ማነቆዎችን መፍታት የሚያስችሉ፣ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ የሚያስችሉ፣ ለአግሮ ኢንዱስትሪ በግብዓትነት የሚያገለግሉ፣ ገበያ ተኮር የሆኑና የተሻሻሉ የሰብል፣ የእንስሳት፣ የደን፣ የአፈርና ውኃ አያያዝ እና የምግብ ሳይንስ ቴክኖሎጂዎች፣ አሠራሮች እና የፖሊሲ አቅጣጫ ጠቋሚ ምክረ ሐሳቦችን በማላመድ፣ በማፍለቅ፣ በማባዛትና በማስረፅ የግብርና ልማቱን ለመደገፍ እየተከናወነ ይገኛል፡፡

በለፉት ሶስት ዓመታት በአጠቃላይ 245 ቴክኖሎጂዎችን/ ምክረ ሐሳቦችን ለማውጣት ታቅዶ 277 ኖሎጂዎችን/ምክረ-ሃሳቦችን (የዕቅዱን 113%) ማውጣት የተቻለ መሆኑን ያሳያል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያን በተመለከተ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሕዝቡን ፍትሐዊ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት በማረጋገጥ እና የተረጋጋ ማሕበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መሠረት በመጣል በሀገራችን ብሎም በክልላችን ሁለንተናዊ ልማትን ለማፋጠን ትኩረት የተሰጠው ንዑስ ዘርፍ ነው፡፡ በመሆኑም ባለፉት ሶስት ዓመታት በኅብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፋፊያ በኩል በዕቅድ ተይዘው የተከናወኑ ሥራዎች በተመለከተ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራትን ማቋቋም በተመለከተ በ2012 ከተደረሰበት 2484 ባለፉት ሶስት ዓመታት ውስጥ 300 ማህበራት በዕቅዱ ዘመን ማጠናቀቂያ ደግሞ ወደ 2012 ከተደረሰበት አፈጻጸም ሳይጨምር 2484 አባላትን ለማቋቋም ታቅዶ ባለፉት 3 የዕቅድ ዓመታት በተደረገው

እንቅስቃሴ 3329 (የዕቅዱን 1109%) ማህበራት ለማቋቋም ተችሏል፡፡ ከዚህ አፈፃፀም መረዳት እንደሚቻለው የዕቅድ ችግር በመኖሩ አፈጻጸሙን ከመጠን በላይ ከፍ ኢንዲል አድርጓል፡፡

በዕቅድ ዘመኑ የመሠረታዊ የገ/ቁ/ብ/ የኅብረት ሥራ ማህበራት ብር 1.341 ቢሊየን ከቁጠባ ለማሰባሰብ ታቅዶ ብር 2.172 ቢሊየን (የዕቅዱን 161.9%) ማሰባሰብ የተቻለ መሆኑ ታውቋል፡፡

የመ/ኅብረት ሥራ ማህበራት የብድር አቅርቦትና ሥርጭትን በተመለከተ የመሠረታዊ ባፉት ሶስታ ዓመታት ብር 10.88 ቢሊየን ብድር ለአባላት ለማሰራጨት ታቅዶ ብር 8.50 ቢሊየን (የዕቅዱን 78%) የተሰራጨ መሆኑ ታውቋል፡፡

የኅበረት ሥራ ማህበራት የኦዲት አገልግሎት በተመለከተ በዕቅድ ዘመኑ በድግግሞሽ ለ214 ዩኒየኖች እና ለ24,685 መሠረታዊ የኅ/ሥ/ማህበራት የሂሳብ ምርመራ ለማድረግ ታቅዶ ለ173 (የዕቅዱን 81%) ዩኒየኖች እና ለ12,569 (የዕቅዱን 51%) መሠረታዊ የኅ/ሥ/ማህበራት የኦዲት አገልግሎት መስጠት ተችሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በኦዲት አገልግሎትን የታዩ ጉድለቶችን ሙሉ በሙሉ ለማስመለስ ታቅዶ 17 ከመቶ የሚሆነው ብቻ እንደተመለሰ ታውቋል፡፡ እስካሁን መመለስ ያልቻለው ጉድለት ከ420 ሚሊየን ብር በላይ መሆኑ መረጃዉ ያሳያል፡፡

### 3.1.2. ውኃና ኢነርጅ ልማት አፈጻጸም

የዘርፉ የትኩረት አቅጣጫዎች የክልሉን ህዝብ የንጹህ መጠጥ ውኃ ተጠቃሚ በማድረግ ጤናው ተጠብቆ በልማቱ የሚኖረው ተሣትፎ እንዲያድግና ሙሉ ጊዜውን በምርት ተግባር ላይ የሚያሳልፍ ብቁ ዜጋ ማፍራት ነዉ፡፡ በመሆኑም ባለፉት ሶስት ኣመታት በዕቅድ ተይዘዉ የተከናወኑ ተግባራትን እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

የክልሉን የንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋን በ2012 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 66.82% በመነሳት ባለፉት ሶስት ዓመታት የ7.24% የሽፋን እድገት በበመጨመር ወደ 74.06.% በማድረስ ለ1,623,657 ህዝብ ተጠቃሚ ለማድረስ ታቅዶ 4.20 % በማሳደግ 74 % የዕቅዱን (58%) በማድረስ 1624,378 (100%) ህዝብ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

የገጠር የንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋን በ2012 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 67.52% በመነሳት ባለፉት ሶስት ዓመታት የ7.02% የሽፋን እድገት በበመጨመር ወደ 74.54.% በማድረስ ለ1,259,854 ህዝብ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 6.33% በማሳደግ 73.85% % የዕቅዱን (58%) በማድረስ 2,236,662 (100% በላይ) ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

በከተማ በ2012 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 67.52% የንጹህ መጠጥ ዉሃ ሽፋን በመነሳት በሶስት ዓመታት ዉስጥ የ4.18 % ሽፋን እድገት በመጨመር የከተማ ንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋን 71.7 % በማድረስ ማሳደግ 363,803 ህዝብ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 4.65% ሽፋን እድገት በመጨመር 72.17 የዕቅዱን % 106 በማድረስ 387,696 (100%) ህዝብ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

የገጠር ውኃ ተቋማትን የብልሽት መጠን ከነበረበት ከ12.89% ላይ 1.13 በመቀነስ ወደ 11.76% ለማድረስ ታቅዶ 1.44 በመቀነስ 11.45% በማዉረድ የዕቅዱን 127% መፈጸም ተችሏል፡፡ ከዉሃ ብክነት ጋር በተያያዘም በሶስት ዓመታት የዕቅድ ዘመን በከተማ ያለዉን የውሃ ብክነትን ምጣኔ 2012 ከተደረሰበት 22.85 % ላይ 0.17 % በመቀነስ ወደ 22.68% ንጽህናውን የጠበቀ የመጠጥ ውሃ ለማዳረስ ታቅዶ፤ በተለያዩ ከተሞች የዉሃ ብክነት መንስኤዎችን በመለየት የዉሃ ብክነቱን ለመቀነስ የሚያስችሉ ስራዎችን በመስራት ወደ 1.34% በመቀነስ 21.52% ማድረስ ተችሏል በዚህም የእቅዱ 105% የተከናወነ ሲሆን ከ10 ዓመቱ ዕቅድ አንጻር ሲታይ ዝቅተኛ በሚባል ደረጃ የተፈጸመ በመሆኑ በቀጣይ የዕቅድ ዘመናት የዉሀ ብክነቱን ለመቀነስ በትኩረት ተይዞ መሰራት እንዳለበት ያመላክታል፡፡

ከአማራጭ የኢነርጂ ምንጮች ቴክኖሎጂዎች ማስፋፊያ ዕቅድ አፈጻጸም አንጻር በክልሉ አማራጭ የኢነርጂ ምንጮችን እና ቴክኖሎጂዎችን በማልማት፣ በማላመድ፣ በማሰራጨት፤ በደን ሀብት ላይ የሚደርሰውን ሚዛናዊ ያልሆነ ተፅዕኖ መቀነስ ተቋሙ ከተቋቋመለት አላማ አንዱ ነዉ፡ በመሆኑም የተሻሻሉ ኃይል ቆጣቢ ምድጃዎች ባለፉት ሶስት ዓመታት 702,000 ሀይል ቆጣቢ ምድጃዎችን በማስመረትና በማሰራጨ 2,087,540 ህዝብ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 583,629 የተሻሻሉ ማገዶ ቆጣቢዎችን በማሰራጨት የዕቅዱን 83% እንዲሁም 2164791 ህዝብ (የዕቅዱን103%) ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል የቤተሰብና ተቋማት ባዮጋዝ ተጠቃሚዎችን ባለፉት ሶስት ዓመታት 6,250,000 ቤተሰብና ተቋማት ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 5,826,000 (የዕቅዱን 93%) ባዮጋዝ ተጠቃሚ እንዲሆኑ አስችሏል፡፡

በሌላ በኩል በክልሉ አማራጭ የኢነርጂ ምንጮችን እና ቴክኖሎጂዎችን በማልማት፣ በማላመድ፣ በማሰራጨት፤ የኤሌክትሪክ አቅርቦትን ጥራትንና ደህንነትን በመቆጣጠር ዘርፉ ለክልሉ ዘላቂ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት የበኩሉን ሚና እንዲጫወት ለማድረግ በገጠር መንደሮችና ከተሞች ከአማራጭ ኢነርጂ ምንጮችና ቴክኖሎጂዎች (የዉሃ ሃይል፣የፀሃይ


ሃይል፣የንፋስ ሃይል) የኤሌክትሪክ ሃይል የተጠቃሚዉን ቁጥር 391,741 ለማድረስ ታቅዶ 347,472 የዕቅዱን 88.7% እንዲሁም ከታዳሽ ኃይል 4.08 ሜጋዋት ለማምረት ታቅዶ 2.36 ሜጋ ዋት (የዕቅዱን 57.8%) ኤሌክትሪክ ሀይል ለገጠሩ ህብረተሰብ ማቅረብ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ ከንጹህ መጠጥ ዉሃ ተግባራት አንጻር በገጠርም ሆነ በከተማ በተከናወኑ ተግባራቶች አብዛኛዉ የክልሉ ህብረተሰብ የንጹህ መጠጥ ዉሃ ተጠቃሚ እንደሆነ የሚያመላክት በመሆኑ ጥሩ አፈጻጸም እንደነበረዉ ያመላክታል፡፡ በመሆኑም በቀጣይ የእቅድ አመታት ይህን አፈጻጸም አጠናክሮ በማስቀጠል እና ዉስንነቶችን በማረም የክልሉ ህዝብ ሙሉ በሙሉ የንጹህ መጠጥ ዉሃ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ይገባል፡፡ በተመሳሳይ በገጠር መጠጥ ዉሃ ተቋማት የተጠቃሚወች ማህበር በማቋቋም የተከናወነዉ ተግባር ጥሩ አፈጻጸም እንደነበረዉ ቢያሳይም በተቃራኒዉ የዉሃ ተቋማትን ብልሽት እና የዉሃ ብክነት መቆጣጠር ግን በ10 ዓመቱ መጨረሻ ከተቀመጠዉ ዕቅድ አንጻር ከፍተኛ ዉስንነት ታይቷል፡፡

### 3.1.3. የመንገድ ዕቅድ አፈጻጸም

በክልላችን የመንገድ ተደራሽነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣውን የኢኮኖሚና ማህበራዊ እድገት ዘላቂነትና ፍትሐዊነት ለማረጋገጥ እንዲሁም ከህዝብ ቁጥር ጋር ቁርኙት ያለው የመንቀሳቀስ ፍላጎትን ታሳቢ ያደረገ የመንገድ መሰረተ ልማት ግንባታ፣የተቀናጀና ተደራሽነቱ የተረጋገጠ የመንገድ መሠረተ ልማት አገልግሎት መዘርጋት ተገቢ መሆኑን በመገንዘብ ባለፉት 3 ዓመታት (2013 እስከ 2015) መንግስት ያቀዳቸውን የተለያዩ እቅዶች በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት የመንገድ መሰረተ ልማት ግንባታዎች ሲሰሩ ቆይተዋል፤ይህም በመሆኑ ህብረተሰቡ የመንገድ አገልግሎት እንዲያገኝ ከመደረጉ በተጨማሪ በህብረተሰቡ ኑሮ ላይ መሻሻልና ብዙ ለውጦች ተመዝግበዋል፡፡


በዚህ መሰረት በመደበኛ በጀት መንገድ ግንባታ ዘርፍ በአስር አመቱ መሪ ዕቅድ መጨረሻ ላይ 2606.2 ኪ/ሜ ለመገንባት እንዲሁም ባለፉት ሶስት ዓመታት 772.2 ኪ/ሜ የመንገድ ግንባታ ለማከናወን ታቅዶ 389.036 ኪ/ሜ ለመገንባት የተቻለ ሲሆን ከሶስት ዓመቱ ዕቅድ አንጻር 50.4% የተከናወነ ሲሆን ከአስር ዓመቱ መሪ ዕቅድ 14.92% ተከናዉኗል፡፡




**ግራፍ-3፡በመደበኛ በጀት የክልል ጠጠር መንገድ ግንባታ አፈጻጸም**

በመሆኑም የመንገድ ዘርፉ ካለዉ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አንጻር ሲታይ አፈጻጸሙ ዉስንነት ያለበት በመሆኑ ባለፉት ሶስት ዓመታት ታቅደዉ ያልተከናወኑ የመንገድ ግንባታዎችን በቀሪ ዓመታት የዕቅድ አካል በማድረግ እንዲከናወኑ ማድረግ ይጠበቃል፡፡

በሌላ በኩል በዩራፕ መንገድ ግንባታ ዘርፍ በአስር ዓመቱ መሪ ዕቅድ መጨረሻ ለመድረስ 7650 ኪ/ሜ መንገድ እንዲሁም ባለፉት ሶስት ዓመታት 650 ኪ/ሜ መንገድ ለመገንባት ታቅዶ በሶስት ዓመት ዉስጥ 935.45 ኪ/ሜ ተከናዉኗል፡፡ አፈጻጸሙም ከሶስት ዓመቱ አንጻር (143%) ሲሆን ከ10 ዓመቱ (12%) በዚህም የክረምት ከበጋ የመንገድ በ10 ዓመቱ መጨረሻ 23702 ኪ/ሜ እንዲሁም ባለፉት ሶስት ዓመትት 4752.4 ክ/ሜ ለመገንባት በዕቅድ ተይዞ በሶስት ኣመት ዉስጥ 4051.4 ኪ/ሜ የተከናወነ ሲሆን ከሶስት ዓመቱ 85.24% እና ከ10 ዓመቱ 17% ለመፈጸም ተችሏል፡፡




**ግራፍ-፡4ክረምት ከበጋ የሚያስተናግዱ መንገዶች ዕቅድ አፈጻጸም**

የመንገድ ጥግግትን በ1000 ኪ.ሜ$^2$ በ10 ዓመቱ መሪ ዕቅድ መጨረሻ 282.9 ኪ/ሜ እንዲሁም ባለፉት ሶስት ዓመታት 179.1 ኪ/ሜ የመንገድ ጥግግቱን ለማሳደግ በታቀደዉ መሰረት ባለፉት ሶስት ዓመታት የዕቅድ ዘመን 171.89 ኪ/ሜ በማከናወን ከሶስት ዓመቱ (95.97%) የተከናወነ ሲሆን ከ10 ዓመቱ (60.76%) መፈጸም ተችሏል። እንዲሁም በአማካኝ ክረምት ከበጋ መንገድ ለመድረስ የሚወስደውን አማካይ የእግር ጉዞ በ2012 በ10 ዓመቱ መጨረሻ ላይ 21.21 ደቂቃ እና ባለፉት ሶስት ዓመታት 33.49 ደቂቃ ለመቀነስ ታቅዶ ባለፉት ተከታታይ ሶስት ዓመታት ዉስጥ ወደ 35.43 ደቂቃ እንዲቀንስ በማድረግ የዕቅዱን (94.52%) ህብረተሰቡ በእግር ይፈጅበት የነበረዉን እርቀት በተወሰነ መልኩ መቀነስ ተችሏል።

የፌደራል አስፓልት መንገድ ግንባታ በ10 ዓመቱ መሪ ዕቅድ መጨረሻ 1997 ኪ/ሜ እንዲሁም ባለፉት ሶስት ዓመታት 362 ለመገንባት በታቀደዉ መሰረት ባለፉት ሶስት ዓመታት ዕቅድ ዘመን 353.3 ኪ/ሜ በማከናወን ከሶስት ዓመቱ (97%) የተከናወነ ሲሆን ከ10 ዓመቱ (17%) መፈጸም ተችሏል።በተጨማሪም የፌደራል ጠጠር መንገድ በ10 ዓመቱ መሪ ዕቅድ መጨረሻ 703.9 ኪ/ሜ እንዲሁም ባለፉት ሶስት ዓመታት 164 ኪ/ሜ መንገድ ለመገንባት በታቀደዉ መሰረት ባለፉት ሶስት ዓመታት የዕቅድ ዘመን 104 ኪ/ሜ በማከናወን ከሶስት ዓመቱ (63.4%) የተከናወነ ሲሆን ከ10 ዓመቱ (14.77%) መፈጸም ተችሏል።

የከተማ አስፋልት መንገድ ግንባታ በ10 ዓመቱ መጨረሻ 201.2 ኪ/ሜ እንዲሁም ባለፉት ሶስት ዓመታት 50.4 ኪ/ሜ ለመገንባት ታቅዶ 59.245 ኪ/ሜ በማከናወን ከሶስት ዓመቱ 117.5% የተከናወነ ሲሆን ከ10 ዓመቱ ዕቅድ ጋር ሲነጻጸር 29.44% ተፈጽሟል። የከተማ ጠጠር መንገድ ግንባታ በ10 ዓመቱ መጨረሻ 8804.5 ኪ/ሜ እንዲሁም ባለፉት ሶስት ዓመታት 2206.8 ኪ/ሜ ለማድረስ ታቅዶ 1911.16 ኪ/ሜ ጠጠር መንገድ የተገነባ ሲሆን የሶስት ዓመቱ አፈጻጸም 86.6% ሲሆን ከ10 ዓመቱ ጋር ሲነጻጸር 21.7% ተፈጽሟል። እንዲሁም የከተማ ኮብል መንገድ ግንባታ በ10 ዓመቱ መጨረሻ 2430 ኪ/ሜ መንገድ እንዲሁም ባለፉት ሶስት ዓመትት 547 ኪ/ሜ ለመገንባት በዕቅድ ተይዞ የሶስት አመቱ ክንዉን 299.63 ኪ/ሜ ሲሆን አፈጻጸሙ በሶስት ዓመታት ዉስጥ 54.77% ከ10 ዓመቱ ዕቅድ አንጻር (12.33%) ለማድረስ ተችሏል።

የመንገድ ስራ ዘርፍ አንዱ አላማ የገጠር ቀበሌዎችን በመንገድ ማስተሳሰር እና ህብረተሰቡ በሰፊዉና በብዙ አማራጭ የመንገድ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ነዉ። በመሆኑም ክረምት ከበጋ በሚሰራ መንገድ የተገናኙ ቀበሌዎች በቁጥር በ10 ዓመቱ 3383 እንዲሁም ባለፉት ሶስት

ዓመታት 274 ቀበሌዎችን በመንገድ ለማገናኘት ታቅዶ የሶስት አመቱ ክንዉን 48 ብቻ ሲሆን አፈጻጸሙ ከሶስት ኣመቱ 17.51% ሲሆን ከ10 ዓመቱ ዕቅድ ጋር ሲነጻጸር (1.41%) በመንገድ ለማገናኘት ተችሏል፡፡

በመንገድ ልማቱ ዘርፍ በሽዎች የሚቆጠሩ ኪሎሜትር መንገዶች ቢገነቡም መነሻችን ከአጠቃላይ በክልሉ መገንባት ከሚገባው የመንገድ መጠን አንፃር በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የነበረ በመሆኑና ከሽፋን አኳያ ብዙ መስራትን ስለሚጠይቅ በቀጣይ የእቅድ ዘመናት ያልተከናወኑትን ግቦች አካቶ በማቀድ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መስራት እንዳለብን ሪፖርቱ ያመላክታል፡፡ በተለይም በመደበኛ እና ገጠር መንገድ ልማት ደረጃ የተገነቡ መንገዶች ዝቅተኛ ከመሆናቸው ባሻገር በሁሉን አቀፍ ገጠር መንገድ ልማት የተገኛኙ ቀበሌዎች ከጠቅላላው 17.51 በመቶ ብቻ መሆናቸውና ክረምት ከበጋ መንገዱ አገልግሎት እንዲሰጥ በማድረግ ረገድ ገና ብዙ ስራዎችን መስራት የሚጠይቅ ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ በመንገድ መሰረተ ልማት ግንባታው ሂደት የተገኙት ውጤቶችና መልካም አፈፃፀሞች ከሚጠይቀውና ከተበጀተው ሃብት አንጻር መልካም ተደርጎ ቢወሰድም በክልሉ ዉስጥ የተረጋጋ ሰላም ባለመኖሩ በታቀደዉ ልክ አለመፈጸማቸዉ እንደ ዋና ችግር የሚወሰድ ሲሆን ከህብረተሰቡ ፍላጎትና ከመንገዶች ደረጃና ጥገና ጋር በተያያዘ አሁንም ያልተፈቱ ችግሮች አሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል የመንገድ መሠረተ ልማት ግንባታዎች ከፍተኛ ካፒታልና ክህሎት የሚጠይቁ በመሆኑ በተፈለገው ፍጥነት መንቀሳቀስ አለመቻል፣ የግንባታ ተቋራጮች እና አማካሪዎች አቅም ውስንነት እና ግንባታዎችን በወቅቱና በጥራት ያለማጠናቀቅ፣ የሚገነቡትን መሠረተ ልማቶች በብቃት የማስተዳደር ተቋማዊ አቅም አነስተኛ መሆን በዘርፉ የሚታዩ መሠረታዊ ችግሮች ናቸው፡፡ በመሆኑም በዘርፉ ፈጣንና አስተማማኝ ለውጥ በማምጣት ለኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ማሳደግ ይገባል፡፡

### 3.1. 4. የማዕድን ሀብት ልማት አፈፃፀም

የክልሉን የሥነ ምድር ጥናት በ1፡50,000 የካርታ መስፈርት ሽፋኑን ወደ 25,871.63 ካ.ኪ.ሜትር ለማሳደግ ታቅዶ አፈጻጸሙም ወደ 25,771 ካ.ኪ.ሜትር ጥናት በማካሄድ ከሦስት ዓመቱ 99.61 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ 16.40 በመቶ መሆኑን ያሳያል፡፡ በተደረገው የስነ-ምድር ጥናትም ወርቅ፣ ኦፓል፣ ግራናይት፣ እብነበረድ፣ ጂስፐር፣ አጌት፣ ባዛልት፣ ኳርቲዝ፣ ብረት፣ ሲናባር፣ ኮፐር፣ ኒኬል፣ ሳልፈር፣ የድንጋይ ከሰል፣ ካኦሊን፣

ራዮላይት፣ ሊትየም ማዕድናት በክልሉ መኖራቸውን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ የክልሉን የማዕድን ልማት ቀጠና በ1፡100,000 በሆነ መስፈርት ለይቶ የመሰረታዊ ጂኦሎጅካል ካርታ ሽፋንን ወደ 20,000 ካ.ኪ.ሜ ለማሳደግ ዒላማ ተይዞ ከ3 ዓመቱ 100 መቶው እንዲሁም ከ10 ዓመቱ 66.67 በመቶ መፈጸም እንደተቻለ ያሳያል፡፡ በ1፡50,000 በሆነ መስፈርት የክልሉን የማዕድን ሀብት አመላካች/አለኝታ 1 ካርታ ለማዘጋጀት ታቅዶ በሶስት ዓመቱም ሆነ በአስር ዓመቱ 1 ካርታ በማዘጋጀት 100 ከመቶው መፈጸም ተችሏል፡ ፡ በክልል ደረጃ የጂኦሳይንስ ቤተ ሙከራ እና ጂኦሙዚየም ማዕከል ለማቋቋም የታቀደ ቢሆንም ማዕከል ማቋቋም አልተቻለም፡፡

ከመረጃው እንደምንረዳው የስነ-ምድር ጥናቱና ካርታ ስራ ሽፋን በማሳደግ እና የልማት ቀጠና ካርታ በማዘጋጀት በኩል የተገኘው አፈጻጸም ጥሩ መሆኑን እና ክልሉ ያለውን የማዕድን ሀብት ለይቶ በማወቅ በኩል ጥሩ አፈጻጸም እንዳለው የሚያሳይ ቢሆንም በአስር ዓመት የተያዘውን ግብ ለማሳካት በቀሪ ዓመታት ከዚህ በተሻለ መንገድ መፈጸም ይጠበቃል፡፡ በሌላ በኩል በክልል ደረጃ መቋቋም ያለበትን ጂኦሳይንስ ቤተ ሙከራ በበጀት እጥረት ምክንያት መቋቋም ባለመቻሉ በክልል ደረጃ መለየት የሚገባቸውን የማዕድን ሀብቶች ለመለየት ችግር ስለፈጠረ በቀጣይ ይህ ቤተ ሙከራ ሊቋቋም እና ወደ ስራ ሊገባ ይገባል፡፡ ተቋሙ በአስር ዓመቱ ፖሊሲ ማትሪክስ የተቀመጠውን ዕቅድ አሟጦ አቅዶ ወደስራ በመግባት በኩል ክፍተቶች ያሉ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን በቀጣይ ቀሪ ዓመታት በሶስት ዓመቱ መታቀድ የነበረባቸው 1,696.79 ካ.ኪ.ሜ የስነ-ምድር ጥናትና ካርታ ሽፋን ተጨምሮ መታቀድ እና መተግበር ይኖርበታል፡፡

የክልሉን የማዕድን ፍለጋና ክምችት ጥናት መረጃን ወደ 533 ካ.ኪ.ሜ ለማሳደግ ታቅዶ ከሶስት ዓመቱ 100 ከመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ 5.47 በመቶ ብቻ መፈጸም ተችሏል፡ ፡ ይህ የሚያሳየው ከአስር ዓመቱ ግብ ለመድረስ ተቀንሰው የታቀዱ 961.35 ካ.ኪ.ሜ የማዕድን ፍለጋና ክምችት ጥናት ተጨምረው መታቀድ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የከበሩና የጌጣጌጥ ማእድናትን (ወርቅ፣ ኦፓል፣ አጌት፣ ጃስፐር) ፍለጋና ክምችት ግመታ ጥናት ወደ 24 ካ.ኪ.ሜ ለማሳደግ ታቅዶ 23.5 ካ.ኪ.ሜ በማከናወን ከሶስት ዓመቱ 97.9 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ 7.94 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ በተደረገው ጥናትም በሰሜን ሸዋ፣ ዚገም፣ ሰሜን ወሎ እና ወልቃይት ጠገዴ የከበሩና ጌጣጌጥ ማእድናት መኖራቸውን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከመረጃው ማረጋገጥ እንደተቻለው የከበሩ ማዕድናት ፍለጋና ክምችት

ተግባርን በትክክል አቅዶ ወደ ተግባር በመግባት በኩል ውስንነቶች እንዳሉ እና በቀጣይም ሳይታቀዱ የቀሩ 36.5 ካ.ኪ.ሜ ጥናት ጨምሮ በማቀድ የተሻለ አፈጻጸም ማስመዝገብ የሚጠበቅ ይሆናል፡፡

<u>ሠንጠረዥ</u>T 1_፡ የሥነ-ምድር ጥናት ዕቅድ መረጃ

| ተ.ቁ | ተግባር | መለኪያ | የ3 ዓመት ዒላማ | ተቋሙ ያቀደው ዒላማ | ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የክልሉ የስነ-ምድር ጥናትና ካርታ ስራ ሽፋን በ 1፡50,000 መስፈርት ማሳደግ | ካ.ኪ.ሜ | 27,568 | 25,871 | -1,696 |
| 2 | የክልሉን የማዕድን ፍለጋና ክምችት ጥናት መረጃ ማሳደግ | ካ.ኪ.ሜ | 1,494 | 533 | -961 |
| 3 | የከበሩና እና የጌጣጌጥ ማዕድናትን (ወረቅ፣ ኦፓል፣ አጌት፣ ጃስፐር) ፍለጋና ክምችት ግመታ ጥናት መረጃ ማሳደግ | ካ.ኪ.ሜ | 61 | 24 | -37 |

ሌላው የኢንዱስት እና ኮንስትራክሽን ማዕድናት ፍለጋና ክምችት ግመታ መረጃን ወደ 558 ካ.ኪ.ሜ ለማሳደግ ታቅዶ ከሦስት ዓመቱ 100 ከመቶ ከአስር ዓመቱ ደግሞ 6.47 ከመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ ከመረጃው መረዳት እንደተቻለው ተቋሙ በሶስት ዓመት ውስጥ አቅዶ መፈጸም ከነበረበት ዒላማ ውስጥ 740 ካ.ኪ.ሜ ቀንሶ በማቀዱ የሶስት ዓመቱን አፈጻጸም 100 ከመቶው መፈጸም የቻለ ቢሆንም በዚህ አካሄዱ የአስር ዓመቱን ዒላማ መድረስ እንደማይቻል ያመላክታል፡፡ ስለዚህ የአስር ዓመቱን ዒላማ ከግብ ለማድረስ በፖሊሲ ማትሪክሱ መሰረት ዕቅዶች ታቅደው ሊፈጸሙ ይገባል፡፡

የብረትና ብረት ነክ ማዕድናት ፍለጋና ክምችት ግመታ ጥናት ቦታዎች መረጃ ሽፋን 58 ካ.ኪ.ሜ ለማድረስ ታቅዶ 62 ካ.ኪ.ሜ በመፈጸም ከሶስት ዓመቱ 106 ከመቶ እና ከአስር ዓመቱ ደግሞ 10 ከመቶ መፈጸም የተቻለ ሲሆን ተቋሙ በሶስት ዓመቱ አቅዶ መፈጸም ከነበረበት ዕቅድ ውስጥ 53.4 ካ.ኪ.ሜ ቀንሰው በማቀድ ከአስር ዓመቱ መድረስ የሚጠበቅባቸውን ዒላማ ለማድረስ የማይቻል ስለሆነ በፖሊሲ ማትሪክስ የተቀመጠውን ዒላማ በትክክል አቅዶ መፈጸም የሚጠበቅ ይሆናል፡፡ ስለሆነም በአስር ዓመቱ የታቀዱ ዒማዎችን ከግብ ለማድረስ ዕቅዶቻችን በተሻለ መጠን አቅደን ወደ ትግበራ ልንገባ ይገባል፡፡

በሌላ በኩል ስትራቴጅካል ጠቀሜታ ያላቸው እሴት የሚጨምሩ 114 አምራች ኢንዱስትሪዎች የምርመራና የምርት ፈቃድ ለመስጠት ዒላማ ተይዞ ለ227 አምራች ኢንዱስትሪዎች የምርመራና የምርት ፈቃድ መስጠት ተችሏል፡፡ ያለው አፈጻጸም ከሦስት ዓመቱም ሆነ ከአስር ዓመቱ ከ100 ከመቶው በላይ የተፈጸመ ሲሆን ይህን ዒላማ በአስር ዓመቱ ለማሳካት እንደሚቻል መረጃው ያሳያል፡፡ የማዕድን ማምረት ስራ ባለፈቃድ ኢንተርፕራይዞችን ወደ 10,959 ለማሳደግ ዒላማ ተይዞ ለ8,452 ኢንተርፕራይዞች የማዕድን ማምረት ስራ ፈቃድ በመስጠት ከሶስት ዓመቱ 77.12 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ ደግሞ 14.33 በመቶ ብቻ መፈጸም ተችሏል፡፡ ከመረጃው ለመረዳት እንደተቻለው አሁን ባለን አፈጻጸም መሠረት የአስር ዓመቱን ዒላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስቸግር እንደሆነ ያሳያል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ተቋሙ ዒላማዎችን በትክክል አቅዶ ወደ ተግባር ከመግባት ይልቅ ዒላማዎችን ቀንሶ እየተገበረ በመሆኑ እንደሆነ ያሳያል፡፡ በሶስት ዓመቱ ታቅዶ መተግበር ከነበረበት የኢንተርፕራይዞች የማምረት ፈቃድ ውስጥ 4,820 ቀንሶ እየተገበረ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ስለዚህ የአስር ዓመቱን ዒላማ ከግብ ለማድረስ ተቀንሰው የታቀዱ ዒላማዎች የዕቅድ አካል ሆነው ተጨምረው በማቀድ ወደ ተግባር ሊገባ ይገባል፡፡

**<u>ሠንጠረዥ2</u> ፡ የማዕድን ፍለጋ፣ ክምችትና የስራ ዕድል ፈጠራ መረጃ**

| ተ.ቁ | ተግባር | መለኪያ | የ3 ዓመት ዒላማ | ተቋሙ ያቀደው ዒላማ | ልዩነት በቅናሽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የኢንዱስት እና ኮንስትራክሽን ማዕድናት ፍለጋና ክምችት ግመታ መረጃን ማሳደግ | ካ.ኪ.ሜ | 1,298 | 558 | - 740 |
| 2 | የብረትና ብረት ነክ ማዕድናት ፍለጋና ክምችት ግመታ ጥናት ቦታዎች መረጃ ሽፋን ማሳደግ | ካ.ኪ.ሜ | 111 | 58 | - 53 |
| 3 | የማዕድን ማምረት ስራ ባለፈቃድ ኢንተርፕራይዞችን ማሳደግ | ካ.ኪ.ሜ | 15,779 | 10,959 | - 4,820 |

ለ183 የኢንዱስትሪ ማእድናት ማምረት ስራ ፈቃድ በመስጠት እሴት ጭማሪ ኢንዱስትሪዎችን እንዲስፋፉ ለማድረግ ዒላማ ተይዞ ለ155 እሴት ጭማሪ ኢንዱስትሪዎች የማምረት ስራ ፈቃድ በመስጠት ከሶስት ዓመቱ 84.7 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ

ደግሞ 73.81 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ ከመረጃው ለመረዳት እንደተቻለው ተቋሙ የአስር ዓመቱን ዒላማ ከግብ ለማድረስ ጥሩ እንደፈጸመ ያሳያል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ተቋሙ ዕቅዱ ከተሰጠው ዒላማ በላይ አቅዶ ወደ ተግባር በመግባቱ ስለሆነ ለወደፊትም ዕቅዶችን አሟጦ በማቀድ ወደ ተግባር መግባት የአስር ዓመቱ ዒላማ ከግብ ለማድረስ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ ለ155 እሴት ጨማሪ ኢንዱስትሪዎችን የኮንስትራክሽን ማዕድናት ማምረት ስራ ፈቃድ በመስጠት እንዲስፋፉ ለማድረግ ዒላማ ተይዞ ለ156 እሴት ጨማሪ ኢንዱስትሪዎች የኮንስትራክሽን ማዕድናት ማምረት ስራ ፈቃድ በመስጠት ከሶስት ዓመቱ 100 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ 31.2 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ ለ400 የከበሩና በከፊል የከበሩ ማእድናት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በመስጠት እሴት የሚጨምሩ ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ ለማድረግ ዒላማ ተይዞ ለ287 ማእድናት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በመስጠት ከሶስት ዓመቱ 71.75 በመቶ ከአስር ዓመቱ ደግሞ 39.32 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ ከመረጃው ለመረዳት እንደተቻለው ለእሴት ጨማሪ ኢንዱስትሪዎች የማምረት ስራ ፈቃድ እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በመስጠት በኩል የተሻለ እንደተፈጸመ የሚያሳይ ሲሆን ለወደፊትም ከዚህ የበለጠ ለመፈጸም ያልተሰሩ ተግባራትን የዕቅድ አካል አድርጎ በመፈጸም ወደ ተግባር ሊገባ ይገባል፡፡

በማዕድን ዘርፍ ከሚሰማሩ ባህብቶች፣ ኩባንያዎች እና ኢንተርፕራይዞች የሚፈጠር የስራ ዕድልን ወደ 116,260 ለማሳደግ ዒላማ ተይዞ ለ108,278 ስራ ፈላጊዎች የስራ እድል በመፍጠር ከሶስት ዓመቱ 93.13 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ 24.33 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ ከመረጃው ለመረዳት እንደተቻለው በማዕድን ዘርፍ ለስራ ፈላጊዎች የስራ ዕድል በመፍጠር ለክልሉ የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት የተፈጠረው የስራ ዕድል አበረታች መሆኑን የሚያሳይ ስለሆነ ለወደፊትም በዚህ ዘርፍ የሚፈጠረውን የስራ ዕድል አጠናክሮ ማስቀጠል የሚጠበቅ ይሆናል፡፡


ከዘርፉ የውጭ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ምርት መጠንን ወደ 45,947 ኪ/ግ ለማሳደግ ዒላማ ተይዞ 59,147 ኪ.ግ በማድረስ ከሦስት ዓመቱ ከ100 በመቶ በላይ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ 38.86 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ ከመረጃው መረዳት እንደሚቻለው የከበሩ ማእድናትን የምርት መጠን ማሳደግ የተቻለው በፖሊሲ ማትሪክ ላይ ከተቀመጠው ዒላማ በላይ 21,025 ኪ.ግ ምርት ለማምረት ተጨማሪ አቅደው ወደስራ

በመግባታቸው የተገኘ ውጤት መሆኑን ያሳያል፡፡ ስለሆነም የአስር ዓመቱን ዒላማ ለማሳካት ምቹ ሁኔታ ሊፈጥር የሚችል ስራ የተሰራ በመሆኑ ለወደፊትም ይህን ውጤት ማስቀጠል ይኖርብናል፡፡

ከኮንስትራክሽንና ኢንዱስትሪ ማዕድናት ዘርፍ የውጭ ምንዛሬ ማስገኛ ምርት መጠንን ወደ 6,412,321 ቶን ለማሳደግ ዒላማ ተይዞ 5,795,729 ቶን በማግኘት ከሶስት ዓመቱ 90.38 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ ደግሞ 25.04 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ የሶስት ዓመቱን አፈጻጸም 100 በመቶ ለመፈጸም ያልተቻለው በፖሊሲ ማትሪክሱ ላይ ከታቀደው ዒላማ ውስጥ 17,352,271 ቶን ምርት ቀንሰው በማቀድ አቅማቸውን አሟጠው መፈጸም ባለመቻላቸው ውጤት ማስመዝገብ አልተቻለም፡፡ ስለዚህ ለወደፊት ትኩረት በመስጠት የውጭ ምንዛሬ የሚያስገኙ ምርቶችን በማምረት ለክልሉ ኢኮኖሚ ድርሻውን ሊወጣ ይገባል፡፡

ከማዕድን ዘርፍ የሚገኝ የውጭ ምንዛሬ ገቢን ወደ 33 ሚሊዮን ዶላር ለማሳደግ ዒላማ ተይዞ 20 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሬ ገቢ በማግኘት ከሦስት ዓመቱ 61.20 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ ደግሞ 11.73 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ ከመረጃው መረዳት እንደተቻለው የተገኘው የውጭ ምንዛሬ ገቢ ከታቀደው ዕቅድ አኳያ ሲታይ በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ተቋሙ የአስር ዓመቱን ዒላማ ከግብ ለማድረስ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ በመፈጸም የውጭ ምንዛሬ ገቢን ሊያሳድግ ይገባል፡፡

ሌላው ከማዕድን ዘርፍ የሚገኘውን የሀገር ውስጥ ገቢ ወደ 212 ሚሊዮን ብር ለማሳደግ ዒላማ ተይዞ 200 ሚሊዮን ብር የሀገር ውስጥ ገቢ በማግኘት ከሶስት ዓመቱ 93.98 በመቶ እንዲሆም ከአስር ዓመቱ ደግሞ 17.87 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ ከመረጃው ለመረዳት እንደሚያሳየው የታቀደውን ዒላማ ሙሉ በሙሉ መፈጸም እንዳልተቻለ እና በዚህ አካሄድ የአስር ዓመቱን ዒላማ ለማሳካት የሚያስቸግር መሆኑን ያሳያል፡፡ በቀሪ ዓመታት ተቋሙ የሀገር ውስጥ ገቢን ለማሳደግ በፖሊሲ ማትሪክሱ የተቀመጠውን ዒላማ ሳይቀንስ በትክክል አቅዶ ወደ ተግባር ሊገባ ይገባል፡፡




**ግራፍ-5፡ከማዕድን ዘርፍ የተገኘ ገቢ**

ከዘርፉ ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የምንጠቀምበት የምርት መጠንን ወደ 15 ሚሊዮን ሜ/ኩ ለማሳደግ ታቅዶ 14 ሚሊዮን ሜ/ኩ የምርት መጠን በማግኘት ለሀገር ውስጥ ፍጆታ እንዲውሉ በማድረግ ከሶስት ዓመቱ 89.66 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ ደግሞ 55.68 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ ከመረጃው ለመረዳት እንደተቻለው የተገኘው ውጤት ጥሩና አበረታች ሲሆን ተቋሙ በፖሊሲ ማትሪክሱ ከታቀደው ዕቅድ በተጨማሪ 7.99 ሚሊዮን ሜ/ኩ ተጨማሪ ዒላማ አቅዶ በመፈጸም የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ እንደቻለ ያሳያል፡፡

ከውጭ የሚገቡ የማዕድን ውጤቶችን በአገር ውስጥ በሚመረቱ የማዕድን ውጤቶች የመተካት አቅምን ወደ 1,037,002 ቶን ለማሳደግ ዒላማ ተይዞ 677,429 ቶን በማምረት የመተካት ስራ የተሰራ ሲሆን ከሶስት ዓመቱ 65.33 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ ደግሞ 6.53 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ ከመረጃው ለመረዳት እንደተቻለው ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በአገር ውስጥ በመተካት የውጭ ምንዛሬን በማስቀረት በኩል የተሰራው ስራ ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡ ውጤቱ የቀነሰበት ምክንያትም በፖሊሲ ማትሪክስ ከተሰጣቸው ዒላማ ውስጥ 18,600 ቶን ቀንሶ በማቀድ አሚጠ መጠቀም ያለበትን አቅም አሚጠ ወደ ተግባር መግባት ባለመቻሉ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ስለሆነም ተቋሙ ለወደፊት እቅዶችን አሚጠ በማቀድ እና ወደ ተግባር በመግባት ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን የመተካት ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡

በማዕድን ሀብት ከማህበረሰቡ ልማት ፈንድ 21 ሚሊዮን ብር በመሰብሰብ የህብረተሰብን ተጠቃሚነት ለማሳደግ ዒላማ ተይዞ 9 ሚሊዮን ብር በመሰብሰብ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ሲሆን ከሦስት ዓመቱ 55.98 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ ደግሞ 9.53 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ ሌላው በማዕድን ስራዎች የተጎዱ 12.73 ሄ/ር መሬት መልሶ በማልማት ወደነበሩበት እንዲመለሱ ለማድረግ ዒላማ ተይዞ 3.2 ሄ/ር መሬት መልሰው እንዲለሙ በማድረግ ከሶስት ዓመቱ 25.25 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ ደግሞ 2.47 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ በመረጃው መሰረት የማህበረሰብ ዒላማ ፈንድ በመሰብሰብ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ በማድረግ በኩል የተሰራው ስራ ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡ በማዕድን ዘርፍ በሚሰማሩ ግለሰቦች የሚጎዱ መሬቶች መልሶ በማልማት በኩል የተሰራው ስራ በጣም ዝቅተኛ እና የሚጎዱ መሬቶችን እንዲያገግሙ በማድረግ በኩል የተሰራው ስራ ዝቅተኛ በመሆኑ ተቋሙ ለወደፊት ትኩረት ሰጥቶ ሊፈጽም ይገባል፡፡

ተቋሙ በሶስት ዓመቱ ውስጥ የታቀዱ ተግባራት በሚፈጽምበት ወቅት ለአፈጻጸም መቀነስ በምክንያትነት የተቀመጡ ችግሮችን ለመጥቀስ ያህልም በተወሰነ ደረጃ መሻሻል ያለ ቢሆንም በየደረጃው ያለ አካል ለዘርፉ ልማት የሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆኑ፤ በሁሉም ወረዳዎች የመዋቅር አለመዘርጋት፣ የሰው ሃይል፣ በጀት እና ግብዓት እጥረት መኖር፣ በማዕድን ስራ ላይ የህገወጥ ሃይሎች መበራከት፣ ከአሠራር ውጭ ፀጋዎችን ለመቆጣጠር የመፈለግ ዝንባሌ መኖር፣ በአሰራሩ መሠረት ሲነጠቁ የማን አለብኝነት ዝንባሌ መኖር፣ ጥሬ ኦፓል ኤክስፖርት መደረጉ ከሚያስገኘው የውጭ ምንዛሬ እና ለዜጎች ከሚፈጥረው የስራ ዕድል አኳያ ብክነት የሚታይበት መሆኑ እና የህገ-ወጥ ዝውውር መበራከት፣ የተሰረዙ ፈቃዶች አስፈላጊ ሰነዶችን አቅርበው የፈቃድ መዝጋት ተግባር አለመፈጸም፣ የማህበረሰብ ልማት ፈንድን ከባለፈቃዶች በመመሪያዉ መሰረት በመሰብሰብ ለማህበረሰቡ የልማት ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጡ ስራዎችን ለመስራት ወቅታዊ እና አገራዊ የሚታዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮች መኖራቸው እንዲሁም ከአጋር አካላት ጋር በተለይም ከገቢዎች፣ ከቤቶችና ኮንስትራክሽን ጋር የገቢ ግብርን ባለፈቃዶች ስለመክፈላቸው እና የተቋራጮች ሙያ ፈቃድ የመስጠትና የማዕድን አጠቃቀም ግንዛቤ ለመፍጠር ፕላት ፎርም አለመኖር የሚሉት ዋና ዋናዎች ናቸው፡፡

የማዕድን ሀብት ለአገር ኢኮኖሚ የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ይህ ዘርፍ የማዕድን ሀብቶችን በጥናት የመለየት፣ ከውጭ የሚመጣ ምርትን

በሀገር ውሰጥ የመተካት፣ የውጭ ምንዛሬ ገቢን የማሳደግ ስራ ሊሰራ የሚገባው ዘርፍ ነው፡፡ በመሆኑም የተቋቋመበት ጊዜ አጭር ቢሆንም በማዕድን ዘርፍ የሚመረቱ የማዕድን ምርቶች በባህላዊ መንገድ በህገወጥ የመመረት እና ምንም እሴት ሳይጨመርባቸው ወደ ገበያ እየቀረቡ ስለሆነ በህገወጥ መንገድ የሚሰማሩ የማዕድን ተጠቃሚዎች ህጋዊ ስርዓት እንዲይዙ፣ ለገበያ የሚቀርቡ ምርቶችን እሴት ተጨምሮባቸው እንዲቀርቡ በማድረግ፣ ለክልላዊ ኢኮኖሚው የሚያስፈልገውን ማዕድን ከቦታ ቦታ ከመንቀሳቀሱ በፊት ከቦታው ላይ ሲመረት ተከታትሎ መዝግቦ በመያዝ የማዕድን ሀብት ለክልሉ ኢኮኖሚ የሚኖረውን ድርሻ የማሻሻል፣ የባለሙያውን የስራ ባህል የማሳደግና የባለቤትነት ስሜት ኖሯቸው እንዲሰሩ የማድረግ እንዲሁም ከአጋር አካላት ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር የበለጠ በማጠናከር በቀጣይ ዓመታት ሊተገበሩ የታቀዱ ዒላማዎችን በመፈጸም ለክልሉ ዕድገትና የህብረተሰቡ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የበኩሉን ድርሻ ሊወጣ ይገባል፡፡

### 3.1.5.መስኖና ቆላማ አካባቢዎች ተግባራት አፈጻጸም

የመስኖ ልማት የግብርና ዝመናን በማረጋገጥ በዘርፉ ምርትና ምታማነትን ለማሳደግ ያለው ሚና ከፍተኛ ነው። ከዚህ አንጻር ባለፉት ዓመታት በመስኖ ልማት ግብርናን ለማዘመንና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተጀመሩ ጥረቶች ቢኖሩም ዘርፉን በሚፈለገው ደረጃ ከማሳደግ አኳያ ብዙ ሥራዎች ይቀራሉ። በመሆኑም በልማት ዕቅዱ ዘመን የግብርናን ዘርፍ ከዝናብ ጥገኝነት በማላቀቅ የምግብ ዋስትናን በቤተሰብ ደረጃ ለማረጋገጥ በሚደረገው ጥረት ውስጥ የመስኖ መሠረተ ልማት አቅርቦትን ማሳደግ ዋነኛ የዘርፉ የትኩረት አቅጣጫ ሆኖ እየተተገበረ ይገኛል፡፡

የአነስተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ የመስኖ ልማት ዝርዝር ጥናትና ዲዛይን ማካሄድ በተመለከተ 666 የጥናትና ዲዛይን ስራ በማካሄድ 116,669 ሄ/ር መሬት ወደ መስኖ ልማት እንዲገባ ለማድረግ ዒላማ ተይዞ 33,496 ሄ/ር ማልማት የሚያስችል 428 የመስኖ ጥናትና ዲዛይን መስራት የተቻለ ሲሆን ከሁለት ዓመቱ ዒላማ አኳያ በጥናት ቁጥር 64.26 በመቶ በሄክታር 28.7 በመቶ መፈጸም የተቻለ ሲሆን ከዘጠኝ ዓመቱ ዒላማ አኳያ ደግሞ በጥናትና ዲዛይን ቁጥር 31.73 በመቶ እንዲሁም በሄክታር ደግሞ 9.53 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ ከመረጃው ለመረዳት እንደተቻለው የመስኖ ጥናትና ዲዛይን ስራዎች በፖሊሲ ማትሪክሱ ላይ የተቀመጠውን ዒላማ በሙሉ አቅዶ ወደ ተግባር በመግባት የህብረተሰቡን የመስኖ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ አለመቻሉን ያሳያል፡፡ ተቋሙ የአነስተኛ እና የመካከለኛ

የመስኖ ልማት ጥናትና ዲዛይን ስራ አፈጻጸሙ ውስንነት ያለበት ቢሆንም ወደ ተግባር የገባ መሆኑ በመልካምነት የሚወሰድ ሲሆን የከፍተኛ መስኖ ልማት ጥናትና ዲዛይን ስራን መስራት አለመቻሉ ክፍተት ያለበት መሆኑን ያሳያል፡፡ ስለዚህ በቀጣይ የትግበራ ወቅት ከዚህ በፊት ሳይታቀዱ የቀሩ ዒላማዎችነ ጨምሮ የዕቅድ አካል በማድረግ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ በመፈጸም በመስኖ የሚጠቀሙ የህ/ሰብ ክፍሎችን የማሳደግ ሊሰራ ይገባል፡፡ በክልል ደረጃ ጥናትና ዲዛይን ለሚሰራላቸው 665 አነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ መስኖ ልማት ፕሮጀክቶችን የግንባታ ክትትልና ቁጥጥር ስራ ለመስራት ዒላማ ተይዞ ለ428 ፕሮጀክቶች የግንባታ ክትትልና ቁጥጥር ስራ በመስራት ከሁለት ዓመቱ 64.36 በመቶ እንዲሁም ከዘጠኝ ዓመቱ ደግሞ 31.73 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ ከመረጃው ለመረዳት እንደተቻለው ጥናትና ዲዛይን የተሰራላቸውን ፕሮጀክቶች በየጊዜው ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ወደ ግንባታ እንዲገቡ ለማድረግ የሚደረገው ጥረትም ውስንነት ያለበት እንደሆነ እና ለወደፊት አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር በማካሄድ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በወቅቱ መፍትሄ የማስቀመጥ ስራ መስራት ይጠበቃል፡፡

በፌደራል ደረጃ ጥናትና ዲዛይን ለሚሰራለት 366,000 ሄክታር የሚያለማ 1 ከፍተኛ መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች የክትትልና ቁጥጥር ስራ ለማካሄድ ዒላማ ተይዞ ከፍተኛ የመስኖ ፕሮጀክቶችን ክትትልና ቁጥጥር ስራዎች መስራት አልተቻለም፡፡ የጥናትና ግንባታ ስራዎች ተጠናቀው ወደ ግንባታ ለሚገቡ 44,620 ፕሮጀክቶች የአካባቢና ማኀበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ ይሁንታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለማሰጠት ዒላማ የተያዘ ቢሆንም ተቋሙ ወደ ግንባታ ለሚገቡ ፕሮጀክቶች ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በቅንጅት በመስራት ሰርተፊኬት እንዲያገኙ አድርጎ ወደ ግንባታ ከማስገባት ይልቅ የተጽዕኖ ግምገማ ተካሂዶ ሰርተፊኬት ሳያገኙ ወደ ግንባታ እንዲገቡ መደረግ በክፍተት የሚታይ ሲሆን ጥናትና ዲዛይን የተሰራላቸው ፕሮጀክቶች የተጽዕኖ ግምገማ አካሂደው ሰርተፊኬት ካገኙ በኋላ ወደ ግንባታ እንዲገቡ ማድረግ የሚጠበቅ ስራ ሊሆን ይገባል፡፡

26,964 ሄክታር ማልማት የሚችሉ 276 የአነስተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ መስኖ ልማት ፕሮጀክቶችን ግንባታ ለማከናወን ዒላማ ተይዞ 36,678 ሄክታር መሬት ማልማት የሚችሉ 352 የአነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ መስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ወደ ግንባታ እንዲገቡ የተደረገ ሲሆን በፕሮጀክት ቁጥር ከሁለት ዓመቱ 127.54 በመቶ እና ከዘጠኝ ዓመቱ 12.7 በመቶ እንዲሁም በሄ.ር ደግሞ ከሁለት ዓመቱ 136 በመቶ እና ከዘጠኝ ዓመቱ 13.14

በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ ከመረጃው ለመረዳት እንደተቻለው ጥናትና ዲዛይን የተሰራላቸውን ፕሮጀክቶች ወደ ግንባታ እንዲገቡ በማድረግ በኩል የተሰራው ስራ የተሻለ እንደሆነ ቢያሳይም ተቋሙ እንዲተገብረው በፖሊሲ ማትሪክሱ የተሰጠውን ዒላማ ሙሉ በሙሉ አቅዶ በመተግበር የህብረተሰቡን የመስኖ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ውስንነት ያለበት በመሆኑ ለወደፊት ትኩረት ሰጥቶ መስራት የሚጠበቅበት ይሆናል፡፡ ሌላው አንድ ከፍተኛ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት ግንባታን በማስጀመር 1,400 ሄ/ር መሬት ወደ መስኖ እንዲገባ በማድረግ በኩል የተሰራ ስራ አለመኖሩን የሚያሳይ በመሆኑ ከፍተኛ ፕሮጀክቶችን ወደ ግንባታ በማስገባት የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይጠበቃል፡፡

**ሠንጠረዥ 3 ፡- ወደ ግንባታ የገቡ የመስኖ ፕሮጀክቶች ዕቅድ**

| ተ.ቁ | ተግባር | መለኪያ | የ2 ዓመት ዒላማ | በተቋሙ በ2 ዓመት የታቀደ | ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አነስተኛ | ቁጥር | 391 | 207 | -184 |
| | | ሄክታር | 31,344 | 11,757 | -19,587 |
| 2 | መካከለኛ | ቁጥር | 141 | 68 | -73 |
| | | ሄክታር | 22,179 | 15,207 | -6,972 |
| 3 | ከፍተኛ | ቁጥር | 1 | 0 | -1 |
| | | ሄክታር | 1,400 | 0 | -1,400 |

35 የተበላሹ የመስኖ ተቋማትን ጥገና ስራ ለማከናወን ዒላማ ተይዞ 29 የተበላሹ የመስኖ ተቋማት ጥገና በማካሄድ ወደ ማልማት እንዲገቡ ማድረግ የተቻለ ሲሆን ከሁለት ዓመቱ 82.86 በመቶ እንዲሁም ከዘጠኝ ዓመቱ ደግሞ 6.47 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ ከመረጃው መረዳት እንደተቻለው ለብዙ ዓመታት ያህል ተቋርጠው የቆዩ የመስኖ ግንባታዎች ወደ ግንባታ እንዲገቡ ማድረግ መቻሉ ጥሩ አፈጻጸም እንደሆነ ያሳያል፡፡ ተቋሙ ለወደፊት በተለያየ ጊዜ ተጀምረው የተቋረጡ የመስኖ ግንባታዎች የሚገኙ ስለሆነ ከፍተኛ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ችግሮች ተለይተው መፍትሄ በማስቀመጥ ወደ ግንባታ እንዲገቡ ማድረግ ይጠበቃል፡፡

በ33,734 ሄክታር የመስኖ ልማት ተቋማት ላይ ሊያገለግሉ የሚችሉ 11,070 የተሻሻሉ የመስኖ ቴክኖሎጅዎችን ተከላና ግንባታ ለማከናወን ዒላማ ተይዞ መቶ ፐርሰንት መፈጸም ተችሏል፡፡ ከመረጃው ለመረዳት እንደተቻለው ዘመናዊ ቴክኖሎጅዎችን ለመስኖ ተጠቃሚዎች በማድረስ በዘመናዊ ቴክኖሎጅ የሚለሙ የመስኖ ተጠቃሚዎችን የማሳደግ ስራ መሰራቱ ጥሩ አፈጻጸም እንዳለው ያሳያል፡፡ አዲስ በሚገነቡ የመስኖ ተቋማት 347 የውሃ ተጠቃሚ ማኅበራትን በማቋቋም ወደስራ እንዲገቡ ማድረግ የተቻለ ሲሆን በመስኖ ዘርፍም ለ46,172 ዜጎች የስራ ዕድል በመፍጠር ከ100 ፐርሰንት በላይ መፈጸም ተችሏል፡

ተቋሙ በሁለት ዓመቱ ውስጥ የታቀዱ ተግባራት በሚፈጽምበት ወቅት ብዙ ችግሮች ያጋጠሟቸው ሲሆን ለመጥቀስ ያህልም በክልላችን የተፈጠረው የጸጥታ ችግር ፕሮጀክቶ ገብተው ስራ መጀመር አለመቻላቸው፣ በመዋቅር መዘግየት ምክንያት የጥናትና ዲዛይን ሥራዎችን በተፈለገው መንገድ መፈፀም አለመቻላቸው፣ ለግንባታ የሚያገለግሉ የፋብሪካ ውጤቶች ዋጋ በመጨመሩና ከገበያ ላይ በመጥፋቱ ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ መጠናቀቅ አለመቻላቸው፣ አማካሪ ድርጅቱ በተሰጠው የውል ጊዜ ጥናቶችን አጠናቆ ማስረከብ አለመቻል፣ የበጀትና የግብዓት እጥረት መኖሩ፤ የግዥዎች መጓተት፣ በአዲስ ወደ ግንባታ በሚገቡ መካከለኛ፣ አነስተኛ እና ጥገና ፕሮጀክቶች ዋጋ ድርድር ረዘም ያለ ጊዜ በመፍጀቱ ውል በመያዝ ግንባታ ለማስጀመር ጫና መፍጠሩ እና ድርጅቶች የዋጋ ማሻሻያ ጥያቄ በተደጋጋሚ መቅረብ ናቸው፡፡

ተቋሙ የቢሮ ቁሳቁሶችን በትውስትና በጋራ ለመጠቀም ጥረት በማድረግ፣ ግልጽና ውስን ጨረታዎችን እንደመነሻ በመውሰድ፣ ለዞን መመሪያዎችና ወረዳዎች ቡድን መሪዎችን እንዲሟሉ በማድረግ፣ ለመስኖ ውኃ ተጠቃሚ ማህበራት በማቋቋሚያ አዋጅና መመሪያ ዙሪያ ስልጠና በመስጠት፣ በተለያዩ ሁኔታዎች የባከነውን ጊዜ ለማካካስ በተደራጀ መልኩ በፍጥነት የግንባታ ርክክብ በመፈጸም፣ የሲሚንቶ እጥረት ጥያቄዎችን ለክልሉ እና ለፌደራል መንግስት በማቅረብ በፌደራል ግብርና ሚኒስቴር አማካኝነት ከሲሚንቶ አቅራቢ ማህበራት ጋር በማስተሳሰር ሲሚንቶ እንዲያገኙ በማመቻቸት፣ ከላይ እስከ ታች ካለው አመራር ጋር ተደጋጋሚ ውይቶችን በማድረግ የግንባታ መዘግየት መንስዔ የሆኑ ችግሮችን ፈትቶ ተቋራጮች ወደ ስራ እንዲገቡ በማድረግ እና ከአማካሪ ድርጅቶችና ከተቋራጮች ጋር ተደጋጋሚ ውይይት በማካሄድ ያጋጠሙ ችግሮች ለመፍታት እንደምቹ ሁኔታና መፍትሄ በመጠቀም የታቀዱ ተግባራት ከግብ ለማድረስ ጥረት ማድረግ ተችሏል፡

የአማራ ክልል ከአለው የቆዳ ስፋት ውስጥ 13.2 ሚሊዬን ሄክታር በመስኖ መልማት የሚችል እና ሰፊ የገጸ ምድር እና የከርሰ ምድር ውሃ ያለው ክልል ነው፡፡ ተቋሙ ይህን ሀብትና ፀጋ ተጠቅሙ 33,496 ሄ/ር ሊያለሙ የሚችሉ 428 የአነስተኛና መካከለኛ የመስኖ ልማት ጥናትና ዲዛይን ስራ በማከናወን 36,678 ሄ/ር የሚያለሙ 352 ፕሮጀክቶች ግንባታ ተጠናቀው ወደ ልማት እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ ይሁን እንጅ ክልሉ ያለውን ሀብት ተጠቅሞ በመስኖ እንዲለማ በማድረግ በኩል እስካሁን በመስኖ እየለማ ያለው መሬት ከአንድ በመቶ በታች እንደሆነ መረጃዎች የሚያሳይ ሲሆን ሁሉም ህብረተሰብ የዓመት ዝናብ ጠብቆ ምርት እያመረተ በመሆኑ የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ አለመቻሉን ያሳያል፡፡
በመሆኑም ተቋሙ በመስኖ እየለማ ያለውን መሬት በመንግስት፣ በግለሰብ እና በልማት ድርጅቶች መረጃ ለይቶ በመያዝ፣ የተቋረጡ ከፍተኛ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ወደ ልማት እንዲገቡ በማድረግ፣ የተጠናቀቁ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ወደ ልማት እንዲገቡ በማድረግ፣ ወደ ማልማት የገቡ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶችን የተለያዩ ብልሽቶች ሲያጋጥሙት ክትትል በማድረግ ቶሎ ወደ ጥገና እንዲደረግና ልማቱን እንዲያስቀጥል በማድረግ እንዲሁም አስፈላጊ ቴክኖሎጅዎችን በሚፈለገው መጠን ለህብረተሰቡ አሰራጭቶ ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ የህብረተሰቡን የመስኖ ተጠቃሚነት በማሻሻልና ህብረተሰቡን ከዝናብ ጥገኝነት በማላቀቅ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በትኩረት ሊሰራ ይገባል፡፡

### 3.1.6. የአካባቢና ደን ጥበቃ ዘርፍ ልማት አፈጻጸም


የአካባቢና ደን ጥበቃ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ትግበራ በልማት ዕቅዶች ውስጥ ሜይንስትሪም ተደርጎ እንዲሰራ ማስተባበርና መምራት፣ ክልላዊ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ቅነሣን የመለካት፣ የመመዝገብ እና የማረጋገጥ ስራ ከአጋር አካላት ጋር በመሆን ተግባራዊ ማድረግ፣ የልማት ፕሮጀክቶች በአካባቢና በማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ሥርዓት ውስጥ እንዲያልፉ ክትትል ማድረግና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፤ የማምረቻና አገልግሎት ሰጭ ተቋማት የአካባቢና ዜጎችን ደህንነት እያከበሩ መሆናቸውን በክትትልና ቁጥጥር በማረጋገጥ የዜጎችን አካባቢ ደህንነት ማስከበር፣ በዘርፉ የህብረተሰቡንና ባለድርሻ አካላትን ግንዛቤ በማጎልበት አጋርነትና ተሳትፎን ማሳደግ፤ የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎና ቅንጅታዊ አሰራር ማጠናከር፣ ወጣቶችና ሴቶች የልማቱ ተሳታፊና ተጠቃሚ መሆናቸውን

ማረጋገጥ፣ የድጋፍ፣ ክትትልና ግምገማ ስርዓት በመዘርጋት በዕቅድ የተያዙ ተግባራት በጥራትና ውጤታማነት እንዲፈጸሙ ማድረግ ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ እነዚህን ተግባራት ለመፈጸም የአስር ዓመት ዕቅድ አቅዶ በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡

በዚህ መሠረት የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖን ለመቋቋምና ለመቀነስ የሚረዱ 16 ዓይነት የአረንጓዴ ቴክኖሎጅዎችን ለማተዋወቅና ለማሸጋገር ዒላማ ተይዞ 14 ዓይነት ቴክኖሎጅዎችን ማስተዋወቅ የተቻለ ሲሆን ከሶስት ዓመቱ 87.50 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ 70 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ የCRGE ተግባሪ መስሪያ ቤቶችና ሌሎች ተቋማት ሜይንስትሪም አድርገው እንዲሰሩ 21 ጊዜ ለመከታተልና ለመደገፍ ዒላማ ተይዞ 12 ጊዜ መከታተልና መደገፍ የተቻለ ሲሆን ከሶስት ዓመቱ 66.67 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ 11 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ ከመረጃው ለመረዳት እንደተቻለው የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖን ለመቀነስ የሚያስችሉ 14 ዓይነት የሆኑ 188,550 የኃይል ቆጣቢ ምድጃዎችና ሶላር ቴክኖሎጅዎችን የማስተዋወቅና ተደራሽ የማድረግ ስራ መሰራቱን ያሳያል፡፡
በደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ፣ አወጋገድና መልሶ ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ ለሚሰማሩ አካላት አጋዥ ቴክኖሎጅዎችን እንዲተገብሩ 20 ጊዜ ክትትል ለማድረግ ዒላማ ተይዞ 2 ጊዜ ብቻ ክትትል በማድረግ ከሶስት ዓመቱ 15.38 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ ደግሞ 10 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ ከመረጃው ለመረዳት እንደተቻለው የሚወገዱ ደረቅ ቆሻሻዎች መልሶ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ለማድረግ እየተደረገ ያለው ጥረት በጣም አነስተኛ እንደሆነ ያሳያል፡፡

በክልሉ የሚካሄዱ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በአካባቢ ላይ ሊያደርሱ የሚችሉትን አሉታዊ ተፅዕኖ መገምገም የሚያስችሉ የአሠራር ሥርዓቶች በመዘርጋት በአካባቢ ላይ የሚያደርሱትን ጉዳት መግታት ወይም ተፅዕኖውን መቀነስ ትኩረት የተሰጠው ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም የተሟላ የአካባቢ ተጽዕኖ ሰነድ ግምገማ ይዘው ለሚቀርቡ 12,200 አዳዲስ የልማት ፕሮጀክቶች የአካባቢ ይሁንታ ፈቃድ ለመስጠት ዒላማ ተይዞ ለ13,936 አዳዲስ የልማት ፕሮጀክቶች የይሁንታ ፈቃድ በመስጠት ከሶስት ዓመቱ ከ100 በመቶ በላይ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ 35 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የተጽዕኖ ሰነድ ግምገማ አዘጋጅተው ወደ ትግበራ ለገቡ 5,000 ነባር የልማት ፕሮጀክቶች የይሁንታ ፈቃድ ለማደስ ዒላማ ተይዞ ለ6,391 ነባር የልማት ፕሮጀክች የይሁንታ ፈቃድ ዕድሳት በመስጠት ከሶስት ዓመቱ ከ100 በመቶ በላይ ከአስር ዓመቱ ደግሞ 43 በመቶ

መፈጸም ተችሏል፡፡ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በአዲስ ከወሰዱ፣ ከነባር ዕድሳት እና ከቅጣት አገልግሎት በመስጠት 2,090,000 ብር ለመሰብሰብ ዒላማ ተይዞ 3,432,310 ብር በመሰብሰብ ከሶስት ዓመቱ 164 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ ከመረጃው ለመረዳት እንደተቻለው በልማት ለሚሰማሩ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ሰርተፊኬት ሰጥቶ ወደ ትግበራ እንዲገቡ በማድረግ በኩል የተሰራው ስራ ጥሩ እንደሆነ ያሳያል፡፡




**ግራፍ 6፡ የልማት ፕሮጀክቶች የይሁንታ ፈቃድና ዕድሳት**

በአደገኛ ኬሚካሎች ላይ 73.3 በመቶ ቁጥጥር ለማካሄድ ዒላማ ተይዞ 56 በመቶ ቁጥጥር ማድረግ የታቻለ ሲሆን ከሶስት ኣመቱ 76.36 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ 56 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡

ሌላው የደን ልማትና ሽፋንን ማሳደግ የተያዘ ግብ ሲሆን በመንግስት ደኖች ውስጥ የተከላ ቦታ በመለየት 277,550 ሄ/ር ላይ ችግኞችን ተከላ ለማካሄድ ዒላማ ተይዞ 12,139 ሄ/ር ችግኞችን በመንግስት ደኖች ውስጥ መትከል የተቻለ ሲሆን ከሶስት ዓመቱ 4.37 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ ደግሞ 23 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ ከመረጃው ለመረዳት እንደተቻለው የደን ሽፋንን ለማሳደግ በደን ሊሸፈን የታሰበው ሄክታር በጣም አነስተኛ እንደሆነ ያሳያል፡፡ አፈጻጸሙ በፖሊሲ ማትሪክስ ከተያዘው ዒላማ አኳያ ሲታይ የተሻለ አፈጻጸም እንዳለው ቢያሳይም ተቋሙ እተገብረዋለሁ ብሎ ካቀደው ዒላማ አኳያ ዝቅተኛ በመሆኑ በቀጣይ ዓመታት የደን ሽፋንን ለማሳደግ በሚደረገው ርብርብ ላይ የተሻለ

በመፈጸም አስተዋጽኦ ልናደርግ የሚገባ ሲሆን በዓመታዊ ዕቅዱና በአስር ዓመቱ ዕቅድ መካከል የመናበብ ክፍተት ያለበት ስለሆነ ሊታይ ይገባል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የደን ሽፋንን ለማሳደግ የተመረጡ 63 የማኅበራት፣ 524 የማኅበረሰብ እና 58 የመንግስት ደኖች የደን አያያዝና አጠቃቀም ፕላን በማዘጋጀት የደን አያያዝን እንዲያሻሽሉ፣ ከፍተኛ የደን ሀብት ዝውውር በሚካሄድባቸው ቦታዎች 429 ኬላዎችን የማጠናከር፣ 131 ኬላዎች የማቋቋም እና 2,169 የደን ልማትና ቁጥጥር ግብረ-ኃይል የማቋቋም ስራ መስራት ተችሏል፡፡ ለ947,346 ሄ/ር የተፈጥሮ ደኖች የተጠናከረ ጥበቃ በማካሄድ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ለመገንባት ለሚደረገው ጥረት አስተዋጽኦ ለማበርከት ዒላማ ተይዞ ለ1,246,272 ሄ/ር የተፈጥሮ ደኖች የተጠናከረ ጥበቃ እንዲያገኙ ማድረግ የተቻለ ሲሆን ከሶስት ዓመቱ ሆነ ከአስር ዓመቱ ከ100 በመቶ በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡

አሳታፊ የደን ልማት አያያዝና አጠቃቀም ስርዓት /PFM/ ተግባራዊ በማድረግ ደን በዘላቂነት እንዲጠበቅ፣ እንክብካቤ እንዲደረግለትና ጥቅም ላይ እንዲውል እየተሰራ ይገኛል፡፡ በዚህ መሠረት 183,087 ሄ/ር መሬት በአሳታፊ የደን አያያዝና አስተዳደር ስርዓት እንዲጠበቅ ለማድረግ ዒላማ ተይዞ 270,731 ሄ/ር መሬት እንዲጠበቅ በማድረግ ከሶስት ዓመቱ እና ከአስር ዓመቱ ከ100 በመቶ በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡ ከመረጃው ለመረዳት እንደተቻለው አሳታፊ የደን ዐያያዥና አጠቃቀም ስርዓትን በመተግበር ደንን ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ መቻሉ አበረታች ስራ የተሰራ ሲሆን በቀጣይ ዓመታትም ሁሉም ደኖች በአሳታፊ የደን ልማት አያያዝን እንዲተገብሩ ማድረግ ይጠበቃል፡፡

358,835 ሄ/ር የተራቆተ ተራራማ መሬት ከንክኪ ነጻ ሆኖ እንዲያገግም ለማድረግ ዒላማ ተይዞ 195,729 ሄ/ር የተራቆተ ተራራማ መሬት እንዲያገግም በማድረግ ከሶስት ዓመቱ 54.55 በመቶ መፈጸም የተቻለ ሲሆን በአስር ዓመቱ በዕቅድ ያልተያዘ በመሆኑና ተቋሙ አቅዶ እየተገበረው የሚገኝ ተግባር ነው፡፡ አፈጻጸሙ እንደሚያሳየው የተራቆተ ተራራማ መሬትን ከህ/ሰቡ ጋር በመወያየትና በመግባባት እንዲከለሉና እንዲያገግሙ በማድረግ የተሰራው ስራ አነስተኛ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን በክልላችን ብዙ የተራቆቱ ተራራማ መሬት መኖራቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት የመከለልና እንዲያገግሙ የማድረግ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡

የደን ዘርፍ ለኢኮኖሚ ዕድገት የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ማሳደግ ሌላው ግብ ተይዞ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ከተለያዩ የደን ምርት ውጤቶች የልማትና ሮያሊቲ ክፍያ 530 ሚሊዮን ብር ለመሰብሰብ ዒላማ ተይዞ 530 ሚሊዮን ብር በመሰብሰብ ከሶስት ዓመቱ 100 ከመቶ መሰብሰብ የተቻለ ሲሆን የሶስት ዓመቱ ዒላማ ከአስር ዓመቱ ዒላማ የበለጠ በመሆኑና የዕቅድ ችግር ስላለበት አፈጻጸሙ ከአስር ዓመቱ ጋር ሲነጻጸር ከሶስት ዓመቱ አፈጻጸም ጋር የበለጠ ስለሆነ ዕቅዱን የማጣጣም ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የተለያዩ የደን ምርት ውጤቶችን በጥራትና በብዛት በማምረት ወደ ውጭ እንዲላኩ በማድረግ 2.962 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሬ ለማስገኘት ታቅዶ 61,365 ሜ/ኩ አጠናና ግንዲላ፣ 10483 ሜ/ኩ ቀርቀሃ እና 2,107 ኩንታል እጣን በመላክ 2.69 ሚሊዬን ዶላር የውጭ ምንዛሬ ማግኘት የተቻለ ሲሆን ከሶስት ዓመቱ 90.82 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ 45 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡

አፈጻጸሙ እንደሚያሳየው ከደን ምርቶች የሚገኝ የውጭ ምንዛሬን ለማሳደግ ጥረት የተደረገ ቢሆንም በቀሪ ዓመታት የውጭ ምንዛሬ የሚያስገኙ ደኖችን አምርቶ ወደውጭ የመላክ ስራን በተለይ ወደውጭ የሚላክ እጣን መጠንን በመጨመር በትኩረት የሚሰራ ተግባር መሆኑን ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል 24,731 ኩ/ል ነጭ ዕጣን፣ 10,661 ከ/ል ጥቁር ዕጣን፣ 2,040 ኩ/ል ሙጫ፣ እና 11,743,495 ኩ/ል ከሰል ህጋዊ በሆነ መንገድ ተመርቶ ወደ ገበያ እንዲቀርብ ማድረግ ተችሏል፡፡ በህገወጥ መንገድ ሲዘዋወሩ ከተወረሱ የደን ምርቶች 5 ሚሊዮን ብር ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ 7.47 ሚሊዮን ብር በመሰብሰብ ከሶስት ዓመቱ 149.4 ፐርሰንት እንዲሁም ከአስር ዓመቱ 62 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ ከመረጃው ለመረዳት እንደተቻለው አሁንም ቢሆን ህገወጥ የደን ዝውውር በከፍተኛ ደረጃ እንደሚካሄድ የሚያሳይ ሲሆን ይህን ህገወጥ የደን ዝውውር ህጋዊ ሆኖ እንዲንቀሳቀስ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ በመስራት የደን ምርት ለኢኮኖሚው የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ማሳደግ ይጠበቃል፡፡

የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችን ልማት እና ሽፋን ማሳደግ ሌላው በግብ ተይዞ እየተተገበረ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በዱር እንስሳት ጥብቅ ስፍራዎች 264 ጊዜ የዱር እንስሳት በሽታ ቅኝት ለማድረግና የሚተላለፉ በሽታዎችን ንክኪ ለመቀነስ ዒላማ ተይዞ 180 ጊዜ የእንስሳት በሽታ ቅኝት በማካሄድ ከሶስት ዓመቱ 68 በመቶ መፈጸም የተቻለ ሲሆን የአስር ዓመቱ ዒላማ ስላልተቀመጠ ከአስር ዓመቱ አፈጻጸሙን ማስላት

አልተቻለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በጥብቅ ስፍራዎች 34 ጊዜ የዱር እንስሳት ቆጠራ ለማካሄድ ታቅዶ 16 ጊዜ ቆጠራ በማካሄድ ከሶስት ዓመቱ 47 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ ደግሞ 9 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ በዚህ ረገድ አፈጻጸሙን ስናይ የዱር እንስሳትን ልማት እና ሽፋን በማሳደግ በኩል የተሰራ ስራ ውስንነት ያለበት እንደሆነ ያሳያል፡፡ የዱር እንስሳትን እንደ ሀብት ቆጥሮ ይዞ ጤንነታቸውን እየጠበቁ የገቢ ምንጭ እንዲሆኑ አስቦ በመስራት በኩል ውስንነት እንደነበረበት መረጃው ያሳያል፡፡

በሌላ በኩል አምስት የዱር እንስሳት ጥብቅ ስፍራዎችን ህጋዊ ሰውነት እንዲያገኙ አለማድረግ፣ በዱር እንስሳት ጥብቅ ስፍራዎች የመሰረተ ልማት (የመንገድ፣ ጽ/ቤት፣ ሎጅና ካምፕ) ግንባታ እንዲሰራላቸው አለመደረጉ ታቅደው ያልተፈጸሙ ተግባራት ሲሆኑ ለወደፊት ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይጠበቃል፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ክፍተቶች ያሉ ቢሆንም በጥብቅ ስፍራዎች የጎብኝዎችን ቁጥር 97,333 (64%) በማድረስ እንዲሁም ከኢኮ ቱሪዝም፣ ከፊልምና ሌሎች አገልግሎቶች 2 ሚሊዮን ብር መሰብሰብ ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ የዱር እንስሳት ለክልሉ ኢኮኖሚ የሚያደርገውን አስተዋጽኦ ለማሳደግ የእንስሳትን ጤንነት የመጠበቅ፣ ህገወጥ ዝውውርን የማስቀረት፣ በቂ በጀት መድቦ መሠረተ ልማት እንዲሟላ የማድረግ እና የዱር እንስሳት ጥብቅ ስፍራዎች ህጋዊ ሰውነት እንዲኖራቸው ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይጠበቃል፡፡

ሌላው በዕቅድ ተይዞ እየተተገበረ የሚገኘው ግብ በአካባቢና ብዝሀ ህይወት ሀብት ላይ ሊከሰት የሚችለውን ጉዳት መቀነስ ነው፡፡ በመሆኑም በክልሉ የሚገኙ መጤና ተስፋፊ ዝርያዎችን ስፋትና ስርጭት የሚያሳይ የጥናት ሰነድ በማዘጋጀት መጤና ተስፋፊ ዝርያዎች መኖራቸውን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ እነዚህ መጤ፣ ተስፋፊና ወራሪ የአረም ዝርያዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ በዓይነትና በመጠን እየጨመሩ የሚገኙ ሲሆን በሥነ ምህዳር ላይ መዛባትን እያስከተሉ ከመሆናቸውም በላይ በምርትና ምርታማነት ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያስከተሉ ይገኛል፡፡ ስለሆነም እነዚህን ዝርያዎች በወቅቱ ከማስወገድ አኳያ 140,500 ሄ/ር መጤ ዝርያዎችን በህብረተሰብ ተሳትፎ ለማስወገድ ዒላማ ተይዞ 278,907 ሄ/ር መጤ ዝርያዎችን በማስወገድ ከሦስት ዓመቱ ከ100 ፐርሰንት በላይ መፈጸም የተቻለ ሲሆን በዚህ ዘመቻም 1,143,136 የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ በጣና ሀይቅ የተከሰተውን የእምቦጭ አረም ለማስወገድ ጥረት እየተደረገ ሲሆን ከአጠቃላይ 2,430 ሄ/ር ካለው የእምቦጭ አረም ስፋት አኳያ 1,578.27 ሄ/ር የእምቦጭ አረም በማሽንና

በህብረተሰብ ተሳትፎ ማስወገድ ተችሏል፡፡ በጣና ሀይቅ ላይ የተከሰተውን የእምቦጭ አረም ለማስወገድ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ቢሆንም አረሙ በየጊዜው እየተባዛ በመምጣቱ በዚህ ከቀጠለ በአጭር ጊዜ በጣና ሀይቅ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚያሳድር በመሆኑ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶና ጥናት ተካሂዶበት በአጭር ጊዜ መፍትሄ እንዲገኝ ሊደረግ ይገባል፡፡

ተቋሙ በሶስት ዓመቱ ውስጥ የታቀዱ ተግባራት በሚፈጽምበት ወቅት ብዙ ችግሮች ያጋጠሙት ሲሆን ለመጥቀስ ያህልም በቀበሌ ደረጃ የአካባቢና ደን ስራዎች በሚፈለገው ደረጃ አለመከናወን፣ የደን ግብረ ሃይልና አየር ንብረት ለውጥ አደረጃጀቶች በአግባቡ እየተመሩ አለመሆናቸው፣ የዋጋ ግብሽቱ እየጨመረ መምጣቱ፣ ከአጋር ተቋማት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር የላላ መሆኑ፣ የበጀትና የግብዓት አቅርቦት ችግር፣ በክልሉ የተፈጠረው የጸጥታ ችግር፣ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው አደገኛ ኬሚካሎች በወቅቱ እንዲወገድ አለመደረጉ፣ የህገ ወጥ ድርጊቶች መበራከት (ፍሳሽና ደረቅ ቆሻሻ፣ ደን ጭፍጨፋ፣ ህገወጥ አደን) እና ለፕሮጀክቶች የሚለቀቀው በጀት በወቅቱ እንዲለቀቅ አለመደረጉ ሲሆኑ እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ እንደምቹ ሁኔታ የተጠቀማቸው መፍትሄዎች የፈጻሚዎችና ባለድርሻ አካላትን ግንዛቤ በማሳደግ፣ ከባለድርሻና አጋር አካላት ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር በማጠናከር፣ ለሥራ አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶችን አቅም በፈቀደ መጠን በማሟላት፣ የመንግስትና ፕሮጀክት ሀብቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ አሟጦ በመጠቀም፣ የአካባቢ ህግ ጥሰት በፈጸሙ አካላት ላይ እርምጃ በመውሰድ እና የአካባቢ ተቆርቋሪ ማህበራትና ክበባት እንዲደራጁና እንዲጠናከሩ በማድረግ ያጋጠሙ ችግሮችን ፈትቶ የታቀዱ ዒላማዎች ለመፈጸም ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ተችሏል፡፡

ተቋሙ በአስር ዓመት ለመተግበር ያቀደውን ዒላማ በጥሩ ሁኔታ እየፈጸመ ይገኛል፡፡ ነገር ግን የአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ልማት አካተው የሚሰሩ ተቋማት በሚፈለገው ልክ መፈጸም አለመቻላቸው፣ የይሁንታ ፈቃድ አግኝተው ወደ ትግበራ የሚገቡ ፕሮጀክቶችን ክትትል በማድረግ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች እየፈቱ ወደ ትግበራ እንዲገቡ አለመደረጉ፣ የከተሞች የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ችግር ያለበት መሆኑ፣ ክልላዊ የሙቀት አማቂ ጋዝ የሚያደርሰውን ተፅዕኖ በጥናት መለየት፣ የተራቆቱ ተራራማ መሬቶችን በደን በመሸፈን የክልሉን የደን መጠን ለማሳደግ የተደረገው ያለው ጥረት ክፍተት ያለበት መሆኑ፣ የዱር እንስሳት ጥብቅ ስፍራዎች በመሰረተ ልማት እንዲሟሉና እንዲጠበቁ በማድረግ በኩል ክፍተት መኖሩ፣ ለዱር እንስሳት የሚደረገው ጥበቃ

የተጠናከረ አለመሆን እና በክልሉ የተከሰቱ መጤ እና ወራሪ ዝርያዎች ማስወገድ አለመቻሉ የሚጠቀሱ ዋና ዋና ክፍተቶች ሲሆኑ እነዚህን ክፍተቶች ሞልቶ ወደ ተግባር በመግባት የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ ትኩረት የሚሰጠው ተግባር ሊሆን ይገባል፡፡

### 3.1.7. ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ልማት አፈጻጸም

ሳይንስና ቴክኖሎጅ የሠው ኃብት አቅምን በመገንባት ተቋማትን መደገፍና ማብቃት እንዲሁም የአሠራር ሥርዓቶችን መዘርጋት፣ የሚለሙ አፕሊኬሽኖችን ስታንዳርዱን የጠበቀ እንዲሆን ጠንካራ ድጋፍ ማድረግ፣ የተለሙ አፕሊኬሽኖች ወደ ስራ እንዲገቡ ማድረግ፣ ችግር ፈች ጥናቶችን ከምርምር ተቋማት ጋር በመቀናጀት ማከናወን፣ ችግር ፈች የቴክኖሎጅ ልየታና ሽግግር ስራ መስራት፣ ከኢኖቬሽን ሚኒስቴር ጋር በጋራ የሚከናወኑ ተግባራትን ትኩረት መስጠት፣ የቴክኖሎጂ ልማትና ሽግግር አቅም ማጎልበት፣ ሁለገብ የማህበረሰብ የመረጃ ማዕከላት ልማትን ማሳደግ፣ የተቀናጀና ተናባቢ አሠራርን ማጎልበት፣ ቢዝነስ ኢንኩቤሽን ማዕከላት ልማትንና የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ግንባታ በክልሉ እንዲሰፋፋና ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ፣ ዲጂታል ኢኮኖሚን በዕድገት ምንጭነት መጠቀም፣ ሳይንስና ቴክኖሎጅ እንዲጎለብት እና የመንግሥትና የህዝብ አገልግሎቶችን ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ መልካም አስተዳደርን ማስፈን እና ቴክኖሎጂን ለምርታማነት ማሻሻያ ማዋል የሚሉት ዋና ዋና ግቦች ሲሆኑ እነዚህን ግቦች ከግብ ለማድረስ ዕቅድ አቅዶ እየተገበረ ሲሆን በሶስት ዓመት ውስጥ የተከናወኑ ተግባራት እንደሚከተለው ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

የቴክኖሎጅ ምርምር፣ ልማት፣ ሽግግርና አጠቃቀም አቅምን ለማጎልበት ለ237 ኢንተርፕራይዞች/ቢዝነስ ኢንኩቤሽን ካፓኒዎች በምርምር የተደገፈ ስልጠና ለመስጠት ዒላማ ተይዞ ለ103 ኢንተርፕራይዞች/ቢዝነስ ኢንኩቤሽን ካፓኒዎች ስልጠና በመስጠት ከሶስት ዓመቱ 43.46 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ ደግሞ 13.04 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ በኢንተርፕራይዞች/ካፓኒዎች የለሙ 36 ቴክኖሎጅዎችን ለማሸጋገር ታቅዶ 23 የለሙ ቴክኖሎጅዎችን ለተለያዩ ተቋማት በማሸጋገር ከሶስት ዓመቱ 63.89 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ 19.17 በመቶ መፈጸም የተቻለ ሲሆን በተሸጋገሩ ቴክኖሎጅዎች ላይ ለ180 ኢንተርፕራይዞች ግንዛቤ ለመፍጠር ዒላማ ተይዞ ለ87 ኢንተርፕራይዞች ግንዛቤ በመፍጠር ከሶስት ዓመቱ 48.33 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ ደግሞ 11 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ ከመረጃው ለመረዳት እንደተቻለው ለኢንተርፕራይዞች የተሰጠው

ስልጠና፣ ግንዛቤ እና የተሸጋገረ ቴክኖሎጅ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ ሲሆን በዚህ አካሄድ በአስር ዓመት የታለመውን ዒላማ ከግብ ለማድረስ የማይቻል መሆኑን ያሳያል፡፡ የቴክኖሎጅ ምርምር፣ ልማት፣ ሽግግርና አጠቃቀም ስልጠና ከተሰጠ በኋላ ቴክኖሎጅዎችን አልምቶ ተቋማት ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችል መሆን የነበረበት ቢሆንም ለምተው የተሸጋገሩ ቴክኖሎጅዎች ቁጥር አነስተኛ ሲሆን የተሰጠው ስልጠና ውጤታማ እንዳልነበረ ያሳያል፡፡ ስለሆነም የሚሰጡ ስልጠናዎችን ጥራት በማስጠበቅ ከስልጠና በኋላ የሚፈለገውን ውጤት ማምጣቱን ክትትል በማድረግ አዲስ ቴክኖሎጅዎችን አልምቶ በማሸጋገር የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በትኩረት ሊሰራ ይገባል፡፡

በምርምር የተለዩ 16 ቴክኖሎጂዎችን ለማሸጋገርና ጥቅም ላይ ለማዋል ዒላማ ተይዞ 9 ቴክኖሎጅዎችን በማሸጋገር በሶስት ዓመቱ 56.25 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ ደግሞ 16.07 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ በተሸጋገሩ ቴክኖሎጅዎችም 35,000 የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ዒላማ ተይዞ 359 የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ በማድረግ ከሶስት ዓመቱ 1.02 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ 0.08 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ በመሆኑም በምርምር የተለዩ ቴክኖሎጅዎችን ለይቶ እንዲሸጋገር በማድረግ በኩል ያለው አፈጻጸም ዝቅተኛ እንደሆነ የሚያሳይ በመሆኑ የአስር ዓመቱን ዒላማ ለማሳካት ከዚህ የበለጠ መስራት የሚጠበቅ ይሆናል፡፡ ሌላው በተሸጋገሩ ቴክኖሎጅዎች ላይ ተጠቃሚ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችም ሲታይ ያለው አፈጻጸም በጣም ዝቅተኛ ሲሆን አፈጻጸሙ የቀነሰበት ምክንያት ተቋሙ በሶስት ዓመት ውስጥ አቅዶ እንዲተገብር ከተሰጠው ዒላማ ውስጥ 20,000 ዒላማ ቀንሶ አቅዶ በመተግበሩ እንደሆነ መረጃው የሚያሳይ ሲሆን በቀጣይ ዓመታት የተሻሉ ቴክኖሎጅዎችን በማሸጋገር የተጠቃሚ የህብረተሰብ ክፍሎችን ለማሳደግ ከዚህ በፊት ያልተፈጸሙ ዒላማችን አካቶ በማቀድ በትኩረት መፈጸም የሚጠበቅ ይሆናል፡፡

ያደገ የቴክኖሎጅ መሠረተ ልማት ሽፋን በማሳደግ በኩል 36 አዲስ የወረዳ ኔት መሠረተ ልማት ለመዘርጋት ዒላማ ተይዞ ለአዊ ብሔረሰብ አስተዳደር ዞን 1 የወረዳ ኔት መሰረተ ልማት በመዘርጋት ከሶስት ዓመቱም ይሁን ከአስር ዓመቱ 2.77 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡ ከዚህ አንጻር የክልሉን ወረዳዎች እና ዞኖች በቴክኖሎጅ መሰረተ ልማት በማገናኘት በኩል የተሰራው ስራ በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ስለሆነም በቀጣይ ዓመታት ወረዳዎችንና

ዞኖችን በቴክኖሎጅ መሰረተ ልማት ለማገናኘት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ መስራት የሚጠበቅበት ይሆናል፡፡

የመሰረተ ልማትና የመረጃ ደህንነትን ማረጋገጥ በተመለከተ 4 የዳታ ማዕከሎች ደህንነታቸውን ለመጠበቅ ዒላማ ተይዞ 3 የዳታ ማዕከሎች ደህንነታቸው ተጠብቀው አገልግሎት እንዲሰጡ በማድረግ ከሶስት ዓመቱ 75 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ 2.14 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ ስለሆነም የዳታ ማዕከሎችን ደህንነት በመጠበቅ በኩል ያለው አፈጻጸም ክፍተት እንዳለበት ያሳያል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያትም ተቋሙ በፖሊሲ ማትሪክስ ከተሰጠው ዒላማ ውስጥ 17 ዒላማ ቀንሶ እየተገበረ በመሆኑ ሲሆን በቀጣይ ዓመታት ከዚህ በፊት ያልተፈጸሙ ዒላማዎች ግምት ውስጥ ያስገባ ዕቅድ በማቀድ ሁሉም የዳታ ማዕከሎች ደህንነታቸው እንዲጠበቅ በማድረግ በኩል በትኩረት ሊሰራ ይገባል፡፡ የቴክኖሎጅ ማዕከላትን ማደራጀትና ማጠናከር በተመለከተ 5 የምርምርና መተግበሪያ ማዕከል ለማቋቋም ዒላማ ተይዞ 5 ማዕከል በማቋቋም ከሶስት ዓመቱ ይሁን ከአስር ዓመቱ 100 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡

ሌላው በኢንኩቤሽን ማዕከል 16 ካምፓኒዎችን በአዲስ እንዲታቀፉ ዒላማ ተይዞ 11 ካምፓኒዎችን እንዲታቀፉ በማድረግ ከሶስት ዓመቱ 68.75 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ ደግሞ 3.67 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ ከመረጃው ለመረዳት እንደተቻለው አዲስ ካምፓኒዎችን እንዲታቀፉ በማድረግ በኩል የተመዘገበው ውጤት ውስንነት ያለበት ሲሆን ለውጤቱ መቀነስ እንደ ምክንያት የታየው ተቋሙ ዕቅዱን በሚያቅድበት ወቅት በፖሊሲ ማትሪክስ ከተሰጠው ዒላማ 32 ቀንሶ አቅዶ በትግበራ በመግባቱ ዝቅተኛ ውጤት ሊያስመዘግብ ችሏል፡፡ ስለሆነም በቀጣይ ዓመታት ከዚህ በፊት ያልተፈጸሙ ተግባራትን አካቶ በማቀድ ወደ ትግበራ ሊገባና ውጤት ሊያስመዘግብ ይገባል፡፡

አፕሊኬሽኖችን ስታንዳርዳቸውን ጠብቆ በጥራት ማልማት፣ ማሸጋገር በተመለከተ የቴክኖሎጅ የመረጃ ቋት፣ የሰልጣኝ ዳታ ቤዝ፣ የሶሽዩ ኢኮኖሚ መረጃ ቋት፣ ሎካል ፖርታል፣ የመኪና አስተዳደር የጂፒኤስ API፣ የግዥ አስተዳደር ስርዓትን ከንብረት ክፍል አስተዳደር ስርዓት ጋር የማካተት ስራ የተሰራ ሲሆን ችግር ፈች የሆኑ የዲጅታል ላይብራሪና ሲሙሌሽን አፕልኬሽኖችን በተለያዩ የትምህርት ተቋማት የማሸጋገር እንዲሁም በለሙ አፕሊኬሽን ተቋማትን ተጠቃሚ በማድረግ የመንግስት አሠራርን

በቴክኖሎጅ የማዘመን ስራ የተሰራ ሲሆን እነዚህን አፕሌኬሽኖች በማልማትና በማሸጋገር እንዲሁም የመንግስት አሰራርን በቴክኖሎጅ በማዘመን በኩል የተሰራው ስራ ውስንነት ያለበት እና የአስር ዓመቱን ዒላማ ከግብ ለማድረስ በቀጣይ ዓመታት ከፍተኛ ጥረት ማድረግ እንደሚጠበቅ ያሳያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በፖሊሲ ማትሪክስ የተሰጠውን ዒላማ ቀንሶ አቅዶ ወደ ስራ በመግባት ለውጤቱ መቀነስ እንደ ምክንያትነት የሚጠቀስ ጉዳይ ሲሆን በቀጣይ ዓመታት ከዚህ በፊት በዕቅድ ያልተካተቱ ዒላማዎችን አካቶ በማቀድ በትኩረት ሊሰራ ይገባል፡፡ አጠቃላይ የለሙና የተሸጋገሩ አፕሊኬሽኖች በሚከተለው ሰንጠረዥ ለማመላከት ተሞክሯል፡፡

<u>ሠንጠረዥ 4</u>፡- በለሙ አፕልኬሽኖች ተጠቃሚ የሆኑ የመንግስት ተቋማት

| ተ.ቁ | የተከናወኑ ተግባራት | መለኪያ | የሶስት ዓመት ዕቅድ | የሶስት ዓመት ክንውን | አፈጻጸም ከሶስት ዓመት | አፈጻጸም ከአስር ዓመት | የዕቅድ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የለሙ አፕሊኬሽኖች ብዛት | በቁጥር | 16 | 11 | 68.75 | 2.89 | -50 |
| 2 | የተሸጋገሩ አፕሊኬሽኖች ብዛት | በቁጥር | 64 | 39 | 60.94 | 11.24 | -9 |
| 3 | በለሙ አፕሊኬሽኖች ተጠቃሚ ተቋማት ብዛት | በቁጥር | 151 | 274 | 181.5 | 40.12 | - |
| 4 | በዳታ ማዕከል ሆስት የሆኑ አኘልኬሽኖች ብዛት | በቁጥር | 19 | 16 | 84.21 | 23.19 | - |
| 5 | ዳታ ማዕከል ላይ የተጫኑ ዌብ ሳይቶች ብዛት | በቁጥር | 142 | 102 | 71.83 | 71.83 | - |
| 6 | የቪዲዮ ኮንፈረንስ አገልግሎት ተጠቃሚ ተቋማት ብዛት | በቁጥር | 624 | 420 | 67.31 | 20.19 | - |
| 7 | በአኘልኬሽን ልማት ላይ ድጋፍ የተደረገላቸዉ ተቋማት ብዛት | በቁጥር | 500 | 296 | 59.2 | 6.96 | -250 |
| 8 | በቴክኖሎጂ የተደገፉ አምራች ተቋማት | በቁጥር | 30 | 29 | 96.67 | 0.68 | -720 |

ሌላው 4 የሀይል አማራጭ ቴክኖሎጅ ለመምረጥ ዒላማ ተይዞ 3 የሀይል አማራጭ ቴክኖሎጅ በመምረጥ ከሦስት ዓመቱ 75 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ ደግሞ 0.9 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ ከተመረጡ የሀይል አማራጭ ቴክኖሎጅዎች ውስጥ 2 የሀይል

አማራጮችን ለማስፋፋት ዒላማ ተይዞ 1 የሀይል አማራጭ ቴክኖሎጅ በማስፋፋት ከሶስት ዓመቱ 50 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ ደግሞ 10 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ ከመረጃው ለመረዳት እንደተቻለው የሀይል አማራጮችን በመምረጥ እና በማስፋፋት በኩል የተገኘው ውጤት ዝቅተኛ እንደሆነ እና የአስር ዓመቱን ዒላማ ከግብ ለማድረስ በቀጣይ ዓመታት እነዚህን የሀይል አማራጮች የመምረጥ እና የማስፋፋት ስራ በትኩረት ሊሰራ ይገባል፡፡ ከዚህም በተጨማሪም በፖሊሲ ማትሪክስ የተሰጠውን ዒለማ ተቀብሎ በማቀድ በኩል ክፍተቶች ያሉበት ስለሆነ እነዚህን ክፍተቶች ሞልቶ ውጤት ማስመዝገብ የሚጠበቅ ተግባር ነው፡፡

በምርምር ስራዎች ያደገ ምርትና ምርታማነትን በተመለከተ 4 የምርምርና ጥናት ሰነድ ለማዘጋጀት ዒላማ ተይዞ 2 ምርምርና ጥናት ሰነድ በማዘጋጀት ከሶስት ዓመቱ 50 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ ደግሞ 9.82 በመቶ መፈጸም የተቻለ ሲሆን 3 የምርምር ስራዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ለማድረግ ዒላማ ተይዞ 2 የምርምር ስራዎችን ተግባራዊ በማድረግ ከሶስት ዓመቱ 66.6 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ ደግሞ 7.14 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ ከመረጃው ለመረዳት እንደተቻው የምርምር ጥናትና ሰነድ በማዘጋጀት የምርምር ስራዎች ተግባራዊ ለማድረግ የተሰራው ስራ ውስንነት ያለበት እና የአስር ዓመቱን ዒላማ ለማሳካት የማይቻል መሆኑን ያሳያል፡፡ ስለሆነም ተቋሙ የምርምርና ጥናት ስራዎችን ተግባራዊ እንዲሆኑ በማድረግ የክልሉን ተጠቃሚነት ለማዘመን ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ሊሰራ ይገባል፡፡

ተቋሙ በሶስት ዓመቱ ውስጥ የታቀዱ ተግባራት በሚፈጽምበት ወቅት ብዙ ችግሮች ያጋጠሙት ሲሆን ለመጥቀስ ያህልም የሪፖርት መዘግየት፣ በየደረጃዉ የሚላኩ መረጃዎች መፋለስ፣ ካምፓኒዎች በመንግስት ግዥ ጨረታ ሂደት ተሳታፊና ተወዳዳሪነት የልዩ ድጋፍ መመሪያ ተጠቃሚ አለመሆን፣ በወረዳና በገጠር በኢንተርፕራይዝ የተደራጁ ወጣቶች ላይ ግልፅ አሠራር አለመኖር፣ የኢንተርኔት አገልግሎት ፍጥነት ዝቅተኛ መሆን፣ የቴክኖሎጂ ተቋማትን ማህበረሰብ፣ የገጠር ወረዳና ቀበሌ መገናኛና መረጃ ማዕከላትን ለማጠናከር የሚደረገው ጥረት እጅግ አናሳ መሆን፣ ፖርታል ላይ መስሪያ ቤቶች መረጃ አለማስገባት እና የሃገር ውስጥ ገበያ ትስስር በሁሉም አካባቢዎች አለመጠናከር ሲሆኑ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የተለያዩ የአቅም ግንባታ ስልጠና በመስጠት፣ በየደረጃዉ ባሉ ባለሙያዎች በራስ አቅም የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች ጥገና በማድረግ፣ለማህበረሰቡ ባለበት አካባቢ

አገልገሎት ከመስጠት አኳያ የቪዲዮ ኮንፈረንስና የፕላዝማ ችሎት አገልግሎት በመስጠት፣ በኢንተርንሽፕ ተማሪዎች ቴክኖሎጅ በመልማቱ ሊወጣ የነበረውን ወጭ በማዳን፣ በየደረጃዉ የሚገነቡ የመንግስት ህንጻዎች የኔት ወርክ ዲዛይን እንዲያካትት ድጋፍ በማድረግ፣ የኢንተርኔት ተደራሽነት ለማሻሻል ድጋፍ በማድረግ፣ የአፕሊኬሽን ልማትና ሙያዊ ድጋፍ ስራ በመስራት፣ በዳታ ማዕከል አፕልኬሽን ሆስት በማድረግ፣ የነፃ ጥሪ ማዕከል አገልግሎት ለህብረተሰቡ ተደራሽ በማድረግ፣ የቴክኖሎጅ መረጣ ስራ በመስራት፣ የቴክኖሎጂ ማላመድ ስራ በመስራት እና ማሳያ የድርብርብ እርሻ ቴክኖሎጂ ትግበራና የማስፋፋት ስራ በመስራት የታቀዱ ተግባራትን ለመፈጸም ጥረት መደረጉን ያሳያል፡፡

ተቋሙ በአስር ዓመት ለመተግበር ያቀደውን ዒላማ ከግብ ለማድረስ ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በሳይንስ ተደግፎ ጥቅም ላይ የዋለ የሀገር በቀል ዕውቀት በማሳደግ፣ የተናበቡ የዋናና መጠባበቂያ ዳታ ማዕከሎች በማጠናከር፣ የተደራጁ የማህበረሰብ ሁለገብ መረጃ ማዕከላት በማቋቋም፣ የቴክኖሎጅ አሸጋጋሪ ተቋማት/ኢንተርፕራይዞች በማሳደግና በተሸጋገሩ ቴክኖሎጅዎች ተጠቃሚ በማድረግ፣ የገጠር መረጃ ማዕከላትን መልሰው በማደራጀት፣ የተስፋፉ የሀይል አማራጭ ቴክኖሎጅ በማሳደግ እና የመንግስት ተቋማትን አሰራር በቴክኖሎጅ በማዘመን የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማሳደግ እና በአስር ዓመት የታቀደውን ዒላማ ከግብ ለማድረስ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ሊሰራ ይገባል፡፡


## 3.2. የከተማ ዘርፍ አፈጻጸም

### 3.2.1. ከተማና መሰረተ-ልማት አፈጻጸም

ከከተማ ልማት ዘርፍ አንጻር የክልላችን ህዝብ አሁን ካለበት የተበታተነ አኗኗር እንዲወጣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶችን ለማቅረብና ኑሮውን ያለማቋረጥ ለማሻሻል ወደ ከተሞች እንዲሰባሰብ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ መከተም (urbanization) በራሱ ግብ ከመሆኑም ባሻገር ለፈጣን እድገትና አጠቃላይ ልማት እጅግ በጣም አስፈላጊ ሂደት ነው፡፡ በመሆኑም በአስር ዓመቱ ስትራቴጅክ እቅድ የክትመት ልማቱን በማጠናከር ምጣኔውን አሁን ካለበት 19.42% ወደ 26.28% ለማሳደግ የተቀመጠውን ግብ ለማሳካት በርካታ ተግባራት የተከናወኑ ሲሆን ዋና ዋናዎቹ ብቁ የሆኑ የገጠር ማዕከላትን በመለየት የከተማነት እውቅና መስጠት እና ለነባር ከተሞች እድገታቸውን ተከትሎ የደረጃ ሽግግር ማድረግ ናቸው፡፡ በዚህም በሶስት አመቱ

የከተማነት መስፈርቱን አሟልተው ለተገኙ 336 የገጠር አገልግሎት መስጫ ማዕከላት የከተማነት እውቅና እንዲያገኙ ለማድረግ ታቅዶ 23 (6.84%) የገጠር ማዕከላት እውቅና የተሰጠ ሲሆን ይህም በክልሉ ያለውን የከተማ ቁጥር በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 660 ወደ 683 ያሳደገው ሲሆን ባለፉት 3 ዓመታት የከተሞች ቁጥር በየዓመቱ በአማካይ 1.1 በመቶ ማደጉን ያሳያል፡፡ ሌላው የክልሉን የከተሞች አደረጃጀት ፈርጅ መወሰኛና ማቋቋሚያ ደንብ መሠረት መስፈርቱን ያሟሉ 327 ከተሞችን የደረጃ ሽግግር ለማድረግ ታቅዶ ወደ መሪ 23፣ ወደ ንዑስ 27፣ ወደ ከተማ አስተዳደር 34፣ ወደ ሪጅዮፖሊታን 5 በድምሩ 89 (27.2%) ከተሞች የደረጃ ሽግግር ማድረግ ችለዋል፡፡ በዚህም ባለፉት ሶስት ዓመታት የክትመት ምጣኔዉን 21.43 በመቶ (81.5%) ማድረስ ተችሏል፡፡

ክትመታችን የገጠር ዕድገትን የሚያፋጥን፣ መሬትንና ሌላ ሃብትን በቁጠባ የሚጠቀም፣ እንቅስቃሴን የሚያሳልጥ፣ ለአካባቢ ተጽዕኖ የማይበገር፣ አካታች፣ አሳታፊ እና ዘላቂ ልማትን በሚያቀናጅ ተዋረድ ባለው የተሟላ ፕላን እንዲመሩ ለማድረግ ታቅዶ እየተሰራ ሲሆን በዚህም ለ996 ከተሞች ካርታና ፕላን (ለ660 ከተሞች የክለሳ ካርታና ፕላን እና ለ336 አዲስ ከተሞች መሠረዊ ካርታና ፕላን) ለማዘጋጀት የታቀደ ሲሆን ባለፉት ሶስት ዓመታት ለ224 (22.4%) ከተሞች መሰረታዊ ካርታ ለ175 (19.6%) ከተሞች ደግሞ መሰረታዊ ፕላን እንዲዘጋጅላቸዉ የተደረገ ሲሆን ለ38 (36.19%) ከተሞች መዋቅራዊ ፕላን ለ52 (21.5%) ከተሞች የአካባቢ ልማት ፕላን (NDP) እንዲዘጋጅላቸዉ ተደርጓል፡፡ የከተሞችን ፕላን ዝግጅትና ትግበራ በህብረተሰቡ ተሳትፎና ባለቤትነት፣ በተሟላ የህግ ማዕቀፍና የአሰራር ሥርዓት እንዲሁም በጠንካራ ዲሲፕሊን ለመምራት ጥረት የተደረገ ሲሆን አሁን በክልሉ ከሚገኙ 996 ከተሞች ውስጥ 676 (67.9%) ከተሞች ከፈርጃቸው ጋር የሚጣጣም የእድገት ፕላን በማዘጋጀት በፕላን እንዲመሩ ተደርጓል፡፡ ይህም ካለፈዉ ሶስት አመት እቅድ አንጻር መሰረታዊ ፕላን 94 ከመቶ ሌሎችን ደግሞ 100%ና ከዚያ በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡




**ግራፍ 7፡-የከተሞችን ፕላን ዝግጅት አፈጻጸም**

ሁሉም ከተሞች በፕላን ወሰን ውስጥ የሚገኘውን የመሬት ሃብታቸውን ቆጥረውና መዝግበው እንዲይዙ በማድረግ ረገድ በአስር አመቱ መሪ የልማት እቅድ 996 ከተሞች የታወቀ የፕላን ወሰን እንዲኖራቸዉና የመሬት ሃብታቸዉን በመቁጠር 248,584.07 ሄክታር ቁራሽ መሬት ለመመዝገብ ታቅዶ እየተሰራ ሲሆን ባለፉት ሶስት ዓመታት 378 (38%) ከተሞች የታወቀ ፕላን ወሰን እንዲኖራቸዉ የተደረገ ሲሆን 576 (57.8%) ከተሞች 139,462 (56%) ሄክታር ቁራሽ መሬት መዝግበዉ መያዝ ችለዋል፡፡

በክልላችን ከገጠር ወደ ከተማ በልዩ ልዩ ምክንያቶች የሚደረግ ፍልሰትን፣ ተፈጥሯዊ እድገትን፣ ከተማ መስፋትን፣ አዳዲስ ከተሞች መፈጠርን ተከትሎ የከተማ ነዋሪው ህዝብ በፈጣን ሁኔታ በመጨመር ላይ ይገኛል፡፡ በዚህም የተነሳ የክልሉ ፕላንና ልማት ቢሮ መረጃ እንደሚያመላክተው በነዚህ ከተሞች ይኖራል ተብሎ የሚጠበቀው ህዝብ ከክልሉ አጠቃላይ ህዝብ (የከትመት ምጣኔ) 22.1 በመቶ እንደሚሸፍን ተገምቷል፡፡

በዚህም ባለፉት ሶስት ዓመታት በማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አቅርቦት የተገልጋዩን የዕርካታ ደረጃ 85 በመቶ ማድረስ፣ የገጠር የአገልግሎት መስጫ ማዕከላትን የከተማነት እውቅና በመስጠት የከትመት ምጣኔን ወደ 21.43% ማሳደግ እንዲሁም ከከተሞች ፈርጅ ለውጥ አንፃር

የተቀመጡ ግቦች አፈፃፀም የተሻሉ ቢሆንም በሁሉም ከተሞች ተዘጋጅተው የወረዱ የማ/ቤታዊ አገልገሎት ስታንዳርዶችን ለመተግበር የአቅም ውስንነት፣ በስታንዳርዱ መሰረት አገልግሎት ለመስጠት የዝግጁነት እንዲሁም የባለቤትነት ስሜት አለመኖር፣ የተደራጀና ዘላቂ የህዝብ ተሳትፎ በማረጋገጥ በኩል ውስንነት መኖር፣ የከተሞችን የገቢ አቅም ከማሳደግ አንጻር ሁሉንም የገቢ አርስቶች በዝርዝር ለይቶ አሟጦ አለመሰብሰብ፣ ብዙ ድካም በሚጠይቁት ላይ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ አለመስራት፣ የፋይናንስ ብክነትን ለመከላከል በወቅቱ ኦዲት አለማድረግ፣ በኦዲት ወቅት በተገኙ ጉድለቶች ላይም ፈጥኖ የማስተካከያ እርምጃ አለመወሰድ፣... ወዘተ ባለፉት ሶስት ዓመታት በዘርፉ የታዩ ዋና ዋና ችግሮች በመሆናቸዉ የአስር ዓመቱን እቅድ በትክክል ለመተግበር በቀጣይ ትኩረት ሰጥቶ ማከናወን ይገባል፡፡

በኢንቨስትመንት ለተጠቃሚዎች የተላለፉ ቦታዎች ለተፈለገው አገልግሎት ጥቅም ላይ ስለማዋላቸው በየደረጃው ባለው አመራርና ፈፃሚ የከተማ ቦታ ልማትና አጠቃቀም ክትትል በማድረግ በበርካታ ከተሞች ታጥረው የተቀመጡ እና በውላቸው መሰረት ባግባቡ ያልለሙ ይዞታዎችን በመለየት ለታለመላቸው አላማ እንዲውሉ ከአልሚዎቹ ጋር በመወያየት ወደ ስራ እንዲገቡ የተደረገ ሲሆን ወደ ልማት መግባት ያልቻሉ 1,312 ይዞታዎችን በመንጠቅ 109.25 ሄ/ር መሬት ወደ መሬት ባንክ እንዲመለስ ተደርጓል፡፡

በከተሞች የደቀቁ አካባቢወችን ማሻሻልና በመልሶ ማልማት በተወሰኑ ከተሞች 63 ሄ/ር መሬት ለማልማት ታቅዶ 2.88 (4.57%) ሄ/ር መሬት ማልማት ተችሏል፡፡

ሌላው ምላሽ የተሰጠበት የመልካም አስተዳደር ጥያቄ የሰነድ አልባና ከፊል ሰነድ አልባ ይዞታዎችን የመለየት፣ የማጣራትና ሰነድ የመስጠት ጉዳይ ሲሆን ከ2013-2015 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ 117,512 የግል ሰነድ አልባ ይዞታዎችን በመለየት ለ61,013 (51.9%) ህጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ/ ሰነድ በ463 ከተሞች ተሰጥቷል፡፡


በሌላ መልኩ ደግሞ በከተሞች የሚስተዋለውን ህገ ወጥ ግንባታና መሬት ወረራ 100% ለመከላከልና መልክ ለማስያዝ በሚደረገው ጥረት 251,718 ህገ- ወጥ ግንባታዎችን የመለየትና ሙሉ በሙሉ ለማፍረስ ታቅዶ እየተሰራ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 55,825 (22.1%) ብቻ ማስወገድ ሲቻል ከዚህ ጋር ተያይዞ በ10 ዓመቱ ልማት እቅድ 667.86 በሶስት ዓመቱ 270 ሄክታር መሬት ወደ መሬት ባንክ ለማስገባት ታቅዶ 295.65 ሄክታር መሬት ወደ መሬት ባንክ ገቢ ማድረግ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙን ስናይ ከ10 ዓመቱ 44.2 በመቶ ሲሆን ከሶስት ዓመቱ ሲታይ

ግን ከእቅድ በላይ መፈጸም እንደተቻለ ያሳያል፡፡ በተጨማሪም በሁሉም ከተሞች የመረጃ አያያዝ ስርዓትን በማዘመን የይዞታ ፋይሎችን በሃርድ እና በሶፍት ኮፒ አደራጅቶ ለመሰነድ ስራወች እየተከናወኑ ሲሆን 1,338,124 የይዞታ ፋይሎችን በሃርድ ኮፒና በሶፍት ኮፒ ለማደራጀት ታቅዶ 1,057,303 ( 79%) በሃርድ ኮፒና 1,218,598 (91%) ፋይሎች ደግሞ በሶፍት ኮፒ ማደራጀት ተቻለ ሲሆን ከሶስት ዓመቱ እቅድ አፈጻጸም አናጻር ስናየዉ ከ100% በላይ እንደተከናወነ ሪፖርቱ ያሳያል፡፡ በዚህም 544 ከተሞች በሃርድ ኮፒ 589 ከተሞች ደግሞ በሶፍት ኮፒ የይዞታ ፋይሎችን ማደራጀት ችለዋል፡፡

የመኖሪያ ቤት ልማትና አስተዳደር ስራዎች የከተሞችን መስፋፋትና የህብረተሰቡን ወደ ከተሞች መሰባሰብ እንዲሁም የኢንዱስትሪ ልማቱን ተከትሎ የመጣው ሰፊ ችግር የመኖሪያ ቤት አቅርቦት ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም በአስር ዓመቱ የልማት እቅድ በከተሞች የቤት አቅርቦት ምጣኔ አሁን ካለበት 64 በመቶ ወደ 80 በመቶ እንዲያድግ 807,079 ቤቶች እንዲገነቡ የሚደረግ ሲሆን (በመንግስት አስተባባሪነት 20 በመቶ፣ በማህበራት 35 በመቶ፣ በግለሰቦች 15 በመቶ፣ በሪልስቴት ገንቢዎች 10 በመቶ፣ በመንግስትና በግል ባለሀብት አጋርነት 15 በመቶ እና በሽርከና/ጆይንት ቬንቸር 5 በመቶ ይሆናል፡፡)

በዚህም መሰረት በተለያዩ የቤት ግንባታ አማራጮች 807,079 መኖሪያ ቤቶች ለመገንባት ታቅዶ በመኖሪያ ቤቶች ሕብረት ሥራ ማህበራት 403,864 ቤቶችን ለመገንባት ታቅዶ 69,698፣ በግለሰቦች 172,367 ቤቶች ለመገንባት ታቅዶ 47,555፣ በሪል-ስቴት 53,065 ቤቶች ለመገንባት ታቅዶ 495፣ ለዝቅተኛ ነዋሪዎች (በኪራይ ቤት ልማት ፕሮግራም) 7,810 የቁጠባ ቤቶች ለመገንባት ታቅዶ 3,119 በጠቅላላው 120,867 (14.9%) ቤቶች ተገንብተው አገልግሎት እንዲሰጡ የተደረገ ቢሆንም በከተሞች የሚታየውን የመኖሪያ ቤት እጥረት ከመፍታት አኳያ ከራስ አገዝ ማህበራትና በግለሰቦች አማራጭ ከሚገነቡ ፕሮግራሞች ውጭ የሌሎች የቤት ልማት ፕሮግራም አማራጮች አፈጻጸም አነስተኛ መሆን ፣ ከላይ እስከታች ድረስ የመኖሪያ ቤት ችግርን በጥናትና በእውነተኛ አቅም ላይ ተመስርቶ ደረጃ በደረጃ ዘላቂ መፍትሄ መስጠት የሚያስችል የፋይናንስ፣ የለማ መሬት፣ ወጪ ቆጣቢ የግንባታ ቴክኖልጂ እና የግንባታ ግብዓት አቅርቦት ችግር እና የዋጋ ንረት፣ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎና ቅንጅታዊ አሠራር ደካማ መሆን፣ እንዲሁም ጠንካራ የቤት አስተዳደር ስርዓት ያለመዘርጋት...ወዘተ የመሳሰለት ችግሮች በእቅድ አፈጻጸሙ የታዩ ናቸው፡፡ በመሆኑም በቀጣይ በሌሎች ከተሞች እየተተገበሩ ያሉ

የተለያዩ የቤት ልማት አማራጮችን ወደ ክልሉ አምጥቶ ተግባራዊ በማድረግ ዘላቂ መፍትሄ መስጠት ይገባል፡፡




**ግራፍ 8፡-የመኖሪያ ቤት ግንባታ አፈጻጸም**

ሌላዉ ከመሬት ዝግጅትና አቅርቦት አንጻር የከተሞችን የመልማት አቅም/ዕድል ታሳቢ ባደረገ መልኩ የመሬት ፍላጎትን ቢያንስ 75% እንዲዘጋጅና እንዲቀርብ በማድረግ የከተማ መሬት 40 በመቶ በጨረታ፣ 60 በመቶ በምደባ እንዲተላለፍ ለማድረግ 59,219.49 ሄክታር መሬት ለጨረታና ለምደባ በማዘጋጀት 51,017 ሄክታር መሬት ለማስተላለፍ ታቅዶ 18,542.92 (31.3%) ሄክታር መሬት በማዘጋጀት 8,472.36 (16.6%) ሄክታር መሬት ማስተላለፍ ተችሏል፡፡

ከከተማ ጽዳትና ዉበት አረንጓዴ ልማት አንጻር የከተሞችን የጽዳት አገልግሎት እና የአረንጓዴ መሰረተ-ልማት ሽፋንና ተደራሽነት በማሳደግ ከተሞች ለሚከሰቱ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ አካባቢያዊና ኢኮሎጅያዊ ተጽዕኖዎች የማይበገሩ፣ ለኑሮ ምቹ እና ተስማሚ ለማድረግ በሁሉም ከተሞች ከሚመነጨው ደረቅ ቆሻሻ 15 በመቶ ከምንጭ በመቀነስ፣ 35 በመቶ መልሶ በመጠቀም እና በመጨረሻም 30 በመቶ በተገቢው እንዲወገድ በማድረግ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር 80 በመቶ እንዲደርስ ታቅዶ ዕየተሰራ ሲሆን ተግባሩን በ26 (3.7%) ከተሞች ተግባራዊ በማድረግ 68 በመቶ ብቻ ነዉ ተግባራዊ ማድረግ የተቻለዉ፡፡

ሌላዉ በሁሉም ከተሞች የአረንጓዴ መሰረተ ልማት ሽፋን በፕላን ላይ ከተቀመጠው የመሬት ድርሻ 30 ከመቶ ሆኖ እንዲለማ እተሰራ ሲሆን በ681 ከተሞች ለአገልግሎት ከተዘጋጀ መሬት 30 በመቶውን ለአረንጓዴ ልማት/ የህዝብ መናፈሻ ያዋሉ ከተሞች ናቸዉ፡፡ ይህን ተግባር ከሶስት ዓመቱ አንጻር ከእቅድ በላይ መፈጸም እንደተቻለ ሪፖርቱ ያሳያል፡፡


ከከተማ መሠረተ-ልማት አቅርቦትና አስተዳደር ስራዎች አንጻር በከተሞች የሚገነቡ የመሰረተ-ልማት አውታሮች ለከተሞች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መስተጋብር እንደ መፍቻ የሚወሰዱ የልማት ማዕከል ናቸው፡፡ ከተሞች የልማት ማዕከልነታቸውን በብቃት እንዲወጡ ለማስቻል የክልሉ መንግስት ከፍተኛ በጀት መድቦ ዘርፈ-ብዙ የመሰረተ-ልማት አውታሮችን የማስፋፋት ሥራዎችን ሲያከናውን ቀይቷል፡፡ በመሆኑም ባለፉት 3 ዓመታት UIIDP ፕሮግራም ተጠቃሚ የሆኑ እና ከፕሮግራሙ ውጭ ያሉ ከተሞች በራሳቸው አቅም የገነቧቸው መሰረተ-ልማቶች ከተቀመጡ ግቦች አንጻር ሲታይ የማህበራዊና አካባቢ ደህንነትን መሰረት ያደረገና የጥራት ደረጃውን የጠበቀ 764.06 ኪ.ሜ የጌጠኛ ድንጋይ (Cobblestone) ንጣፍ መንገድ ለመገንባት ታቅዶ 301.21 (39.39%) ኪ.ሜ፣ 4,024 ኪ.ሜ ጠጠር መንገድ ለመገንባት ታቅዶ 1,853.73 (46%) ኪ.ሜ፣ 4,844.56 ኪ.ሜ አዲስ መንገድ ከፈታ/ጥርጊያ መንገድ ለመገንባት ታቅዶ 2,601.80 (53.7%) ኪ.ሜ፣ 93.74 ኪ.ሜ አስፓልት መንገድ ለመገንባት ታቅዶ 52.81 (56.33%) ኪ.ሜ፣ 1,350.95 ኪ.ሜ የጎርፍ ማስወገጃና መከላከያ ግንብ ለመገንባት ታቅዶ 484.26 (35.84%) ኪ.ሜ የተገነባ ሲሆን 630 መለስተኛና ከፍተኛ ድልድይ ለመገንባት ታቅዶ በቁጥር 92 (14.6%) ድልድይና 1320 ( 19.75%) ደረጃዉን የጠበቀ ስላብ ከልበርት ግንባታ ማከናወን የተቻለ ሲሆን 7232.88 ኪሎ ሜትር የመንገድ ዳር መብራት 2,255 የዉሃ ቦኖ ለመዘርጋት ታቅዶ 1,575 (21.77%) የመንገድ ዳር መብራት እና 1,939 ( 85.98%) የዉሃ ቦኖ መገንባት ተችሏል፡፡

በመሪ የልማት እቅዱ በከተሞች የምግብ ዋስትና ስርዓትን በማስፋት የከተማ ድህነትን ለመቀነስ በ972 ከተሞች የሚገኙ ነዋሪዎች በምግብ ዋስትና ስርዓት ተጠቃሚ እንዲሆኑ እየተሰራ ሲሆን ባለፉት ሶስት ዓመታት በ17 ከተሞች 25,341 አባወራወች/እማወራወች በምግብ ዋስትና ፕሮግራም ተጠቃሚ እንዲሆኑ የተደረገ ሲሆን የመስራት አቅም ያላቸውና ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ 3,618,276 ዜጎች የከተሞችን ገጽታ ሊቀይሩ በሚችሉ የማህበረሰብ አቀፍ ስራዎች እንዲሳተፉ በማድረግ በከተማ ያለዉን 58 በመቶ የድህነት ምጣኔ ወደ 38 በመቶ ዝቅ ለማድረግ ታቅዶ 81,983 (2.26%) ዜጎች በከተማ ምግብ ለስራ

እንዲሰማሩ ሲደረግ የከተማ ድህነት ምጣኔንም 38 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡ እንዲሁም በከተሞች የሚገኙ የመስራት አቅም የሌላቸዉና ለማህበራዊ ችግር ለተጋለጡ 689,195 የአካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ የአዕምሮ ህሙማን እና ህጻናት እና 44,000 የጎዳና ተዳዳሪዎች የማህበራዊ ሴፍቲኔት ድጋፍና የመሰረታዊ የማህበራዊ አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ ታቅዶ እየተሰራ ሲሆን 18,117 እማወራ/አባወራ በምግብ ዋስትና ፕሮግራም የቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚ መሆን ችለዋል፡፡

### 3.2.2. የመሬት ዘርፍ ልማት አፈጻጸም

የሁለተኛ ደረጃ ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በመስጠት፣ አስተማማኝ የመሬት መረጃ በማደራጀት፣ እያንዳንዱ መሬት ለልማታችን የላቀ ድርሻ ሊያበረክት በሚችልበት ሁኔታ የመሬት አጠቃቀምን ተግባራዊ ማድረግ እንዲሁም አሉታዊ ተጽእኖዎችን በመከላከል ዘላቂ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ስነ ምህዳራዊ ልማት ማስፈን የዘርፉ የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸዉ፡ በመሆኑም ለባለይዞታዎች የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ የማሳ ካርታ በመስጠት የይዞታና የመጠቀም መብት ዋስትና ማረጋገጥ እንዲሁም የማሳ ካርታን የብድር ዋስትና በማድረግ ባለይዞታዎች የብድር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል አንዱ ተግባር ሲሆን በአስር ዓመቱ የዕቅድ ዘመን በ2,627,135 ባለይዞታዎች ሥር ለሚገኝ 10,684,831 ማሳዎች ካርታ በማዘጋጀት እና የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ድብተር በመስጠት በ2012 ከተደረሰበት 172,100 ባለይዞታዎች በ10 ዓመቱ የዕቅዱ ዓመታት የማረጋገጫ ደብተር የተሰጣቸውን ባለይዞታዎች ብዛት ወደ 2,799,235 ለማድረስ ታቅዶ ባለፉት ሶስት ዓመታት በ 794,403 ባለይዞታዎች ሥር ለሚገኝ 3,394,131 ማሳዎች የ2ኛ ደረጃ ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ከማሳ ካርታ ጋር ተሰጥቷል፡፡ በዚህ በኩል የተመዘገበው አፈፃፀም ከባለይዞታዎች አንፃር 30.2 በመቶ እንዲሁም ከማሳ ብዛት አኳያ 31.8 በመቶ ሲሆን ከሶስት ዓመቱ እቅድ አንጻር ግን ሁለቱንም ከ100% በላይ መፈጸም ተችሏል፡፡




**ግራፍ 9፡-የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ አፈጻጸም**

ከዚህ ጋር ተያይዞ 110,000 የይዞታ ማረገገጫ ደብተርን የብድር ዋስትና በማድረግ ባለይዞታዎች 5,500,000,000 ብር የብድር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ 12,529 (11.4%) ባለ ይዞታወች የብር 805,740,095 (14.6%) ብድር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ የተቻለ ሲሆን ከሶስት ዓመቱ እቅድ አንጻር በባለይዞታ 65.45% በብር 92.73% መፈጸም ተችሏል፡፡

**<u>ሰንጠረዥ</u> 5፡- የይዞታ ማረገገጫ ደብተርን የብድር ዋስትና ማድረግ**

| የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት | መለኪያ | የ10 ዓመት ዒላማ | ሦስት ዓመት እቅድ | ክንዉን ከ2013-2015 | አፈጻጸም | አፈጻጸም ከ10ዓ መቱ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረገገጫ ደብተርን የብድር ዋስትና በማድረግ ተጠቃሚ የሆኑ ባለይዞታዎች | ባለይዞታ ቁጥር | 110,000 | 19,142 | 12,529 | 65.45 | 11.4 |
| ወንድ | በቁጥር | 70,000 | 12,333 | 9,079 | 73.62 | 13 |
| ሴት | በቁጥር | 40,000 | 6,808 | 3,964 | 58.23 | 9.9 |

የመሬት መረጃን ኮምፒውተራይዝድ ማድረግን በተመለከተ ባለፉት ሶስት ዓመታት ለ 1,078,128 ባለይዞታዎች ሥር ለሚገኝ 7,163,633 ማሳዎች የመሬት መረጃን ወደ ኮምፒውተር በማስገባት በ2012 ከተደረሰበት 4,324,207 ባለይዞታዎች እና 18,869,210 ማሳዎች ወደ 5,402,335 ባለይዞታዎችና 26,032,843 ማሳዎች ለማድረስ በማቀድ ባለፉት 3 የዕቅድ ዓመታት በተከናወነው ተግባር በ990,791 ባለይዞታዎች ሥር ለሚገኙ 4,408,168 ማሳዎች የመሬት መረጃ ወደ ኮምፒውተር ማስገባት ተችሏል፡፡ በዚህ በኩል የተመዘገበው አፈፃፀም ከባለይዞታዎች አንፃር 92 በመቶ እንዲሁም ከማሳ ብዛት አኳያ 62 በመቶ ተፈጽሟል፡፡ በመሆኑም እስከካሁን ድረስ የመሬት መረጃ ወደ ኮምፒውተር የገባላቸውን ባለይዞታዎች ብዛት 5,314,998 እንዲሁም የማሳዎች ብዛት 23,277,378 ማድረስ ተችሏል ከዚህ ተግባር አንጻር ወደ ኮምፒዉተር የገባዉን የመነሻ መረጃ ከሁለተኛዉ የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን ሪፖርት የተወሰደ ነዉ፡፡

ለባለይዞታዎች የመሬት አጠቃቀም እቅድ አዘጋጅቶ ርክክብ በማድረግ ዝርዝር የመሬት አጠቃቀም ጥናትና ትግባራ በማድረግ ዘላቂ ልማት ማረጋገጥ በዚህ ስር በክልሉ በገጠር መሬት ላይ የሚታውን የተዛባ የመሬት አጠቃቀም እና የአካባቢ መጎሳቆልን ለመከላከል መሠረታዊ የመሬት አጠቃቀምና አያያዝ ዘዴዎችን ተግባራዊ ማድርግ አስፈላጊነቱ ታምኖበት ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ተገብቷል፡፡ የገጠር መሬትን በጥናትና በህግ አግባብ በመምራት ዘላቂነት ያለው ልማትን ለማስፈንና መሬትን ለላቀ ጥቅም ማዋል እንዲቻል የገጠር መሬት የአጠቃቀም ዕቅድ ትኩረት የተሰጠው ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም በዕቅድ ዘመኑ በ1,543 ቀበሌወች በ1,840,108 ባለይዞታዎች ሥር ለሚገኝ 6,318,535 ማሳዎች የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ አዘጋጅቶ ለመስጠት ታቅዶ በ712(46.14%) ቀበሌወች ለ775,292 (42.1%) ባለይዞታወች 3,257,757 (51.56%) ማሳወች የመሬት አጠቃቀም እቅድ አዘጋጅቶ ማስረከብ ተችሏል፡፡ በዚህም ርክክብ በማድረግ በ2012 ከተደረሰበት 250,800 ባለይዞታዎች ወደ 1,026,092 ባለይዞታዎች 1,147,000 ማሳዎች ወደ 4,404,757 ማሳወች ማሳደግ ተችሏል፡፡

የተዘጋጀውን የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ለተጠቃሚዎች ርክክብ ከማድረግ አኳያ በዕቅዱ ዘመን በ3,425 ቀበሌወች ለ1,262,228 ባለይዞታዎች ሥር የሚገኙ 4,111,565 ማሳዎችን ርክክብ ለማድረግ ታቅዶ ባለፉት 3 አመታት በተደረገው እንቅስቃሴ በ791 ቀበሌወች ለ632,201 ባለይዞታዎች ሥር ለሚገኑ 2,737,502 ማሳዎችን ርክክብ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህ በኩል

የተመዘገበው አፈፃፀም ከባለይዞታ አንፃር 50.1 በመቶ እንዲሁም ከማሳ ብዛት አኳያ 66.6 በመቶ ነዉ፡፡


## ሰንጠረዥ6 ፡-የመሬት አጠቃቀም እቅድ

| የአፈጻጸም አመላካቾች/የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት | የ10 ዓመት ዒላማ | የ3 ዓመት ዒላማ | የ3 ዐአመት ክንዉን | አፈጻጸም | ከ10 ዓመቱ ያለው አፈጻጸም |
|---|---|---|---|---|---|
| አሳታፊ የመሬት አጠቃቀም እቅድ ዝግጅት የቀበሌ ብዛት | 1,543 | 743 | 712 | 95.83 | 46.1 |
| ባለይዞታ ብዛት | 1,840,108 | 809,048 | 775,292 | 95.83 | 42.1 |
| ማሳ ብዛት | 6,318,535 | 3,045,111 | 3,257,757 | 106.98 | 51.6 |
| የተዘጋጀውን የመሬት አጠቃቀም እቅድ ለተጠቃሚዎች ማስረከብ ቀበሌ ብዛት | 797 | 703 | 690 | 98.15 | 86.6 |
| ባለይዞታ ብዛት | 1,262,228 | 1,062,795 | 632,201 | 59.48 | 50.1 |
| ማሳ ብዛት | 4,111,565 | 3,507,628 | 2,737,502 | 78.04 | 66.6 |

በተበታተነ ሁኔታ የሚኖረውን አ/አደር በቀበሌ ማእከል በማሰባሰብ  የቀበሌ ማእከላት ግንባታ እና የመሰረተ ልማት ስራዎች እንዲከናወኑ ድጋፍ በማድረግ፣ ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች ተደራሽነት ምቹ ሁኔታ በመፍጠር የገጠር ቀበሌ ማእከላት የእድገት ማእከል እንዲሆኑ ማስቻል እንደ አቅጣጫ የተቀመጠ ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም በመሪ የልማት እቅዱ የ1,638 ቀበሌዎችን የቀበሌ ማዕከላት አዲስ ፕላን በማዘጋጀት፣ በ910 የቀበሌ ማዕከላት 22,796 ሄክታር ሥፋት ያለው 701,400 የቤት መስሪያ ቦታዎችን በመሸንሸን፣ ለ508,800 ነዋሪዎች የቤት መስሪያ የግንባታ ቦታ በማስረከብ፣ ነዋሪዎች በተሰጣቸው የቤት መስሪያ ቦታ ላይ ቤት ግንባታቸውን አጠናቀው ወደ ቤታቸው እንዲገቡ ለማድረግ ታቅዶ በሶስት ዓመቱ የ508 (31%) ቀበሌ ማዕከላት ፕላን ተዘጋጅቶ፣ በ972(106.8%)  ቀበሌዎች 12,509 ሄክታር (54.9%) ሥፋት ያለው መሬት  57,446 (8.2%) የቤት መስሪያ ቦታዎች ተሸንሽነው፣ ለ48,611 ተጠቃሚዎች (የዕቅዱን 9.6%) የቤት መስሪያ የግንባታ ቦታ ርክክብ የተደረገ ሲሆን ለ27,399 (30.8%) የቤት ግንባታ ላጠናቀቁ ተጠቃሚወች ካርታ መስጠት ተችሏል፡፡

በዚህ በኩል ባለፉት 3 የዕቅድ ዓመታት የተከናወኑ ሥራዎች ተበታትኖ የሚኖረውን አርሶ አደር በቀበሌ ማዕከላት ለማሰባሰብ የተደረገው ጥረት የማዕከላት ፕላን ከማዘጋጀትና የመስሪያ

ቦታዎችን ከመሸንሸን አኳያና ተጠቃሚው በየቀበሌ ማዕከላቱ የመኖሪያ ቤቱን ግንባታ አጠናቆ በገነባው መኖሪያ ቤት መኖር ላይ የአፈጻጸም ዉስንነቶች መኖራቸዉን መረጃዉ ያሳያል፡፡




**ግራፍ 10፡-የቀበሌ ማእከላት አዲስ ፕላን ማዘጋጀት**

ለህዝብ ጥቅም ሲባል መሬታቸውን ለሚለቁ ባለይዞታዎች ተገቢውን ካሳ እንዲከፈላቸው በማድረግ እና የተነሽዎችን ፍላጎት እና አቅም መሠረት ያደረገ የመልሶ ማቋቋም ሥራዎችን በማከናወን ኑሮአቸውን በዘላቂነት እንዲመሩ ማስቻል ትኩረት የተሰጠው ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም በዕቅድ ዘመኑ ለህዝብ ጥቅም ሲባል 207,391 ሄክታር መሬታቸውን ለለቀቁ 829,565 ባለይዞታዎች 311,087 ቢሊዮን ብር በህግ የተፈቀደውን የካሳ መጠን በማስላት እንዲከፈል ለማድረግ ታቅዶ እስከ 2015 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ 26,126 ሄክታር ሥፋት ያለውን ይዞታቸውን ለልማት ሲባል ለለቀቁ ለ161,756 ባለይዞታዎች ብር 24,927 ቢሊየን የካሣ ክፍያ ተፈጽሟል፡፡ ይህ አፈጻጸም እንደሚያሳየው የተገመተላቸው ተጠቃሚዎች 19.5% ሲሆኑ የካሳ ክፍያ ከመፈፀም አንፃር ደግሞ 8.0% ማከናወን ተችሏል፡፡

በተመሳሳይ በልማት ምክንያት የተፈናቀሉ ባለይዞታዎችን በዘላቂነት መልሶ ከማቋቋም አንፃር በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ በዚህም በራሳቸው የካፒታል አቅም በተለያዩ አማራጭ የሥራ ዘርፎች እንዲሳተፉ ድጋፍ ለማድረግ በተያዘው ዕቅድ መሠረት 44,889 (9%) የሚሆኑ ተነሽዎች በተለያዩ የኑሮ አማራጭ ዘርፎች እንዲደራጁ ተደርጓል፡፡ ከእነዚህ ይዞታቸውን

ከለቀቁ ባለይዞታዎች መካከል ለ4,371 (52.7%) ተነሽዎች 1,060 ሄክታር (የዕቅዱን 51.1%) ትክ የእርሻ መሬት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ከዚህም በላይ ለ 31,062 (37.4%) ግለሰቦች ትክ የመኖሪያ ቤት አቅርቦት እንዲሁም ለ 8,252 (33.2%) ለሚሆኑ ተነሽዎች ትክ የመሥሪያ ቦታ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

በዕቅድ ዘመኑ 67,000 ሄክታር መሬት በጥናት በመለየት በገጠር መሬት ኢንቨስትመንት በባለሀብቶች እየለማ ያለውን መሬት ከ212,678 ሄክታር ወደ 279,678 ከፍ ለማድረግና ምርታማነትን ለማሳደግ ታቅዶ ባለፉት 3 የዕቅድ ዓመታት 38,390 (57.3%) ሄክታር መሬት በጥናት መለየት የተቻለ ሲሆን በተመሳሳይ 67,000 ሄክታር መሬት ለባለሃብቶች ለማስተላለፍ ታቅዶ 63,049 (94.1%) ሄክታር መሬት በማስተላለፍ በመሬት ኢንቨስትመንት በባለሀብቶች እየለማ ያለው መሬት 275,727 (98.58%) ሄክታር ማድረስ ተችሏል፡፡
በገጠር መሬት የሚታዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመለየት እና ከመሬት ጋር የተያያዘ ሕገወጥነት ሕዝቡን በንቃት በማሳተፍ ዘላቂ መፍትሔ መስጠት ዋነኛ ተግባር ተደርጎ የተወሰደ ነው፡፡ በመሆኑም ባለፉት 3 የዕቅድ ዓመታት በተጭበረበረ ማስረጃ የይዞታ መሬታቸውን ያለአግባብ እንዲያጡ የተደረጉ 17,866 ተጎጅዎች የመሬት መረጃ በማጥራት ያለአግባብ የተወሰደባቸውን መሬት ለማስመለስ ታቅዶ የ 13,243 ባለመብቶችን (74%) መሬት በህዝብ ውሳኔ እንዲመለስላቸው ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ሳይኖራቸው መሬት ይዘው ይጠቀሙ ከነበሩ 13,955 (የዕቅዱን 88%) ግለሰቦች በሕገወጥነት ይጠቀሙበት የነበረውን 4,340 ሄክታር (የዕቅዱን 29%) መሬት እንዲመልሱ ተደርጓል፡፡ ከዚህም ባሻገር ባለፉት 3 የዕቅድ ዓመታት 225,585 (ወጣቶችን፣ ሴቶችን፣ ህፃናትንና አካል ጉዳተኞችን) ከትርፍ መሬት ተጠቃሚ በማድረግ 64,980 ሄክታር መሬት ለማስተላፍ ታቅዶ 68,252 ሄክታር መሬት ለ 256,449 ተጠቃሚዎች (የዕቅዱን 114%) የመሬት ባለቤት እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል፡፡

### 3.2.3. ባህልና ቱሪዝም ልማት አፈጻጸም


የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ከተቋቋመበት ዓላማ በመነሣት የባህል እሴቶችና ታሪካዊ ቅርሶችን፣ የብሔር ብሔረሰቦችን ቋንቋ፣ ባህልና ታሪክ በመጠበቅና በማልማት እንዲሁም የተፈጥሮ መስህቦችን ለአገር ውስጥና ለውጪ ቱሪስቶች መዳረሻ በማድረግ የቱሪዝም ኢንዱስትሪውን ለማበልጸግና የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ዘላቂ ለማድረግ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡

በአስር አመት ዘመኑ 160 ሰነዶች በክልሉ የሚዘወተሩ የስነ-ቃል ዘውጎችን ለመሰብሰብ እና ለማደራጀት ታቅዶ በሶስቱ ዓመታት ውስጥ በ281 ሰነዶች በማሰባሰብ ከተያዘው ዕቅድ በላይ ለማከናወን ተችሏል፡፡ 147 ነባር የባህል ቡድኖችን በድግግሞሽ 441 ጊዜ በሙያ፣ በስልጠና እና በቁሳቁስ ለመደገፍ ታቅዶ በሶስቱ ዓመታት 1546 ጊዜ በመደገፍ የባህል ቡድኖችን የማጠናከር ስራ ተሰርቷል፡፡ ሌላዉ 1,800 አዳዲስ የኪነጥበብ ክበባትን ለማቋቋም ታቅዶ (በ2013፣በ2014 እና በ2015) ውስጥ 414 አዳዲስ ክበባትን ማቋቋም በመቻሉ አፈጻጸሙን ከአስር አመት ዕቅዱ አንጻር 23 በመቶ ለማከናወን ተችሏል፡፡ ይህም በመደረጉ በክልሉ የሚገኙ የኪነጥበብ ክበባትና የባህል ቡድኖችን እንደ አንድ የልማት መሳሪያ በመጠቀም አመራሩ እና ህብረተሰቡ ክበባቱንና ባህል ቡድኖቹን የባለቤትነት እና የእኔነት ስሜት እያደገ እንዲመጣ ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል፡፡

130 የህዝብ ቤተ-መጽሀፍቶችን በቁሳቁስ፣በስልጠና እና በቴክኖሎጂ ለማጠናከር ታቅዶ ባለፉት ሶስቱ ዓመታት ውስጥ 85 የህዝብ ቤተ-መጽሃፍትን 548 ጊዜ በድግግሞሽ በቴክኖሎጂ፣ 278,662 የተለያዩ መጽሀፍትን በድጋፍና በግዥ በማሰናሰብ፣ በቁሳቁስ እና በአደረጃጀት የማጠናከር ስራ ተሰርቷል፡፡ አፈጻጸሙ በአስር አመት ዕቅድ ከተያዘው አንጻር ከዕቅድ በላይ ማከናወን ሲቻል ለህዝብ ቤተመጻሕፍት ተደራሽ ለማድረግ 1,000,000 መጽሀፍቶችን እና የተለያዩ ህትመቶችን በግዥና በስጦታ ለማሰባሰብ ታቅዶ በሶስቱ ዓመታት ውስጥ 278,662 የተለያዩ የህትመት ውጤቶችን ተደራሽ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህም በአስር አመቱ ከተያዘው ዕቅድ አንጻር አፈጻጸሙን 27.87 ለማድረስ ተችሏል፡፡

በ2,956 ቅርሶች ላይ የጉዳት መጠን ልየታ በማካሄድ ለ292 ቋሚ ቅርሶች የጥገና ስራ ለመስራት ታቅዶ በሶስቱ ዓመታት ለ909 ቅርሶች የጉዳት መጠን ልየታ በመስራት ለ141 ቋሚ ቅርሶች የጥገና ስራ ለማከናወን የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ በአስር አመቱ ከተያዘው ዕቅድ አንጻር የጉዳት መጠንን በማጥናት ደረጃ 30.75 በመቶ እና የጥገና ስራ በመስራት ደረጃ 48.29 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡ እንዲሁም 5,452 ለሚሆኑ ተንቀሳቃሽ ቅርሶች የጥገና ስራ ለመስራት ታቅዶ ለ1821 (33.4%) ተንቀሳቃሽ ቅርሶች የጥገና ሰራ ማከናወን ሲቻል ለ2,956 ቋሚና ለ118,068 ተንቀሳቃሽ ቅርሶች እንክብካቤ እና የጽዳት ስራ ለመስራት ታቅዶ በሶስቱ ዓመታት ለ3,422( >100%) ቋሚ እና ለ66,242 (56.1%) ተንቀሳቃሽ ቅርሶች በድግግሞሽ የጽዳት እና የእንክብካቤ ሥራ ተሰርቷል፡፡

ግራፍ 11፡ **ጥገና የተደረገላቸው ተቋማት**




ለ2,956 ቋሚ ቅርሶች የይዞታ ማረጋገጫ እና ለ2,956 ቋሚ ቅርሶች የወሰን ክለላ ስራ ለመስራት ታቅዶ በሶስቱ ዓመታት ለ1,327 ቋሚ ቀርሶች የይዞታ ማረጋገጫ ማሰጠት ሲቻል ለ357 ቋሚ ቅርሶች የወሰን ክለላ ስራ መስራት ተችሏል፡፡ ይህም በመሆኑ አፈጻጸሙን ይዞታ ከማረጋገጥ አንጻር 44.89 በመቶ እና የወሰን ክለላ ከማድረግ አንጻር 12.08 በመቶ ለማከናወን ተችሏል፡፡ በባህል፣ በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ቅርስ ጥበቃ እንክብካቤ፣ በቤተ-መጽሀፍትና ሙዜዬም ግንባታ 7,683,401 የህብረተሰብ ክፍሎችን በማሳትፍ 160,424,675 ብር ግምት ያለው አስተዋጽኦ ለማበርከት ታቅዶ በሶስት ዓመታት ውስጥ ለ522,949 ወንድና ለ522,549 ሴት በድምሩ 1,045,498 የህብረተሰብ ክፍሎችን በማሳተፍ የ139,439,853 ብር አስተዋፆ ተደርጓል፡፡ ተሳትፎ ካደረጉት ውስጥ 50 በመቶ ሴቶች 45 በመቶ ወጣቶች እና ቀሪው 55 በመቶ አዋቂዎች በጉልበት፣በገንዘብ፣ በቁሳቁስ እና በሙያ ተሳትፎ አድርገዋል፡፡ የተሳትፎ አፈጻጸሙ ከአስር አመት ዕቅዱ አንጻር 13.61 በመቶ እና እንዲሁም በገንዘብ ሲተመን ከዕቅዱ አንጻር 86.92 በመቶ ማከናወን ተችሏል፡፡ ከዚህ ውስጥ (68 በመቶ) በቅርስ ጥበቃ እና እንክብካቤ፣ (20 በመቶ) በቤተ-መጽሃፍት እና በባህል ማዕከል ግንባታ ቀሪው (12 በመቶ) በመዳረሻ ልማት ተሳትፎ ያደረጉ ናቸው፡፡

335 የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶችን ለመመዝገብ ታቅዶ በሶስቱ ዓመታት 279 የማይዳሰስ ቅርስ ለመመዝገብ በመቻሉ አፈጻጸሙ በአስር ዓመቱ ከተያዘው ዕቅድ አንጻር 83.28 በመቶ ለማከናወን ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በክልሉ የሚገኙ 2 የማይዳሰስ ቅርስ በዩኒስኮ ለማስመዝገብ እንዲቻል መረጃውን የማደራጀት ስራ ተሰርቷል፡፡ በተለያዩ ጊዜያት በህገ-ወጥ

የቅርስ ዝውውር እና ስርቆት ከቅርስ ተቋማት የተዘረፉ 1,953 ቅርሶችን ለማስመለስ ታቅዶ በሶስቱ ዓመታት ውስጥ 20 ቅርሶችን የማስመለስ ስራ ተሰርቷል፡፡


በአስር አመቱ እቅድ ውስጥ ለ4,280 አዲስ እና ነባር የሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የሙያ ድጋፍና ክትትል ስራ ለማካሄድ ታቅዶ በሶስት ዓመታት ውስጥ ለ789 የሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ኢንቨስትመንትፕሮጀክቶች የሙያ ድጋፍና ክትትል ስራ የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙም ከአስር ዓመቱ ዕቅድ አንጻር 18.43 በመቶ ለማድረስ ተችሏል፡፡ ይሁን እንጅ የባለ ኮከብ ሆቴሎችን ቁጥር ለማሳደግ እቅድ ታቅዶ እየተሰራ ቢሆንም ምንም ዓይነት የሆቴል የደረጃ ማሻሻል ስራ አልተሰራም፡፡

ክልሉን የሚጎበኙ የሀገር ውስጥ ቱሪስት ፍሰትን **63,829,357** ለማድረስ ታቅዶ በሶስት ዓመታት ውስጥ **15,113,565** ማድረስ አፈጻጸሙ ከአስር አመት ዕቅድ አንጻር 23.68 በመቶ ለማድረስ የተቻለ ሲሆን ክልሉን የሚጎበኙ የውጭ ሀገር ቱሪስት ፍሰትን 907,033 ለማድረስ ታቅዶ በሶስት ዓመታት **29,825** ማድረስ በመቻሉ አፈጻጸሙ ከአስር አመት ዕቅድ አንጻር 3.29 በመቶ ለማድረስ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙ ያነሰበት ምክንያት በኮረና ቫይረስ እና ክልሉ ከጸጥታ ስጋት በቅርብ ጊዜ የወጣ ባለመሆኑ ምክንያት የውጭ ሀገር ጎብኝዎች ቁጥር በመቀነሱ ነው ፡፡ ክልሉን ከሚጎበኙ የሀገር ውስጥ ቱሪስቶች የሚገኘውን ገቢ **9,638,055,419** ብር ለማድረስ በዕቅድ ተይዞ በሶስት ዓመታት ውስጥ **5,253,588,211** ብር በማድረስ የእቅዱን 54.51 በመቶ ማድረስ ሲቻል ክልሉን ከሚጎበኙ የውጭ ሀገር ቱሪስቶች የሚገኘውን ገቢ 1,553,203,637 ብር ለማድረስ ታቅዶ በሶስት ዓመታት ውስጥ 98,616,903 ብር ማድረስ በመቻሉ አፈጻጸሙ ከአስር አመቱ ዕቅድ አንጻር 6.35 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡

ከዕቅዱ አንጻር የውጭ ሀገር ቱሪስት ፍሰት ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት በክልሉ የተረጋጋ ሰላም አለመኖር ለቱሪስት ፍሰቱ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩ፣የቱሪስት መዳረሻዎችን በማልማት ለቱሪስቱ ምቹ አለማድረግ እንዲሁም መዳረሻዎችንና የመስህብ ቦታዎችን በሚገባ ማስተዋዎቅ ባለመቻሉ እንደ ምክንያት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡አጠቃላይ ክልሉን ከሚጎበኙ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ቱሪስቶች 3.58 ቢሊዬን ብር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 2.6 ቢሊዬን ብር ገቢ ማግኘት በመቻሉ አፈጻጸሙ ከዕቅዱ አንጻር 72.9 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡ ከውጭ ሀገር ቱሪስት ፍሰት የተገኘ ገቢን ስንመለከት የቱሪስት ፍሰቱ ቀንሶ ገቢው ያደገበት ምክንያት የቱሪዝም ምርትና አገልግሎቶች አይነት በመጨመሩ እንዲሁም ለቱሪዝም ምርትና አገልግሎቶች የመሸጫ ዋጋ ግሽበት በማሳየቱ ነው፡፡

### 3.2.4. የገቢዎች ስራዎች አፈጻጸም

ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን የክልሉን መደበኛ ገቢ በ2012 ከነበረበት ብር 11.06 ቢሊዮን በእቅድ ዘመኑ መጨረሻ ወደ ብር 178.02 ቢሊዮን እንዲሁም የክልሉን የከተማ አገልግሎት ገቢ ከነበረበት 1.86 ቢሊዮን በአስር አመት እቅዱ መጨረሻ ወደ 20.23 ቢሊዮን ብር ማድረስ የተያዘው ግብ ሲሆን ይህን ግብ ከዳር ለማድረስ በርካታ ስራዎችን በማከናወን በየዓመቱ አዳጊ የገቢ እቅድ በማቀድና በመሰብሰብ እድገት ያለው ገቢ ሲሰበሰብ የቆየ ሲሆን ባለፉት ሶስት ዓመታት ከመደበኛ ገቢ ብር 74.85 ቢሊዮን፣ ከከተማ አገልግሎት ገቢ ብር 10.35 ቢሊዮን፣ ከቀጥታ ታክስ ገቢ 44.18፣ ቀጥታ ካለሆነ ታክስ ገቢ 27.63፣ ታክስ ያልሆነ ገቢ 2.95 በቢሊዮን ብር በድምሩ ብር 159.96 ቢሊዮን ብር ማድረስ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም ከመደበኛ ገቢ 42.04 በመቶው እንዲሁም ደግሞ ከከተማ አገልግሎት ገቢ 51.16 በመቶ ከቀጥታ ታክስ ገቢ 44.97 በመቶ፣ ቀጥታ ካልሆነ ታክስ ገቢ 41 በመቶ፣ ታክስ ያልሆነ ገቢ 23.54 በመቶ ሲሳካ በድምሩ ከተቀመጠው ግብ አንጻር ሲወሰድ 42.5 በመቶው ያህሉ የተሰበሰበ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በሶስት አመቱ የእቅድ ዘመን የክልሉ ገቢ እድገት እያስመዘገበ የመጣ ሲሆን የእድገት ምጣኔውን ስናይ በአማካይ በብር 37.3 ቢሊዮን እድገት የነበረውን መሆኑን ያመለክታል፡፡




**ግራፍ፤12 የገቢ አሰባሰብ ተግባራት**

በእቅድ ዘመኑ የታሰበውንና የክልሉ ኢኮኖሚ የሚያመነጨውን እምቅ ገቢ መሰብሰብ ያላስቻሉ ከቁጥጥር ውጭ የነበሩ የሰላምና መረጋጋት የነበሩ ችግሮች መሆናቸው ቢታወቅም በፈጻሚው፣ በአስፈጻሚው፣ በባለ ድርሻ አካላት በኩል የነበረው የትኩረት ማነስም ለገቢ መሰብሰቡ ግብ አለመሳካት የራሳቸው ድርሻ እንዳለበት መገንዘብ ይገባል፡፡

በሌላ በኩል የግብር ከፋዮች ቁጥር በሚፈለገው አግባብ አለመጨመርና አብዛኛው ግብር ከፋይም ግብር መክፈል ግዴታ ስለመሆኑ ካለመገንዘቡም ባሻገር ግብርን በማጭበርበርና በመደበቅ እንዲሁም የታክስ ህግን በመጣስ የሚጠበቅበትን መክፈል ባለቻሉ የታለመውን የገቢ ግብ ማሳካት እንዳይቻል ማድረጉን ሪፖረቱ ያሳያል፡፡

### 3.2.5. ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ልማት አፈጻጸም

ኢንቨስትመንትን መሳብ በሚመለከት ክልሉ ባለው ምቹ የሃብት አማራጭና በተሰሩ የተለያዩ የፕሮሞሽን ስራዎች በሦስት ዓመቱ ለ58,682 ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለመስጠት ግብ ተቀምጦ ለ11,159 ባለሀብቶች ፈቃድ በመስጠት 19% የተፈፀመ ሲሆን ከአስር ዓመቱ ኢላማ አኳያ 3.96 በመቶ ብቻ እንደተፈፀመ ያሳያል፡፡ በተመሳሳይ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከተሰጣቸው ባለሀብቶች ውስጥ ከፍተኛ የትኩረት አቅጣጫ የሆነውን አምራች ኢንዱስትሪዎች ፈቃድ መስጠት በተመለከተ በሦስት ዓመቱ ለ8,288 ባለሀብቶች ፈቃድ በመስጠት 499 ቢሊዮን ብር የተመዘገበ ካፒታል በመያዝ እና ወደ ስራ ሲገቡ 1.2 ሚሊዮን የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ3,241 ባለሀብቶች ፈቃድ በመስጠት 788 ቢሊዮን ብር የተመዘገበ ካፒታል እና 1.9 ሚሊዮን የስራ እድል ለሚፈጥሩ ፕሮጀክቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንደተሰጠ ያመለክታል፡፡ ከመረጃዉ በመነሳት በሦስት ዓመት ዉስጥ የአምራች ኢንዱስትሪዎችና ሌሎች ፕሮጀክቶችን ፈቃድ በመስጠት በኩል የአስር ዓመቱን ዒላማ ከግብ ለማድረስ በቀሪ ዓመታት ዉስጥ ለመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች የመስሪያ ቦታ(መሬት) አቅርቦት እንዲሁም ለአነስተኛ ኢንዱስትሪዎች የመስሪያ ሼድ ችግርን በመቅረፍ በፖሊሲ ማትሪክሱ መሰረት ተግባራት ታቅደው ሊፈጸሙ ይገባል፡፡


**ሠንጠረዥ-7፡ ለባለሀብቶች የተሠጠ የኢንቨስትመት ፈቃድ**

| ተግባር | መለኪያ | መነሻ (2012) | የ3 ዓመት ዒላማ | ተቋሙ ያቀደው ዒላማ | የ3 ዓመት ክንዉን | የዕቅድ ልዩነት በቅናሽ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ለባለሀብቶች የተሰጠ የኢንቨስትመንት ፈቃድ | በቁጥር | 150,000 | 58,682 | 8,288 | 11,159 | -50,394 |
| የተመዘገበ ካፒታል | በብር | 307 | 1,690 | 499 | 788 | -1,191 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| በቢሊዮን | | | | | | |
| ሊፈጥሩት የሚችሉት የሥራ ዕድል በሚሊየን | በቁጥር | 1 | 4.5 | 1.2 | 1.9 | -3.2 |

የመረጃ ምንጭ ፡ አብክመ ኢ/ኢ/ቢሮ 2016 መረጃ

ነባር አምራች ኢንዱስትሪዎችን ማጠናከርን በሚመለከት በክልሉ እስከ አሁን ድረስ 3,461 አነስተኛ፣ 814 መካከለኛ እና 460 ከፍተኛ በድምሩ 4,735 አምራች ኢንዱስትሪዎች ለማድረስ ታቅዶ 2,425 አነስተኛ፣804 መካከለኛ እና 317 ከፍተኛ በድምሩ 3,546 አምራች ኢንዱስትሪዎች ማድረስ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ ከሦስት ዓመቱ 95.8% በመፈፀም ከ10 ዓመቱ ደግሞ 46.6% ማድረስ ተችሏል፡፡ ከዚህ ውስጥ ባለፉት ሶስት ዓመታት 220 አነስተኛ፣ 154 መካከለኛ፣ 108 ከፍተኛ በድምሩ 482 አምራች ኢንዱስትሪዎች ወደ ምርት የገቡ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ከመረጃዉ ለመረዳት እንደተቻለዉ ከጠቅላላ አምራት ኢንዱስትሪዎች ዉስጥ ወደ ምርት የገቡት 13.8% ብቻ ሲሆኑ ቀሪዎች 86.2% ወደ ማምረት ተግባር እንዳልተሸጋገሩ ያሳያል፡፡ አምራች ኢንዱስትሪዎች ለኢኮኖሚው በክልልም ደረጃም ሆነ እንደ አገር ያበረከቱት አስተዋጽኦ ቀላል የሚባል ባይሆንም ከዘርፉ ከሚጠበቀው አንፃር በጣም ዝቅተኛ ነዉ፡፡ ለዚህም ምክንያቱ አምራች ኢንዱስትሪዎች በብድር አቅርቦት እጥረት፣የሰለጠነ የሰዉ ሀይል ችግር፣ የግብዓት አቅርቦት ዉስንነት እና ከፍተኛ የሆነ የሀይል አቅርቦት ችግር በማጋጠሙ አምራች ኢንዱስትሪዎችም ሆኑ ሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ሰፊ የስራ እድል በመፍጠር እና ኢኮኖሚያዊ የመዋቅር ለዉጥ በማምጣት ረገድ ዉስንነት የሚታይባቸዉ እንደሆነ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በመሆኑም በዘርፉ የሚስተዋለዉን ችግር በመቅረፍ በቀጣይ ቀሪ ዓመታት ነባር አምራች ኢንዱስትሪዎችን በማጠናከር ሁሉንም ወደ ምርት የማስገባት ተግባር ልዩ ትኩረት ሊሠጠዉ ይገባል፡፡




**ግራፍ 13፡ በክልሉ ዉስጥ የሚገኙ ነባር አምራች ኢንዱስትሪዎች ያሉበት ሁኔታ**

ለአምራች ኢንዱስትሪዎች እና ሌሎች ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የመሬት አቅርቦትን ማሳደግ በተመለከተ ባለፉት ሶስት ዓመታት ለሁሉም አምራች ኢንዱስትሪ ቀጠናዎች ለሚገኙ የተለያዩ ፕሮጀክቶች አገልግሎት የሚውል በሳይት ፕላንና በካርታ የተመለከተ 12,327 ሄ/ር መሬት ለማዘጋጀት ታቅዶ 11,531.95 ሄ/ር መሬት 93.5% ማዘጋጀት የተቻለ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 2,358.8ሄ/ር ከ3ኛ ወገን ነጻ ማድረግ ተችሏል፡፡ ይህም በሦስት ዓመት በሳይት ፕላንና በካርታ ከተመላከተዉ ዉስጥ ከ3ኛ ወገን ነፃ የሆነዉ 19% ሲሆን ከ10 ዓመቱ ደግሞ 7.4% ብቻ መሆኑ ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል በሦስት ዓመቱ ለ1,306 አምራች ኢንዱስትሪዎች 2,183.87 ሄ/ር መሬት በመስጠት 28.2% መፈፀም ተችሏል፡፡በተመሳሳይ ከአምራች ኢንዱስትሪ ውጭ ለሌሎች (ግብርና ፣ሆርቲካልቸር እና አገልግሎት) ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች አገልግሎት የሚውል በሳይት ፕላንና በካርታ 35,683 ሄ/ር መሬት ለማዘጋጀት ታቅዶ 51,677.2ሄ/ር መሬት 100% ማዘጋጀት የተቻለ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 53,948ሄ/ር ከ3ኛ ወገን ነጻ ማድረግ ተችሏል፡፡ በመሆኑም በዚህ ዙሪያ ያሉ ችግሮች የመስሪያ ቦታ ከ3ኛ ወገን ነፃ ለማድረግ የካሳ ክፍያ ችግር፣መሬቱን ለማስረከብ የመሬት ባለይዞታዎች ፈቃደኛ አለመሆን እና ከመሬት አስተዳደር ፅ/ቤት ጋር በመመሪያዉ መሠረት በቅንጅትና በትብብር መስራት አለመቻል ሲሆኑ በቀጣይ ቀሪ ዓመታት ችግሮችን በመፍታት ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የመስሪያ ቦታ ከ3ኛ

ወገን ነፃ የሚሆንበትን ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ጉዳዩ በቀጥታ ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት ይጠበቃል፡፡


የኢንዱስትሪ ክላስተር አደረጃጀቶችን ከማጠናከር አንጻር በፌደራል መንግስት ወጭ 4 ከፍተኛ ኢንዱስትሪ ፓርኮችን ማለትም ባህርዳር፣ ኮምቦልቻ፣ ደብረ ብርሀን እና ቡሬ ኢንዱስትሪ ፓርኮችን መገንባት የተቻለ ሲሆን አረርቲ ኢንዱስትሪ ፓርክ በክልሉ መንግስት በመገንባት ለባለሀብቶች የማስተላለፍ ስራ ተሰርቷል፡፡ ከእነዚህ ዉስጥ ቡሬ፣ ደ/ብርሀን እና ኮምቦልቻ ፓርኮች የተሻለ እንቅስቃሴ የሚታይባቸዉ ቢሆኑም ባህርዳር ኢንዱስትሪ ፓርክ እስካሁን ድረስ ምንም አይነት እንቅስቃሴ የሌለዉ መሆኑን መረጃዉ ያሳያል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የሀገር ውስጥ ግጭት፣የአጎዋ የገበያ ዕድል መዘጋት፣ በግብዓት አቅርቦት እና በውጪ ምንዛሪ እጥረት ኢንዱስትሪዎች ፓርኮች ወደ ተግባር እንዳይሸጋገሩ እና በመሪ እቅዱ የተቀመጠዉን ግብ እንዳያሳኩ ካደረጉ ዋና ዋና ምክንያቶች ዉስጥ ተጠቃሾ ናቸዉ፡፡ ስለሆነም ከፌደራል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ጋር በመነጋገር እና ችግራቸዉን በመፍታት ፓርኮችን ወደ ስራ በማስገባት በ10 ዓመት የተቀመጠዉን ግብ ማሳካት ይጠበቃል፡፡በተጨማሪም ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ከፌደራል ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን ጋር የጋራ ስራዎችን በጋራና በመደጋገፍ የሚሰሩበት እንዲሁም የሪፖርት ቅብብሎሽ የአሰራር ሥርዓት የሌለዉ በመሆኑ በቀጣይ ሊታሰብበት ይገባል፡፡

**ሠንጠረዥ 8፡ የኢንዱስትሪ ክላስተር አደረጃጀትን ማጠናከር**

| ተ.ቁ | ኢንዱስትሪ ፓርኮች | ስፋት በሄ/ር | የተገነባ ሼድ ብዛት | ለባለሀብቶች የተላለፈ ሼድ/መሬት ብዛት | ወደ ማምረት የገቡ ባለሀብቶች | ለባለሀብቶች ያልተላለፉ ሼዶች/መሬት ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ባህርዳር | 150 | 8 | 5 | 0 | 3 |
| 2 | ደ/ብርሀን | 154.8 | 8 | 8 | 5 | |
| 3 | ኮምቦልቻ | 75 | 9 | 7 | 7 | 2 |
| 4 | ቡሬ | 260 | | 33 | | 40 ሄ/ር |
| 5 | አረርቲ | 106.7 | | 4 | | 100 ሄ/ር |

የመረጃ ምንጭ ፡ ከኢንዱስትሪ ፓርኮች የተሰበሰበ መረጃ 2016 ዓ.ም

**የኢንዱስትሪ መንደር አደረጃጀቶችን ማጠናከር፡** አምራች ኢንዱስትሪዎችን ለማሳደግ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር በኩል ዕድገት ተኮር በሆኑና ለኢኮኖሚ ግንባታውም ሆነ ለሥራ ዕድል ፈጠራ የላቀ ጠቀሜታ ላላቸው እንዲሁም የግብርናውን ምርት በግብዓትነት ለሚጠቀሙ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች አገልግሎት የሚሰጡ 28 የኢንዱስትሪ መንደሮች እንዲቋቋሙ ተደርጓል፡፡ በዚህም 2,817 ኢንዱስትሪዎች የገቡ ሲሆን ከእነዚህ ዉስጥ ወደ ግንባታ የገቡ 36%፣ ቅድመ- ግንባታ ላይ ያሉ 30%፣ ግንባታ ያጠናቀቁ 21% እና ወደ ምርት የገቡት 2.2% ብቻ መሆኑን መረጃዉ ያሳያል፡፡ ለዚህ ዋነኛ ምክንያቱ በተቋሙ ከላይ እስከታች ተግባራትን ለመፈፀም የአቅም ክፍተት መኖር፣ የአምራች ኢንዱስትሪዎችን አቅም ሊያጠናክር የሚችል ወርክሾፕ አለመኖር፣የገበያ ትስስር ችግር፣ለኢንቨስትመንቱ በቂ መሰረተ ልማት አለመሟላትና የሀይል አቅርቦት ችግር እና የዶላር እና የብድር አቅርቦት እጥረት መኖር ይጠቀሳሉ፡፡ በመሆኑም በቀጣይ ቀሪ ዓመታት ለክልሉ ኢንቨስትመንት ማነቆ የሆነውን የሃይል አቅርቦት ችግር መፍታት፣ኢንዱስትሪ ፓርኮች ኮርፖሪሽንን ማጠናከር፣ በቂ የኢንቨስትመንት መሬት ማዘጋጀት፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ማጠናከር፣ የአቅም ግንባታ ስራ ማከናወን እና ከብድር አቅራቢ ተቋማት ጋር በትብብር በመስራት የኢንዱስትሪ መንደሮችን ዉጤታማ በማድረግ ሁሉንም ኢንዱስትሪዎችን ወደ ምርት ማስገባት በልዩ ትኩረት ሊሰራ የሚገባዉ ተግባር ነዉ፡፡




**ግራፍ 14፡ በኢንዱስትሪ መንደር ዉስጥ የገቡ ባለሀብቶች ያሉበት ሁኔታ**

የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም ወጥ እና ሳይንሳዊ በሆነ አሰራር መለካትን በሚመለከት የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ሌሎች ድጋፎች ዋና ዓላማቸው አምራች ኢንዱስትሪዎች ምርት አምርተው ውጤታማ ለመሆን ችግር የሆነባቸውን ጉዳይ ለይቶ በመፍታት በሙሉ አቅማቸው እንዲያመርቱ ማደረግ ነው፡ ስለሆነም የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም በሳይንሳዊ መንገድ መለካት ያሉበትን የእድገት ሁኔታ ማወቅና የቀጣይ ድጋፍና ክትትል ስራዎች አመላካች እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ባለፉት ሶስት ዓመታት ካሉት ኢንዱስትሪዎች ውስጥ 50 ፐርሰንት በመለካት የማምረት አቅማቸዉን 69 ፐርሰንት ለማድረስ ታቅዶ 2,564 አምራች ኢንዱስትሪዎች የማምረት አቅማቸው የተለካ ሲሆን አፈፃፀሙም 56.4 ፐርሰንት ነዉ፡፡ ከመረጃዉ ለመረዳት እንደተቻለዉ የኢንዱስትሪዎች የማምረት አቅም በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 62% በ2015 ዓ.ም ወደ 56.4% መዉረዱን ያመለክታል፡፡ በዚህም በሦስት ዓመት ከተቀመጠዉ ኢላማ አንፃር የ12.6 በመቶ ቅናሽ ያሳያል፡፡ በተመሳሳይ የሦስት ዓመት አማካይ የማምረት አቅም በንዑስ ዘርፉ ሲታይ የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ዘርፍ 65.3 በመቶ፣ የቆዳ ኢንዱስትሪዎች 59.8 በመቶ፣ የምግብና መጠጥ 61.2 በመቶ፣ የኬሚካልና የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪዎች 55.9 በመቶ እና የማኑፋክቸሪንግ ቴክኖሎጂና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪዎች 36.7 በመቶ ነው፡፡ በዚህ በኩል ከሚያጋጥሙ ችግሮች መካከል

የውጭ ምንዛሪ እጥረት፣ የግብዓት አቅርቦትና የጥራት ውስንነት፣የክልሉ የፀጥታ ችግር፣ የፋይናንስ ማነቆዎች፣ የሰለጠነ የሰው ሀይል አቅርቦት ውስንነት፣ የኢንዱስትሪ አስተዳደር ችግር፣ኋላቀር ቴክኖሎጂ መጠቀም፣የገበያ ትስስር እና የሀይል አቅርቦት ችግር፣የመንግስት ድጋፍና ክትትል ዉስንነት መኖራቸው ዋና ዋና ተጠቃሽ ምክንያቶች ናቸው፡፡ ስለሆነም በቀጣይ ቀሪ አመታት አምራች ኢንዱስትሪዎች የገጠማቸዉን ችግር በመፍታት በመሪ እቅዱ የተቀመጠዉን 85% የማምረት አቅም ለማድረስ በልዩ ትኩረት ሊሠራ ይገባል፡፡

የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ከደረጃ ሽግግር አንጻር የኢንዱስትሪዎች ሁለንተናዊ ችግሮቻቸው ከተፈቱላቸው የማምረት አቅማቸው ከማደጉ በተጨማሪ የካፒታልና የሰው ኃይል ጭማሬ ያደርጋሉ፡፡ ይህ ደግሞ ደረጃቸውን ካሉበት ወደ ቀጣዩ የተሻለ ደረጃ ከፍ ያደርጋቸዋል፡፡ ባለፉት ሶስት ዓመታት ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ 193፣ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ 67 በድምሩ 260 አምራች ኢንዱስትሪዎችን የደረጃ ሽግግር ለማድረግ ታቅዶ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ 153፣ ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ 18 በድምሩ 171 አምራች ኢንዱስትሪዎች የደረጃ ሽግግር አድርገዋል፡፡ በዚህም ከሦስት ዓመቱ 65.7 ፐርሰንት የተፈፀመ ሲሆን ከአስር ዓመቱ ደግሞ 11.32 በመቶ ብቻ መፈፀሙን መረጃዉ ያመለክታል፡፡ ከመረጃዉ ለመረዳት እንደተቻለዉ አብዛኞቹ አምራች ኢንዱስትሪዎች የደረጃ ሽግግር እያደረጉ አለመሆኑን ያሳያል፡፡ በመሆኑም በቀጣይ ቀሪ ዓመታት የተቀናጀ ድጋፍ በመስጠትና አቅማቸዉን በመገንባት ደረጃቸዉን ማሻሻል ይጠበቃል፡፡

**ሠንጠረዥ9 ፡ የአምራች ኢንዱስትሪዎች የደረጃ ሽግግር ማድረግ**

| ተግባር | መለኪያ | መነሻ (2012) | የ3 ዓመት ዒላማ | ተቋሙ ያቀደው ዒላማ | የ3 ዓመት ክንዉን | የዕቅድ ልዩነት በቅናሽ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ ደረጃ ሽግግር ያደረጉ ኢንዱስትሪዎች | በቁጥር | 121 | 193 | 193 | 153 | |
| ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ የደረጃ ሽግግር ያደረጉ ኢንዱስትሪዎች | በቁጥር | 13 | 67 | 67 | 18 | |
| ድምር | በቁጥር | 134 | 260 | 260 | 171 | |

የመረጃ ምንጭ ፡ አብክመ ኢ/ኢ/ቢሮ 2016 መረጃ

በአምራች ኢንዱስትሪዎች እና በሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የኤክስፖርት ገቢን ማሳደግን በሚመለከት የውጭ ምንዛሬ ገቢ ከማሳደግ አንጻር 71 አምራች ኢንዱስትሪዎች ኤክስፖርት እንዲያደርጉ በማድረግ 121 ሚሊዮን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 54 አምራች ኢንዱስትሪዎች ምርታቸውን ወደ ውጭ በመላክ 201 ሚሊዩን ዶላር ማግኘት ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙ በኢንዱስትሪ 76% ሲሆን በገቢ መጠን ከ100 ፐርሰንት በላይ ነው፡፡ 15 ሆርቲካልቸር ፕሮጀክቶችን በመለየት 47 ሚሊዮን ዶላር እንዲያስገቡ ታቅዶ 10 የሚሆኑ ምርታቸውን ኤክስፖርት በማድረግ 35.212 ሚሊዮን ዶላር ማግኘት የተቻለ ሲሆን በአምራች ኢንዱስትሪዎችና በሌሎች ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በድምሩ 64 ኢንዱስትሪዎች ኤክስፖርት እንዲያደርጉ በማድረግ 194.316 ሚሊዩን ዶላር ማግኘት ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙ በጥቅል በኢንዱስትሪ 79% ሲሆን በገቢ 100 ፐርሰንት ነው፡፡ በዋናነት ኤክስፖርት ከሚደረጉ ምርቶች ዉስጥ ጣይና (ከሰሊጥ የተቀነባበረ ምግብ)፣ቢራ፣ የእንስሳት መኖ (protien powder)፣የአልኮል መጠጦች፣MDF፣ play wood፣ግሬይ ፋብሪክስ፣ክር፣ጋርመንት፣የትራስ ልብስ፣ ጓንት፣ቦርሳ፣ ቀበቶ፣ያለቀለት ቆዳ፣ብርጭቆና ጠርሙስ ተጠቃሽ ናቸዉ፡፡

ተኪ ምርት የሚያመርቱ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ከመደገፍ አንጻር  ስትራቴጅክ ተኪ ምርትን በማምረት  የገቢ ምርትን መቀነስ  በተቋሙ እንደ አንድ ተግባር የተያዘው በ2015 በጀት ዓመት በመሆኑ በ2013 እና 2014 አፈጻጸሙን መለካት አልተቻለም፡፡ይሁን እንጅ ከ2015 በጀት ዓመት ጀምሮ እንደ ግብ የተቀመጡ ስትራቴጅክ ተኪ ምርት የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎችን በመለየት ትኩረት ተሰጥቶ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ በዚህ መሠረት 287 ተኪ ምርት የሚያመርቱ አምራች ኢንዱስትሪዎችን በመለየት 116.39 ሚሊዮን ዶላር ለማዳን ታቅዶ 401 ተኪ ምርት የሚያመርቱ አምራች ኢንዱስትሪዎችን በመደገፍ 1.2 ቢሊዩን ዶላር የውጭ ምንዛሬ የዳነ ሲሆን የእቅዱን 100 ፐርሰንት መፈጸም ተችሏል፡፡በመሆኑም ኢንዱስትሪዎች የሀገር ውስጥ ግብዓት በመጠቀምና ከውጪ የሚገባን ምርትን ለመተካት የተሄደበት መንገድ መልካም የሚባሉ ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡ በተለይም የማዕድን ምርትን በማሳደግና የግብርና ምርት ግብዓቶች በማቅረብ ኢንዱስትሪው የሀገር ዉስጥ ምርት የሚጠቀምበትና በሂደት የገቢ ንግድ የሚተካበት ሁኔታ የማመቻቸት ስራዎች እየተሰሩ ነው፡፡ በዚህም ከዚህ በፊት ከውጪ የሚገባዉን የቢራ ብቅል፣ የምግብ ዘይት፣ ፓስታና አልሚ ምግቦች፣ የተማሪዎች ዩኒፎርም፣የአልኮል መጠጦች፣MDF፣ play wood፣ግሬይ ፋብሪክስ፣

ክር፣ጋርመንት፣የትራስ ልብስ፣ ጓንት፣ቦርሳ፣ቀበቶ፣ያለቀለት ቆዳ፣ብርጭቆ፣ ጠርሙስ እና የፀጥታ አካላት የደንብ ልብስ በሀገር ውስጥ የማምረት ስራ እየተሰራ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ። ስለሆነም ይህ ተግባር ለኢኮኖሚዉ ትልቅ ፋይዳ የሚጫወት በመሆኑ በዚህ በኩል የሚታዩ ክፍተቶችን በመፍታት ከፍተኛ ርብርብ ማድረግ ይጠበቃል።

**ሠንጠረዥ10 ፡ የተኪ ምርት መጠንና የዳነ ዉጭ ምንዛሬ**

| ተግባር | መለኪያ | መነሻ (2012) | የ3 ዓመት ዒላማ | ተቋሙ ያቀደው ዒላማ | የ3 ዓመት ክንዉን | የዕቅድ ልዩነት በቅናሽ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ተኪ ምርቶችን የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎች ብዛት | በቁጥር | 524 | 1,692 | 287 | 401 | -1,405 |
| የተለዩ ተኪ ምርቶች አይነት | በቁጥር | 62 | 196 | 62 | 79 | -134 |
| የተመረቱ ተኪ ምርቶች በመጠን | በቶን | 0.016 | 132,000 | 132,000 | 1,675,218 | 0 |
| የዳነ የዉጭ ምንዛሬ መጠን በሚሊዮን ዶላር | ዶላር | 47.51 | 140 | 125 | 1274 | 15.23 |

የመረጃ ምንጭ ፡ አብክመ ኢ/ኢ/ቢሮ 2016 መረጃ

አዳዲስ ኢንዱስትሪዎችን ማቋቋም እና ወደ ምርት ማስገባትን በሚመለከት ባለፉት ሦስት ዓመታት 385 አነስተኛ፣ 203 መካከለኛ 147 ከፍተኛ በድምሩ 736 አምራች ኢንዱስትሪዎችን ለማቋቋም ታቅዶ 220 አነስተኛ፣154 መካከለኛ 108 ከፍተኛ በድምሩ 482 አምራች ኢንዱስትሪዎች በማቋቋም ከሦስት ዓመቱ 65.6 በመቶ ከአስር አመቱ ደግሞ 0.82 በመቶ ብቻ መፈፀም ተችሏል። ከመረጃዉ ለመረዳት እንደሚቻለዉ ተቋሙ በሦስት ዓመት ዉስጥ አቅዶ መፈፀም ከነበረበት ዒላማ ዉስጥ 11,378 ኢንዱስትሪዎችን ቀንሶ በማቀዱ የሦስት ዓመቱ አፈፃፀም የተሻለ ቢሆንም የአስር ዓመቱን ኢላማ ለማሳካት የሚያስቸግር መሆኑን መረጃዉ ያመለክታል። ለዚህም ውጤቱ የቀነሰበት ምክንያት የብድር አቅርቦት ችግር፣ ማሽን ለማስመጣት ከፍተኛ የሆነ የዉጭ ምንዛሬ እጥረት (LC ለመክፈት መቸገር)፣ በየደረጃዉ

የሚገኘዉ ውሳኔ ሰጭ አካል በቁርጠኝነት የተሻለ አቅም ያለዉን ባለሀብት በመመልመልና በፍጥነት የመስሪያ ቦታ የመስጠት ችግር በመቅረፍ ተቋሙ ለወደፊት በፖሊሲ ማትሪክሱ መሠረት እቅዶችን አሟጦ በማቀድ አዳዲስ ኢንዱስትሪዎችን ማቋቋምና ወደ ምርት የማስገባት ስራ ሊሰራ ይገባል።

**ሠንጠረዥ-11፡ አዳዲስ ኢንዱስትሪዎች ማቋቋም እና ወደ ምርት ማስገባት**

| ተግባር | መለኪያ | መነሻ (2012) | የ3 ዓመት ዒላማ | ተቋሙ ያቀደው ዒላማ | የ3 ዓመት ክንዉን | የዕቅድ ልዩነት በቅናሽ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የአነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ብዛት | ቁጥር | 2,714 | 9,003 | 385 | 220 | -8,618 |
| የመካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ብዛት | ቁጥር | 651 | 2,142 | 203 | 154 | -1,939 |
| የከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ብዛት | ቁጥር | 238 | 969 | 147 | 108 | -822 |
| ድምር | ቁጥር | 3,603 | 12,114 | 736 | 482 | -11,378 |

የመረጃ ምንጭ ፡ አብክመ ኢ/ኢ/ቢሮ 2016 መረጃ

በአጠቃላይ ኢንቨስትመንት በመሳብ በኩል ክልሉ ባለው ምቹ የሃብት አማራጭና በተሰሩ የተለያዩ የፕሮሞሽን ስራዎች በሦስት ዓመቱ ባለሀብቶች ፈቃዱ በመስጠት 19% የተፈፀመ ሲሆን ከአስር ዓመቱ ኢላማ አኳያ 3.96 በመቶ ብቻ እንደተፈፀመ ያሳያል። በተመሳሳይ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከተሰጣቸው ባለሀብቶች ውስጥ ከፍተኛ የትኩረት አቅጣጫ የሆነውን አምራች ኢንዱስትሪዎች ፈቃድ መስጠት በኢላማዉ ከተቀመጠዉ አኳያ ዝቅተኛ መሆኑን ያመለክታል።

ባለፉት ሶስት ዓመታት ነባር አምራች ኢንዱስትሪዎችን በማጠናከር ወደ ምርት ማስገባት 220 አነስተኛ፣154 መካከለኛ፣ 108 ከፍተኛ በድምሩ 482 አምራች ኢንዱስትሪዎች ወደ ምርት የገቡ ሲሆን ይህም ከጠቅላላ አምራት ኢንዱስትሪዎች ዉስጥ ወደ ምርት የገቡት 13.8% ብቻ መሆኑን ያሳያል።

የኢንዱስትሪ መንደር አደረጃጀቶችን ማጠናከር፡በክልሉ 28 ኢንዱስርቲ መንደሮች በመገንባት 2,817 ኢንዱስትሪዎች የገቡ ሲሆን ከእነዚህ ዉስጥ ወደ ግንባታ የገቡ 36%፣ ቅድመ-ግንባታ ላይ ያሉ 30%፣ ግንባታ ያጠናቀቁ 21% እና ወደ ምርት የገቡት 2.2% ብቻ መሆኑን መረጃዉ ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም ወጥ እና ሳይንሳዊ በሆነ አሰራር መለካት፡ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ሌሎች ድጋፎች ዋና ዓላማቸው አምራች ኢንዱስትሪዎች ምርት አምርተው ውጤታማ ለመሆን ችግር የሆነባቸውን ጉዳይ ለይቶ በመፍታት በሙሉ አቅማቸው እንዲያመርቱ ማድረግ ሲሆን ባለፉት ሶስት ዓመታት ካሉት ኢንዱስትሪዎች ውስጥ 50 ፐርሰንት በመለካት የማምረት አቅማቸዉን 69 ፐርሰንት ለማድረስ ታቅዶ 2,564 አምራች ኢንዱስትሪዎች የማምረት አቅማቸው የተለካ ሲሆን አፈፃፀሙም 56.4 ፐርሰንት ነዉ፡፡ ከመረጃዉ ለመረዳት እንደተቻለዉ የኢንዱስትሪዎች የማምረት አቅም በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 62% በ2015 ዓ.ም ወደ 56.4% መዉረዱን ያመለክታል፡፡ በዚህም በሦስት ዓመት ከተቀመጠዉ ኢላማ አንፃር የ12.6 በመቶ ቅናሽ ያሳያል፡፡


የክልሉ አምራች ኢንዱስትሪ የእድገት ደረጃ ከአገር አቀፉ አንፃር ሲታይ በእጥፍ የሚያንስ እና ዓመታዊ እድገቱም በጣም አዝጋሚ ብቻ ሳይሆን ዘርፉ በኢኮኖሚ ውስጥ ያለዉ ድርሻ በጣም ዝቅተኛ እና በጅምር ያለ መሆኑን አመላካች ነው፡፡ ለዚህም ምክንያቶቹ በተቋሙ ዉስጥ ከላይ እስከታች ተግባራትን ለመፈፀም የአቅም ክፍተት መኖር፣ የአምራች ኢንዱስትሪዎችን አቅም ሊያጠናክር የሚችል ወርክሾፕ አለመኖር፣የገበያ ትስስር ችግር፣ለኢንቨስትመንቱ በቂ መሰረተ ልማት አለመሟላትና የሀይል አቅርቦት ችግር እና የዶላር እና የብድር አቅርቦት እጥረት መኖር ይጠቀሳሉ፡፡በመሆኑም በቀጣይ ቀሪ ዓመታት በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን በመፍታት የኢኮኖሚ ሽግግር ማምጣት በሚችሉ መካከለኛና ከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎችን በመደገፍ በተለይ ኤክስፖርት እና ስትራቴጅክ ተኪ ምርት በሚያመርቱ ላይ በማተኮር የተለያዩ የማበረታቻ ስትራቴጅዎችን በመከተልና በመተግበር የገቢ ንግድን መቀነስና የወጭ ንግድን በማሳደግ ቀጣይነት ላለው የኢኮኖሚ እድገት መረባረብ ይጠበቃል፡፡

### 3.2.6. የንግድ እና ገቢያ ልማት ዘርፍ ዕቅድ አፈፃፀም

የንግድ ዘርፍ ዘመናዊ የግብይት ልማት ስርዓት በመዘርጋት የሸማቹን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣ ጠንካራ የንግድ ሬጉላቶሪ ስርዓት በመዘርጋት ህገወጥ ንግድን መከላከል፣ የግብይት መሠረተ ልማትን በማስፋፋት ለገበያ የሚቀርቡ ምርቶችን ማሳደግ፣ ለውጭ ገበያ የሚቀርብ ምርት መጠንን በመጨመር የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ማሳደግ ሲሆኑ

እነዚህን ግቦች ከግብ ለማድረስ የአስር ዓመት ስትራቴጅክ ዕቅድ አቅዶ እየተገበረ ሲሆን በሶስት ዓመት ውስጥ የተከናወኑ ተግባራት እንደሚከተለው ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

የንግድ ስርዓቱን ፍትሃዊነትና የተረጋገጠ ለማድረግ ግብ ተይዞ ለ312,496 የንግድ ማኅበረሰብ አዲስ የንግድ ፈቃድ ለመስጠት ዒላማ ተይዞ 270,215 አዲስ የንግድ ፈቃድ በመስጠት ከሶስት ዓመቱ 86.47 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ 22 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ ለ1,246,558 ነጋዴዎች የንግድ ፈቃድ ዕድሳት ለመስጠት ታቅዶ 1,002,257 ዕድሳት በመስጠት ከሶስት ዓመቱ 80.4 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ ደግሞ 67.55 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ በሶስት ዓመቱም ከንግድ ፈቃድ፣ ዕድሳትና ልዩ ልዩ አገልግሎቶች 384,787,379 ብር መሠብሰብ የተቻለ ሲሆን የገቢ አሰባሰባችን ወጥነት ያለው ሳይሆን ወጣ ገባ ያለበት መሆኑን ያሳያል፡፡ ከመረጃው ለማረጋገጥ እንደተቻለው የንግድ ስርዓቱን ለማረጋገጥ ለንግዱ ማኅበረሰብ የተሰጠው አዲስ የንግድ ፈቃድ እና ዕድሳት ያለው አፈጻጸም ውስንነት ያለበት መሆኑን እና የሚመዘገበው ውጤትም ከዓመት ዓመት ብዙም ለውጥ የሌለው መሆኑን ያሳያል፡፡ አፈጻጸምሙም በዚህ ፍጥነት የሚሄድ ከሆነ ከአስር ዓመቱ ዒላማ ለመድረስ የማይቻል እንደሆነ ያሳያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተቋሙ በፖሊሲ ማትሪክስ የተሰጠውን ዒላማ በትክክል አቅዶ ከመተግበር ይልቅ አዲስ ፈቃድ መስጠት 17,135 እንዲሁም ዕድሳት 277,341 ቀንሶ አቅዶ ወደ ተግባር በመግባቱ ለአፈጻጸሙ መቀነስ አንዱ ምክንያት እንደሆነ ያሳያል፡፡




**ግራፍ 15፡ የንግድ ፈቃድ ዕድሳትና ፈቃድ መስጠት**

ሌላው ህጋዊ የንግድ ሽፋንን ወደ 56 በመቶ ለማሳደግ ዒላማ ተይዞ 39 በመቶ በማድረስ ከሶስት ዓመቱ 69.64 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ ደግሞ 55.71 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ ይህ የሚያሳየው ህጋዊ የንግድ ሽፋንን በማሳደግ በኩል የተሰራው ስራ ውስንነት ያለበት መሆንና አሁንም ቢሆን ህገወጥ የንግድ እንቅስቃሴ የሚካሄድ መሆኑን ያሳያል፡፡ ስለሆነም የህብረተሰቡን ፍትሃዊ የግብይት ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የንግድ ሽፋኑን የማሳደግ ስራ በትኩረት ሊሰራ ይገባል፡፡

የአገልግሎት ተደራሽነትን በማሳደግ የግብይት ስርዓቱን ለማቀላጠፍ ለ856 የገበያ ማዕከላትን የመሰረተ ልማት እንዲሟሉላቸው ለማድረግ ታቅዶ ለ371 የገበያ ማእከላት መሠረተ ልማት እንዲሟሉ በማድረግ ከሶስት ዓመቱ 43.34 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ ደግሞ 15.71 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ ይህ የሚያሳየው አብዛኛው የገበያ ማእከላት መሠረተ ልማት ተሟልቶላቸው ግብይት እየፈጸሙ እንዳልሆነ እና አብዛኛው ግብይቶች የሚካሄዱት ከህጋዊ ገቢያ ውጭ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ስለሆነም የገበያ ማዕከላትን የማጠናከር መሠረተ ልማት እንዲሟሉላቸው የማድረግ እና የማዘመን ስራ በትኩረት ሊሰራ ይገባል፡፡


የውጪ ምንዛሬ ግኝታችንን ለማሳደግ ለዉጪ ገበያ የሚቀርቡ አስገዳጅ የግብርና ምርቶች ወደ ውጭ የመላክ እና ገቢን የማሳደግ ስራ ተሰርቷል፡፡ አገራችንን በውጭ ምንዛሬ ተወዳዳሪ የሚያደርጉና ወደ ውጭ የተላኩ አስገዳጅ የግብርና ምርቶች ሰሊጥ፣ ነጭ ቦሎቄ፣ ቀይ ቦሎቄ፣ አኩሪ አተር፣ ማሾ እና ቡና ሲሆኑ ከእነዚህ ምርቶች የውጭ ምንዛሬ ገቢ ማግኘት ተችሏል፡፡ የተገኘው የውጭ ምንዛሬ ገቢ ከታቀደው ዒላማ አኳያ ሲታይ ዝቅተኛ እንደሆነ እና ለወደፊት ትኩረት ተሰጥቶ መሰራት ያለበት መሆኑን የሚያመላክት ሲሆን የተገኘው ገቢም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**<u>ሠንጠረዥ 12</u>፡- የከግብርና አስገዳጅ ምርቶች የተገኘ የውጭ ምንዛሬ ገቢ**

| ተ.ቁ | የምርት ዓይነት | መለኪያ | የሶስት ዓመት ዕቅድ | የሶስት ዓመት ክንውን | አፈጻጸም ከሶስት ዓመት | አፈጻጸም ከአስር ዓመት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የቀረበ ሰሊጥ | ኩ/ል | 5,250,754 | 2,484,046 | 47.31 | 13.9 |
| 2 | የተገኘ ገቢ | ሚሊ/ዶላር | 755 | 419 | 55.49 | 15.96 |
| 3 | የቀረበ ነጭ ቦሎቄ | ኩ/ል | 1,315,952 | 588,105 | 44.69 | 10.68 |
| 4 | የተገኘ ገቢ | ሚሊ/ዶላር | 103 | 45 | 43.3 | 10.10 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | የቀረበ ቀይ ቦለቄ | ኩ/ል | 432,492 | 200,963 | 46.47 | 10.60 |
| 6 | የተገኘ ገቢ | ሚሊ/ዶላር | 27 | 16 | 59.77 | 14.28 |
| 7 | የቀረበ አኩሪ አተር | ኩ/ል | 2,790,233 | 4,633,457 | 166.06 | 36.28 |
| 8 | የተገኘ ገቢ | ሚሊ/ዶላር | 133 | 320 | 240.11 | 50.16 |
| 9 | የቀረበ ማሾ | ኩ/ል | 1,243,335 | 872,398 | 70.17 | 15.46 |
| 10 | የተገኘ ገቢ | ሚሊ/ዶላር | 113 | 78 | 69.51 | 15.10 |
| 11 | የቀረበ ቡና | ኩ/ል | 8,833 | 6,905 | 78.17 | 51.5 |
| 12 | የተነኘ ገቢ | ሚሊ/ዶላር | 2.287 | 2.012 | 87.98 | 100 |
| | **ጠቅላላ የተገኘ ዶላር** | **ሚሊ/ዶላር** | **1,133.287** | **880.012** | **77.65** | **20.28** |

ሌላው የውጭ ምንዛሬ ገቢ የሚገኘው ከእንስሳትና እንስሳት ተዋጽኦ ከዳልጋ ከብት፣ ከበግና ፍየል እና ከዓሳ ምርት የሚገኙ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ምርቶች 5,945,428 ዶላር ለማግኘት ዒላማ ተይዞ 4,052,558 ዶላር በማግኘት ከሶስት ዓመቱ 68.12 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ ደግሞ 20.26 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ የተገኘውን ገቢ ስንመለከት ከዳልጋ ከብት የተገኘው ገቢ በጣም ዝቅተኛ እና በአስር ዓመት ይደረስበታል ተብሎ ከሚጠበቀው ዒላማ አኳያ ብዙ የሚቀር መሆኑን ያሳያል፡፡ ስለዚህ ክልላችን በእንስሳት ሀብታችን ከሌሎች ክልሎች ጋር ሲነጻጸር የተሻለ የእንስሳት ሀብት የሚገኝበት እንዲሁም ብዙ ወንዞችና ሀይቆች የሚገኙበት ክልል ቢሆንም ከሚገኘው ምርት የውጭ ምንዛሬ በሚፈለገው ልክ ማግኘት እንዳልቻልን የሚያሳይ ስለሆነ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራ ይገባል፡፡




**ግራፍ16 ፡- ከእንስሳት ሀብት የተገኘ የውጭ ምንዛሬ**

የንግድ ውድድር እና ሸማቾች ጥበቃ ማኅበር ማቋቋም በተመለከተ ሸማች ማህበራትና ዩኒየንኖች በማቋቋምና በማጠናከር የሸማቹን ጥቅም ከማስከበር አኳያ የሸማች ህብረት ስራ


ማህበራትን በማጠናከር የገበያ ማረጋጋት ስራ በመስራት ረገድ 1,388 የሸማች ጥበቃ ማኅበራትን ለማቋቋም ታቅዶ 652 የሸማች ጥበቃ ማኅበራትን በማቋቋም ከሶስት ዓመቱ 46.97 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ 388,037 ሸማች የማህበረሰብ ክፍሎች የደረሰኝ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል ዒላማ ተይዞ 293,255 የሸማች ማህበረሰብ ደረሰኝ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ የተቻለ ሲሆን ከሶስት ዓመቱ 75.57 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ ደግሞ 10.53 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ 878,921 የንግድ ድርጅቶች ወቅታዊ የዋጋ ዝርዝር እንዲለጥፉ ለማድረግ ታቅዶ 743,254 ድርጅቶች የዋጋ ዝርዝር እንዲለጥፉ በማድረግ ከሶስት ዓመቱ 84.56 በመቶ እንዲሁም ከአስር ዓመቱ 17.92 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ ከመረጃው ለመረዳት እንደተቻለው የሸማች ጥበቃ ማኅበር በማቋቋም ህጋዊ ንግድን ለማጠናከር እና የሸማቹን ማሕበረሰብ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የተገኘው ውጤት ዝቅተኛ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን ነጋዴዎች ትክክለኛ የሆነ የዋጋ ዝርዝር በመለጠፍ ለሸማቹ ማኅበረሰብ ደረሰኝ በመስጠት በኩል ከፍተኛ ክፍተት እንዳለበት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ስለዚህ ህጋዊ ንግድን ለማረጋገጥ በነጋዴው በኩል ህጋዊ ሆኖ እንዲሰራ አስፈላጊ መረጃዎችን አሟልቶ ለሸማቹ ማህበረሰብ እንዲሰጡ ለማድረግ ከነጋዴውና ከዘርፍ ማኅበራት ጋር በቅንጅት መስራት ይጠበቃል፡፡

ተቋሙ በሶስት ዓመቱ ውስጥ የታቀዱ ተግባራት በሚፈጽምበት ወቅት ብዙ ችግሮች ያጋጠሟቸው ሲሆን ለመጥቀስ ያህልም በህገ-ወጥ ነጋዴዎች ላይ የሚወሰደው ህጋዊ እርምጃ አናሳ በመሆኑ ህገወጦችን ለማስተካከል መቸገር፣ የበጀትና ግብዓት አቅርቦት እጥረት፣ የንግዱ ማህበረሰብ የንግድ ስራ ፈቃዱን በወቅቱ አለማደስ፣ የንግድ ድርጅቶች ደረሰኝ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን፣ የድጎማ ተጠቃሚ አሽከርካሪዎች ምንም አገልግሎት ሳይሰጡ የድጎማ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ የተዘረጋ አሰራር አለመኖር፣ የንግድና ግብይት ስርዓቱን ለማሳለጥ የአጋር አካላት ተሳትፎ ውስንነት ያለበት መሆኑ፣ ሁሉም ነጋዴ የግዥ ደረሰኝ ይዞ አለመገኘት፣ በየደረጃው የሚገኝ ፈፃሚ አካል በቁርጠኝነት ስራዎችን የመፈጸም ውስንነት መኖሩ፣ ለቆዳና ሌጦ አቅራቢዎች የመጋዘን መስሪያ የቦታ ችግር መኖሩ፣ የቁም እንስሳትን ኤክስፖርት ለማድረግ ምቹ ሁኔታ አለመፈጠር፣ ለቁም እንስሳት የገበያ ማዕከል በአዋጁ መሰረት ባለመሰጠቱ በየሰፈሩና በአስፓልቱ ግብይት መፈጸሙና ህገወጥ ደላላውንና ነጋዴውን ለመቆጣጠር አስቸጋሪ መሆኑ፣ የመሰረታዊ ምርት (ስንዴ፣ ስኳርና የምግብ ዘይት እንዲሁም የነዳጅ እና ቤንዚን) አቅርቦት እጥረት መኖሩ፣ የስሚንቶ ምርት አቅርቦት ስርዓት የሌለው መሆኑ፣ የዋጋ ንረት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ

መምጣት፣ በግብይት ማዕከል የእንስሳት ምርት ጥራት ቁጥጥር ባለሙያ አለመኖርና በግብይት ማዕከል ተገኝቶ መሸኛ አለመስጠት፣ በሲስተም መቆራረጥ ኦላይን የንግድ ፈቃድና ዕድሳት ለመስጠት መቸገር እና በክልሉ ወቅታዊ የሰላም እጥረት መኖሩ ናቸው፡፡

### 3.2.7. ሥራና ሥልጠና ልማት አፈጻጸም

የሥራ ዕድል ፈጠራ እና ኢንተርፕራይዝ ልማት ስራዎች አፈጻጸምን በሚመለከት የስራ እድል ፈጠራ ስራዉ በ3 ዓመት ውስጥ በከተማና በገጠር አዲስ ኢንተርፕራይዞችን በማቋቋም፣ነባር ኢንተርፕራይዞችን በማጠናከር፣ በመንግስት ትልልቅ ፕሮጀክቶችና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች እንዲሁም በመንግስት መስሪያ ቤቶችና በልማት ድርጅቶች ውስጥ 3,200,813 የስራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡አፈፃፀሙም ከ3 ዓመቱ 87.19% ሲሆን ከ10 ዓመቱ ደግሞ 26.15% መሆኑን ያሳያል፡፡ ከተፈጠረው የስራ ዕድል ውስጥ ቋሚ የስራ እድል በከተማ እና በገጠር 61.24% እና 54.3% ሲሆን ጊዜያዊ ደግሞ 36.18% እና 40.7% በቅደም ተከተል መሆኑን ያመለክታል፡፡ በተጨማሪም የስራ እድል ፈጠራዉ በከተማ እና በገጠር በዋና ዋና ዘርፎች ስንመለከት በከተማ አገልግሎት ዘርፍ 456,442 (50.5%)፣ኢንዱስትሪ 363,560(40%) እና ግብርና ዘርፍ 86,443(9.5%) ድርሻ ሲኖራቸዉ በገጠር ግብርና 897,418(74%)፣አገልግሎት 173,532(14.4) እና ኢንዱስትሪ 140,953(11.6) ድርሻ እንዳላቸዉ መረጃዉ ያሳያል፡፡ በመሆኑም በዚህ መንገድ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥን ለማረጋገጥ ስለማያስችልና እየተደረጉ ያሉ ፈርጀ ብዙ እንቅስቃሴዎችን የሚደግፍ ስለማይሆን በቀጣይ ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉትን አቅጣጫዎች ከግምት ዉስጥ በማስገባት የክልሉን ስራ አጥነት ምጣኔ እንዲቀንስ እንዲሁም በዘላቂ የስራ ዘርፎች ማለትም በአምራች ኢንዱስትሪዎች የስራ ስምሪትን እውን ለማድረግ ችግሮችን መለየትና የመፍትሄ ሀሳቦችን ማመንጨት ላይ በትኩረት መስራት ይጠይቃል፡፡




**ግራፍ17 ፡የስራ እድል ፈጠራ ስራ በዋና ዋና ዘርፎች የከተማ ና ገጠር ንፅፅር**

የሀገር ውስጥ የሥራ ስምሪት አገልግሎትን በሚመለከት በአሁኑ ወቅት በክልላችንም ሆነ በአገር አቀፍ ደረጃ ሥራ አጥነት እንደጉልህ ችግር ሆኖ ይታያል፡፡ በ2013ዓ.ም በተደረገ የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ጥናት በአማራ ክልል ከአስር አመት በላይ ያለዉ የስራ አጥ ሰዎች ቁጥር 891,911 የነበረ ሲሆን ከዚህ ዉስጥ እድሚያቸዉ ከ15-29 የሆኑ ወጣቶች ከፍተኛዉን ድርሻ ይዘው ይገኛሉ፡፡እድሜያቸዉ ለስራ ከደረሱ የከተማ ነዋሪዎች ዉስጥ የከተማ ስራ አጥነት ምጣኔ በ2013 17.9 በመቶ እና በ2014 ዓ.ም 19.9 በመቶ የሚሆኑት ስራ የሌላቸዉ ሲሆን የ2014 ዓ.ም የ2 በመቶ ጭማሪ አለው፡፡ በከተማ እድሚያቸዉ 15-29 ካሉ ወጣቶች ዉስጥ የ2014 የማዕከላዊ ስታትስቲክስ የናሙና ጥናት እንደሚያመለክተው በ2013 23.6 በመቶ ሲሆን በ2014 ዓ.ም 28.8 በመቶ የሚሆኑት ስራ እንደሌላቸዉ ያሳያል፡፡ በዚሁ የእድሜ ክልል ውስጥ በ2013 ዓ.ም ከነበረዉ ስራ አጥ ቁጥር ጋር ሲነፃፀር በ2014 ዓ.ም የ5.2 በመቶ ጭማሪ አለው፡፡የሥራ አጥነት ቁጥር መጨመር ለኢኮኖሚ እድገት መቀነስ፣በየጊዜው ለሥራ ፍለጋ ከገጠር ወደ ከተሞች ለመፍለስ ምክንያት ከመሆኑም በላይ የወጣት ስራ አጥነት ውጤቱ ለህገ- ወጥ ድርጊቶች መስፋፋት፣ ለግጭቶች እና አለመረጋጋት ችግሮች መነሻ መሆኑ አይቀርም፡፡ በመሆኑም በአስር ዓመቱ 722,389 በአገር ውስጥ የሥራ ስምሪት ድጋፍ በማድረግ ዜጎችን የስራ እድል ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ በ3 ዓመት ዉስጥ 300,875 ዜጎች ተጠቃሚ ሲሆኑ አፈፃፀሙ ከ3 ዓመት 41.65% ሲሆን ከአስር ዓመቱ ደግሞ 10.27% የተከናወነ መሆኑን ያሳያል፡፡

በተጨማሪም በአገር ውስጥ ስራና ሰራተኛ ለማገናኘት ጥያቄ ለሚያቀርቡ አዲስ ፈቃድ መስጠት በተመለከተ በአስር ዓመት 450 በ3 ዓመት ደግሞ 111 ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ ለ96 ኤጀንሲዎች ፈቃድ ተሰጥቷል ፡፡ አፈፃፀሙ ከ3 ዓመቱ 86.48% ሲሆን ከአስር ዓመቱ ደግሞ

21.33% መሆኑን ያሳያል፡፡ መረጃው እንደሚያመለክተው ለስራ ፈላጊ ዜጎች በአገር ውስጥ የስራ ስምሪት ተጠቃሚ ለማድረግ ከታቀደው አንፃር ዝቅተኛ በመሆኑ ተቋሙ በአገር ውስጥ የስራ እድል ፈጠራ ስራ ከአሰሪ ና ሰራተኛ አገናኝ ድርጅቶች ጋር በቅንጅት መስራት የስራ ስምሪቱን ከደላሎች በማዉጣት የዜጎችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ይጠበቃል፡፡

በሌላ በኩል የውጭ አገር የሥራ ስምሪት አገልግሎቶችን ሀገራት በከፊል ያልተማረዉንም ሆነ የተማረዉን የህብረተሰብ ክፍል አማራጭ የስራ እድሎችን ለመፍጠር የተለያዩ ስልቶችን በመንደፍ በርካታ ተግባራትን እንደሚያከናወኑ ይታወቃል፡፡ ከዚህ አኳያ የኢትዮጵያ መንግስት ከአጋር እና ወዳጅ አገራት ጋር የጋራ ስምምነት በመፍጠር የዜጎች መብት እና ደህንነት ተጠብቆ በህጋዊ ኤጀንሲዎች አማካኝነት የውጭ አገር የሥራ ስምሪት እየተሰጠ ይገኛል፡፡ በመሆኑም እንደ ክልል 26,384 ዜጎችን የውጭ አገር የስራ ስምሪት ለመስጠት ታቅዶ 3,467 ወይም 13.64% ብቻ ተከናውኗል፡፡,ከመረጃው ለመረዳት እንደሞከርነው ክልሉ በሚሊዮን የሚቆጠር ስራ ፈላጊ ያለዉ ቢሆንም በመንግስት ፍላጎት መሰረት የሚመጡ የውጭ አገር የስራ እድሎችን ለመጠቀም የተሰራዉ ስራ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም፡፡ በመሆኑም በቀጣይ ቀሪ ዓመታት በዚህ ዙሪያ የሚስተዋለውን ችግር ማለትም የሙያ ክህሎት ስልጠና፣ፓስፖርት ለማውጣት በኢሚግሬሽን ኤጀንሲ በኩል ያለው አሰልቺ ቢሮክራሲ ከሚመለከታቸው አጋር አካላት ጋር በቅንጅት በመፍታት በውጭ አገር የስራ እድል ለማግኘት ፍላጎት ያላቸውን ዜጎች ተጠቃሚ ማድረግ ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ አይሆንም፡፡

በሌላ በኩል የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ከሚሰጣቸው ኢንተርፕራይዞች መካከል በትኩረት ዘርፍ የተሰማሩ በ10 ዓመት 143,565 ኢንተርፕራይዞች በ3 ዓመት ደግሞ 35,064 ኢንተርፕራይዞችን ከደረጃ ደረጃ እንዲሸጋገሩ በማድረግ ተጠቃሚነታቸዉን ለማሳደግ ታቅዶ፣ 30,898 ኢንተርፕራይዞችን ከደረጃ ደረጃ በማሸጋገር ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ የተቻለ ሲሆን ከጥቃቅን ጀማሪ ወደ ጥቃቅን ታዳጊ የተሸጋገሩ 88.47%፣ ከጥቃቅን ታዳጊ ወደ ከጥቃቅን መብቃት 88.37%፣ከጥቃቅን መብቃት ወደ አነስተኛ ጀማሪ 90.51%፣ከአነስተኛ ጀማሪ ወደ አነስተኛ ታዳጊ 79.91%፣ከአነስተኛ ታዳጊ ወደ አነስተኛ መብቃት 90.65%፣ከአነስተኛ መብቃት ወደ ታዳጊ መካከለኛ የተሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች 99.24% ሲሆን ጥቅል አፈፃፀሙ ከ3 ዓመት 88.11% ሲሆን ከ10 ዓመቱ ደግሞ 21.52% የደረጃ ሽግግር ያደረጉ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በተመሳሳይ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ከሚሰጣቸው ኢንተርፕራይዞች መካከል በትኩረት ዘርፍ የተሰማሩ በ10 ዓመት 14,944 ሞዴል ኢንተርፕራይዞችን በ3 ዓመት ደግሞ 3,619 ሞዴል ኢንተርፕራይዞችን በመፍጠር ተጠቃሚነታቸዉን ለማሳደግ ታቅዶ

4,073 ሞዴል ኢንተርፕራይዞችን ማፍራት ተችሏል። አፈፃፀሙ ከ3 ዓመት 112.54 ሲሆን ከ10 ዓመት ደግሞ 27.25 ነው። የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ከሚሰጣቸው ኢንተርፕራይዞች መካከል የ5,935 ኢንተርፕራይዞችን ተሞክሮ በመቀመር እና ከተቀመሩት ውስጥ የ2,963 ኢንተርፕራይዞችን ተሞክሮ ለ74,960 ኢንተርፕራይዞች በማስፋት ተጠቃሚነታቸዉን ማሳደግ በ3 ዓመት ደግሞ የ1,627 ኢንተርፕራይዞችን ተሞክሮ በመቀመር እና ከተቀመሩት ውስጥ የ727 ኢንተርፕራይዞችን ተሞክሮ ለ18,144 ኢንተርፕራይዞች በማስፋት ተጠቃሚነታቸዉን ለማሳደግ ታቅዶ፣1,523 ኢንተርፕራይዞች ምርጥ ተሞክሮ ተቀምሮ፣ለ7,599 ኢንተርፕራይዞች ተሞክሯቸዉ የሰፋ ሲሆን በዚህም 24,567 ኢንተርፕራይዞች ተጠቃሚ ሆነዋል። አፈፃፀሙ ከ3 ዓመቱ በመቀመር 93.60%፣በማስፋት 104.5%፣በተጠቃሚነት 407% ሲሆን ከ10 ዓመቱ ደግሞ በመቀመር 2.57%፣በማስፋት 256%፣በተጠቃሚነት 32.77% መሆኑን ያመለክታል። በዚህ ዙሪያ የተከናወኑ ተግባራት ከእቅድ በላይ ቢሆንም ተግባሩ መሬት ላይ ያመጣዉን ለዉጥ በማየት ወደ ተግባር መግባት፣ የኢንዱስትሪዎችን የደረጃ ሽግግር በማድረግ ሞዴል ኢንተርፕራይዞችን መፍጠር የሚለዉን ግብ ለማሳካት አሁን ላይ የሚታየውን የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን የድጋፍ አሰጣጥ የጥራት ጉድለት ማሻሻል የሚያስችል አሰራር በመዘርጋት በቀጣይ ቀሪ ዓመታት የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ተግባራት ዉጤት በሚያመጣና የዜጎችን ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ መልኩ መስጠት ይገባል።

የትምህርትና ስልጠና አግባብነትና ጥራትን ከማሻሻል አንጻር አመታዊ የመንግስት ቴክኒክ እና ሙያ ኮሌጆች የመደበኛ አዲስ ሰልጣኝ ቅበላ በ2012 ከነበረበት 52,596 በ2022 ዓ.ም 136,418 በማሳደግ ጠቅላላ ቅበላዉን በዕቅድ ዘመኑ 922,059 ሰልጣኞችን በማፍራት የኢንዱስትሪዉን የሰለጠነ የሰዉ ሃይል ፍላጎት ማሟላት፣በ3 ዓመት ደግሞ ወደ 70,005 በማሳደግ ጠቅላላ ቅበላውን 191,502 ሰልጣኞችን ለማፍራት ታቅዶ በ3 ዓመት ውሰጥ ከዓመታዊ ቅበላው 20,748 የደረሰ ሲሆን ጠቅላላ ቅበላው 45,134 መድረሱን ያሳያል። አፈፃፀሙ ዓመታዊ ቅበላው ከ3 ዓመት 29.63% ከ10 ዓመት ደግሞ 15.20% ብቻ መፈፀሙን ያሳያል።

ከዚህ ባሻገር ዓመታዊ የመንግስት ቴክኒክ እና ሙያ ኮሌጆች የመደበኛ ነባር ሰልጣኝ ቅበላ በ2012 ከነበረበት 67,989 በ2022 ዓ.ም 159,652 በማሳደግ ጠቅላላ ቅበላዉን በዕቅድ ዘመኑ 1,093,379 ሰልጣኞችን በማፍራት የኢንዱስትሪዉን የሰለጠነ የሰዉ ሃይል ፍላጎት ማሟላት በ3

ዓመት ደግሞ ወደ 81,928 በማሳደግ ጠቅላላ ቅበላውን 238,392 ሰልጣኞችን ለማፍራት ታቅዶ በ3 ዓመት ውስጥ ዓመታዊ ቅበላው 78,670 ደርሶ የነበረ ሲሆን ጠቅላላ ቅበላው 161,001 ማድረስ ተችሏል፡፡አፈፃፀሙ ከዓመታዊ ቅበላው ከ3 ዓመት 96% ሲሆን ከ10 ዓመት ደግሞ 49.27% መሆኑን ያመለክታል፡፡የጠቅላላ ቅበላው ከ3 ዓመት 67.5% ሲሆን 10 ዓመት ደግሞ 1.72%ነው፡፡ ከመረጃዉ ለመረዳት እንደተቻለዉ የመደበኛ ሰልጣኝ ቅበላ መርሀግብር አፈጻጸም በዚህ ዘርፍ ከተያዘው ግብ አኳያ መልካም አፈጻጸም የታየበት ነው፡፡ ለዚህም ውጤት መምጣት አዎንታዊ አስተዋጽኦ ከነበራቸው ጉዳዮች ውስጥ በአዲስ የሚከፈቱ ማሰልጠኛዎች ቁጥር እየጨመረ መምጣቱ፣በቴክኒክና ሙያ ዘርፍ የመሰልጠን ፍላጎት እያደገ መምጣቱ እንዲሁም በየአመቱ የኮሌጆች የመቀበል አቅማቸው እያደገ መምጣቱ ይጠቀሳሉ፡፡ በ3 ዓመት የታየዉ አፈፃፀም በቁጥር ደረጃ የተሻለ ቢሆንም በ10 ዓመቱ የተቀመጠዉን የሰለጠነ እና ለአምራች ኢንዱስትሪዉ ግብዓት የሚሆን በክህሎቱ ብቁ የሰዉ ሀይል ከማፍራት አንፃር ሲታይ አሁንም በርካታ ቅሬታ የሚነሳበት በመሆኑ በቀጣይ ቀሪ ዓመታት በገበያ ተፈላጊ የሆኑ እና እዉቀቱ ፣ ክህሎቱ ያደገ ስራ ፈላጊ ዜጋ በመፍጠር በኩል የተሻለ ዝግጅትና ርብርብ ማድረግ ይጠበቃል፡፡ ከዚሁ ጋር በተገናኝ የግል እና መንግታዊ ያልሆኑ ኮሌጆች የመደበኛ **አዲስ ሰልጣኝ** ቅበላ በ2012 ከነበረበት 47,240 በ2022 ዓ/ም በ133,116 በማሳደግ ጠቅላላ ቅበላዉን በዕቅድ ዘመኑ 180,356 ሰልጣኞችን በማፍራት የኢንዱስትሪዉን የሰለጠነ የሰዉ ሃይል ፈላጎት ማሳደግ፣ በ3 ዓመት ደግሞ 17,064 ማድረስና ጠቅላላ ቅበላው ደግሞ 49,542 ሰልጣኞጭን ለማፍራት ታቅዶ ቅበላው 17,783 የደረሰ ሲሆን ጠቅላላ ቅበላው ደግሞ 30,986 ሆኗል፡፡ አፈፃፀሙም ከ10 ዓመቱ 13.35% ሲሆን ጠቅላላ ቅበላው ደግሞ 17.18% ነው፣ ከ3 ዓመቱ ድግሞ 104.2% ሲሆን ጠቅላላ ቅበላው ደግሞ 62.54% መሆኑን ያሳያል፡፡ የመደበኛ **ነባር ሰልጣኝ** ቅበላን በሚመለከት በ2022 ዓ/ም በ20,602 በማሳደግ ጠቅላላ ቅበላዉን በዕቅድ ዘመኑ 122,524 ሰልጣኞችን በማፍራት የኢንዱስትሪዉን የሰለጠነ የሰዉ ሃይል ፍላጎት ማሳደግ፣ በ3 ዓመት ደግሞ 37,123 ማድረስና ጠቅላላ ቅበላው ደግሞ 105,854 ሰልጣኞን ለማፍራት ታቅዶ 16,107 የደረሰ ሲሆን ጠቅላላ ቅበላው ደግሞ 63,285 ሆኗል፡፡ አፈፃፀሙምም ከ10 ዓመቱ 78.18% ፣ ጠቅላላ ቅበላው ደግሞ 51.65% ሲሆን ከ3 ዓመቱ ድግሞ 43.38% እንዲሁም ጠቅላላ ቅበላው ደግሞ 59.78% መድረሱን ያመለክታል፡፡

የገበያ ልማትና ግብይት ሥራዎች አፈጻጸምን በሚመለከት የጥቃቅንና ከማኑፋክቸሪንግ ዉጭ የሆኑ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን፣ መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች፣ ከከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች፣

ከመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (መያድ)፣ ኢንተርፕራይዞችን እርስ በርስ ትስስር (በምርትና ግብዓት) እንዲሁም በግልና በተቋማት በሚፈጠር የገበያ ትስስር በ10 ዓመት ውስጥ ለ290,000 ኢንተርፕራይዞችንና 870,000 አንቀሳቃሽን የብር 22,350,000,000፣ በ3 ዓመት ደግሞ ለ87,000 ኢንተርፕራይዞች፣ ለ261,000 አንቀሳቃሾች፣ ብር 6,525,000,000 የገበያ ትስስር በመፍጠር የኢንተርፕራይዞችን ተጠቃሚነት ለማሳደግ ታቅዶ፣ ለ107,978 ኢንተርፕራይዞች (426,812 አንቀሳቃሾች) የብር 16,736,551,000 ትስስር ተፈጥሮላቸዋል፣ አፈፃፀሙም ከ3 ዓመት በኢንተርፕራይዝ 124%፣ በአንቀሳቃሽ 65.41%፣ በብር 256% ሲሆን ከ10 ዓመቱ ደግሞ በኢንተርፕራይዝ 37.23%፣ በአንቀሳቃሽ 49.05%፣ በብር 74.88% መከናወኑን ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል የውጭ አገር የገበያ ትስስር በመፍጠር በ10 አመት አሁን ካሉት 92 ኢንተርፕራዞች በተጨማሪ 200 ኢንተርፕራዞችን ወደ ዉጭ ገበያ በማስገባት 409,090,909 USD በማግኘት 876 አንቀሳቃሾችን በአለም አቀፍ ገበያ በምርት ጥራትና መጠን ተወዳዳሪነታቸውንና ተጠቃሚነታቸውን ለማሳደግ እንዲሁም በ3 ዓመት ደግሞ 60 ኢንተርፕራይዞች 12,727,272 USD ትስስር ለመፍጠር ታቅዶ፣ ለ127 ኢንተርፕራይዞች 3,569,480 USD ትስስር ተፈጥሮላቸዋል፡፡ አፈፃፀሙ ከ3 ዓመቱ በኢንተርፕራይዝ 211%፣ በUSD 28% ሲሆን ከ10 ዓመቱ ደግሞ በኢንተርፕራይዝ 63.5%፣ በአሜሪካ ዶላር ደግሞ 0.87% መሆኑን ያሳያል፡፡ በመሆኑም በቀጣይ ቀሪ ዓመታት በኢንተርፕራይዞች ዙሪያ የሚስተዋለዉን የምርት መጠን እና የጥራት ዉስንነት በማስተካከል የሚመረተዉ ምርት በአለም ዓቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆን ድጋፍ መስጠት እና ማበረታቻዎችን በመንደፍ የተሻለ የገበያ ትስስር በመፍጠር የሚታየዉን የዉጭ ምንዛሬ እጥረት መቅረፍ ይገባል፡፡

ብድር እና ቁጠባ ማመቻቸትን በተመለከተ በ10 ዓመት ውስጥ ከአበዳሪ ተቋማት ጋር በመቀናጀት ለ350,000 አዳዲስ እና ነባር ኢንተርፕራይዞች የብር 24,500,000,000 የብድር አገልግሎት በማቅረብ በዘመኑ መመለስ ያለበት ብድር 100% እንዲመለስ እና የህብረተሰቡን የቁጠባ ባህል እና ግንዛቤ በማሳደግ የብድሩ 80 በመቶ ከህብረተሰቡና ከትምህርት ተቋማት ተማሪዎች በሚሰበሰብ ቁጠባን ለማሳደግ እንዲሁም በ3 ዓመት ደግሞ 105,000 ኢንተርፕራይዞች ብር 7,350,000,000 ቢሊዮን ለመስጠትና ቁጠባውን 5,880,000,000 ቢሊዮን ለማድረስ ታቅዶ ለ100,031 ኢንተርፕራይዞች ብር 8,201,178,952 ብድር ተጠቃሚ የሆኑ ሲሆን ለዚህ አገልግሎት የሚውል ብር10,347,295,954 በቁጠባ ተሰባስቧል፡፡ አፈፃፀሙም ከ3 ዓመት በኢንተርፕራይዝ 95.26%፣በብር111.58% ሲሆን ከ10 ዓመቱ ደግሞ

በኢንተርፐራይዝ 28.58%፣በብር 33.47% መሆኑን ያሳያል፡፡ በመረጃው እንደተመላከተዉ በ3 ዓመት ያለው አፈፃፀም የተሻለ ቢሆንም ከ10 ዓመቱ መሪ እቅድ አንፃር ሲታይ በኢንተርፐራይዝ 28% እና በብር 33% መሆኑን ያሳያል፡፡ በተመሳሳይ በ10 ዓመቱ መሪ ዕቅድ ባይታቀድም በ3 ዓመት ውስጥ የስራ ዕድል ፈጠራውን ለማገዝ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ እንዲተገበር ከመንግስት በጀት የተመደበ ብር 1,474,569,557 9,203 ኢንተርፐራይዞች የተሰራጨ ሲሆን አመላለሱን በተመለከተ በ2013 ዓ.ም 70.32%፣በ2014 ዓ.ም 69% እና በ2015 ዓ.ም 75% ብድር ማስመለስ ተችሏል፡፡መረጃው እንደሚያመለክተው በመደበኛም ሆነ በተዘዋዋሪ የተሰራጨዉ ብድር አመላለስ ዝቅተኛ እና የቀጣይ የትዉልዱን ጥሪት የሚያሳጣ በመሆኑ በሚቀጥለዉ ቀሪ ዓመታት ከብድር አስመላሽ ግብረ ሀይልና ከአበዳሪ ተቋማት ጋር በመናበብ ና በቅንጅት በመስራት የተሻሉ የብድር አመላለስ ስትራቴዎችን በመንደፍ የተሰራጨ የመደብኛ እና ተዘዋዋሪ ብድር በሙሉ ማስመለስ ይገባል፡፡

**ሠንጠረዥ13 ፡ በሦስት ዓመት ዉስጥ የተሠራጨ እና የተመለሰ የብድር መጠን**

| ተግባር | መለኪያ | የ10 እቅድ | የ3 ዓመት እቅድ | የ3 ዓመት ክንዉን | ከ10 ዓመቱ ያለዉ ድርሻ (%) |
|---|---|---|---|---|---|
| የተቆጠበ የገንዘብ መጠን በቢሊዮን | በብር | 19.6 | 5.88 | 8.3 | 42.3 |
| የብድር ተጠቃሚ ኢንተርፐራይዞች ብዛት | በቁጥር | 350,000 | 105,000 | 97,160 | 27.76 |
| የተሠራጨ የብድር መጠን በቢሊዮን | በብር | 24.5 | 7.35 | 7.32 | 28.87 |
| የተመለሰ የብድር መጠን በመቶኛ | በመቶኛ | 100 | 100 | 71.44 | 71.4 |

**የመረጃ ምንጭ፡** ስራ እና ስልጠና ቢሮ 2016 ዓ.ም

ግንባታና ግብዓት አቅርቦት ስራዎችን በሚመለከት በ10 ዓመት ውስጥ የማሰልጠኛ ኮሌጆችን ከነበሩበት 94 ወደ 154፣የፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆችን ከ19 ወደ 28 በማሳደግ ጥራትን እና ተደራሽነትን ማረጋገጥ፣በ3 ዓመት ደግሞ 112 ኮሌጆችና 20 ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ለማሳደግ ታቅዶ፣ 13 ተጨማሪ ኮሌጆች ተከፍተው ወደ 107 እንዲሁም 4 ተጨማሪ ቴክኒክ ኮሌጆች በመክፈት ወደ 23 ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ አድገዋል፡፡አፈፃፀሙ ከ3 ዓመቱ ኮሌጅ 95.53%፣ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች 115% ሲሆን ከ10 ዓመቱ ደግሞ በኮሌጆች 69.4%፣በፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች 82.14% መሆኑን ያሳያል፡፡ በተመሳሳይ በ3 ዓመት 114 አዲስ የአንድ ማዕከላት አገልግሎት መክፈት፣34,200,000 ብር ግንባታ ገንዘብ ለማሰባሰብ ታቅዶ፣ በእቅድ ዘመኑ ከመንግስት እና ከህዝብ ብር 1,050,819,154 በመሰበሰብ ተጨማሪ 40 አዲስ ማዕከላት እንዲከፈቱ ተደርጓል፡፡

የሼድ አቅርቦትን ከማሳደግ አንጻር በ10 ዓመት ውስጥ በገጠር እና በከተማ የነበሩትን 15,518 ሼዶች ቁጥር ወደ 35,518 በማሳደግ ለ100,000 ኢንተርፕራይዞች እንዲሁም በ3 ዓመት ደግሞ ወደ 6,000 በማሳደግ እና መሰረተ ልማት እንዲሟላላቸው በማድረግ ለ30,000 ኢንተርፕራይዞች ለማስተላለፍ ዕቅድ ተይዞ 6,010 ሼዶች ተገንብተው ለ25,027 ኢንተርፕራይዞች ተላልፈዋል፡፡አፈፃፀሙም ከ3 ዓመት በሼድ 100%፣በኢንተርፕራይዝ 83.42% ሲሆን ከ10 ዓመት ደግሞ በሼድ 30.05%፣በኢንተርፕራይዝ 25.02% መሆኑን ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ የስራ እድል ፈጠራ ስራዉ በ3 ዓመት ውስጥ በከተማና በገጠር አዳዲስ ኢንተርፕራይዞችን በማቋቋም፣ነባር ኢንተርፕራይዞችን በማጠናከር፣ በመንግስት ትልልቅ ፕሮጀክቶችና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች እንዲሁም በመንግስት መስሪያ ቤቶችና በልማት ድርጅቶች ውስጥ 3,200,813 የስራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡ የስራ እድል ፈጠራዉ በከተማ እና በገጠር በዋናዋና ዘርፎች ስንመለከት በከተማ አገልግሎት ዘርፍ 456,442 (50.5%)፣ ኢንዱስትሪ 363,560(40%) እና ግብርና ዘርፍ 86,443(9.5%) ድርሻ ሲኖራቸዉ በገጠር ግብርና 897,418(74%)፣አገልግሎት 173,532(14.4) እና ኢንዱስትሪ 140,953(11.6) ድርሻ እንዳላቸዉ መረጃዉ ያሳያል፡፡ አፈፃፀሙም ከ3 ዓመቱ 87.19% ሲሆን ከ10 ዓመቱ ደግሞ 26.15% ብቻ መሆኑን ያሳያል፡፡ ከተፈጠረው የስራ ዕድል ውስጥ ቋሚ የስራ እድል በከተማ እና በገጠር 61.24% እና 54.3% ሲሆን ጊዜያዊ ደግሞ 36.18% እና 40.7% በቅደም ተከተል መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይህ የሚያሳየዉ ከተፈጠረው የስራ እድል ውስጥ በጊዜያዊነት የተፈጠረው የስራ እድል ቁጥር ያለው ድርሻ ቀላል እንዳልሆነ ያሳያል፡፡ የክልሉ የስራ እድል

ፈጠራ ስትራቴጅ እንደሚያሳየው የስራ እድል ፈጠራው በበቂ ዝግጅት ተመርቶ በተቻለ መጠን የስራ እድል የሚፈጠርላቸው ዜጎች በቋሚና ዘላቂ የስራ ዘርፎች እንዲሰማሩ ከተቀመጠው አቅጣጫ አኳያ ስራ ፈላጊ ዜጎች የራሳቸውን ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን በማቋቋም በሚደረግላቸው ድጋፍ እንዲቋቋሙ የተደረገው ጥረት ከተፈጠረው የስራ እድል ጋር ሲነጻጸር ያለው ድርሻ ከፍተኛ ቢሆንም ከሚፈለገው ውጤት አኳያ ገና ብዙ የሚቀረው መሆኑን በመገንዘብ በቀጣይ ቀሪ ዓመታት በልዩ ትኩረት መስራት ይገባል፡፡
የአገር ዉስጥም ሆነ የዉጭ አገር ስራ ስምሪት ክልሉ ካለዉ የስራ አጥ ቁጥር አንፃር ዝቅተኛ ሲሆን በቀጣይ ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉትን አቅጣጫዎች ከግምት ዉስጥ በማስገባት የክልሉን ስራ አጥነት ምጣኔ እንዲቀንስ እንዲሁም በዘላቂ የስራ ዘርፎች ስምሪትን እውን ለማድረግ ችግሮችን በመለየትና የመፍትሄ ሀሳቦችን በማመንጨት በትኩረት መስራትን ይጠይቃል፡፡

የገበያ ልማትና ግብይት ሥራዎች በሦስት ዓመቱ በሀገር ውስጥ ገበያ በዕድገት ተኮር ዘርፍ የተሰማሩትን የኢንተርፕራይዞችን ምርትና አገልግሎት በሀገር ውስጥ ገበያ በማስተሳሰር ከሽያጭ የሚገኘውን ገንዘብ በማሳደግ ኢንተርፕራይዞችን እና አንቀሳቃሾችን ተጠቃሚ በማድረግ የገበያ ተወዳዳሪነትንና ትርፋማነትን ለማሳደግ ከተያዘው ግብ አንጻር በገበያ ትስስር የተገኘ ገንዘብ ፣ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች እንዲሁም በአንቀሳቃሾች ተጠቃሚነት ረገድ የተሻለ ቢሆንም በውጭ አገር የገበያ ትስስር በመፍጠር የሚገኘውን የውጭ ምንዛሬ በእቅድ ዘመኑ ውስጥ በማሳደግ ኢንተርፕራይዞችን እንዲሁም አንቀሳቃሾችን በዓለም አቀፍ ገበያ በማስተሳሰር በምርት ጥራትና መጠን ተወዳዳሪነታቸውንና ተጠቃሚነታቸውን ለማሳደግ የተያዘው ግብ አኳያ ዝቅተኛ እና አዝጋሚ በመሆኑ በቀጣይ ተግዳሮቶችን በሚገባ በመለየት የተሻለ ስራ መስራት ይገባል፡፡

በመጨረሻም ስራ እድል ፈጠራው ግቦች በበቂ ሁኔታ አለመከናወን እንደምክንያት የሚጠቀሱት የስራ እድል ፈጠራ ስራዉ በዘርፎች ወይም የሴክተሮች የመቀናጀት፣በባለቤትነትና በሃላፊነት ስሜት የመስራት ጉድለት፣ የመስሪያና መሸጫ ቦታ እና ሼድ አቅርቦት ችግር፣ ከፍተኛ የሆነ የሀይል አቅርቦት እጥረት፣ በወቅታዊ የሰላም እጦት ምክንያት በሙሉ አቅም ማምረት አለመቻል፣ የገበያ ትስስር ችግር፣ ለስራ ማስጀመሪያ የሚዉል የብድር አቅርቦት ዉስንነት፣ ለዉጭ ገበያ የሚቀርበዉ ምርት በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ አለመሆን፣ ማሽነሪ ለማስገባት የዉጭ ምንዛሬ እጥረት እና አብሮ ለመስራትና ለመለወጥ በኢንቀሳቃሾች በኩል ያለ የአመለካከት ችግር መኖር ተግባሩ በሚፈለገዉ ደረጃ ግቡን እንዳያሳካ እየፈተነዉ ይገኛል፡፡

በመሆኑም በቀጣይ ቀሪ ዓመታት በዘርፉ የተንሰራፋዉን የግብዓትና የአመለካከት ችግር በመቅረፍ እና አዳዲስ ኢንተርፕራይዞችን በከተማ እና በገጠር በማቋቋም የስራ እድል ፈጠራ ተግባሩን ዘላቂ ማድረግ ይጠበቃል፡፡

## 3.3. የማህበራዊ ልማት ዘርፍ አፈጻጸም

### 3.3.1. የትምህርት ዘርፍ አፈጻጸም

ትምህርት ለቴክኖሎጂ መሻሻል፣ ለማህበራዊ ለውጥና ለኢኮኖሚ ዕድገት ቁልፍ መሣሪያ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ዛሬ በሣይንስና ቴክኖሎጂ እድገት ያመጡ አገሮች የሰው ሀብታቸውን ከአገራቸው ልማት እንዲሁም አለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን ጋር በማስተሳሰርና በማዘጋጀት በመተግበራቸው ውጤታማ ሊሆኑ ችለዋል፡፡ የውጤታማነታቸው ሚስጢር የሚያስፈልጋቸውን የሰው ሀይል በፖሊሲ አቅጣጫ በማስቀመጥ፣ ፖሊሲውን ለመተግበር የሚያስችሉ የረጅምና የአጭር ጊዜ እቅዶችን በማውጣት በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ የሰው ሀብት ማልማት መቻላቸው ነው፡፡ ከላይ እስከ ታች በሚገኘው የትምህርት መዋቅር  የክልላችን የትምህርት ልማት የአስር አመት እቅድ ላይ የተለዩትን የትኩረት መስኮች እና የማስፈጸሚያ ስልቶች የርብርብ  ማዕከል በማድረግ በመሰራት ላይ ይገኛል፡፡ ከዚህ አኳያም የዘመኑ የክልላችን የትምህርት ዘርፍ ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች፡-ማለትም በመልካም ስነምግባር የታነፁ ዜጎች፣ የገበያን ፍላጎትን መሠረት ያደረገ ጥራት ያለው ትምህርት፣ የትምህርት ሥርዓቱን በዲጂታል ቴክኖሎጂ መደገፍ፣አካታች የሆነ ትምህርት ተሳትፎና ውስጣዊ ብቃት፣ከሥራ ጋር የተሳሰረ የጎልማሶች እና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት፣  የተጠናከረ ያልተማከለ የትምህርት ሥርዓት እና የትምህርት ጥራት የማረጋገጥ ሥርዓት ናቸው፡፡ እነዚህ ወሣኝ ጉዳዩች ለመፈጸም በየደረጃው ባሉ የትምህርት ዘርፍ አማካይነት የተለያዩ ተግባራት የተከናወኑ ሲሆን ባለፉት ሶስት የእቅድ ዘመናት(ከ2013 እስከ 2015) የትምህርት ዘርፍ የእቅድ አፈፃፀም ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

በመልካም ሥነ ምግባር የታነፁና ለሥራ ዝግጁ የሆኑ ተማሪዎችን ማፍራትን በሚመለከት በትምህርት ጥራትና አግባብነት ውስጥ የመጀመሪያው ተግባር በመልካም ሥነ ምግባር የታነፁና ለሥራ ዝግጁ የሆኑ ተማሪዎችን ማፍራትና ማረጋገጥ ነው፡፡ የመጀመሪያው በአዲስ የተዘጋጀው የአንደኛ ደረጃ የግብረ ገብነት ትምህርት መጻሕፍት ወደ አፍ መፍቻ ቋንቋዎች የመተርጎም ስራ ሲሆን ከ1ኛ-6ኛ ክፍሎች የግብረገብ ትምህርት መማሪያና ማስተማሪያ መጻሕፍት በትምህርት ሚኒስተር በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተዘጋጅተዋል፡፡ በ2015 የትምህርት

አመት መጽሐፍቱን ከእንግሊዝኛ ወደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የመተርጎም ሂደት በአማርኛ ቋንቋ ተጠናቆ ወደ አዊኛ፣ ህምጠኛ እና ኦሮሞኛ ቋንቋ የሚደረገው የትርጉም ስራ በመሰራት ላይ ነው፡፡ በተማሪዎች ስነ ምግባርና ባህሪ የረኩ የተቋም ማህበረሰብ ክፍል እና ወላጆች ብዛት በመቶኛ በ2014 ዓ.ም ከነበረበት 60.15% ወደ 69% ማድረስ ነበር፡፡ በዚህም መሰረት በተደረገ የናሙና ጥናት በጥቅሉ የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው የተቋማትና የወላጆች እርካታ 52.4% ሲሆን ከ10 አመቱም ሲወሰድ አፈጻጸሙ ተመሳሳይ ነው፡፡ ይህ ውጤት በ2014 ዓመት ከተመዘገበው በ7.75% ያነሰ ሲሆን ከሶስት አመት ዕቅዱ 16.6% እንዲሁም ከ10 አመቱ 47.6% የቀረው መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህም በተማሪዎች ስነምግባር የወላጆችና የተቋማት እርካታ ከአማካይ በላይ ቢሆንም አፈጻጸሙ ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡ በመሆኑም በቀጣይ የእቅድ አመታት የተማሪዎችን ስነምግባር ለማሻሻል የሚያስችሉ አሰራሮችን መተግበር ይገባል፡፡

የአጠቃላይ ትምህርት ጥራትና አግባብነት ዘርፍ ዋና ዋና ግቦች አፈጻጸምን በሚመለከት የትምህርት ተደራሽነት እና ውስጣዊ ብቃት ከማሳደግ አንጻር በዚህ ግብ ስር ከታቀዱት ዋና ተግባራት መካከል የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም የመጀመሪያው ነው፡፡ ስለሆነም ህፃናት የተስተካከለ የአካልና የአእምሮ፣ የስሜትና የማህበራዊ ግንኙነት እድገት በማዳበር ለመደበኛው ትምህርት እንዲዘጋጁ የሚያመቻች እንዲሁም በየደረጃው አካባቢያቸውን እንዲገነዘቡና እንዲያውቁ የሚያደርግ ፕሮግራም ነው፡፡ይህንን አገልግሎት ለማስፋፋት መንግሥት ልዩ ትኩረት በመስጠት የመደበኛው አፀደ ህፃናት አገልግሎት እንደተጠበቀ ሆኖ ሌሎች አማራጭ ፕሮግራሞችን እና የተፋጠነ የትምህርት ዝግጁነት በመጠቀም በስፋት በማዳረስ ላይ ይገኛል፡፡ የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም አፈፃፀምን በሚመለከት በ2012 ትምህርት አመት37.21% እና 32% የነበረውን የቅድመ አንደኛ ደረጃ ጥቅል እና ንጥር ተሳትፎ በ2015 ትምህርት አመት 895,404 ነባርና አዲስ ገቢ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ተማሪዎችን በማሳተፍ ጥቅል ተሳትፎውን ወደ 46.33% እንዲሁም ንጥር ተሳትፎን 779,564 ወደ 45.5 ለማድረስ ታቅዶ ጥቅል ተሳትፎው ከሶስት አመቱ 86.27%) እና ንጥር ቅበላው 33.00%(72.52%) እንዲሁም ከአመቱ 39.97% እና እና ከአመቱ 33.% የደረሰ ሲሆን ከመነሻው አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር ጥቅል ተሳትፎው የ2.76 እንዲሁም ንጥር ቅበላው የ7.75% እድገት ያሳዩ ቢሆንም ከታለመው ግብ አንጻር አፈጻጸሙ የጥቅል ተሳትፎው በ13.73% እንዲሁም **ንጥር ቅበላው** በ12.64% ያነሰ መሆኑን ስለሚያመለክት ከአስር አመቱ

ግብ ለመድረስ የ60.03% እና 60.25% ቀሪ ተግባር(back log) መኖሩን በመገንዘብ ከወዲሁ በቀጣይ ዘመን እቅዶች ላይ ጨምሮ ማቀድና መተግበር ይገባል፡፡

በአጠቃላይ በክልላችን በዚህ መርሃ ግብር በ2015 በጀት አመት የተመዘገበው ውጤት በአገር አቀፍ ደረጃ በ2015 የትምህርት አመት ከተመዘገበው 61.18% አማካይ ጥቅል ተሣትፎ አንፃር ሲመዘን በ14.85% የወረደ አፈጻጸም የተመዘገበ ሲሆን በአለም አቀፍ ደረጃ በቅደመ መደበኛ ትምህርት መርሃ-ግብር ሀገራት ቢያንስ 80% አፈጻጸም እንዲኖራቸው እንደ ስታንዳርድ ከተቀመጠው አንጻርም የክልላችንም ይሁን የአገራችን አፈፃፀም ዝቅተኛ መሆኑን በግልጽ ስለሚያሳይ በቀጣይ የተጠናከሩ ስራዎችን መስራት ይጠበቃል፡፡

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት በስምንት ዓመት የሚጠናቀቅ ሆኖ፣ በመሠረታዊና አጠቃላይ ትምህርት ለሚቀጥለው የትምህርት ደረጃ የሚያዘጋጅና በሂደት የሚዳብር መሠረታዊ ችሎታ ያላቸውን ዜጎች የሚያፈራ ነው፡፡ይህ ፕሮግራም መሠረታዊ ትምህርትን (ማንበብ፣ መፃፍ፣ ሃሣብን በቃል መግለጽ፣ መሠረታዊ ስሌትና ችግሮችን መፍታት መቻልን) ለተማሪዎች የሚያስጨብጥና ህፃናትን ለቀጣይ አጠቃላይ ትምህርትና ስልጠና የሚያዘጋጅ በመሆኑ አንገብጋቢ የሆነውን የትምህርት እድል መፍጠሪያ ሆኖ ተወስዷል፡፡ በመሆኑም በ2012 ዓ/ም ጥቅል የአንደኛ ክፍል የትምህርት ተሣትፎው 86.88% እንዲሁም **ንጥር ተሳትፎው 74.14**% የነበረ ሲሆን በ2015 የትምህርት ዘመን ጥቅል ተሳትፎውን ወደ 104.36% እንዲሁም **ንጥር ተሳትፎን** ወደ 100% ለማድረስ ታቅዶ በሶስት አመቱ **ጥቅል ተሳትፎው** 88.26%(84.57%) እና **ንጥር ቅበላው 78.29**% የደረሰ ሲሆን ከመነሻው አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር ጥቅል ተሳትፎው የ1.38% እንዲሁም **ንጥር ቅበላው የ4.14**% እድገት ያሳዩ ቢሆንም ከሶስት አመቱ ግብ አንጻር አፈጻጸሙ የጥቅል ተሳትፎው በ16.07% እንዲሁም **ንጥር ቅበላው** በ21.71% ያነሰ ስለሆነ ከአስር አመቱ ግብ ለመድረስ የ16.07% እና 21.71% ያልተሰሩ ቀሪ ተግባራት እንዳሉብን መረጃው በግልጽ ያሳያል፡፡

የአንደኛ ደረጃ(1ኛ-6ኛ ክፍል) ተማሪዎች ጥቅልና ንጥር ተሳትፎን በሚመለከት በ2012 ዓ/ም **ጥቅል** የአንደኛ ደረጃ(1ኛ-6ኛ ክፍል) የትምህርት ተሣትፎው 85.13% እንዲሁም **ንጥር ተሳትፎው 73.01**% የነበረ ሲሆን በ2015 የትምህርት ዘመን ጥቅል ተሳትፎውን ወደ 88.81% እንዲሁም **ንጥር ተሳትፎን** ወደ 82.31% ለማድረስ ታቅዶ በሶስት አመቱ **ጥቅል ተሳትፎው 63.73**%(71.75%) እና **ንጥር ቅበላውም 63.73**%(77.42) እንዲሁም ከአስር

አመቱ **ጥቅል ተሳትፎው 64.92%** እና **ንጥር ቅበላውም 63.73%** የደረሰ ሲሆን ከተደረሰበት አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር ጥቅል ተሳትፎው በ21.4% እና 9.27% በማነስ የተከናወነ ሲሆን በአጠቃላይ ከታለመው ግብ አንጻር አፈጻጸሙ የጥቅል ተሳትፎው በ10.31% እንዲሁም **ንጥር ቅበላው** በ18.58% ያነሰ ስለሆነ ከአስር አመቱ ግብ ለመድረስ ከጥቅል ተሳትፎው አንጻር 19.66% የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች ትምህርት ቤት አለመግባታቸውንና የንጥር ቅበላውም በ36.27% የሚሆኑት ተማሪዎች በእድሜያቸው የገቡ ባለመሆናቸው ንጥር ቅበላው ያልተሳካ መሆኑን በመገንዘብ በትኩረት ልንሰራው እንደሚገባ ያመለክታል፡፡ የ2015 የትምህርት ዘመን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም አፈጻጸማችን ከአገራዊ አማካይ ጥቅል ተሳትፎው 110.22% እና ንጥር ተሳትፎ 92.6% ክንውን ጋር ሲወዳደር ጥቅል ተሳትፎው የ31.72% እንዲሁም የንጥር ተሳትፎው 28.87% በማነስ ልዩነት ያስመዘገበ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ስለሆነም በ2030 እ.ኤ.አ. ሁሉም ወንዶችና ልጃገረዶች ጥራቱንና ፍትሃዊነቱን የጠበቀ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ያጠናቅቃሉ የሚለውን የዘላቂ ልማት ግብ ለማሣካት አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡

በመሆኑም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም ጥቅልም ሆነ ንጥር የትምህርት ተሣትፎ በየዓመቱ እያሽቆለቆለ መሄዱን ያሳያል ፡፡ በዕቅድ ዘመኑ መጀመሪያ አካባቢ ወሣኝ የትምህርት ግብአቶችን በማሟላት ረገድ ከፍተኛ መሻሻሎች ያሉ ቢሆንም በትምህርት አመራሩ ትኩረት ማነስ ምክንያት የተማሪዎች ተሣትፎ ቀንሷል፣ የህፃናት ጉልበት ለተለያዩ ስራዎች መፈለግ፣ የትምህርት ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያሉ ወጭዎችን መሸፈን አለመቻል፣ ወላጆቻው በትምህርት ዘለቄታዊ ጥቅም ላይ ያላቸው ግንዛቤ አናሣ መሆኑ እንዲሁም በክልሉ በተደጋጋሚ እየተከሰተ ያለው ግጭትና ከላይ እስከታች የሚገኙ የትምህርት አመራሮች ትኩረት ማጣት መሠረታዊ ምክንያቶች ተደርገው ሊታዩ ይችላሉ፡:

የመካከለኛ ደረጃ (7ኛ-8ኛ ክፍል) ተማሪዎች ጥቅልና ንጥር ተሳትፎን በሚመለከት፡- በ2012 ዓ/ም **ጥቅል** የመካከለኛ ደረጃ(7ኛ-8ኛ ክፍል) የትምህርት ተሣትፎው 77.15% እንዲሁም **ንጥር ተሳትፎው 47.17%** የነበረ ሲሆን በ2015 የትምህርት ዘመን ጥቅል ተሳትፎውን ወደ 88.26% እንዲሁም **ንጥር ተሳትፎን** ወደ 82.31% ለማድረስ ታቅዶ **ጥቅል ተሳትፎው** 59.39%(77.23%) እና **ንጥር ቅበላው 44.26**%(53.77%) እንዲሁም ከአስር አመቱ ግብ አንጻር ሲታይ **ጥቅል ተሳትፎው** 60.5% እና **ንጥር ቅበላው 44.26**% ነው፡፡ በመሆኑም ክንውኑ ከመነሻው አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር ጥቅል ተሳትፎው የ17.76% እና **ንጥር ቅበላው**

በማነስ የተከናወነ ሲሆን በአጠቃላይ ለሶስት አመት ከታለመው ግብ አንጻር አፈጻጸሙ የጥቅል ተሳትፎው በ28.87% እንዲሁም **ንጥር ቅበላው** በ38.05% ያነሰ ስለሆነ ከአስር አመቱ ግብ ለመድረስ ከጥቅል ተሳትፎው አንጻር በ28.87% የሚሆኑ ተማሪዎች ትምህርት ቤት አለመግባታቸውንና የንጥር ቅበላውም ወደ 38.05% የሚሆኑት ተማሪዎች በእድሜቸው የትምህርት ተጠቃሚ አለመሆናቸውን ያመለክታል፡፡ከዚሁ ጋር በተገናኘ የ2015 የትምህርት ዘመን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም አፈጻጸማችን ከአገራዊ አማካይ **ጥቅል ተሳትፎው** 107.94% እና **ንጥር ቅበላው 98.24**% ክንውን ጋር ሲወዳደር በ48.55% እና በ53.98% በማነስ ልዩነት ያስመዘገበ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ (9ኛ-12ኛ ክፍል) ትምህርት ፕሮግራም ዋና ዓላማ የሀገራችን ኢኮኖሚ የሚፈልገውን በመካከለኛ ደረጃ የሚገኝ የሰለጠነ የሰው ኃይል ማዘጋጀት ነው፡፡ይህ ዘርፍ የመካከለኛ ገቢ ራዕያችንን በአጭር ጊዜ ውስጥ በማሳካት ቴክኖሎጂ የሚጠቀም፣በእውቀት፣ በክህሎት፣በአስተሳሰብ፣ በችሎታና በተወዳዳሪነት ላይ የተመሰረተ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማህበረሰብ ለመገንባት ከፍተኛ ድርሻ ያለው ነው፡፡አንድ አገር የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን በሚፈለገው ደረጃ አለማሳካቱ የመካከለኛ ገቢ መመዘኛን ለማሟላት በሚደረገው ጥረት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡

በመሆኑም በ2012 ዓ/ም የደረጃውን ጥቅል የትምህርት ተሳትፎ ምጣኔ 36.38% እንዲሁም **ንጥር ቅበላው 27.84**% የነበረ ሲሆን በ2015 ዕቅድ ዘመን ጥቅል የትምህርት ተሳትፎ ምጣኔ 47.97% እንዲሁም **ንጥር ቅበላው** 41.99% ለማድረስ ታቅዶ በሶስት አመቱ በርካታ ስራዎች ተከናውነው በ2015 ዓ/ም የሁለተኛ ደረጃ ጥቅል የትምህርት ተሣትፎው 37.71%(78.61%) እና **ንጥር ቅበላው** 29.69%(70.70%) እንዲሁም ከአስርአመቱ ጥቅል የትምህርት ተሣትፎው 50.28% እና **ንጥር ቅበላው** ደግሞ 39.58% መድረሱን ያሳያል፡፡ ይህ አፈጻጸም ከመነሻው የትምህርት ዘመን አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር ጥቅል ተሳትፎው የ1.33% እንዲሁም **ንጥር ቅበላው ደግሞ የ1.85**% በማደግ የተከናወነ ቢሆንም በአጠቃላይ በ2015 ይደረስበታል ተብሎ ከታለመው ግብ አንጻር አፈጻጸሙ የጥቅል ተሳትፎው በ10.26% እንዲሁም **ንጥር ቅበላው** በ12.3% ያነሰ ስለሆነ ከአስር አመቱ ግብ ለመድረስ ከጥቅል ተሳትፎው አንጻር በ10.26% የሚሆኑ ተማሪዎች ትምህርት ቤት አለመግባታቸውንና የንጥር ቅበላውም ወደ 12.3% የሚሆኑት ተማሪዎች በእድሜቸው የትምህርት ተጠቃሚ አለመሆናቸውን ያመለክታል፡፡ከዚሁ ጋር በተገናኘ የ2015 የትምህርት ዘመን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም አፈጻጸማችን

ከአገራዊ አማካይ **ጥቅል ተሳትፎው** 46.1% ክንውን ጋር ሲወዳደር በ8.39% በማነስ ልዩነት ያስመዘገበ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ስለሆነም በ2030 እ.ኤ.አ. ሁሉም እድሚያቸው ለደረጃው ትምህርት የደረሱ ወንዶችና ልጃገረዶች ጥራቱንና ፍትሃዊነቱን የጠበቀ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ያጠናቅቃሉ የሚለውን የዘላቂ ልማት ግብ ለማሣካት ካለማስቻሉም በተጨማሪ በዓለም ባንክ የመካከለኛ ገቢ ኢኮኖሚ እርከን ላይ የሚገኙ አገሮች ኢኮኖሚያቸው መሸከም የሚችል የሰው ሀብት ከማፍራት አንፃር ሊያሳኩት ይገባል ተብሎ ከተቀመጠው 72% የአጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ጥቅል የትምህርት ተሣትፎ አኳያም ሲታይ አሁን ያለንበት ሁኔታ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል 2ኛ ደረጃ ንጥር የትምህርት ተሣትፎ ዝቅተኛ እንዲሆን ከሚያደርጉት ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ተማሪዎች እዚህ የትምህርት እርከን ላይ ከመድረሳቸው በፊት በታችኛው የትምህርት እርከኖች ላይ በሚፈለገው አግባብ በእድሜያቸው የትምህርት ተጠቃሚ እየሆኑ ባለመምጣታቸው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለዚህ የተማሪዎችን በእየርከኑ በእድሜያቸው እንዲማሩ ማድረግ በስነ-ትምህርት መርህና እና በተጨባጭም እውነታውም ለተማሪዎቹ ህይወት በጣሚ አስፈላጊና ጠቃሚ መንገድ መሆኑን በመረዳት በፍጹም ቁርጠኝነት ልንተገብረው ይገባል፡፡


ለአጠቃላይ ትምህርት ጥቅል የትምህርት ተሣትፎ ግብ አለመሳካት በዋናነት የሚጠቀሱ ተግዳሮቶች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በበቂ ሁኔታ አለመስፋፋት፣ የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች ወደ 2ኛ ደረጃ ያላቸው ሽግግር አነስተኛ መሆኑ እና የተማሪዎች የማቋረጥ ምጣኔ ከፍተኛ እየሆነ መምጣቱ፣የወላጆችና ማህበረሰቡ አስተሳሰብ እየወረደ መምጣቱ፣ ክልላችን በትግራይ ወረራ በርካታ ትምህርት ቤቶች እንዲወድሙ መደረጋቸውና ለክልሉ ተማሪዎች የስነ-ልቦና ችግር መፍጠሩ፣የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በትምህርት ስርዓቱ ላይ ፈጥሮት የነበረው ጫና እንዲሁም በየደረጃው ያለው የትምህርት አመራርና የመንግስት ወሳኝ አካላት ለትምህርት ስርዓቱ መጠናከር ያደረጉት አስተዋጽኦ በቂ አለመሆኑ..ወዘተ ዋና ዋና ችግሮች ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ከአንደኛ ደረጃ የሚመጣውን ሰፊ የተማሪ ኃይል ሊሸከም የሚችል የትምህርት ቤት መስፋፋት በእቅድ ላይ ተመሥርቶ መስራት፣ ከዝቅተኛ ክፍል ጀምሮ ስምንተኛ ክፍል እስከሚደርሱ ድረስ ተከታታይነት ባለው ሂደት ተማሪዎችን በማብቃት ወደ ቀጣዩ ክፍል እንዲሸጋገሩ ማድረግ በቀጣይ የሚተኮርበት ጉዳይ መሆን አለበት፡፡ ስለሆነም የመካከለኛ ገቢ ኢኮኖሚ እርከን ላይ የሚገኙ አገሮች ኢኮኖሚያቸውን መሸከም የሚችል የሰው ሀብት ከማፍራት አንጻር የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎአቸው ቢያንስ 72%


ለማድረስ የትምህርት አቅርቦትንና ፍላጎትን ባጣጣመ መልኩ ማስፋፋት በየደረጃው ካሉ አካላት በቀጣይ የሚጠበቅ ከባድ የቤት ስራ እየሆነ መጥቷል፡፡

በአጠቃላይ ከሁለተኛ ደረጃ (9ኛ-12ኛ ክፍል) ጥቅል ተሳትፎ አኳያ አፈጻጸማችን አገራችን ከምትፈልገው በመካከለኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ሃይል አኳያ ሲታይ በጣም ዝቅተኛና አሣሣቢ ጉዳይ ነው፡፡በፎኖተ ካርታው ጥናት መሠረት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ሆኖ እንዲደራጅ በመደረጉ ተማሪዎች የ2ኛ ደረጃ ትምህርትን በበቂ እድሜያቸው ስለሚያጠናቅቁ የቀጣዩን የህይወት መስመራቸውን ለመትለም የሚቸገሩ አለመሆናቸውን እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም ከቴክኒክና ሙያ ትምህርት ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ድረስ እንደአቅማቸው መሳተፍ እንደሚችሉ ቢታሰብም የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቀለል ባለ መልኩ ከታችኛው ክፍል በትውውቅና እጅን ከማፍታታት አኳያ ስለማይጀመር፤ የሥራ ፈጠራ ጽንሰ ሃሳብ ከታችኛው የክፍል ደረጃዎች ተጣጥሞ ስለማይቀርብ፤ ወጣቶች 12ኛ ክፍልን ሲጨርሱ ባሉበት ቦታ በቂና ተገቢ ሥልጠና በመስጠት ወደ ሥራ ስለማይሰማሩ ችግሩ የገዘፈ እንዲሆን ስለሚያደርገው እነዚህን ክፍተቶች በሚሞላ መልኩ መንቀሳቀስና የተማሪዎቹን የቀጣይ ህይወት ብሩህ እንዲሆን ማድረግ ላይ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

**ግራፍ-18- በየደረጃው የተማሪዎች ጥቅል ተሳትፎ**



**ግራፍ.19 በየደረጃው የተማሪዎች ንጥር ተሳትፎ**



የልዩ ፍላጐት ኘሮግራም እንዲተገበር የትምህርትና ስልጠናው ፖሊሲ በፈጠረው ምቹ ሁኔታ መሰረት ልዩ ፍላጐት ያላቸውን ጨምሮ ሁሉም ህፃናትና ወጣቶች እንደ ችሎታቸውና እንደ ፍላጐታቸው መማር ያለባቸው መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ፕሮግራሙ በክልላችን የሚሰጠው በሁለት መልኩ ነው፡፡የመጀመሪያው ከ1ኛ-4ኛ ክፍል ላሉ ህፃናት የተለየ ልዩ ፍላጎት (special need) ክፍል በማደራጀት የሚሰጥ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከ5ኛ -12ኛ ክፍል ላሉ ህፃናት በአካቶ ትምህርት ፕርግራም (inclusive education) አማካይነት የሚሰጥ ይሆናል፡፡

የቅድመ መደበኛ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ፕሮግራም ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ለቀጣይ እንቅስቃሴያቸውና መሰረታዊ ክሂሎች ማለትም ለዓይነ-ስውራን የብሬል አጠቃቀምንና ከቦታ ቦታ እንቅስቃሴን መስማት ለተሳናቸው የምልክት ቋንቋን እንዲሁም የአእምሮ እድገት ውስንነት ላለባቸው የህይወት ክሂሎችን ለመማር ይረዳቸዋል፡፡ ሆኖም ትምህርትና ስልጠናው ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በቅድመ መደበኛ ትምህርት ደረጃ ያልተዘጋጀ ቢሆንም በመደበኛው መርሃ-ግብር ጥቂት ህጻናትን ለመድረስ ተሞክሯል፡፡በዚህ መሠረት በ2012 የትምህርት ዘመን ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በቅድመ መደበኛ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎው 0.03% የተደረሰበት መሆኑን ያሳያል፡፡ በቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም የትምህርት መርሀግብር በሶስት አመት ውስጥ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚገባቸውን አካል ጉዳተኛ ህጻናትን በማሳተፍ በ2015 የትምህርት ዘመን ጥቅል ተሳትፏቸውን ወደ 0.1% ለማሳደግ ታቅዶ ተግባሩን ለመፈጸም እንቅስቃሴ ሲደረግ ቆይቶ ጥቅል ተሳትፎውን ወደ 0.53% በማድረስ ከመነሻ አመቱ ከተደረሰበት ክንውን አንጻር በ0.5% እድገት ያለው እና ይደረስበታል ተብሎ ከተያዘው ግብ አኳያ ሲወሰድ ከ100% በላይ እንዲሁም በአስር አመቱ ይደረስበታል ተብሎ ከታቀደውም አኳያም ከ100% በላይ የተከናወነ በመሆኑ አበረታች አፈጻጸም ስላለው ይህን ማስቀጠል ላይ መስራት ይጠበቅብናል፡፡

ከመጀመሪያ ደረጃ ልዩ ፍላጎት ትምህርት(1ኛ-6ኛ) አንፃር በ2012 የትምህርት ዓመት ጥቅል የትምህርት ተሣትው 2.4% የነበር ሲሆን በ2015 የትምህርት ዘመን ጥቅል ተሳትፎውን 5.96% ለማድረስ ታስቦ የጥቅል ተሳትፎው ክንውን 3.86%(64.76%) እንዲሁም ከአመቱ 43.5% መፈጸሙን ያመለክታል፡፡ ይህ አፈጻጸም ከ2012 የትምህርት ዘመን ከተደረሰበት ግብ አንጻር ሲታይ የ1.47% እድገት ያሳየ እና በ2015 የትምህርት ዘመን እንዲሳካ ታስቦ ከተቀመጠው ግብ አንጻር የተከናወነው በ3.79% እንዲሁም ከአመቱ ግብ በ56.5 በማነስ

መሆኑን ማየት ተችሏል፡፡ በመሆኑም የአስር አመቱን ግብ ከማሳካት አኳያ የመጀመሪያ ደረጃ(1ኛ-6ኛ) ልዩ ፍላጎት ትምህርትን ግብ በማሳካት ረገድ ወደፊት መሰራት ያለበት የ56.5% ያህል ቀሪ ተግባራት መኖራቸውን ይጠቁማል፡፡ በተጨማሪም የክልላችን የዚህ ትምህርት ፕሮግራም አፈጻጸምን ከአገራዊው 10.09% ክንውን ጋር ስናየው በ6.28% ወደኋላ የቀረ አፈጻጸም መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ከመካከለኛ ደረጃ(7ኛ-8ኛ) አካቶ ትምህርት አንፃር በ2012 በጀት ዓመት ጥቅል የትምህርት ተሣትፎው 1.19% የደረሰ ሲሆን ይህን የተሳትፎ ምጣኔ በ2015 የትምህርት ዘመን 3.44% ለማድረስ ታስቦ የጥቅል ተሳትፎው ክንውን 2.97%(86.33%)እንዲሁም ከአመቱ ግብ አንጻር 51.11% መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይህ አፈጻጸም ከ2012 የትምህርት ዘመን ከተደረሰበት ግብ አንጻር ሲታይ የ1.78% እድገት ያሳየ ቢሆንም በ2015 የትምህርት ዘመን እንዲሳካ ታስቦ ከተቀመጠው ግብ አንጻር የተከናወነው በ1.98% በማነስ መሆኑን ማየት ተችሏል፡፡ በመሆኑም የአስር አመቱን ግብ ከማሳካት አኳያ መካከለኛ ደረጃ(7ኛ-8ኛ) አካቶ ትምህርትን በማሳካት ረገድ ወደፊት መሰራት ያለበት የ48.89% ያህል ቀሪ ተግባራት መኖራቸውን ይጠቁማል፡፡

የሁለተኛ ደረጃ(9ኛ-12ኛ) አካቶ ትምህርት ፕሮግራም አፈጻጸምን በሚመለከት በ2012 የትምህርት ዘመን ጥቅል የትምህርት ተሣትፎው 0.34% የደረሰ ሲሆን ይህን የትምህርት ተሳትፎ በ2015 የትምህርት ዘመን ወደ 0.67% ከፍ አድርጎ ለማከናውን ታስቦ የተሳትፎው ምጣኔ ክንውን 1.10% መሆኑን ያሳያል፡፡በመሆኑም እንደመነሻ ከተወሰደው የትምህርት ዘመን አፈጻጸም አንጻር የ0.76% እድገት ያለው እና ከሶስት አመትም ይሁን ከአስር አመቱ አፈጻጸሙ ከ100% በላይ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በአጠቃላይ የልዩ ፍላጎትና አካቶ የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ፕሮግራሙን ለማጠናከር በሌሎቹ ትምህርት ፕሮግራሞች ላይ የታዩት ተግዳሮቶች እንዳሉ ሆኖ በተለየ መልኩ ደግሞ የድጋፍ መስጫ ማዕከላትን የማደራጀትና የማጠናከር፣ አዳዲስ ልዩ ፍላጎት ዩኒት የመክፈት፣ ለወርሃዊ ቀለብ እና ለአልባሣት የሚሆን የበጀት ድጋፍ የማድረግ፣የብሬል የመማሪያና ማስተማሪያ መፃህፍት አቅርቦት፣ የግንዛቤ ማሣደጊያ ተግባራትን የመፈፀምና መምህራን የማሰልጠንና የማሠማራት ተግባራት ወዘተ የመሳሰሉትን ተግዳሮቶች በመፍታት አፈጻጸሙ ላይ መሻሻሎች እንዲመጡ ትኩረት ሰጥቶ መስራትን ይጠይቃል፡፡

ከስራና ገበያ ፍላጐት ጋር የተሳሰረ እና የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ተሳትፎን በመተግበር ጐልማሶች በፍላጐታቸውና ችግራቸው ላይ የተመሰረተ፣ የዕለት ተግባራቸው ጋር የተገናዘበ፣ ወዲያውኑ ሊተገብሩት የሚችሉ፣ ለህይወታቸው ቅርብ የሆነ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማታቸውን የሚያሻሽሉበት የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጐልማሶች ትምህርት እንዲያገኙ ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው።ይህንን ማድረግ ሲቻል ደግሞ ምርታማነቱ ያደገ፣ ጤንነቱ የተጠበቀ፣ ገቢው የተሻሻለ፣ በምክክር ዘይቤው የተለወጠ ህብረተሰብ መፍጠርና መካከለኛ ገቢ ያላቸውም ሆነ ከዚያ በላይ ሀብት መገንባት ይቻላል።

ጐልማሳውን የመፃፍን፣ ማንበብና የማስላት ክህሎትን ከማሰልጠን ባሻገር የሕይወት ክህሎትን ማሳደግ ያስፈልጋል። ለዚህም በአለፈው አመት የትምህርት መስጫ ጣቢያዎችን፣ ማዕከላትንና አመቻቾችን ማስፋፋትና ማሻሻል እና ከስራና ገበያ ፍላጐት ጋር የተሳሰረ ትምህርት ፕሮግራም ተሳትፎ ማሳደግ እንደ ዋና ዋና ተግባራት ታቅደው የተተገበሩ ሲሆን አፈጻጸማቸው ቀጥሎ ቀርቧል። በ2012 ዓ/ም የክልላችን የጎልማሶች የመሠረታዊ ትምህርት ተሳታፊዎች 65,639 የነበሩ ሲሆን 95% ጎልማሶችን የመሠረታዊ ትምህርት እንዲያጠናቅቁ ለማድረግ የተያዘውን ግብ ለማሳካት የታቀደ ቢሆንም በርካታ ጎልማሶች ትምህርት ያላገኙ መሆኑን በመነሻ ዘመኑ የተደረሰበት አፈጻጸም በግልጽ ያመለክታል። ይህን ግብ በአስር አመቱ ለማሳካት ለሶስት አመታት ሲሰራ ቆይቶ እስከ 2015 የትምህርት ዘመን በፕሮግራሙ በመሳተፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በሶስት አመቱ በግብ የተያዘው ብዛት 1,262,105 ጎልማሶች ሲሆኑ በእድሉ ተሳታፊ የሆኑት ጎልማሶች ቁጥር 240,774 (የ2014ን ሳይጨምር) ወይም ከእቅዱ 19.07% እንዲሁም ከአስር አመቱ 2.95% ብቻ የሚሆኑት ተሳታፊ መሆናቸውን ያሳያል። ከዚህ አንጻር በቀጣይ 97.05% ያህል ጎልማሶች የትምህርት እድል ያላገኙ እና ፕሮግራሙም በእጅጉ ትኩረት የተነፈገው መሆኑን በመገንዘብ ያላሰለሰ ርብርብ በማድረግ የጎልማሶችን ትምህርትና ክህሎት የማግኘት መብት ብቻ ሳይሆን የክልሉንም የመልማት ፍላጎት ሊያሟሉ የሚችሉ የተማሩና የተካኑ ጎልማሶችን የማፍራት ተልእኮ በአግባቡ መወጣት ይገባናል። በተጨማሪም በዚህ ፕሮግራም ተሳታፊ ከነበሩት ውስጥ ማንበብ፣ መጻፍና ማስላት እንዲችሉ የተደረጉ ጎልማሶች ብዛት 130,825 ሲሆኑ አፈጻጸሙ ከተሳታፊዎች አንጻር ሲወሰድ 54.34% የደረሰ መሆኑን ያመለክታል። በተሳታፊነት ከዘለቁትም ውስጥ 45.66% ያህሉ ጎልማሶች ማንበብ፣ መጻፍና ማስላት አለመቻላቸውን ከመረጃው መገንዘብ ይቻላል። ስለሆነም በሶስት ዓመታቱ

የአስር አመቱ እቅድም ይሁን ከዚያ በፊት ግቡን ከማሳካት አንጻር የተደረገው ጥረት አበረታች ባለመሆኑ  በርካታ የህብረተሰቡ ክፍል ከስራ ጋር የተዛመደ የትምህርትና ክህሎት ተሳታፊነቱ ዝቅተኛ መሆኑን ተገንዝበን የፕሮግራሙን አስፈላጊነትና ለክልሉ የሚኖረውን ፋይዳ በማየት እስካሁን የሄድንበትን የተሳሳተ መንገድ አስተካክለንና ለፕሮግራሙ ስኬታማነት የሚመጥን አሰራርና አደረጃጀት በመፍጠር በቁርጠኝነት ልንተገብረው የግድ መሆኑን ልናየው ይገባል፡፡

ከስራ ጋር የተሳሰረ እና የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት በማከናወን ረገድ ካጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች መካከል የሚሰጠው ሥልጠና ከጉልማሳው ሕይወት ማለትም ግብርና፣ ጤና፣ የሕይወት ክህሎት፣ ወዘተ. ጋር የተቆራኘ አለመሆን፣ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሴክተር መ/ቤቶች መካከል ያለው ቅንጅታዊ አሠራር ጠንካራ አለመሆን፣ተአማኒና ወቅታዊ መረጃ አለመኖር፣ የግብአቶች አለመሟላት፣ኘሮግራሙን ለመምራት በየደረጃው የተቋቋሙት የቦርድና የቴክኒክ ኮሚቴዎች ተግባራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ አለመግባት፤ መርሀግብሩን ለትምህርት ሴክተር ብቻ መተው፣የኮቪድ ወረርሽኝ መከሰት፣ የሰሜን ጦርነት መካሄዱና በክልላችን ህዝብና በሀብት ላይ ጉዳት መድረሱ.. ወዘተ ተጠቃሾች ናቸው፡፡

በሌላ በኩል ባለፉት ዘመናት የትምህርት እድል አግኝተው ደረጃውን የሚመጥን ምዘና ያልወሰዱና የመርሳት ችግር ላይ የሚገኙ ጎልማሶች ስርዓቱን ጠብቀው በስታንዳርዱ መሰረት ምዘና እንዲወስዱ እድል የሚሰጥ የምዘና አይነት የትምህርት ብርሀን ምዘና በሚል ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡ በመሆኑም የትምህርት ብርሀን ምዘና የወሰዱ ጎልማሶች እና ታዳጊዎች ብዛት በቁጥር 381,661 ሲሆኑ የትምህርት ብርሃን ምዘና ከወሰዱ ጎልማሶችና ታዳጊዎች መካከል ስታንዳርዱን ያሟሉት ብዛት 311,549 ወይም 81.6%(32%ሴቶች) መሆናቸውን ያመለክታል፡፡አፈጻጸሙ ከዚህ ግብ አንጻር አበረታች ቢሆንም ከታሰበው ግብ አንጻር በ18.4% ክፍተት ያለበት በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ያመለክታል፡፡

የትምህርት መስጫ ጣቢያዎችን፣ ማዕከላትንና አመቻቾችን ማስፋፋትና ማሻሻልን በተመለከተ የተቋቋሙ መማማሪያ ጣቢያዎችን ስንመለከት በ2012 ትምህርት ዘመን መጨረሻ ተቋቁመው ከነበሩት 14,404 የትምህርት መስጫ ጣቢያዎች በሶስት አመቱ መጨረሻ(2015) 74,230 ለማድረስ ታቅዶ የነበረ ሲሆን በሶስት አመታት 16,557 ጣቢያዎች የተቋቋሙ ሲሆን የእቅድ አፈጻጸሙ ከሶስት ወራት እቅድ  22.3% እንዲሁም ከአመቱ(13.56%) ብቻ ሆኗል፡፡የዚህን ግብ አፈጻጸም ተደርሶበት ከነበረው ግብ አንጻር ሲመዘን በ2,153 ጣቢያዎች ወይም በ3% ያህል

እድገት ያለው ቢሆንም ለሶስት አመት ከተያዘው ግብ አንጻር ግን በ77.7% ያህል ግቡ አለመሳካቱን ያመለክታል፡፡ በተጨማሪም የክልላችን የጎልማሶች መማሪያ ጣቢያዎች ማቋቋም ግብ ከአገራዊ ተመሳሳይ ወቅት አፈጻጸም ጋር ሲመዛዘን በእጅጉ የወረደ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም የግቡን የአስር አመት አፈጻጸም ስኬታማ ለማድረግ በእነዚህ ሶስት አመታት ውስጥ ታቅደው ያልገነባናቸውን 57,673(77.7%) የመማሪያ ጣቢያዎች በመጨመር በጠቅላላው 105,541 ለመገንባትና ተጨማሪ ጎልማሶችን የትምህርት እድል ተጠቃሚ የማድረጉ ጉዳይ ከወዲሁ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

ከዚሁ ጋር በተገናኘ ቅጥር የተፈጸመላቸው አመቻቾችን አፈጻጸም በሚመለከት በ2012 የትምህርት ዘመን 7,830 ያህል አመቻቾች በቅጥር ወደ ስራ ተሰማርተው የነበረ ሲሆን በሶስት አመታት ውስጥ 42,224 አመቻቾችን ቅጥር ለመፈጸም ታስቦ 10,443(56.75 ሴቶች) አመቻቾችን ቅጥር በማከናወን የሶስት አመት እቅዱን 24.73% እና ከአመቱ እቅድ 8.55% በመፈጸም የተከናወነ ሲሆን ክንውኑ ከመነሻ ግቡ አኳያ የተወሰነ እድገት ያሳየ ቢሆንም እንዲሳካ ከታለመው የሶስት አመታት ግብ አንጻር ግን በ75.2% ወደኋላ የቀረ መሆኑን መረጃዎቹ በግልጽ ያሳያሉ፡፡ ስለሆነም የዚህ ትምህርት ፕሮግራም የአመቻቾች አቅርቦት እቅድ ከፍተኛ ተግዳሮት የገጠመውና በቀጣይ አመታት የልማት እቅዶቻችን በማካካስ ግቡ የአስር አመቱን ኢላማ እንዲያሳካ በውል ሊሰራ ይገባል፡፡

የትምህርት ፍትሃዊነት አፈፃፀምን ስንመለከት የትምህርት ፍትሀዊነትን ለመለካት የምንጠቀምባቸው አመልካቾች ጾታዊ ክፍተት፣ የከተማና ገጠር ክፍተት፣ በብሔረሰብ ቋንቋዎችና በልዩ ፍላጎት ትምህርት ያለው ልዩነት ነው፡፡

የትምህርት ተሣትፎ ፆታዊ ክፍተት አፈፃፀም በሚመለከት የአንድ የትምህርት ስርጭት ፍትሃዊነት ከሚገለጽባቸው መለኪያዎች አንዱ በወንድና በሴት መካከል ያለውን የትምህርት ስርጭት ማመጣጠን ነው፡፡ የሀገራችንን ልማት ለማፋጠን ከግማሽ በላይ የሚሆነውን የልማት አቅም ወደ ጎን በመተው እድገት ማምጣት አይቻልም፡፡ ስለዚህ ሴቶች በትምህርትን አጎልብቶ በግብርናውም ሆነ በኢንዱስትሪው ልማት እንዲሣተፉ ማድረግ ሃብትን በአግባቡ ለመጠቀም ያስችላል፡፡ሴቶች ከተማሩ የዜግነት መብታቸውን በአግባቡ ከመተግበራቸውም በላይ በህብረተሰቡ ውስጥ በራሣቸውም ሆነ በሌሎች ላይ የሚንፀባረቀውን ኢ-ዲሞክራሲያዊ አመለካከት ለመለወጥ አመቺ ሁኔታ ይፈጥራሉ፡፡

ከዚህ በመነሣት በመርሃ ግብሩ መጨረሻ ላይ በሁሉም ደረጃዎች ላይ በጥቅል የትምህርት ተሣትፎ ፆታዊ ክፍተት ወደ 1 ለማድረስ ታቅዶ የተለያዩ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ የሴቶችን ትምህርት ጠቀሜታ ለማጉልበት ይቻል ዘንድ ለመምህራን፣ለር/መምህራን፣ለወላጆች፣ ለትምህርት አመራሮች፣ ለአስተዳደር አካላት፣ ለታዋቂ የአገር ሽማግሌዎችና ለሀይማኖት አባቶች የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ አውደ ጥናትና ስልጠና ተዘጋጅቶ ተሰጥቷል፡ ከዚህም ሌላ የሴቶችን ትምህርት ጠቀሜታ የሚያስገነዝቡ በራሪ ፅሁፎች፣ ብሮሽሮች፣ ፖስተሮች ወዘተ ተዘጋጅተው ተሰራጭተዋል፡፡ለሴት ተማሪዎች ሞዴል ሆነው እንዲያገለግሉ ሴት መምህራን መመደብ ሲሆን በዚህም በክልላችን በመርሃ ግብሩ በቅደመ ስራ ላይ ስልጠና ከሚገቡት መካከል 50% ለብቻ ለሴቶች የትምህርት እድል እርስ በርስ ተወዳድረው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡በተጨማሪም በቀሪው 50% ደግሞ ከወንዶች ጋር እኩል ይወዳደራሉ፡፡


ከላይ የተዘረዘሩት ተግባራት ድምር ውጤትም ሲታይ የተማሪዎች የጥቅል ትምህርት ተሣትፎ ፆታዊ ክፍተት እና የፆታዊ ምጥጥን አፈፃፀምን ስናይ የፆታዊ ምጥጥን በማሻሻል ረገድ የፆታዊ ልዩነት ጠቋሚን በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 1.00 ላይ ለማቆየት ታቅዶ በ2015 የትምህርት ዘመን 0.99 ሲመዘገብ፣ በአንደኛ ደረጃ(1ኛ-6ኛ) በ2012 ከነበረበት 0.94 በ2015 የትምህርት ዘመን ወደ 0.98 ለማድረስ ታቅዶ 0.99 ማድረስ ተችሏል፡፡ክልላችን በዚህ የትምህርት እርከን የሚገኙ ህጻናት የጾታ ምጥጥንን ከአገራዊ የጾታ ምጥጥን ክንውን 0.91 ጋር ስናየው በ0.08 የጾታ ምጥጥንን እድገት ያስመዘገበ በመሆኑ ሊበረታታ የሚገባው ተግባር መሆኑን ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል የመካከለኛ ደረጃ(7ኛ-8ኛ) ትምህርት የጾታዊ ምጥጥን በ2012 ዓ.ም 1.1 የነበር ሲሆን በ2015 የትምህርት ዘመን 1.23 ምጥጥን ደረጃ ላይ መድረሱን ያሳያል፡፡ ከአገራዊ አፈጻጸሙ 0.96 እንዲሁም የሁለተኛ ደረጃ የጾታዊ ምጥጥን በ2012 ከነበረበት 1.08 በ2015 ትምህርት ዘመን ምጥጥኑ ወደ 1.29 የደረሰውን አፈጻጸም በተመሳሳይ ሁኔታ ከአገራዊ አፈጻጸሙ 0.96 ጋር ስናወዳድራቸው በ0.27 እና 0.33 ያህል ከሚፈለገው የጾታዊ ምጥጥን ግብ አንጻር የክልላችን ክፍተቱ ሰፊ በመሆኑ በርካታ ስራዎችን ልንሰራ እንደሚገባን ያመለክታል፡፡በመሆኑም ከዚህ አፈፃፀም የምገነዘበው በቅድመ አንደኛ እና በአንደኛ ደረጃ የወንዶች ተሳትፎ ብልጫ ያለው መሆኑን ሲሆን በመካከለኛ አንደኛ ደረጃ እና በሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የሴቶች ተሳትፎ ከወንዶች የሚበልጥ መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች የፆታ ምጥጥንን ወደ 1.0 ለማምጣት ከፍተኛ ጥረት ማድረግ የሚጠበቅ ይሆናል፡፡

**ሠንጠረዥ 14. በየደረጃው የተማሪዎች ጾታዊ ምጥጥን**


| ዓመት | ቅድመ መደበኛ | 1ኛ-6ኛ | 7ኛ-8ኛ | 9ኛ-12ኛ |
|---|---|---|---|---|
| 2012 | 0.00 | 0.94 | 1.1 | 1.08 |
| 2013 | 0.99 | 0.97 | 1.13 | 1.16 |
| 2014 | 0.98 | 0.102 | 0.89 | 0.81 |
| 2015 | 0.99 | 0.99 | 1.23 | 1.29 |

በተመሳሳይ የሴት መምህራን፣ርዕሰ መምራንና ሴት ባለሞያዎች ጾታዊ ድርሻን ስንወስድ ደግሞ የሴት መምህራን ድርሻ በቅድመ 1ኛ ደረጃ ትምህርት በ2012 ከነበረበት 94.3% በ2015 የትምህርት ዘመን 94.51% ለማድረስ ታቅዶ የሴት መምህራን ድርሻ በሶስት አመት በቅድመ 1ኛ ደረጃ ትምህርት 91.8%(97.13%) ድርሻ እንዲሁም ከአስር አመቱ 96% አፈጻጸም መድረሱን ያሳያል፡፡

የሴት መምህራንን ድርሻ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ2012 ዓ.ም ከነበረው 45.94% በ2015 የትምህርት ዘመን 47.16% ድርሻ እንዲኖራቸው ታስቦ 47.2%(100%) እንዲሁም ከአስር አመቱ እቅድ 94.4% የደረሰ ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 25.89% በ2015 የትምህርት ዘመን 27.12% ለማድረስ ግብ ተወስዶ በሶስት አመቱ 26.4%(97.3%) የደረሰ ሲሆን ከአስር አመቱ ደግሞ 88% የሴት መምህራን ድርሻ በ2ኛ ደረጃ ትምህርት የደረሰ መሆኑን ያሳያል፡፡



በሌላ በኩል የመጀመሪያ ደረጃ የሴት ርእሰ-መምህራን ድርሻ በ2012 የትምህርት ዘመን ከነበረበት 6.52% በ2015 የትምህርት ዘመን ወደ 12.08% ድርሻ ለማድረስ ታስቦ ድርሻው 7%(57.94%) እንዲሁም ከአስር አመቱ 28% ሆኗል፡፡ በተመሳሳይ የሁለተኛ ደረጃ የሴት ርዕሰ-መምህራን ድርሻ በ2012 የትምህርት ዘመን ከነበረበት 1.38 በ2015 ወደ 5.47% ከፍ ለማድረግ ታቅዶ ድርሻው 2.5%(45.7%) እና ከአመቱ 16.66% ላይ ያለ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በተጨማሪም የመጀመሪያ ደረጃ የሴት ሱፐርቫይዘሮች ድርሻ ከነበረበት 2.5% በሶስት አመቱ(2015) 15.26% ለማድረስ ታቅዶ 3.6%(23.59%) የተከናወነ ሲሆን ከአመቱ ደግሞ 8% ብቻ መከናወኑን ያሳያል፡፡




**ግራፍ 20-የሴት ርዕሰ መምህራን ድርሻ**

የክልላችን የሴት መምህራን፣ርዕሰ መምራንናሱፐርቫይዘሮች ድርሻን ለማሳደግ የታለሙት ግቦች የሴት መምህራን ድርሻ በቅድመ 1ኛ ደረጃ፣በ1ኛ ደረጃና በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ድርሻቸው እያደገ የመጣ በመሆኑ ሊበረታታ የሚችል አፈጻጸም ነው፡፡ ሆኖም ግን ሴት የትምህርት አመራሮችን ወደ ቦታው ለማምጣትና ድርሻቸውን ከፍ በማድረግ ሀላፊነት እንዲወጡ በማድረግ በኩል የታለሙት ግቦች መሻሻል ቢታይባቸውም በሚፈለገው መልኩ እየተሰራ አለመሆኑን ያሳያል፡፡ በመሆኑም በሴት መምህራንና ር/መምህራን በየደረጃው የመጣው ለውጥ የሚናቅ ባይሆንም የሴቶች ሴቶች የሚገባቸውን ያህል ድርሻ እየወሰዱ ባለመሆናቸው ከዚህ አፈጻጸም ትንተና በመነሳት በቀጣይ የእቅድ ዘመናት ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ተግባራት ናቸው፡፡

**በከተማ እና በገጠር የሚታየውን የትምህርት ፍትሃዊ ስርጭት** አለመመጣጠን ለማጥበብ ትኩረት የተደረገው በገጠር አካባቢዎች ትምህርት ማስፋፋት የነበረ ሲሆን በመጀመሪያ ደረጃ

ትምህርት ፕሮግራም በ2012 ዓ/ም በጥቅል የትምህርት ተሣትፎ የከተማ ገጠር ክፍተት 0.79 የነበረውን በቀጣዮቹ የእቅድ አመታት ወደ 1 ለማድረስ የታቀደ ቢሆንም ክፍተቱ ከመጥበብ ይልቅ እየሰፋ በመሄድ ላይ በመሆኑ በሚቀጥሉት ዓመታት ገጠርን ማዕከል ያደረጉ ስራዎችን አልሞ መስራት የሚጠይቀን ይሆናል፡፡

የትምህርት ውስጣዊ ብቃት አፈፃፀምን በተመለከተ በክልሉ የትምህርት ስርዓት አንዱ አንገብጋቢ ችግር ከፍተኛ የማቋረጥ መጠንና ክፍል መድገም ናቸው፡ለትምህርት ውስጣዊ ብቃት መጓደል ደግሞ የመንግስትና የህዝብ ሀብት በአግባቡ ስራ ላይ የመዋል ብቃትን ይቀንሳሉ፡፡ከዚህ በመነሳት በመርሃ ግብሩ የታቀደው ትምህርትን ተከታትሎ የማጠናቀቅ ምጣኔን ለማሳደግ የመጠነ ማቋረጥና መጠነ መድገም መቀነስ ነበር፡፡

የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ማቋረጥ እና ክፍል መድገም አፈፃፀም አንጻር በመጀመሪያ እና መካከለኛ ደረጃ(1ኛ-6ኛ) ትምህርት ፕሮግራም የማቋረጥ ምጣኔ በ2012 የትምህርት ዘመን 2.44% የነበረውን በ2015 የትምህርት ዘመን የተማሪዎች ማቋረጥ ምጣኔን ወደ 2% ለማውረድ ታስቦ ለዘመኑ ከተመዘገቡት ተማሪዎች መካከል 143,207 (57475ሴቶች) (2.49%) የሚደርሱ ህጻናት ትምህርታቸውን ያቋረጡ መሆናቸውን ያመለክታል፡፡ ከተቀመጠው ግብ አንጻር በ0.49% ያህል ባለመሳካት የተከናወነ መሆኑን ሲያመለክት እንዲሁም በእቅድ ዘመኑ የተማሪዎች ማቋረጥ ምጣኔ ለመነሻነት ከተወሰደውና ከተደረሰበት ግብ አንጻር ሲመዘን የተማሪዎች ማቋረጥ ከመቀነስ ይልቅ በ0.15% እየጨመረ መምጣቱን ያሳያል፡፡ በየዘመኑ የተመዘገበው የማቋረጥ ምጣኔም በተከታታይ የመጨመር አዝማሚያ ያስመዘገበ መሆኑን መመልከት ይቻላል፡፡

በመካከለኛ(7ኛ-8ኛ) ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም የማቋረጥ ምጣኔ በ2012 የትምህርት ዘመን የተማሪዎች ማቋረጥ ምጣኔ 2.44% የነበረውን በ2015 የትምህርት ዘመን የተማሪዎች ማቋረጥ ምጣኔን ወደ 2% ለማውረድ ታስቦ ለዘመኑ ከተመዘገቡት ተማሪዎች መካከል 107,274(40899 ሴቶች)(3.73%) የሚደርሱ ህጻናት ትምህርታቸውን ያቋረጡ መሆናቸውን የሚመለክት ሲሆን ከተቀመጠው ግብ አንጻር በ1.73% ያህል ባለመሳካት የተከናወነ መሆኑን ያመለክታል፡፡ እንዲሁም በእቅድ ዘመኑ የተማሪዎች ማቋረጥ ምጣኔ ለመነሻነት ከተወሰደውና ከተደረሰበት ግብ አንጻር ሲመዘን የተማሪዎች ማቋረጥ ከመቀነስ ይልቅ በ1.29% ያህል

የጨመረ መሆኑን ያሳያል። በየዘመኑ የተመዘገበው የማቋረጥ ምጣኔ በተከታታይ የመጨመር አዝማሚያ አለው።


የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች የማቋረጥና መድገም አፈፃፀም በሚመለከት በአጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ኘሮግራም የተማሪዎች ማቋረጥን ከ2% በታች የማወረድ ግብ ተወስዶ በሶስቱ ተከታታይ አመታት የታየውን የማቋረጥ ምጣኔ ብንመለከት በ2013 የትምህርት ዘመን ከተመዘገቡት 2ኛ ደረጃ ተማሪዎች መካከል 30,244(3.19%)፣ በ2014 የትምህርት ዘመን ከተመዘገቡት ተማሪዎች መካከል 65621(6.7%) እንዲሁም በ2015 የትምህርት ዘመን ከተመዘገቡት ተማሪዎች መካከል 77,103(8.01%) ከትምህርት ገበታ ውጭ የነበሩ መሆናቸውን ያሳያል።የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ኘሮግራም የተማሪዎች ማቋረጥ በተከታታይ እየጨመረ በመምጣቱ በ2015 የትምህርት ዘመን የተማሪዎች የማቋረጥ ምጣኔን ከ4% በታች ለማውረድ የተቀመጠው ግብን ከማሳካት ይልቅ ያለመሳካቱን መጠን በ6.01% እንዲያሽቅብ ያደረገው በመሆኑ በአጠቃላይ በሶስቱ የእቅድ አመታት 172,948 ተማሪዎች ያቋረጡ ሲሆን በአማካይ ወደ 6% ሊሆኑ የሚችሉት የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች የመማርና ራሳቸውን የመለወጥ መብታቸውን የተነፈጉ መሆናቸውን ያሳያል።የዚህን ፕሮግራም አፈጻጸም ስንመለከት የተማሪዎች ማቋረጥ አዝማሚያው እጅግ እየጨመረ የመጣ ስለሆነ ከአለም አቀፉ ትምህርትን ለሁሉም ከማዳረስ አንጻር የተቀመጠውን የዘላቂ ልማት ግብ ከመሳካት አንጻር ከፍተኛ ተግዳሮት ሊገጥመው እንደሚችል ታውቆ እነዚህን ክፍተቶች ሊሞላ የሚችል የትምህርት እቅድ አዘጋጅቶ በበቂ ሁኔታ እንቅስቃሴ ውስጥ መግባት ይገባል።

*ሠንጠረዥ15- በየደረጃው የተማሪዎች ማቋረጥ ምጣኔ*

| የትም. ዘመን | 1ኛ-6ኛ | 7ኛ-8ኛ | 9ኛ -12ኛ |
|---|---|---|---|
| 2013 | 4.7 | 3.14 | 3.19 |
| 2014 | 4.7 | 1.40 | 6.7 |
| 2015 | 3.73 | 1.25 | 8.01 |

በሌላ የትምህርት ብቃትና ጥራት መለኪያ አመልካች የሆኑት የተማሪዎች በየእርከኑ የመድገም፣ የመዝለቅና የማጠናቅ ምጣኔ ናቸው። በዚህ መሰረት የ1ኛ ክፍል የመድገም መጠንን በ2012 የትምህርት ዘመን ከነበረበት 7% በሶስቱ አመታት እቅዶችን በመፈጸም በ2015 የትምህርት ዘመን ወደ 5% የማውረድ ግብ ተጥሎ፡- በአማካይ ወደ 4.14% ማውረድ

የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ ከመነሻ ዘመኑ በ2.85% እና ከተጣለው ግብ አንጻር በ0.86% በማውረድ የእቅዱን 82.8% በማከናወን የሚያበረታታ ውጤት የመጣ ቢሆንም ከታለመው ግብ አንጻር በ0.86% በማነስ የተፈጸመ ስለሆነ ቀጣይ እቅድ ላይ አካትቶ የአስር አመት ግቡን ማሳካት ይገባል፡፡





በሌላ በኩል የ6ኛ ክፍልን የማጠናቀቅ ምጣኔን ስናይ በዚህ እቅድ የመነሻ ትምህርት ዘመን(2012) የተደረሰበት ምጣኔ 71.7% የነበር ሲሆን በ2015 የትምህርት ዘመን የተማሪዎች 6ኛ ክፍልን የማጠናቀቅ ምጣኔን ወደ 80% ለማሳደግ ታቅዶ የግቡ አፈጻጸም በአማካይ 64.9% መሆኑን ያሳያል፡፡ የዚህ ግብ አፈጻጸም ከእቅዱ ዘመን በፊት ከተደረሰበትም ይሁን ከዘመኑ የትምህርት ግብ ጋር ሲታይ በ6.8% እና 15.1% በቅደም ተከተል በማነስ የተከናወነ መሆኑን ስለሚያመላክት የአስር አመቱን ግብ ከማሳካት አንጻር ባለፉት ሶስት አመታት እንዲሳካ ከታቀደው ውስጥ 15.1% ያህሉ የተሳካ አለመሆኑ ታውቆ ከቀጣይ አመታት እቅዶች ጋር ተካቶ እንዲፈጸም አልሞ መስራት ይጠበቅብናል፡፡

የ7ኛ ክፍልን የመዝለቅ ምጣኔም ታቅዶ ሲሰራበት የቆየ ሲሆን በዚህ ግብ የመነሻ ትምህርት ዘመን(2012) የተደረሰበት ምጣኔ 73.4% የነበር ሲሆን በሶስት አመት ተግባራትን በመከወን በ2015 የትምህርት ዘመኑ የተማሪዎች 7ኛ ክፍልን የመዝለቅ ምጣኔን ወደ 74% ለማሳደግ ታቅዶ የግቡ አፈጻጸም በአማካይ ወደ 49.9% ያሽቆለቆለ መሆኑን ያሳያል፡፡ የዚህ ግብ አፈጻጸም ከእቅዱ ዘመን በፊት ከተደረሰበትም ይሁን ከዘመኑ ግብ ጋር ሲታይ በ23.5% እና 24.1% በቅደም ተከተል በመቀነስ የወረደ አፈጻጸም መሆኑን ያሳያል፡፡

በተጨማሪም የ8ኛ ክፍልን የማጠናቀቅ ምጣኔን ስናይ በዚህ ግብ የመነሻ ትምህርት ዘመን(2012) የተደረሰበት ምጣኔ 71% የነበር ሲሆን ተተከታታይ የሶስት አመታት እቅዶችን በመከወን በ2015 የትምህርት ዘመን መጨረሻ የተማሪዎች 8ኛ ክፍልን የማጠናቀቅ ምጣኔን ወደ 77% ለማሳደግ ታቅዶ የግቡ አፈጻጸም በአማካይ ወደ 60.86% የደረሰ መሆኑን ያሳያል፡፡ የዚህም ግብ አፈጻጸም ከእቅዱ ዘመን በፊት ከተደረሰበትም ይሁን ከዘመኑ እቅድ አፈጻጸም ጋር ሲታይ በ10.14% እና 16.16% በቅደም ተከተል የቀነሰ አፈጻጸም ስለሆነ የአስር አመቱን ግብ ከማሳካት አንጻር የዚህ ግብ አፈጻጸም 16.16% ወደኋላ በመቅረቱ ቀሪውን ከቀጣይ እቅዶች ጋር በመጨመር ግቡን ለማሳካት ጥረት የሚጠይቅ መሆኑን ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ የክልላችን ተማሪዎች በየአመቱ ወደ ላይኛዎቹ የትምህርት እርከኖች የመዝለቅ እድላቸው በእጅጉ ችግር እየገጠመው መሆኑን በአንክሮ በማየትና በመገምገም እስካሁን የታዩትን ውድቀቶች ሊያካክሱ የሚችሉ እቅዶችን በቀጣዩ አመታት በማቀድ የተማሪዎችን በየእርከኑ የማጠናቀቅ እና ወደቀጣዩ እርከን የመሸጋገር ተግዳሮቶችን በመለየት በትጋት መስራት ይገባዋል፡፡




ሥርዓተ-ትምህርቱን የጥራት ደረጃውን ጠብቆ ማዘጋጀት፣መተግበርና መገምገምን በሚመለከት የስርዓተ-ትምህርት ዝግጅት፣ ትግበራና ግምገማ ስራዎች አፈጻጸምን በሚመለከት አዲስ ስርዓተትምህርት በሙሉ ትግበራ ደረጃ ማካሄድ፡-በ2015 ዓ.ም ሙሉ ትግበራ የሚደረግባቸው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ መማሪያና ማስተማሪያ መጽሐፍት ብዛት በዘመኑ 340 ለማድስ ታቅዶ ሙሉ ትግበራ የሚደረግባቸውን መጻሕፍት ብዛት 324 (162 መማሪያ፣ 162 ማስተማሪያ) ማድረስ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ 95.3% ነው፡፡ የተሟላ አፈጻጸም ማስመዝገብ ያልተቻለው የትርጉም ስራው ሳይጠናቀቅ በመቅረቱ ወደ ሙሉ ትግበራ ያልተገባበት

በኦሮሞኛ ቋንቋ የሥነ ጥበብ ትምህርት 16 (8 መማሪያ፣ 8 ማስተማሪያ) መጽሐፍት በመኖራቸው ነው፡፡ ነገርግን በ2015 ዓ.ም ዝግጅቱ ተጠናቆ ለህትመት ዝግጁ ሆኗል፡፡

የሙሉ ትግበራ መጽሃፍት ትውውቅን በተመለከተ የመጽሃፍት ትውውቅን በሚመለከት አዲሱን ሥርዓተ ትምህርት ሙሉ ትግበራ የሚፈጽሙ በሁሉም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ላሉ 152,840 መምህራን እና ቅድመ አንደኛ ክፍል ደረጃ 1 ለሚያስተምሩ 9,193 አመቻቾች የሥርዓተ ትምህርት የትውውቅ ስልጠና አግኝተው ወደ ስራ ገብተዋል የሚል አመልካች ተዘጋጅቶ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡

በመጀመሪያ በክልሉ 9,511 የአንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ 2,323 የጉድኝት ማዕከላት እና ከ 152,840 በላይ የመጀመሪያና የመካከለኛ ደረጃ መምህራን ያሉ ሲሆን ሙሉ ትግበራ የተገባበትን አዲሱን ሥርዓተ ትምህርት ለሁሉም መምህራን በማስተዋወቅ የመማር መስተማሩን ስለሆነም ሥርዓተ ትምህርቱን ለመምህራን ለማስተዋወቅ  አስተባባሪ በነበሩ አካላት የማሰልጠኛ ሞጁል ተዘጋጅቶ የአሰልጣኞች ስልጠና የሚሰጡ ዋና አሰልጠኞችን መጽሐፍት ካዘጋጁ መምህራን መካከል 73 (ወንድ-70 ሴት-3) ተመልምለው ስልጠና በመስጠት የማዘጋጀት ስራ ተሰርቷል፡፡ ከዚህም በመቀጠል 657 (ወንድ 482፣ ሴት 175 ) በክልል ደረጃ ለጉድኝት አሰልጣኞች ስልጠና የሚሰጡ መምህራን እንዲሰለጥኑ ተደርጓል፡፡ደት የተቃና እንዲሆን ምቹ ሁኔታ መፍጠር የቢሮው ቀዳሚ ተግባር መሆኑ ይታወቃል፡፡በዚህም ሂደት በክልል ደረጃ መሰልጠን ያለባቸው 20,317 የአንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን ሲሆኑ በጉድኝት ማዕከል ደረጃ ደግሞ 132,523 የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን ይሰለጥናሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም በክልል ደረጃ የሚሰጠው ሥልጠና ለሁሉም 21 ዞኖች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በዚህም ሂደት  የአሰልጣኖች ስልጠና የወሰዱ መምህራን በድምር21,538 ( ወንድ 14,544፣ ሴት 6,994) ሲሆኑ ከተያዘው ዕቅድ አንጻር አፈጻጸሙ 106% ይሆናል፡፡ በተለያየ ዙር እና የሥልጠና ማዕከላት  በአሰልጣኝነት የተሳተፉ መምህራን 1,680( ወንድ 1,294፣ ሴት 386) ሲሆኑ  የዞንና የወረዳ ባለሙያዎች 534(ወንድ 449፣ ሴት 85) በአስተባባሪነት በሂደቱ ተሳትፈዋል፡፡ መረጃ ከላኩት 19 ዞኖች እና ከተማ አስተዳደሮች ሥልጠናውን ይወስዳሉ ተብለው የተለዩት 110,953 (ወንድ 59,170፣ ሴት 51,783) መምህራን ሲሆን ስልጠና የወሰዱት 98,192  (ወንድ 53,172፣ ሴት 45,020) መምህራን ናቸዉ አፈጻጸሙም 89% መሆኑን የተላከው መረጃ ያሳያል፡፡ በተለያየ ምክንያት 12,761( 5,998 ሴት 6,763) መምህራን ወይም 11% የመጽሐፍ ትዉዉቅ ስልጠናውን

አልወሰዱም፡፡ ይህም ዞንና ወረዳ የ2016 ዓ.ም ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ሥልጠና ያልወሰዱ መምህራንን በትምህርት አይነት በመለየ የሥርዓተ ትምህርት ትዉዉቅ ማድረግ የሚገባ መሆኑን መረጃዉ ያስገነዝባል፡፡

የመጽሃፍት አቅርቦትን በሚመለከት የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ የተማሪ መፀሀፍት ጥምርታ በዘመኑ 1፡3 እንዲሆን በተያዘው እቅድ መሰረት የተሰሩ ዝርዝር ስራዎች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡ በሙሉ ትግበራ ሊገቡ በሚችሉ 460 የየትምህርት አይነቱ መጽሃፍት ለተማሪዎች 1 ለ 1 ለማዳረስ በቁጥር የሚያስፈልገው የመጽሃፍት ብዛት 31,668,812 ይሆናል፡፡ ለዚህ የሚያስፈልገው በጀት ከፍተኛ በመሆኑ በዘመኑ 1 ለ 3 ለማዳረስ 8,888,172 መጽሃፍትን ለማሳተም ጥረት በመደረግ ላይ ነው፡፡ እየታተመ ያለውን መጽሐፍት የናሙና ማረጋገጥ ስራ እስከ ነሀሴ 10 የተሰራ ቢሆንም  አስከ 3ኛዉ ሩብ ዓመት የገባዉ 1,438,324( አማርኛ፣ ሂሳብና አካባቢ ሳይንስ-7ኛ ክፍል፤ እንግሊዝኛ 5 እና 6ኛ ክፍል፤ አካባቢ ሳይንስ 6ኛ ክፍል እና አዊኛ ቋንቋ 3፣6ና 7ኛ ክፍል) 9የትምህርት ዓይነት ብቻ ነበር፡፡ እስከ አራተኛዉ ሩብ ዓመት ለህትመት ከተሠጡት 44 ዓይነት ማስተማሪያ መጽሐፍት መካከል ተጨማሪ 12 ዓይነት መጥተዉ የመጽሐፍቱን ትክክለኛ ነት ከካሜራ ሬዲዉ ጋር ተረጋግጦ ለሚመለከተዉ ክፍል ተልኳል፡፡ በመሆኑም ከ44 ዓይነት መጽሐፍት 21 ዓይነት አገር ዉሥጥ ገብተዋል፡፡ ሌሎች 23 ዓይነት መጽሐፍት በጉዞላይ እንደሆኑ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

በተጨማሪም ቢያንስ ለመምህራን የሚሆን በትምህርት ቤት ደረጃ ሁለት ሁለት በየትምህርት አይነቱ እንዲደርስ ታስቦ 52 የትምህርት አይነት የተማሪዎች መጽሐፍት ብዛት 944,882 ታትሞ እንዲደርስ ተደርጓል፡፡በሦስቱ የብሔረሰብ ቋንቋዎች ትርጉም የተሰራላቸው መጽሐፍት፣ አፋን ኦሮሞ አፍመፍቻ እና ኽምጣና አፍመፍቻ ቋንቋ በአጠቃላይ 82 አይነት 835,732 የተማሪ መማሪያ መጽሐፍት ለተማሪዎች 1፡1 በሚደርስ ሁኔታ የዝርዝር መግለጫ ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው የስራ ክፍል በመሰጠት ህትመቱ እየተካሄደ ሲሆን የህትመት ናሙና የማረጋገጥ ስራም ተሰርቷል፡፡ በሦስቱ የብሔረሰብ ቋንቋዎች ትርጉም የተሰራላቸው መጽሐፍት፣ አፋን ኦሮሞ አፍመፍቻ እና ኽምጣና አፍመፍቻ ቋንቋን ጨምሮ በአጠቃላይ 82 አይነት 835,732 (የአፋን ኦሮሞ 326427፣ የኽምጠኛ 220821፣ አዊኛ 288484) የተማሪ መማሪያ መጽሐፍት ለተማሪዎች 1፡1 በሚደርስ ሁኔታ የዝርዝር መግለጫ ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው የስራ ክፍል በመሰጠት ህትመቱ ተጠናቆ ለተማሪዎች በመሰራጨት ላይ ይገኛል፡፡

በአጠቃላይ በክልላችን የትምህርት ስርዓት ውስጥ የትምህርት ጥራትን ከሚያመጡ ጉዳዮች ውስጥ የመማሪያና ማስተማሪያ መጻህፍት አቅርቦትና ስርጨት ወሳኝ ጉዳይ ተደርጎ ይታያል፡፡ በመሆኑም መንግስት ለመጽህፍት ህትመት በየዘመኑ በርካታ ሀብት ወጭ እንደሚያደርግ ይታመናል፡፡ሆኖም ግን በየጊዜው በሚካሄደው የስርተ-ትምህርት መሻሻል ምክንያት ጥቅም ላይ የዋሉ ነባር መጽሀፍት መስጠት የሚገባቸውን አገልግሎት ሳይሰጡ ስለሚቀየሩ እና በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት መጀመሪያ ወቅት እነሱን ሊተኩ የሚገባቸው መጽሀፍት ሳይዘጋጁና ሳይሰራጩ ቀድመው ስራ ላይ እንዳይውሉ ስለሚደረጉ በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች የሚገኙ ተማሪዎች የመጽሀፍት አቅርቦት ስለማይደረግላቸው ሲቸገሩና የትምህርቱን ጥራት በእጅጉ እየጎዳ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በዚህ ሶስት አመታት በተለይም ከ2014 ትምህርት ዘመን ጀምሮ ተግባራዊ እንዲደረግ የተደረገው የስርተ-ትምህርት መሻሻል በተለያዩ ምክንያቶች በሚፈጠር የመጽሀፍት አቅርቦት አለመኖር አሁን በመማር ላይ ያሉት ተማሪዎች የችግሩ ገፈት ቀማሽ ቀማሽ አድርጓቸዋል፣በትምህርት አቀባበላቸውም የሚያስከትለው የትምህርት ጥራት መጓደል ቀላል የሚባል ሊሆን አይችልም፡፡ ስለዚህ የትምህርት ቢሮው፣የመንግስት የበላይ አመራሮች፣ ተራድኦ-ድርጅቶችና ማህበረሰቡ በጋራ ተረባርበው ይህን ችግር መፍታት ይገባቸዋል፡፡

የስርዓተ-ትምህርት ግምገማ (ጥናትና ምርምር፣ የፈተና ውጤት ማሻሻል) ስራዎች አፈጻጸም
የክልል እና ሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አፈፃፀም አንጻር የአጠቃላይ የትምህርት ዓላማዎችና ግቦች በተገቢው መጠንና መለኪያዎች ግባቸውን መምታታቸውና የመማር ማስተማሩ ሂደት በጥራትና ሚዛኑን የጠበቀ ሁኔታ ለማረጋገጥ የሚያስችል የትምህርት ምዘና ሥርዓትን ማጠናከር ዋና የትኩረት ጉዳይ ሲሆን በሶስቱ አመታት የዕቅድ ዘመኑም ታቅዶ ሲሰራ ቆይቷል፡፡


በመሆኑም የ8ኛ ክልላዊ ፈተና ተመዝነው 50% እና በላይ አምጥተው ያለፉ ተማሪዎች በ2012 የትምህርት ዘመን 25.2% ከተደረሰበት በሶስቱ አመታት መጨረሻ በ2015 የትምህርት ዘመን 43% ለማድረስ ታልሞ 47.84%(100% በላይ) የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙ ከአስር አመቱ እቅድ አንጻር 63.7% መከናወኑን ያመለክታል፡፡ በተመሳሳይ የ12ኛ ብሄራዊ ፈተና ተመዝነው 50% እና በላይ አምጥተው ያለፉ ተማሪዎች በ2012 የትምህርት ዘመን 26.6% ከተደረሰበት በሶስቱ አመታት ሲሰራ ቆይቶ በ2015 የትምህርት ዘመን 43% ለማድረስ ታልሞ 4.01%(9.32%) የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙ ከመነሻ ዘመኑ በ1.83% እንዲሁም በሶስቱ አመታት እያሽቆለቆለ መምጣቱን ከእቅዱ ያመለክታል፡፡ የዚህ ግብ አፈጻጸም ከ2013

የትምህርት ዘመን ከተመዘገበው የተሻለ ውጤት ካስመዘገቡ ተማሪዎች መጠን በ2014 እና 2015 የትምህርት ዘመናት ውጤቱ በእጅጉ እያሽቆለቆለ በመምጣቱ ከ50% እና በላይ አምጥተው ያለፉት ተማሪዎች ቁጥር በሚያሳስብ እና በአገሪቱ የትምህርት ምዘና ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ወርዶ በሁለቱ አመታት የተመዘገበው የማለፍ ምጣኔ ሳይሳካ ቀርቶ በአማካይ 96.19% የሚደርሱ የ12ኛ ክፍል ምዘና የወሰዱ ተማሪዎች ከ50% በታች ያስመዘገቡ ሆነዋል፡፡ በመሆኑም የአስር አመቱን ግብ ለማሳካት በቀጣይ ቀሪ የእቅዱ አመታት 96.19% ተማሪዎች ከወደቁበት ሁኔታ አንስቶ እቅዱን በ100% ማሳካት የሚከብድ ቢሆንም ቢያንስ ወደ ዩኒቨርስቲ የሚገቡ ተማሪዎችን ድርቀት መቅረፍ በሚቻልበት መንገድ አልሞ መስራትን ይጠይቃል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን 12 አመታትን ሙሉ ሲማሩና ጊዜያቸውን እና የቤተሰቦቻቸውን ሀብት እና ጊዜ ሲያባክኑ እና የክልሉ ሀብት ባክኖ ከመቅረቱም ባሻገር ከዚህ ውድቀት በመነጨ ምክንያት የተማሪዎቹና ወላጆቻቸው የስነ-ልቦና ስብራት ይፈጥራል ፤ ከታች በመማር ላይ ያሉትን ተማሪዎች ተስፋ ያጨልማል፣የተማሪዎችን ወላጆች በልጆቻቸው የመተማመን ደረጃቸውን ስለሚያሳጣ ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት እንዳይልኩ ያደረጋቸዋል፣ተማሪ የማይገባባቸው ዩኒቨርስቲዎችን እንፈጥራለን እንዲሁም በሰፊው እየታዩ የመጡትን የስራ አጥነት፣የኑሮ ውድነትና የሰላምና አለመረጋጋት ችግሮች እንዲባባስ ዋነኛ ተጨማሪ መንስኤ ሊሆን እንደሚችል ታምኖበት ችግሩን በመረባረብ በአጭርና ረጂም ጊዜ እቅዶች መፍታት ይገባል፡፡

ይህ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ውጤት አለማስመዝግብ አዝማሚያ ከ2013 የትምህርት ዘመን ጀምሮ እያሽቆለቆለ መጥቶ ምንም መፍትሄ ሳይሰጠው አሁንም አሳዛኝና አሳፋሪ ውጤት ሆኖ ቀጥሏል፡፡ ምንም እንኳን በታችኛው የትምህርት እርከኖች የሚገኙት ተማሪዎች ውጤትም እየቀነሰ የመጣ መሆኑ ቢታወቅም የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ውጤት ደግሞ እጅግ አሳሳቢ ከሚባል ደረጃ መድረሱን ያመለክታል፡፡ በዚህ ግብ አፈጻጸም ይህን ያህል መውደቅና ማሽቆልቆል በሌሎቹ የ1ኛ፣መካከለኛና 2ኛ ደረጃ ተማሪዎች ውጤት መውረድ ምክንያቶች ይሆናሉ ተብለው ከሚጠቀሱት ውስጥ የሚከተሉትን ማለትም፡- በየደረጃው የሚገኘው የትምህርት አመራርናየሚመለከታቸው አካላት ትኩረት ማነስ፣የትምህርት ቤቶች መራቅ፣ የተማሪዎች ወላጆች ለትምህርት የሚሰጡት ግምት አናሳ በመሆኑ የልጆቻቸውን ጉልበት መጠቀም ዝንባሌና ተግባር፣የትምህርት ግብአቶች በበቂ ሁኔታ አለመሟላት፣የመምህራን የስነ-ምግባርና የመያ ብቃት ችግር ውስጥ መሆኑ፣ተማሪዎች ትምህርታቸውን የወደፊት የህይወት

ዓላማቸው ማሳኪያ አድረገው አለመረዳት፣በየወቅቱ እየተከሰቱ ያሉት ግጭቶችና ጦርነቶች…ወዘተ የመሳሰሉትን ለ12ኛ ክፍል ተማሪዎች አስደንጋጭ ውጤት መውደቅም ምክንያት ተደርገው የሚወሰዱ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ውጤት ይህን ያህል በተጋነነ ሁኔታ ማሽቆልቆል ጋር በተገናኘ ሊታዩ የሚገባቸው ግልጽነት የሌላቸው አካዳሚክ ወይም ስነ-ትምህርታዊ፣ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ትርጉም ተሰጥቶት በክልሉ የበላይ አመራር የሚመራ የሙያተኞች ቡድን ከዩኒቨርስቲዎች ጋር በመተባበር ጥልቅ የሆነ ጥናት ሊሰራለትና መፍትሄ ሊፈለግለት ይገባል፡፡

**ግራፍ 21-- በ8ኛና 12ኛ ክፍል ፈተና ከ50› ያመጡ ተማሪዎች በመቶኛ**




በሁሉም የትምህርት አይነቶች በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች ምዘና ውጤትን በሚመለከት በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 50% እና በላይ ያመጡ ተማሪዎች በ2012 የትምህርት ዘመን 87% የነበሩ ሲሆን በ2013 የትምህርት ዘመን 67.08%፣በ2014የ ትምህርት ዘመን 85.3% እንዲሁም በ2015 የትምህርት ዘመን 88.5% ያስመዘገቡ ሲሆን የግቡ አፈጻጸም እየተሻሻለ መምጣቱን ቢያሳይም ከመነሻ ዘመኑ አንጻር የሶስቱ አመታት አፈጻጸም በአማካይ ሲወሰድ 80.29% በመሆኑ በ6.71% ዝቅ ብሎ የተከናወነ መሆኑን ያመለክታል፡፡

በሁሉም የትምህርት አይነቶች በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 35% የሚሆኑ ተማሪዎች 75%ና በላይ ያመጡ ተማሪዎች በ2012 የትምህርት ዘመን

25.9% የነበሩ ሲሆን የሶስቱ አመታት አፈጻጸም በአማካይ ሲወሰድ 26.8% ያስመዘገበ ሲሆን የግቡ አፈጻጸም ከመነሻ ዘመኑ አንጻር የሶስቱ አመታት አፈጻጸም በአማካይ በተሻለ ሁኔታ የተከናወነ መሆኑን ማየት ቢቻልም ከግቡ አፈጻጸም አንጻር በ8.2% በመቀነሱ ግቡ አለመሳካቱን ያመለክታል፡፡ በተመሳሳይ በሁሉም የትምህርት አይነቶች በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 15% የሚሆኑ ተማሪዎች ደግሞ 85%ና በላይ ማምጣት ግብ ተጥሎ በርካታ ተግባራት የተከናወኑ ሲሆን አፈጻጸሙም በአማካይ 13.7% የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙ ለመነሻነት ከተወሰደው 12.8% አንጻር መሻሻል የታየበት ቢሆንም ከግቡ አፈጻጸም አኳያ ክንውኑ በ1.3% በማነስ መሆኑን ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች፣50%፣ 75% እና 85% እና በላይ ውጤት ለማስመዘገብ ከተሰራው ስራ አንጻር ግቦቹን ለማሳካት በየግቦቹ በ6.71%፣8.2% እና 1.3% በቅደም ተከተል በማነስ የተከናወኑ ስለሆነ በቀሪዎቹ የትምህርት ዘመናት እነዚህን ክፍተቶች መሙላት የሚያስችል እቅድ በማቀድ የአስር አመቱን ግቦች ማሳካት እንደሚቻል ተስፋ የሚሰጥ አፈጻጸም መሆኑን ያመለክታል፡፡

የሒሳብና ሳይንስ ትምህርትን ጥራት ከማሻሻል አንጻር በዚህ ረገድ የሂሳብና ሳይንስ ትምህርቶችን የመማር ማስተማር ሂደት በቴክኖሎጂ በማስደገፍ የተማሪዎችን ውጤት ለማሻሻል በየደረጃው የቴክኖሎጂ፣ ምህድስና፣ የስነጥበብና ሂሳብ ትምህርት (STEAM) ፕሮግራም ላብራቶሪ የተሟላላቸው የትምህርት ተቋማት ድርሻን ከፍ ማድረግ እና በክልል ደረጃ በፈጠራ ስራ እውቅና የተሰጣቸው መምህራንና ተማሪዎች ማሳደግ ስራዎችን ላይ ትኩረት ተስጥቷል ፡፡

በዚህ ረገድ በ2013 የትምህርት ዘመን የተሟላ ቤተሙከራ ከነበራቸው 598(97.2%) 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣ በ2014 የተሟላ ቤተሙከራ ከነበራቸው 297(46.3%) ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንዲሁም የተሟላ ቤተሙከራ ከነበራቸው 334 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 6.3%፣ 5.9% እንዲሁም 29% ለSTEAM ፕሮግራም የተሟላ ላብራቶሪ በቅደም ተከተል አደራጅተዋል፡፡ ይህም በአማካይ ለSTEAM ፕሮግራም የተሟላ ላብራቶሪ 13.7% መሆኑን ያሳያል፡፡ በመሆኑም የሳይንስ ቤተሙከራ አደረጃጀትን ለማሻሻል ቀጣይነት ያለው ጥረት መደረግ እንዳለበትና ስራው በጅምር ደረጃ ያለ መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡

በሌላ በኩል በክልል ደረጃ በፈጠራ ስራ እውቅና የተሰጣቸው ተማሪዎች በሶስት አመቱ ለ45 በፈጠራ ስራ እውቅና የተሰጣቸው ተማሪዎች ለመስጠት ታቅዶ ለ40 (88.8%) በፈጠራ ስራ እውቅና የተሰጣቸው ተማሪዎች ናቸው፡፡ ክንውኑ አመቱ እቅድ ጋር ሲታይ(66.6%) መፈጸሙን ያመለክታል፡፡ በተመሳሳይ በክልል ደረጃ በፈጠራ ስራ እውቅና የተሰጣቸው መምህራን በሶስት አመቱ ለ22 በፈጠራ ስራ እውቅና ለመስጠት ታቅዶ ለ24(100% በላይ) እንዲሁም ከአመቱ 80% በፈጠራ ስራ እውቅና የተሰጣቸው መምህራን ናቸው፡፡

በአጠቃላይ የሳይንስ ትምህርቶች በተግባር ተደግፌው እንዲሰጡ ለማድረግ አጋዥ የሆነውን የአኒሜሽን ቡድን በትምህርት ቤት፣ በወረዳ፣ በዞን/ከተማ አስተዳደር እና በክልል ደረጃ በማደራጀት የበኩላቸውን እንዲወጡ በመከታተል፣ በመደገፍና በማሰማራት ተግባርና ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ማድረግ በየደረጃው ያለው የትምህርት አመራር ሚና በጣም ከፍተኛ መሆኑን በመገንዘብ እየተስተዋሉ ያሉ የተለያዩ ምክንያቶችን ደረጃ በደረጃ በመፍታት ለተማሪዎች ውጤት መሻሻል ምቹ ሁኔታ መፍጠር ቀዳሚ ተግባር ነው፡፡

የትምህርት ጥራትና ተገቢነት አፈፃፀምን በተመለከተ በአገራችን ብሎም በክልላችን የተማሪዎችን የመማር ውጤትና ስነ ምግባር ለማሻሻል የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅ በ1998 ዓ/ም በአገር አቀፍ ደረጃ መዘጋጀቱ ይታወሣል፡፡ በክልላችን ደግሞ ከ1999 ዓ/ም ጀምሮ ተግባራዊ መሆን ጀምሯል፡፡ ፓኬጁ ለትምህርት ጥራት መጠበቅ መሠረታዊ የሆኑና እርስ በርሣቸው የሚመጋገቡ ስድስት መርሃ ግብሮች ያሉት ሲሆን የእነዚህ መርሃ ግብሮች የሶስት አመታት ዕቅድ አፈፃፀም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የተማሪ ሴክሽን ጥምርታን ከማሻሻል አንጻር በ2014 የትምህርት ዘመን በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት 1:37 የነበረውን የተማሪ ሴክሽን ጥምርታ በ2015 የትምህርት ዘመን ለማስቀጠልና የ2ኛ ደረጃ ትምህርት 1:57 የተማሪ ሴክሽን ጥምርታ 1:40 ለማድረስ ታቅዶ የነበረ ሲሆን እስከ 2015 የትምህርት አመት መጨረሻ በጥቅሉ በአንደኛና መካከለኛ ደረጃዎች 3,591,326 ተማሪዎች በ96,978 ሴክሽኖች በመማር ላይ የነበሩ ሲሆን ጥምርታው 1: 37(100%) እንደሆነ ሲቀጥል የ2ኛ ደረጃ ትምህርት የተማሪ ሴክሽን ጥምርታ ደግሞ 962,713 ተማሪዎች በ17,880 ሴክሽኖች በማስተማር 1:54(74.3%) የደረሰ ቢሆንም ከስታንዳርዱ ጋር ሲነጻጸር በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የተማሪ ሴክሽን ጥምርታ 1:40 ለማድረስ ከታሰበው አኳያ በ25.7% ያልተሳካ በመሆኑ ከዚህ በመነሳት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተጨማሪ

ሴክሽኖችን በመክፈት የተማሪዎችን መጨናነቅ መቀነስ እንደሚገባና በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ተማሪ ሴክሽን ጥምርታ በአለበት እንዲቀጥል ማድረግ እንደሚያስፈልግ መረዳት ይቻላል፡፡

የትምህርት ቤቶች የንጹህ የመጠጥ ውሀ አቅርቦት አፈጻጸምን በሚመለከት ንጹህ የመጠጥ ውሀ ያላቸው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት በ2012 ከተደረሰበት 73.86% በ2015 ትምህርት ዘመን 85% ለማድረስ ታቅዶ 76.4%(89.88%) የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውሃ ያላቸው ሲሆን ከአስር አመቱ እቅድ አንጻር ተመሳሳይ ክንውን አላቸው፡ ፡ በተመሳሳይ ንጹህ የመጠጥ ውሀ ያላቸው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት በ2012 ከተደረሰበት 44.25% በ2015 ትምህርት ዘመን ወደ 85.0% ለማድረስ ታቅዶ 45.4%(53.41%) ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውሃ ያላቸው ሲሆን ከአስር አመቱ አፈፃፀም አንጻር 46.58% ያልተሳካ ግብ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በሁሉም ደረጃዎች ንጹህ የመጠጥ ውሀ አቅርቦቶች ግብ በሚፈለገው መጠን የተከናወነ አለመሆኑን በመገንዘብ በቀጣይ ክፍተቶችን መሙላት ይጠበቅብናል፡፡

የመፀዳጃ ቤት ያላቸው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ብዛት በ2012 ከተደረሰበት 83.98% እስከ 2015 ትምህርት ዘመን መጨረሻ 87.18% ለማድረስ ታቅዶ በሶስቱ አመታት የክልሉ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 97.3%(100%) የመጸዳጃ ቤት አገልግሎት ያገኙ መሆናቸውን እንዲሁም አፈጻጸሙ ከአስር አመቱ አንጻር ተመሳሳይ ክንውን አለው፡፡ በመሆኑም የዚህ ግብ አፈጻጸም አበረታች ሲሆን በሌላ በኩል ደረጃውን የጠበቀ የመፀዳጃ ቤት ያላቸው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ብዛት 40.0% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 2,946 ወይም 32.1% ትምህርት ቤቶች ደረጃውን የጠበቀ መጸዳጃ ቤት ያላቸው ሲሆን ከታቀደው አፈፃፀሙ 80.2% ሆኗል፡፡


በሁለተኛ ደረጃ የመፀዳጃ ቤት ያላቸውን ት/ቤቶች ብዛት በ2012 የትምህርት ዘመን ከተደረሰበት 97.64% በ2015 የትምህርት ዘመን መጨረሻ 98.35% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 641 ወይም 97.3% ትምህርት ቤቶች መጸዳጃ ቤት ያላቸው ሲሆን ከታቀደው አፈፃፀሙ 98.9% ሆኗል፡፡ ደረጃውን የጠበቀ የመፀዳጃ ቤት ያላቸውን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ብዛት እስከ 2015 ትምህርት ዘመን መጨረሻ 70% ለማድረስ ታቅዶ በክልሉ ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 510 ወይም 77.4%

ትምህርት ቤቶች ደረጃውን የጠበቀ መጸዳጃ ቤት ያላቸው ሲሆን ከታቀደው አፈፃፀሙ 139.0% ሆኗል፡፡

በሌላ በኩል የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ አገልግሎት ያላቸውን ትምህርት ቤቶች በ2012 የትምህርት ዘመን ከተደረሰበት 18.06% በሶስቱ የትምህርት አመታት እቅዶችን በመተግበር በ2015 የትምህርት አመት መጨረሻ በአማካይ ወደ 41.6% ለማሳደግ ግብ ተውስዶ ወደ 30% በማድረስ አፈጻጸሙ 72.83% ሲሆን ከመነሻ ዘመኑ ከተደረሰበት አፈጻጸም አኳያ ለውጥ ቢኖረውም ከተቀመጠው ግብ አንጻር መከናወን የነበረበት 27.16% የሴች ንጽህና መጠበቂያ አገልግሎት መስጫ ክፍሎች አለመዘጋጀታቸውን ስለሚያመለክት ቀሪ ተግባራትን በቀጣይ እቅዶች በማካተት የአስር አመት ግቡን ማሳካት እንዳለብን ከወዲሁ ይጠቁማል፡፡

የተቋማት ግንባታ፣ ማስፋፋት፣ እድሳት እና ጥገና ስራዎች አፈጻጸምን በተመለከተ በመንግስት፣ በህብረተሰ እና በአጋር አካላት የተገነቡ አዲስ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት በ2012 የተምህርት ዘመን 75 የነበረውን ለሶስተ ተከታታይ የእቅድ ዘመናት ግንባታ በማካሄድ በ2015 የትምህርተ ዘመን መጨረሻ 480 አዲስ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ለመገንባት ግብ ተወስዶ 135(38.12%) ትምህርት ቤቶች የተገነቡ ሲሆን አፈጻጸሙ ለመነሻነት ከተወሰደው አመት አንጻር እድገት ሲያሳይ በሶስት አመታት እንዲከናወን ከተቀመጠው ግብ አንጻር ደግሞ በ61.88% ያህል አለመሳካቱን እና ከአስርአመቱ እቅድ አንጻር 15% ብቻ የተከናወነ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል አዲስ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ግንባታ ብዛት በ2012 የትምህርት ዘመን 20 ከነበረበት ለሶስት ተከታታይ የእቅድ ዘመናት ተጨማሪ ግንባታ በማካሄድ በ2015 የትምህርት ዘመን መጨረሻ 215 አዲስ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ለመገንባት ግብ ተወስዶ 50(23.25%) አዲስ ትምህርት ቤቶች የተገነቡ ሲሆን አፈጻጸሙ ለመነሻነት ከተወሰደው አመት አንጻር እድገት ሲያሳይ ከተቀመጠው ግብ አንጻር ደግሞ በ67.75% ያህል አለመሳካቱን እና 10.61% ብቻ የተከናወነ መሆኑን መገንዘብ እንችላለን፡፡ በመሆኑም በክልላችን እየታየ ያለውን የተማሪ ክፍል ጥምርታ ችግር በማሻሻል ወደ ስታንዳርዶቹ የተጠጋ የክፍል ተማሪ ጥምርታ ለማምጣትና የተማሪዎችን በማይመች የትምህርት ሁኔታን ለመለወጥ እየተሰራ ያለው ተግባር እንዳለ ሆኖ ከሚፈለገው ውጤት አንጻር ስናየው ግን የአስር አመቱን ግቦች ከማሳካት አኳያ በ61.88% እና በ67.75% ወደኋላ የቀረንበት ግብ መሆኑን በመረዳት በቀጣይ የእቅድ አመታት ግቦቹን ሊያሳኩና ቀሪ

ስራዎቹን ሊያካክስ በሚቻልበት ሁኔታ እቅዶቻችንን በመከለስ ለገቢራዊነታቸው ርብርብ ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡




ከዚሁ ጋር በተገናኘ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እድሳትን በሚመለከት በሶስቱ አመታት አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን እድሳት በማካሄድ በሶስት አመት መጨረሻ በ2015 ትምህርት ዘመን 5,573 አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ለማደስ ግብ ተይዞ 4,188(75.14%) ያህሉን ትምህርት ቤቶች ማደስ የተቻለ እና ከአስር አመቱ እቅድ አንጻር 37.85% የተከናወነ መሆኑን ያሳያል፡፡ በመሆኑም ከሶስቱ አመት አንጻር ከግብ ስኬቱ አንጻር ስንወስደው ከታቀደው ውስጥ 24.86% የሚሆኑ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እድሳት አለመከናወኑን ያመለክታል፡፡

በተመሳሳይ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ተቋማትን በማስፋፋት ሪገድ ደረጃቸውን ያሳደጉ (ከ1ኛ - 6ኛ ወደ 1ኛ - 8ኛ) ትምህርት ቤቶች ብዛት በ2012 የትምህርት ዘመን ከነበረበት 68% በሶስቱ የእቅድ ዘመናት ትምህርት ቤቶችን በማስፋፋት በ2015 ትምህርት ዘመን መጨረሻ 74% ትምህርት ቤቶችን ለማስፋፋት ግብ ተቀምጦ 70(94.59%) እና ከአስር አመቱ 82.35% የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ተቋማትን በማስፋፋት ትምህርት ቤቶች ደረጃቸውን ከአንደኛ ደረጃ ወደ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ (ከ1ኛ - 6ኛ ወደ 1ኛ - 8ኛ) ያሳደጉ መሆናቸውን ያመለክታል፡፡ አፈጻጸሙ ከመነሻ(baseline)አመቱ አንጻር ስንለካው አበረታች ለውጥ የታየበት ቢሆንም በሶስት አመት እንዲሳካ ከተቀመጠው ግብ አፈጻጸም አንጻር ሲወዳደር ግን የ34.73%(75 ት/ቤቶች) ባለመስፋፋታቸው እድገት ማግኘት አለመቻላቸውን ይጠቁማል፡፡

በተመሳሳይ የ2ኛ ደረጃ (9-12)ትምህርት ቤቶች እድሳትን በሚመለከት በሶስቱ አመታት የ2ኛ ደረጃ (9-12)ትምህርት ቤቶችን እድሳት በማካሄድ በ2015 ትምህርት ዘመን 145 የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ለማደስ ግብ ተይዞ 141(97.24%) እና ከአስር አመቱ 16.8% ያህሉን ትምህርት ቤቶች ማደስ የተቻለ ሲሆን ከግብ ስኬቱ አንጻር ስንወስደው ከታቀደው ውስጥ 2.76% የሚሆኑ የ2ኛ ደረጃ (9-12)ትምህርት ቤቶች እድሳት አለመከናወኑን ያመለክታል፡፡ የ2ኛ ደረጃ (9-12) ተቋማትን በማስፋፋት ሪገድ ደረጃቸውን ወደ ኮምፕሬንሲብ ደረጃ ለማሳደግ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ቁጥር በሶስቱ የእቅድ ዘመናት ትምህርት ቤቶችን በማስፋፋት በ2015 ትምህርት ዘመን መጨረሻ 204 ትምህርት ቤቶችን ለማስፋፋት ግብ ተቀምጦ፡- የማስፋፋት እቅዱ ሙሉ በሙሉ አልተሳካም እንዲሁም 9 ኮሌጆችን ለማደስና ለማስፋፋት ታስቦ ተግባሩ አለመካናወኑን ያሳያል፡፡ በመሆኑም 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ደረጃቸውን ወደ ኮምፕሬንሲብ ደረጃ ለማሳደግ ኮሌጆችን ለማደስና ለማስፋፋት የተቀመጡት ግቦች አለመሳካታቸውንና የአስር አመቱ ግብን ለማሳካት በቀጣይ የእቅድ ክለሳ ዘመናት 204 የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን እና 9 ኮሌጆችን ለማስፋፋት ታቅዶ ያልተሳካውን ግብ በማካተት በቀጣይ አመታት እንዲተገበር ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡

የትምህርት ቤቶችን ደረጃ በቀጣይነት በማሻሻል ለመማር ማስተማር ሂደቱ ምቹ ከማድረግ አንጻር የክልላችን ትምህርት ቤቶች በግብአት፣ በሂደት እና በሚያስመዘግቡት ውጤት ሲመዘኑ ደረጃቸው ያልተሻሻለ እና ለመማር ማስተማር ምቹ ያልሆኑ ናቸው፡፡ ይህን ሁኔታ በመቀየር የትምህርት ቤቶችን ደረጃ በቀጣይነት በማሻሻል ለመማር ማስተማር ሂደቱ ምቹ ለማድረግ ደረጃ 3 እና ደረጃ 4 የደረሱ የቅድመ አንደኛ ደረጃ፣ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ድርሻ ማሳደግ የሚያስችሉ ስራዎችን ለማከናወን ባለፉት ሶስት አመታት እንቅስቃሴ ሲደረግ ቆይቷል፡፡


ከቅርብ አመታት ወደዚህ በክልሉ የቅድመአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የኢንስፔክሽን ስታንዳርድ ተዘጋጅቶ ደረጃ መስጠት የተጀመረ በመሆኑ በደረጃው ያለውን የጥራት ችግር ለመረዳት እና ለማሻሻል አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ ከዚህ በመነሳት በ2012 የትምህርት ዘመን ደረጃ 3 የደረሱ የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ብዛት 4% የደረሰውን ውጤት 2015 አመት መጨረሻ ድረስ 33% ለማድረስ ታቅዶ የነበረ ሲሆን አጠቃላይ የኢንስፔክሽን አገልግሎት ከአገኙ እና ደረጃ ከተሰጣቸው የቅድመ አንደኛ ትምህርት ቤቶች መካከል በሶስት አመቱ አማካይ 6.96%(30.18%) እንዲሁም ከአስር አመቱ 9.94% የሚሆኑት ደረጃ 3

ሆነዋል፡፡ ይህም በሶስት አመት ከታቀደው አፈፃፀሙ በ93.04% በማነስ የተከናወነ ሲሆን በመነሻነት ከተወሰደውም አንጻር የተሻለ መሆኑን ያሳያል፡፡

በሌላ በኩል በኢንስፔክሽን በ2012 የትምህርት አመት ከተደረሰበት 14.05% ደረጃ 3 የደረሱ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ብዛት እስከ 2015 አመት መጨረሻ 33% ለማድረስ ታቅዶ የነበረ ሲሆን አጠቃላይ በሶስት አመት የኢንስፔክሽን አገልግሎት ከአገኙ እና ደረጃ ከተሰጣቸው የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 13.1%(39.59%) እና ከአመቱ እቅድ 18.71% ትምህርት ቤቶች ደረጃ 3 ሆነዋል፡፡ ይህም በሶስት አመት ከታቀደው 19.9% በማነስ የተከናወነ ሲሆን ለመነሻነት ከተወሰደው አንጻር 0.95% በማነስ የተከናወነ መሆኑን ያሳያል፡፡ በተጨማሪ በኢንስፔክሽን በ2012 የትምህርት ዘመን ከተደረሰበት 17.07 ደረጃ 3 የደረሱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ብዛት እስከ 2015 አመት መጨረሻ 33% ለማድረስ ታቅዶ የነበረ ሲሆን በሶስት አመቱ አጠቃላይ የኢንስፔክሽን አገልግሎት ከአገኙ እና ደረጃ ከተሰጣቸው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 24.3%(73.63%) እንዲሁም ከአስር አመቱ 34.71% ትምህርት ቤቶች ደረጃ 3 ሆነዋል፡፡በመሆኑም በሶስት አመቱ ከታቀደው 8.7% በማነስ የተከናወነ መሆኑን ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል ደረጃ 4 የደረሱ የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መጠን 18% ፣የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ብዛት እስከ 2015 አመት መጨረሻ 18%፣ ደረጃ 4 የደረሱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን መጠን እስከ 2015 አመት መጨረሻ 18% እንዲሁም ደረጃ 4 የደረሱ የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች 70 ለማድረስ ታቅዶ የነበረ ሲሆን ሁሉም ትምህርት ቤቶችና ኮሌጆች ደረጃ 4 አለመድረሳቸውን ያመለክታል፡፡ ይህን የክልላችን አፈጻጸም ከአገራዊ አፈጻጸሙ ጋር ስናወዳድረው በቅድመ-መደበኛ ትምህርት 8%፣ የአንደናና መካከለኛ ትምህርት ቤቶች 8% እንዲሁም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 36% የሚደርሱት ደረጃ 4 መድረሳቸውን ማየት ይቻላል፡፡

በመሆኑም በአጠቃላይ የትምህርት ቤቶችን ደረጃ በቀጣይነት በማሻሻል ለመማር ማስተማር ሂደቱ ምቹ ለማድረግ ደረጃ 3 ለማድረስ የተደረገው ጥረት ባይናቅም በቀጣይ አንድም ትምህርት ቤት ደረጃ 4 ማድረስ አለመቻሉ ጋር ሲነጻጸር የተሻለ መስሎ ቢታይም በሁሉም ረገድ በሚገባ ሊታይ የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ የትምህርት ቤቶችን ደረጃ ወደ 3 እና 4 የማሳደጉ ተግባር አሁን ያሉበትን ተግዳሮቶች በመፈተሽ በሚፈለገው ደረጃ ውጤት እንዲያመጣ ማድረግ የሚችል እቅድ በማዘጋጀት ለተግባራዊነቱ በጋራ መረባረብ ይገባል፡፡

**ግራፍ-22-ደረጃ 3 የደረሱ ትምህርት ቤቶች**




የመምህራን እና የትምህርት አመራሩን የትምህርት ደረጃ በማሟላት ረገድ ለደረጃው የተቀመጠውን (ሰርተፊኬትና በላይ) የትምህርት ደረጃ የሚያሟሉ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን ብዛት በ2012 ከነበረበት 3,117 በ2015 አመት መጨረሻ ወደ 16,539 ለማድረስ ታቅዶ የነበረ ሲሆን በሶስት አመት 21,134 በማድረስ ከእቅዱ 127.6% መፈጸም ተችሏል። በተመሳሳይ የዲፕሎማ የትምህርት ደረጃ የሚያሟሉ አንደኛ እና የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት መምህራን ብዛት በ2015ዓ.ም 100% ለማድረስ ታቅዶ 99.1% መፈጸም ተችሏል። ለደረጃው የተቀመጠውን የመጀመሪያ ዲግሪና የትምህርት ደረጃ የሚያሟሉ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን ብዛት በ2015 አመት መጨረሻ 100 ለማድረስ ታቅዶ 99.6% መፈጸም ተችሏል።

የትምህርት አመራር የትምህርት ደረጃ ማሻሻልን በሚመለከት ለደረጃው የተቀመጠውን የመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት ደረጃ የሚያሟሉ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ር/መምህራን ብዛት በመቶኛ በ2015ዓ.ም 86.41% ለማድረስ ታቅዶ 84.6%(97.9%) መድረሱን ያሳያል። ለደረጃው የተቀመጠውን ሁለተኛ ዲግሪ የትምህርት ደረጃ የሚያሟሉ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ር/መምህራን ብዛት በመቶኛ 2015 አመት መጨረሻ 79.5% ለማድረስ ታቅዶ 79.9%(100% በላይ) መፈጸም ተችሏል። ለደረጃው የተቀመጠውን (የመጀመሪያ ዲግሪ) የትምህርት ደረጃ የሚያሟሉ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ የክላስተር ሱፐርቫይዘሮች ብዛት በ2015ዓ.ም 100% ለማድረስ ታቅዶ 97.9% መከናወኑን ያመለክታል። ለደረጃው የተቀመጠውን (ሁለተኛ ዲግሪ) የትምህርት ደረጃ የሚያሟሉ የሁለተኛ ደረጃ

ሱፐርቫይዘሮች ብዛት በ2015 ዓ.ም 100% ለማድረስ ታቅዶ 94.7% የደረሰ መሆኑን ማየት ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ ለደረጃው የተቀመጠውን የትምህርት ደረጃ የሚያሟሉ የኮሌጅ አሰልጣኝ መምህራን በ2015 ዓ.ም 93% ለማድረስ ታቅዶ 89.7% የደረሰ መሆኑን ማየት ተችሏል፡፡ በመሆኑም በየደረጃው ያሉ መምህራንና የትምህርት አመራርን የትመህርት ደረጃቸው እንዲያድግ ከተቀመጡት ግቦች አንጻር አበረታች ውጤቶች የተመዘገቡ ሲሆን ከአገራዊ አፈጻጸሙም በሁሉም ደረጃዎች የተቀራረበ ክንውን ያለው ሲሆን የቀሩትን የማሟላት ስራ በቀጣይ በማከናወን የክልሉን የመምህራንና ትምህርት አመራር አቅርቦቱን ወደሚፈለገው ደረጃ ለማምጣት የሚቻል በመሆኑ ተስፋ ሰጭ ክንውን ነው፡፡

በሌላ በኩል በክልላችን በስራ ላይ የሚገኙ መምህራንን ለደረጃው የሚፈለገውን የትምህርት ደረጃ እንዲያሟሉ ለማድረግ በርካታ ስራዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል፡፡ በተሰጠው መጠነ ሰፊ የስልጠና እድል ስታንዳርዱን አሟልተው በስራ ላይ የተሰማሩት መምህራን ቁጥር አበረታች ቢሆንም የመምህርነት ሙያ ሁሌም ማንበብንና መማርን የሚጠይቅ ሙያ በመሆኑ በቅድመ ስራ ስልጠና በተገኘ እውቀትና ክህሎት ብቻ ማስተማር እንደማይቻል ግልጽ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር መምህራን በስራ ላይ እያሉ እውቀታቸውንና የሙያ ክህሎታቸውን የሚያዳብሩበት የተከታታይ ሙያ ማሻሻያ መርሀ ግብር ተዘርግቶ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡

በመሆኑም በ2015 የትምህርት አመት በተከታታይ ሙያ ማሻሻያ (ተሙማ) የተሳተፉ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ መምህራን ድርሻ ወደ 100.0% ከፍ ለማድረግ ታቅዶ በማስተማር ላይ ከነበሩ 146,005 (ወንድ 77,130፣ ሴት 68,875) መምህራን መካከል የፕሮግራሙ ተሳታፊዎችን 140,527 (ወንድ 74,028፣ ሴት 66,499) ወይም 96.2% (ወንድ 96.0%፣ ሴት 96.6%) በማድረስ ከእቅዱ 96.2% መፈጸም ተችሏል፡፡ በፕሮግራሙ የሚሳተፉ የሁለተኛ ደረጃ መምህራንን ድርሻ 100.0% ለማድረስ ታቅዶ በማስተማር ላይ ከነበሩት 43,462 (ወንድ 31,974፣ ሴት 11,488) መምህራን መካከል ተሳታፊዎችን 42,232 (ወንድ 31,192፣ ሴት 11,040) ወይም 97.2% (ወንድ 97.6%፣ ሴት 96.1%) በማድረስ ከእቅዱም 97.2% መፈጸም ተችሏል፡፡

በ2015 ትምህርት ዘመን የርዕሰ-መምህራንን ሙያ ለማጎልበትም የሙያ ማሻሻያ ፕሮግራሙ ታቅዶ ተፈጽሟል፡፡ በመሆኑም በተከታታይ ሙያ ማሻሻያ (ተሙማ) የተሳተፉ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ር/መምህራን ድርሻ በአመቱ መጨረሻ 100.0% ለማድረስ ታቅዶ በስራ ላይ ከነበሩት ር/መምህራን መካከል የፕሮግራሙ ተሳታፊዎችን 8,906 (ወንድ 8,301፣ ሴት 605)

ወይም 97.0% (ወንድ 97.3%፣ ሴት 93.8%) በማድረስ ከእቅዱም 97.0% መፈጸም ተችሏል፡፡ በፕሮግራሙ የሚሳተፉ የሁለተኛ ደረጃ ር/መምህራንን ድርሻ በ2015 የትምህርት ዘመን መጨረሻ 100.0% ለማድረስ ታቅዶ በስራ ላይ ከነበሩት ር/መምህራን መካከል የፕሮግራሙ ተሳታፊዎችን 623 (ወንድ 608፣ ሴት 15) ወይም 96.4% (ወንድ 96.5%፣ ሴት 93.8%) በማድረስ ከእቅዱም 96.4% መፈጸም ተችሏል፡፡

በመጨረሻም በ2015 ትምህርት ዘመን ይህ ፕሮግራም ለጉድኝት ሱፐርቫይዘሮች እንዲደርስ ክትትትል የተደረገ ሲሆን በተከታታይ ሙያ ማሻሻያ (ተሙማ) የተሳተፉ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ጉድኝት ሱፐርቫይዘሮችን ድርሻ በአመቱ መጨረሻ 100.0% ለማድረስ ታቅዶ በስራ ላይ ከነበሩት የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ሱፐርቫይዘሮች መካከል የፕሮግራሙ ተሳታፊዎችን 2,176 (ወንድ 2,100፣ ሴት 76) ወይም 98.1% (ወንድ 98.2%፣ ሴት 95.0%) በማድረስ ከእቅዱም 98.1% መፈጸም ተችሏል፡፡ በፕሮግራሙ የሚሳተፉ የሁለተኛ ደረጃ ሱፐርቫይዘሮችን ድርሻ በአመቱ መጨረሻ 100.0% ለማድረስ ታቅዶ በስራ ላይ ከነበሩት የሁለተኛ ደረጃ ሱፐርቫይዘሮች መካከል ተሳታፊዎችን 223 (ወንድ 209፣ ሴት 14) ወይም 98.7% (ወንድ 98.6%፣ ሴት 100.0%) በማድረስ ከእቅዱም 98.7% መፈጸም ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የመምህራንን ከስራ የመልቀቅ ምጣኔ በ2014ዓ.ም ከነበረበት 1.4% በ2015ዓ.ም ወደ 1.3% ዝቅ ለማድረግ ታቅዶ የነበረ ሲሆን በሁሉም ደረጃ በማስተማር ላይ ከነበሩት 202,696 (ወንድ 110,190፣ ሴት 92,506) መምህራን መካከል እስከ 2015 አመት መጨረሻ የለቀቁ መምህራን 4,151 (ወንድ 2,643፣ ሴት 1,508) ወይም 2.0% (ወንድ 2.4%፣ ሴት 1.6%) የደረሰ ሲሆን አፈጻጸሙ ከእቅዱ ጋር ሲነጻጸር 63.5% ነበር፡፡ ይሁንና የመልቀቅ ምጣኔው ከ2014 ከተመዘገበው የመልቀቅ ምጣኔ ጋር ሲነጻጸር የጨመረ በመሆኑ በቀጣይ ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይጠይቃል፡፡

ውጤታማ የሀብት አጠቃቀም ስርዓትን ማጎልበት እንዲቻል በትምህርትና ስልጠና ዘርፉ ከክልል እስከ ትምህርት ቤት ድረስ የመንግስት የበጀት ድርሻን ከፍ ማድረግ አንድ ተግባር ነው፡፡ መንግስት ከአለው ውስን ሀብት ለመምህራንና ሰራተኞች ደመወዝና ስራ ማስኬጃ፣ በትምህርት ቤቶች የነፍስወከፍ ድጎማ እንዲመደብ በማድረግ እና ጥራት ያለው ትምህርት አቅርቦት እንዲሻሻል በአግባቡ የተደራጁ ትምህርት ቤቶች ግንባታዎችን ማስፈጸሚያ በጀት መመደብ የሚጠበቅበት ሲሆን ሰፋፊ ስራዎች በመሰራት ላይ ናቸው፡፡

ከዚህ አንጻር በሶስት አመት ውስጥ በትምህርትና ስልጠና ዘርፉ የመንግስት በጀት ድርሻ በ2012 የትምህርት ዘመን ከነበረበት 68% በ2015 የትምህርት ዘመን ድርሻውን ወደ 70.58 ለማሳደግ ግብ ተይዞ በአማካይ 78.5%(100%) ሀብት ከመንግስት መመደቡን ያሳያል። በተመሳሳይ በዘርፉ የሚታየውን የሀብት ጉድለት ለመሙላት ህብረተሰቡ፣መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅተቶች፣፣በግል ባለሀብቶችና በተቋማት የውስጥ ገቢ የተሰበሰበ ሀብት ድርሻ በመቶኛ በ2012 የትምህርት ዘመን ከነበረበት 11% በ2015 የትምህርት ዘመን ድርሻውን ወደ 15 ለማሳደግ ግብ ተይዞ 19.3%(100% በላይ) ሀብት መመደቡን ያሳያል።


የአጋር ድርጅቶች ድርሻን ከፍ እንዲል ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ በዘመኑ የተለያዩ ድርጅቶች እንዲሳተፉ ተደርጓል። የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻል ለፍትሀዊነት (GEQIP-E)፣ የተባበሩት መንግስታት የሕፃናት መርጃ ድርጅት (UNICEF) እና ሌሎችም አካላት በዘርፉ ያበረከቱትን አስተዋጽኦ በዚህ ሪፖርት የፕሮጀክቶች አፈጻጸም በሚዳሰሰብት ክፍል በዝርዝር ቀርቧል። ይህን ለማገዝም በትምህርት ተቋማት በህብረተሰብ፣ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች፣ በግል ባለሀብቶች እና በተቋማት የውስጥ ገቢ የተሰበሰበ ሀብት በስራ ላይ ውሏል።በመሆኑም በሶስት አመቱ ገቢ በመሰብሰብ በ2015 የትምህርት ዘመን ድርሻውን ወደ 17.28% ለማሳደግ ግብ ተይዞ በአማካይ 7.66%(44.36% ) ሀብት መመደቡን ያሳያል።

### 3.3.2. የጤና ልማት ዘርፍ አፈጻጸም

ጤናው የተጠበቀ የሰው ኃይል ልማት ወይም ሰብዓዊ ሀብት የጉልበት ምርታማነትን በማሳደግ ፈጣን ኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣትና ብሎም ልማትና ብልፅግናን ለማረጋገጥ ወሳኝ ሚና ይኖረዋል።በዘርፉ ቀጣይነት ያለው ህዝቡ በየደረጃው የሚጠቀምበት ልማትን ለማረጋገጥ ህዝቡ የጤናኤክስቴንሽን ፓኬጁን ሙሉ በሙሉ በመተግበር የራሱን ጤና ራሱ እንዲያመርት ማድረግ፣ህብረተሰቡ በአቅራቢያው የህክምና አገልግሎቶችን እንዲያገኝ የጤና ተቋማትን ማስፋፋት፣ደረጃቸውን በጠበቁና ብቁ ባለሙያዎች በተሟላላቸው ጤና ተቋማት ጥራቱን የጠበቀ የፈውስ ህክምናና የማገገም አገልግሎቶችን በተሟላ ሁኔታ ማቅረብ፣መሰረታዊ የጤና አገልግሎት አሀድን የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል፤ጤና ጣቢያና ጤና ኬላ ትስስር ማጠናከር፣ ምርጥ ተሞክሮዎችን በማስፋት በክልሉ ተቀራራቢ የጤና አገልገሎት አሰጣጥ እንዲኖር ማድረግ፣በተጠናከረ የበሽታ ቅኝት፣ዝግጁነት፣ምላሽ የህብረተሰብ ጤና ድንገተኛ አደጋዎችና ወረርሽኝን መቀነስ የክልሉን የመካከለኛ የጤና ባለሙያዎች ፍላጎት ለማሟላት የጤና ሳይንስ


ኮሌጆችን አቅም ማሳደግ፣የህብረተሰብ ጤና ምርምርና ልማት፣የቴክኖሎጂ ሽግግር ስርዓት 132 ማጠናከር፣ውስጣዊ አሰራራቸውንና አደረጃጀታቸውን ማሻሻል፣የጤናተቋማትን የውስጥ ገቢ በማሳደግ የጤናውን ዘርፍ የፋይናንስ አቅም ማጎልበት፣በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል የመረጃ አያያዝ፣አጠቃቀምና የሪፖርት ስርዓትን ማጠናከር፣ የተጀመረውን የጤና ልማት ሰራዊት ግንባታ ሂደት በማጠናከር በክልሉ ውስጥ የአመለካከትና የክህሎት መቀራረብና የመፈፀም አቅም እንዲፈጠር ማድረግ፣የግብዓት አቅርቦት ስርጭት አስተዳደርና አጠቃቀም ማሻሻል የሚሉት ይሆናሉ፡፡የጤናዉ ዘርፍ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ለማስቻል የ10 ዓመት ግቦች ተቀምጠው ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡

የእናቶች ጤና አገልግሎት ከመስጠት አንጻር የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን በ2012 50% ከነበረበት በ2015 ወደ 51.2% ለማሳደግ የታቀደ ቢሆንም የዳሰሳ ጥናት ያልተሰራ በመሆኑ አሁን ያለበትን የአፈጻጸም ደረጃ ማወቅ አልተቻለም፡፡ በመሆኑም የእናቶች የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት የእናቶች እና ህጻናት ሞትን ከመቀነስ አኳያ ፋይዳው ዘርፈ ብዙ በመሆኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የዳሰሳ ጥናቱ እንዲከናወን ማድረግ እና ክልሉ ያለበትን ደረጃ አውቆ በቀጣይ ቀሪ አመታት የተሻለ ተግባር በማቀድ እና ወደተግባር በማስገባት በልዩ ትኩረት ሊሰራ ይገባል፡፡ በሌላ በኩል የእናቶች የቅድመ ወሊድ (ANC4) ክትትል 4ጊዜ አገልግሎት ያገኛሉ ተብሎ በ2012 ዓ.ም 51% ከነበረበት በ2015 74% ለማድረስ ታቅዶ በሶስት አመቱ በአማካይ 73.3% የደረሰ ሲሆን በአስር ዓመቱ 77% ነዉ፡፡ መረጃው እንደሚያመለክተው የእናቶች የቅድመ ወሊድ(ANC4) ክትትል 4ጊዜ አገልግሎት አፈጻጸም ከመነሻ ዘመኑ ጋር ሲወዳደር በ22% እድገት ቢያሳይም በ3 ዓመት ከተቀመጠዉ ኢላማ አንጻር በ0.7% ዝቅ ያለ መሆኑን ያሳያል፡፡ በመሆኑም በቀሪ አመታት የእናቶችን እና ህጻናትን ሞት ለመቀነስ የቅድም ወሊድ ክትትል አገልግሎት ዋነኛ መሳሪያ በመሆኑ እና ከአለም አቀፍ ስምምነቱ አንጻር የተቋማት እና የባለሙያዎችን ስታንዳርድ በማሟላት ከሚመለከታቸው አካለት ጋር በልዩ ትኩረት በመስራት ግቡን ማሳካት ይጠበቃል፡፡




**ግራፍ 23፡- የቅድመ ወሊድ 4 ጊዜ ክትትል ያደረጉ እናቶች**

ከዚህ ባሻገር በጤና ተቋም በሰለጠነ ባለሙያ በመታገዝ ለእናቶች የወሊድ አገልግሎት ለመስጠት በ2012 ከነበረበት 56% በ2015 ወደ 67% ለማድረስ ታቅዶ በሶስት አመት በአማካይ 64% እናቶች አገልግሎቱን ያገኙ ሲሆን አፈጻጸሙም ከአስር ዓመቱ 67.3% ማድረስ ተችሏል፡፡ መረጃው እንደሚያመለክተው በሰለጠነ ባለሙያ የእናቶች የወሊድ አገልግሎት አሰጣጥ አፈጻጸም ከመነሻ ዘመኑ ጋር ሲወዳደር በ11% እድገት ያሣየ ቢሆንም እንዲሳካ ከታሰበው የ3 ዓመት ኢላማ አንጻር በ3% ዝቅ በማለቱ ኢላማዉን ማሳካት አልቻለም፡፡ ስለሆነም በቀሪ አመታት ከዚህ የበለጠ በመስራት ግቡን ለማሳካት የሰለጠነ ባለሙያ በስታንዳርዱ መሰረት 1፡5,000 በማሟላት የህጻናትንና የእናቶችን ሞት መቀነስ ከተቋሙ ይጠበቃል፡፡




ግራፍ 24 ፡-በሰለጠነ ባለሙያ የወሊድ አገልግሎት ያገኙ እናቶች

በተጨማሪ የድህረ ወሊድ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት መጠን በ2012 42% ከነበረበት በ2015 66% ለማድረስ ታቅዶ በሶስት አመቱ በአማካይ 80.8% የደረሰ ሲሆን ከአስር ዓመቱ ደግሞ 85% ደርሷል፡፡መረጃው እንደሚያመለክተው ከመነሻ እቅዱ በ38.8% እድገት በማከናወን ከታሰበው የ3 ዓመት ኢላማ አንጻር በ14.8% ከፍተኛ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ስለሆነም በቀሪ አመታት ይህን ውጤት ያስገኙ ተግባራትን ተሞክሮ በመቀመር እና በማስፋት የግቡን ቀጣይነት ማረጋገጥ ይጠበቃል፡፡አማካይ የመኖር ዕድሜ ጣሪያ ከ65.5 ወደ 67.6 አመት ለማሳደግ ታቅዶ በ2013 በተሰራ ጥናት አማካይ የመኖር ዕድሜ ጣሪያ 68.7 ዓመት መድረሱን ያሳያል፡፡

የህጻናት ጤና አገለግሎትን ስንመለከት በሶስት ዓመት መጨረሻ እድሜቸው ከ1 ዓመት በታች ያሉ ህጻናት ሞት ምጣኔን ከ58 ከ1000 ህፃናት ወደ 44 ከ1000 ህፃናት ለመቀነስ እቅድ የተያዘ ቢሆንም ከ2019 እ.ኤ.አ በኋላ የዳሰሳ ጥናት ያልተሰራ በመሆኑ አሁን ያለበትን የአፈጻጸም ደረጃ ማወቅ አልተቻለም፡፡በመሆኑም በህይወት ከተወለዱ ህጻናት ሞትን ከመቀነስ አኳያ ፋይዳው ዘርፈ ብዙ በመሆኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የዳሰሳ ጥናቱ እንዲከናወን በማድረግ ክልሉ ያለበትን ደረጃ አውቆ በቀጣይ ቀሪ አመታት የተሻለ ተግባር በማቀድ እና ወደ ተግባር በማስገባት በልዩ ትኩረት ሊሰራ ይገባል፡፡

በሌላ በኩል የመጀመሪያ ዙር የኩፍኝ በሽታ መከላከያ ክትባት ያገኙ ህጻናት ሽፋን በመቶኛ በ2012 87% ከነበረበት ወደ በ2015 91% ከፍ ለማድረግ ታቅዶ 95.4% ማድረስ ተችሏል፡፡ ከአስር ዓመቱ 96.4% ነው፡፡ መረጃው እንደሚያመለክተው የመጀመሪያ ዙር የኩፍኝ በሽታ መከላከያ ክትባት ያገኙ ህጻናት አፈጻጸም ከመነሻ ዘመኑ ጋር ሲወዳደር በ8.4% እድገት

በማስመዝገብ ከ3 ዓመት ኢላማ አንጻር በ4.4% ከፍ ያለ መሆኑን ያመለክታል።በተመሳሳይ ከሁለት ዓመት በታች የእድገት ክትትል የተደረገላቸው ህጻናት ሽፋን በመቶኛ በ2012 ከነበረበት 40% በ2015 ወደ 55% ከፍ ለማድረግ ታቅዶ በ2015 66 % ማድረስ ተችሏል። መረጃው እንደሚያመለክተው ከ2 ዓመት በታች የእድገት ክትትል የተደረገላቸው ህጻናት አፈጻጸም ከመነሻ ዘመኑ ጋር ሲወዳደር በ26% እድገት ያስመዘገበ ሲሆን እንዲሳካ ከታሰበው የ3 ዓመት ኢላማ አንጻር በ11% ከፍ ያለ መሆኑን ቢያሳይም የአስር ዓመት ግቡን ለማሳካት ከዚህ የበለጠ መስራት ይጠበቃል።

በሌላ በኩል ሙሉ በሙሉ የመደበኛ ክትባት ያገኙ ህጻናት ሽፋን በመቶኛ በ2012 ከነበረበት 87% በ2015 ወደ92% ከፍ ለማድረግ ታቅዶ በ2015ዓ.ም 94% ሲሆን ከአስር አመቱ 99% ነው።መረጃው እንደሚያመለክተው ሙሉ በሙሉ የመደበኛ ክትባት ያገኙ ህጻናት አፈጻጸም ከመነሻ ዘመኑ ጋር ሲወዳደር በ7% እድገት ያሳየ ሲሆን እንዲሳካ ከታሰበው የ3 ዓመት ኢላማ አንጻር በ2% ጭማሪ ቢያሳይም የ10 ዓመት ግቡን ለማሳካት የመደበኛ ክትባት ሽፋንን ትኩረት መስጠት ይገባል።

ሶስተኛ ዙር የፔንታቫለንት ክትባት ህጻናት ሽፋን በመቶኛ በ2012 ከነበረበት 91% በ2015 ወደ 95% ከፍ ለማድረግ ታቅዶ 2015 100% የደረሰ ሲሆን ከአስር ዓመቱ 100% መሆኑን ሲያመለክት አፈጻጸሙም ከመነሻ እቅዱ ጋር ሲወዳደር በ9% እድገት ያሳየ ሲሆን እንዲሳካ ከታሰበው የ3 ዓመት ኢላማ አንጻር በ5% ከፍ ያለ መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ በቀሪ አመታት የተጀመረዉን ተግባር ማስቀጠል ይገባል።

ከእርግዝና እና ወሊድ ጋር በተያያዘ የእናቶች ሞት ምጣኔ ከ 401 ከ100,000 በህይወት ከተወለዱ ህፃናት ወደ 326 ከ100,000 ለመቀነስ ታቅዶ በ2020 እ.ኤ.አ በተሰራ ጥናት 267 ከ100,000 በህይወት ከተወለዱ ህፃናት መቀነስ ቢቻልም በአሁኑ ስዓት የዳሰሳ ጥናት ያልተሰራ በመሆኑ አሁን ያለበትን የአፈጻጸም ደረጃ ማወቅ አልተቻለም። በመሆኑም የህጻናት ጤና አገልግሎት የእናቶች እና ህጻናት ሞትን ከመቀነስ አኳያ ፋይዳው ዘርፈ ብዙ በመሆኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የዳሰሳ ጥናቱ እንዲከናወን በማድረግ ክልሉ ያለበትን ደረጃ አውቆ በቀጣይ ቀሪ አመታት የተሻለ ተግባር በማቀድ እና ወደ ተግባር በማስገባት በልዩ ትኩረት ሊሰራ ይገባል።

በተመሳሳይ እድሜቸው ከ5 ዓመት በታች ያሉ ህጻናት ሞት ምጣኔ ከ69 ከ1000 በህይወት ከተወለዱ ህፃናት ወደ 53 ከ1000 በህይወት ከተወለዱ ህፃናት ለመቀነስ ታቅዶ አሁን ያለንበትን ለማወቅ የተሰራ የዳሰሳ ጥናት ባለመኖሩ በዚህ ዙሪያ ያለበትን ደረጃ ማወቅ አልተቻለም፡፡ በተጨማሪም የጨቅላ ህጻናት ሞት ምጣኔ ከ46 ከ1000 በህይወት ከተወለዱ ህፃናት ወደ 31 ከ1000 ህፃናት ለመቀነስ ታቅዶ አሁን ያለንበትን ለማወቅ የተሰራ የዳሰሳ ጥናት ባለመኖሩ አሁን ያለበትን የአፈጻጸም ደረጃ ማወቅ አልተቻለም፡፡ በመሆኑም የጨቅላ ህጻናት ሞትን መቀነስ ትዉልድን የመታደግ ተግባር በመሆኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የዳሰሳ ጥናቱ እንዲከናወን በማድረግ እና ክልሉ ያለበትን ደረጃ አውቆ በቀጣይ ቀሪ አመታት የተሻለ ተግባር በማቀድ እና ወደ ተግባር በማስገባት በልዩ ትኩረት ሊሰራ ይገባል፡፡

የወጣቶች እና አፍላ ወጣቶች ጤና አገልግሎትን በሚመለከት በአፍላ ወጣቶች የሚከሰተውን እርግዝና በ2012 ከነበረበት 16% በ2015 ወደ 11% ለማዉረድ በታቀደዉ መሰረት በ2015 9.5% ዝቅ ማድረግ የተቻለ ሲሆን በአስር ዓመቱ 59% ሆኗል፡፡ መረጃው እንደሚያመለክተው በአፍላ ወጣቶች የሚከሰተውን እርግዝና አፈጻጸም ከመነሻ ዘመኑ ጋር ሲወዳደር በ5% ዝቅ ለማድረግ የታቀደ ሲሆን እንዲሳካ ከታሰበው የ3 ዓመት ኢላማ አንጻር በ1.5% መቀነስ ተችሏል፡፡በመሆኑም በቀሪ አመታት ኢላማውን ለማሳካት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ከዚህ የበለጠ በመስራት ግቡን ማሳካት ይጠበቃል፡፡

በተመሳሳይ የተላላፊ በሽታዎችን መከላከል እና መቆጣጠር፡ የወባ በሽታ መከላከልና መቆጣጠር በተመለከተ የወባ በሽታ በባለፈው ሶስት ዓመት ጋር ሲነፃፀር በእጅጉ የጨመረ ሲሆን በወባ አዲስ የሚያዙ ሰዎች ምጣኔ(ከ1,000 ተጋላጭ ሰዎች መካከል) በ2012 ከነበረበት 18 በ2015 ወደ 14 ለመቀነስ ታቅዶ በ2015 ወደ 43 ማደጉን ያሳያል ፡፡ የወባ በሽታ መከላከልና መቆጣጠር አፈጻጸሙ ከመነሻ ዘመኑ አፈጻጸም ጋር ሲወዳደር በ25 ጭማሪ ቢያሳይም እንዲሳካ ከታሰበው የ3 ዓመት ኢላማ አንጻር መቀነሱን ያመለክታል፡፡ ስለሆነም በቀሪ አመታት በአዲስ ስትራቴጅ በማዘጋጀት እና የቅድመ መከላከል ስራዉን በማጠናከር የወባበሽታንመከላከል ካልተቻለሰዎች በወባ መያዝ ስርጭቱን መቀነስሲገባው በከፍተኛ ቁጥር የጨመረ ስለሆነ በወባ ከመያዝ በፊት እና ከተያዙ በኋላ መቆጣጠር ክልሉ ያለበትን ደረጃ አውቆ ግቡን ለማሳካት በልዩ ትኩረት መስራት ይገባል፡፡

ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ለመከላከል እና ለመቆጣጠር በአዋቂዎች የሚከሰት የደም ግፊት በሽታን የመቆጣጠር ሽፋን በ2012 ከነበረበት 26% በ2015 ወደ 46% ከፍ ለማድረግ ታቅዶ

በ2015 88.7% የደረሰ ሲሆን ከአስር ዓመቱ 88.7% ነው፡፡ መረጃው እንደሚያመለክተው የደም ግፊት በሽታን የመቆጣጠር አፈጻጸም ከመነሻ ዘመኑ ጋር ሲወዳደር በ62.7% እድገት የተከናወነ ሲሆን እንዲሳካ ከታሰበው የ3 ዓመት ኢላማ አንጻር በ42.7% ከፍተኛ ስለሆነ በቀሪ አመታት ኢላማውን ለማሳካት የተከናወኑ ተግባራትን ወደ ኋላ እንዳይመለስ በመስራት ግቡን ማሳካት ይጠበቃል፡፡

በአዋቂዎች የሚከሰት የስኳር በሽታን የመቆጣጠር ሽፋን 24% ወደ 50% ከፍ ለማድረግ ታቅዶ በ2015 85.6% የደረሰ ሲሆን ከአስር ዓመቱ 85.6% ነው፡፡ የስኳር በሽታን የመቆጣጠር አፈጻጸም ከመነሻ ዘመኑ ጋር ሲወዳደር በ61.6% እድገት የተከናወነ ሲሆን እንዲሳካ ከታሰበው የ3 ዓመት ኢላማ አንጻር በ35.6% ከፍተኛ ስለሆነ በቀሪ አመታት ኢላማውን ለማሳካት የተከናወኑ ተግባራትን ከዚህ የበለጠ በመስራት ግቡን ማሳካት ይጠበቃል፡፡

የኤችአይቪ ኤድስ በሽታን መከላከል እና መቆጣጠር በተመለከተ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በሀገራችንና በክልላችን እያደረሰ ያለው የጤና፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ከፍተኛ ነው፡፡ ስለሆነም HIV ከእናት ወደልጅ እንዳይተላለፍ ፀረ HIV ህክምና እና መድሃኒት የሚወስዱ እናቶች ሽፋን በ2012 ከነበረበት 71% በ2015 ወደ 95% ከፍ ለማድረግ ታቅዶ በ2015ዓ.ም 68.4% የደረሰ ሲሆን ከአስር ዓመቱ 68.4% ሲሆን ከመነሻ ዘመኑ ጋር ሲወዳደር በ24% በልጫ ያሳየ እና እንዲሳካ ከታሰበው የ3 ዓመት ኢላማ አንጻር በ26.6% ዝቅ ማለቱን ያመለክታል፡፡በመሆኑም ክልሉ ያለበትን ዝቅተኛ አፈጻጸም በመገንዘብ በቀሪ አመታት HIV ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ ከአጋር አካላት ጋር በጋራ በመሆን በልዩ ትኩረት ከዚህ የበለጠ በመስራት ግቡን ማሳካት ይጠበቃል፡፡

የኤችአይቪ ምርመራ ውጤታቸውን ያወቁ ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝባቸው ሰዎች ምጣኔ በ2012 ከነበረበት 69% በ2015 ወደ 95% ከፍ ለማድረግ ታቅዶ በ2015 90% የደረሰ ሲደርስ ከአስር ዓመቱ 94.7% እንዲሁም ከመነሻ ዘመኑ ጋር ሲወዳደር በ21% ጭማሪ እና እንዲሳካ ከታሰበው የ3 ዓመት ኢላማ አንጻር በ5% ዝቅ ማለቱን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም በቀሪ አመታት ከዚህ የበለጠ በመስራት ግቡን ማሳካት ይጠበቃል፡፡ የHIV ውጤታቸውን ካወቁት መካከል የፀረ HIV መድሀኒት ህክምና ሽፋን በ2012 ከነበረበት 68% በ2015 ወደ 95% ከፍ ለማድረግ ታቅዶ በ2015 99% ማድረስ ተችሏል፡፡መረጃው እንደሚያመለክተው በHIV ውጤታቸውን ካወቁት መካከል የፀረ HIV መድሀኒት ህክምና አፈጻጸም ከመነሻ ዘመኑ ጋር ሲወዳደር በ31% ጭማሪ ያሳየ ሲሆን እንዲሳካ ከታሰበው የ3 ዓመት ኢላማ አንጻር ሲታይ

በ4% ብልጫ በማስመዝገብ የተሻለ ተግባር የተፈፀመ እንደሆነ ቢያሳይም በአሁኑ ሰዓት የሚስተዋለዉን የመድሀኒት አቅርቦት እጥረት በመፍታት እና ለሁሉም ተደራሽ በማድረግ ተግባሩ ወደ ኋላ እንዳይመለስ በትኩረት መስራት ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም የፀረ HIV መድሀኒት ከሚወስዱት ውስጥ በደማቸው ያለው HIV ቫይረስ መጠን በሚሊ ሊትርከ 1,000 ኮፒ በታች የሆኑት(viral suppression) ሽፋን በ2012 ከነበረበት 47% በ2015 ወደ 95% ከፍ ለማድረግ ታቅዶ በ2015 ዓ.ም 95% ማድረስ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም ከአስር ዓመቱ 95% ፣ ከመነሻ ዘመኑ ጋር ሲወዳደር በ48% እድገት በማስመዝገበ በ3 ዓመት ኢላማ የተቀመጠዉን 100% ያሳካ መሆኑን ያሣያል፡፡


የቲቢ በሽታን መከላከል እና መቆጣጠርን በተመለከተ በእቅድ ዘመኑ የቲቢ በሽታ ስርጭት በክልላችን በስፋት የሚገኝ ሲሆን የሁሉም ዓይነት ቲቢ ተጠርጣሪ ልየታ በስትራቴጂያዊ ዘመኑ ከሚጠበቀው የሁሉም ዓይነት የቲቪ በሽታዎች ልየታ በመቶኛ 56% ወደ 75% ከፍ ለማድረግ ታቅዶ በ2015 75.3% የተቻለ ሲሆን ከአስር ዓመቱ 75.3% ነው ፡፡መረጃው እንደሚያመለክተው የቲቢ በሽታ ስርጭት አፈጻጸም ከመነሻ ዘመኑ ጋር ሲወዳደር በ19.3% እድገት የተከናወነ ሲሆን እንዲሳካ ከታሰበው የ3 ዓመት ኢላማ አንጻር በ0.3% ከፍ ያለ መሆኑን ያመለክታል፡፡ የቲቪ ህክምና ሙሉ በሙሉ ያጠናቀቁ የቲቪ ህሙማን ሽፋን በ2012 ከነበረበት 94% በ2015 ወደ 95% ከፍ ለማድረግ ታቅዶ በ2015 94% የደረሰ ሲሆን ከአስር ዓመቱ 94% እንዲሁም እንዲሳካ ከታሰበው የ3 ዓመት ኢላማ አንጻር የተሻለ አፈጻጸም ስለሆነ ተቋሙ ወደኋላ እንዳይመለስ በልዩ ትኩረት በመስራት ግቡን ማሳካት ይጠበቃል፡፡

መድሃኒት የተላመደ ቲቪ ልየታ በ2012 38% በ2015 ወደ 69.8% ከፍ ለማድረግ ታቅዶ በ2015 88% የደረሰ ሲሆን ከአስር ዓመቱ 88% የደረሰ ሲሆን ከመነሻ ዘመኑ ጋር ሲወዳደር በ50% እድገት የተከናወነ እና እንዲሳካ ከታሰበው የ3 ዓመት ኢላማ አንጻር በ18.2% ከፍ ያለ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ስለሆነም በቀሪ አመታት በ10 ዓመት የተቀመጠዉን ኢላማ ለማሳካት የተከናወኑ ተግባራትን በማስቀጠል ግቡን ማሳካት ይጠበቃል፡፡

የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የሃይጅን እና የአካባቢ ጤና አጠባበቅን በማሻሻል ረገድ (Improve hygiene and sanitation) በአካባቢ ንጽሕና አጠባበቅ የሞዴል ቤተሰቦች ሽፋን በ2012 ከነበረበት 38% በ2015 ወደ 85% ከፍ ለማድረግ ታቅዶ በሦስት ዓመቱ አማካይ 72% የደረሰ ሲሆን ከአስር ዓመቱ ደግሞ 72% መሆኑን ያሳያል፡፡መረጃው እንደሚያመለክተው በአካባቢ ንጽሕና አጠባበቅ የሞዴል ቤተሰቦች አፈጻጸም ከመነሻ ዘመኑ ጋር

ሲወዳደር በ34% እድገት ያስመዘገበ ቢሆንም በሦስት ዓመት እቅዱ እንዲሳካ ከታሰበው ኢላማ አንጻር በ13% ቅናሽ ያሳየ በመሆኑ በቀሪ አመታት በንጽህና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎች ለመካለከል በልዩ ትኩረት ማከናወን ይጠበቃል፡፡


ሜዳ ላይ ከመጸዳዳት ነጻ የሆኑ ቀበሌዎች ሽፋን በ2012 ከነበረበት 85% በ2015 ወደ 50% ከፍ ለማድረግ ታቅዶ በ2015 15% የደረሰ ሲሆን ከአስር ዓመቱ 17% ነው፡፡ መረጃው እንደሚያመለክተው ሜዳ ላይ ከመጸዳዳት ነጻ የሆኑ ቀበሌዎች አፈጻጸም ከመነሻ ዘመኑ ጋር ሲወዳደር በ70% ዝቅ ያለ አፈጻጸም ሲያሳይ እንዲሳካ ከታሰበው የ3 ዓመት ኢላማ አንጻር በ35% ዝቅተኛ ስለሆነ በቀሪ አመታት በልዩ ትኩረት አቅዶ በንጽህና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎችን ለመካለከል፣የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጁን ለማሳካት እና ንጹህ የሆነ አካባቢ ለመፍጠር በሙሉ አቅም በመስራት ግቡን ማሳካት ይጠበቃል፡፡




**ግራፍ 25 ፡- ሜዳ ላይ ከመጸዳዳት ነጻ የሆነ ቀበሌ ሽፋን**

ጤና መድህንን በማስፋፋት የማህበረሰብ አቀፍ ጤናን ከማሻሻል አንጻር በሀገራችንም መደበኛ ባልሆነው የኢኮኖሚ ዘርፍ ለተሰማሩ የህብረተሰብ ክፍሎች የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ሥርዓት መሰረት በሁሉም ዞን በሚገኙ ወረዳዎች እና የከተማ አስተዳዳሮች የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ሥርዓት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም በ2012 ከነበረበት 62% በ2015 ወደ 96% ከፍ ለማድረግ ታቅዶ በ2015 93% የደረሰ ሲሆን ከአስር ዓመቱ ደግሞ 93% እና ከመነሻ ዘመኑ ጋር ሲወዳደር 31% እድገት ያስመዘገበ ቢሆንም በሦስት ዓመት እቅዱ

እንዲሳካ ከታሰበው ኢላማ አንጻር በ3% ዝቅ ያለ መሆኑን ያሳያል፤በመሆኑም በጤና መድህን ዙሪያ ያለውን የአመለካከት እና የመድሃኒት አቅርቦት ችግር በመፍታት በክልሉ ተጠቃሚ መሆን ያለበትን የህብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ በማድረግ በአስር አመት የተቀመጠውን ኢላማ ለማሳካት በትኩረት የሚሰራ ተግባር ሊሆን ይገባል።




**ግራፍ 26 ፡- ማህበረብ አቀፍ የጤና መድህን አባል ማፍራት ስራ አፈጻጸም**

በአጠቃላይ በእናቶች ጤናአገልግሎት የአፈፃፀም አመልካቾች የሶስት ዓመቱ እቅድ ሲታቀድ መነሻ ከተደረገዉ አፈጻጸም አንጻር ሲታይ ለዉጥ ተመዝግቧል።ነገር ግን መድረስ ከሚጠበቅበት አንጻር ሲታይ ደግሞ በአንዳንድ መለኪያዎች አፈጻጸሙ ዝቅተኛ ስለሆነ በተለይም የቅድመ መወሊድ አገልግሎት (ANC4) እና በሰለጠነ ባለሙያ በመታገዝ የወሊድ አገልግሎት ያገኙ እናቶች ሽፋን በ3 ዓመት ይደረሳል ተብሎ ከታቀደው ኢላማ አንጻር አፈፃፀሙ ስለቀነሰ ለዘርፉ ሊሰጠው ከሚገባው ትኩረት አንፃር ሊመጥን የሚችል የክትትልና ድጋፍ ስርአት መዘርጋት፣የተቋማት እና የባለሙያዎችን ስታንዳርድ በማሟላት በቀሪ አመታት በልዩ ትኩረት ዝቅተኛ አፈጻጸም የታየባቸውን ተግባራት እቅድ በማቀድ እና አፈፃፀሙን ለማሻሻል ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። በተመሳሳይ የህጻናት ጤና አገለግሎት የአፈፃፀም አመልካቾች የሶስት ዓመቱ አፈፃፀም የተሻለ መሆኑን የሚያሳይ ስለሆነ በቀጣይ በ10 ዓመት የተቀመጠዉን ኢላማ ለማሳካት የክትባት አገለግሎት ተደራሽነትን በማሳደግተግባሩን አጠናክሮ መቀጠል ይገባዋል።

በመጨረሻ የመሰረታዊ ጤና አገለግሎት ሽፋኑን ለማሳደግ የተደረጉ ጥረቶች ያሉ ቢሆንም ክልሉ ካለበት የጤና ችግር እና መድረስ ከሚገባን አንፃር ሲታይ ገና ረጅም ርቀት መጓዝ ይጠበቃል። በመሆኑም በግንባታ ወቅት የሚታይ የጥራት መጓደል፤ የግንባታዎችመጓተት፤

በዝተኛ ዋጋ ጫረታዉን ማሸነፍ፤ የተቋራጮች የአቅም ዉስንነት እንዲሁም የአማካሪ ሙያተኞች ክትትል ማነስ የጤና ተቋማት ግንባታዎች በሚፈለገዉ ወቅት እንዳይጠናቀቁ ከሚያደርጉ ዋና ዋና ምክንያቶች በመሆናቸው በቀሪ ዓመታት ችግሩን በመቅረፍ ስታንዳርዱን ለማሟላት መስራት ይጠበቃል።

### 3.3.3. የሴቶች፣ህጻናት እና ማህበራዊ ልማት አፈጻጸም

የሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥን በሚመለከት ሴቶች በኢኮኖሚው ዘርፍ ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን በሚመለከት ሴቶች በኢኮኖሚው ዘርፍ ፍትሃዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ በአስር አመቱ የልማት እቅዳችን ሴቶች በህብረት ስራ ማህበራት መደራጀታቸው የገቢ አቅማቸውን ለማሳደግ የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ በመሆኑ ተሳትፎና ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ የተለየ ትኩረት ሰጥቶ ለመስራት ታቅዷል።በዚህም መሰረት በባለፉት ሶስት የዕቅድ ዘመን ለ3,271,594 ሴቶች በህብረት ስራ ማህበራት ጠቀሜታና ፋይዳ ዙሪያ ግንዛቤ በመፍጠር 307,664 ሴቶች በተለያዩ የህብረት ሥራ ማህበራት አባል እንዲሆኑ ተደርጓል።የሴቶች ድርሻም በ2012 ከነበረበት 19.2% በ2015 ወደ 29% ለማሳደግ ታቅዶ 34% ደርሷል። በመሆኑም በ10 ዓመቱ የልማት ዕቅዳችን 754,492 (247,219 እማወራ 507,273 ባለትዳር) ሴቶች የሁለተኛ ደረጃ የገጠር መሬት ባለቤት እንዲሆኑ ታቅዶ 801,267( 272,294 (110.14%) እማወራ እና 528,973 (104.2%)ባለትዳር) ሴቶች የሁለተኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እንዲያገኙ የተደረገ ሲሆን መረጃው እንደሚያመለክተው ሴቶች በኢኮኖሚው ዘርፍ ፍትሃዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የስራ አጥነት ችግር በመቅረፍ ሰፊ የሥራ ዕድል ለመፍጠር በ10 ዓመቱ የልማት እቅድ አፈጻጸም ከመነሻ ዘመኑ ጋር ሲወዳደር በ14.8% እድገት የተከናወነ ሲሆን እንዲሳካ ከታሰበው የ3 ዓመት ኢላማ አንጻር በ5% ከፍ ያለ ሲሆን በሌላ በኩል ሴቶች የሁለተኛ ደረጃ የገጠር መሬት ባለቤት እንዲሆኑ ከታቀደው አንጻር ለእማወራ(104.2) እና ለባለትዳር(110.14) አፈጻጸም ደርሷል።በመሆኑም በቀሪ አመታት ኢላማውን ለማሳካት የተገኘው አፈጻጸም ወደ ኋላ እንዳይመለስ የተከናወኑ ተግባራትን ከዚህ የበለጠ በመስራት ግቡን ማሳካት ይጠበቃል።

በተመሳሳይ ሴቶች በኢኮኖሚው ዘርፍ ፍትሃዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የቁጠባ እና የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ ሲሆን በዚህም መሰረት በባለፉት ሶስት ዓመታት 3,263,045 ሴቶች የብደር አገልግሎት ተጠቃሚ በማድረግ የሴቶች የብድር ተጠቃሚነት ድርሻ በ2012 73 % ከነበረበት በ2015 ወደ 76 % ለማድረስ የታቀደ ሲሆን በዚህም 2,363,610

ሴቶች የብደር አገልግሎት ያገኙ ሲሆን በ2014 የሴቶች የብድር ተጠቃሚነት ድርሻ 62% ደርሷል፡፡ ይህም በ2015 የሴቶች የብደር ተጠቃሚነት ይደርስበታል ተብሎ ከታቀደው 76% ወደኋላ የተመለሰ መሆኑን ያሳያል፡፡ መረጃው እንደሚያመለክተው ሴቶችን  የቁጠባ እና የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ አፈጻጸም ከመነሻ ዘመኑ ጋር ሲወዳደር በ 3% እድገት የተከናወነ ቢሆንም እንዲሳካ ከታሰበው የ2 ዓመት አፈጻጸም  አንጻር በ14%  ወደ ኋላ የተመለሰ ስለሆነ በቀሪ አመታት ኢላማውን ለማሳካት በልዩ ትኩረት  ከዚህ የበለጠ በመስራት የሴቶችን የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ በማድረግ ግቡን ማሳካት ይጠበቃል፡፡ለዚህም ምክንያቶች በክልላችን በነበረው ጦርነት ምክንያት ጥቂት የማይባሉ የአበዳሪ ድርጅቶች መውደማቸው፣በጦርነቱ ምክንያት አብዛኛው ሴቶች አከባቢያቸውን ለቅቀው በመሰደዳቸው እና በCOVID-19 አብዛኛው የንግድ እንቅስቃሴ የተገደበ በመሆኑ ሴቶች የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ያደረጉ ዋናዋና ምክንያቶች ናቸው፡፡

በተጨማሪም የሴቶችን የቁጠባ ባህል ለማዳበር በባለፉት ሶስት ዓመታት 3,601,718 ሴቶች ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል፡፡ ግንዛቤ ከተፈጠረላቸው ውስጥም 3,097,099 ሴቶች በቁጠባ አገልግሎት ተጠቃሚ በማድረግ በ2012 የቁጠባ መጠኑ ከነበረበት ብር 408.63 ሚሊዩን በ2015 መጨረሻ ብር 1,266,759,000 ለማድረስ ታቅዶ 732,933 ሴቶች ብር 1,497,453,638 እንዲቆጥቡ ሆኗል፡፡ይህም ከቆጣቢዎች አኳያ 24% እና በብር 100% የደረሰ ሲሆን መረጃው እንደሚያመለክተው የአንድ መስኮት አገልግሎት የሚሰጡ ማዕከላት አፈጻጸም ከመነሻ ዘመኑ ጋር ሲወዳደር በ8  እድገት የተከናወነ ሲሆን እንዲሳካ ከታሰበው የ3 ዓመት ኢላማ አንጻር በ9 ከፍ ያለ ቢሆንም በቂ ባለመሆኑ  በቀሪ አመታት በሌሎች አካባቢዎች ማዕከላትን በማስፋት ኢላማውን ለማሳካት በልዩ ትኩረት ተደራሽ ማድረግ ይጠበቃል፡፡

በሌላ በኩል ፆታዊ ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች የስነልቦና፣የአእምሮ ጤና፣የህክምና አገልግሎት የሚያገኙባቸው የአንድ መስኮት አገልግሎት የሚሰጡ ማዕከላት(one stop service) በ2012 ከነበሩበት 2 ማዕከላት በ2015 ወደ 10 ለማሳደግ ታቅዶ ወደ 19 ማድረስ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በኢኮኖሚው መስክ የተመዘገቡ ስኬቶች እንደተጠበቁ ሆነው ማነቆ ሆነው ከሚታዩ ተግዳሮቶች መካከል በዋነኛነት ከሚጠቀሱት መካከል ለሴቶች የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት በሚፈለገው መልኩ ተደራሽ አለመሆን፣ በህብረት ስራ ማህበራት በአባልነት እና በአመራርነት ያላቸው ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆን፣የሴቶች የስራ አጥነት ችግር ከመቅረፍ አኳያ በሚፈለገው ደረጃ የደረሰ አለመሆኑ፣የሴቶችን ጉልበት እና ጊዜን የሚቆጥቡ ቴክኖሎጂዎች

አቅርቦት ተደራሽ፣ ምቹና ዋጋቸው ተመጣጣኝ አለመሆን፤ ሴቶች የሚያመረቱባቸው እና የመሸጫ ቦታዎች አለመስፋፋት፤ የገበያ ትስስር ዝቅተኛ መሆን እንዲሁም ሴቶች በኢኮኖሚው መስክ ያላቸው ተጠቃሚነት ለማሳደግ የሚደረገው ድጋፍ እና ክትትል አነስተኛ መሆን በየደረጃው የተጠናከረ የመረጃ ስርዓት አለመኖር የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ በመሆኑም በቀሪ ዓመታት እነዚህን ችግሮች በልዩ ትኩረት አቅዶ መፈጸም ከቢሮው ይጠበቃል፡፡

የሴቶች **ማህበራዊ** ተጠቃሚነትን ከማሳደግ አንጻር መንግስት በህብረተሰቡ ዉስጥ የቆየዉን የጠበቀ እርስ በእርስ የመደጋገፍ ባህልን መልካም አጋጣሚ በመጠቀም በህዝቡ አቅም ድጋፍ የሚፈልጉ ለችግር ጋላጭ የሆኑትን የህብረተሰብ ክፍሎች ለመንከባከብ እንዲቻል የማህበረሰብ ድጋፍ እና እንክብካቤ ጥምረት በህግ የተደገፈ የህብረተሰብ ተቋም ሆኖ በክልሉ በሚገኙ በሁሉም ቀበሌዎች ለማቋቋም ጥረት ተደርጓል፡፡ በመሆኑም 2012 ከነበረበት 3,718 በ2015 ወደ 3,965 ቀበሌዎች የማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍ እና እንክብካቤ ጥምረቶች በማቋቋም የማህበረሰብ አባላትን አባል ማድረግ ከነበረበት ከነበረበት 10,414,668 ወደ 11,355,756 በማሳደግ የሀብት ማሰባሰቡ ስራ ከነበረበት ብር 342,945,181 ወደ ብር 635,737,509 ማሳደግ የተቻለ ሲሆን በባለፉት ሶስት ዓመታት 577,985( ወንድ 276,349 ሴት 301,636) ለችግር ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ አፈጻጸሙም ከ3 ዓመት ኢላማ አንጻር በ10,777,771 ዝቅ ያለ ስለሆነ የማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍ እና እንክብካቤ ጥምረቶች ለችግር ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ እንዲያገኙ ለማድረግ በቀሪ አመታት በልዩ ትኩረት በማቀድ ልዩልዩ ገቢዎችን በማሰባሰብ ተደራሽ ማድረግ ይጠበቃል፡፡

የሴቶች **ፖለቲካዊ** ተሳትፎን ማጎልበትን በተመለከተ በ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ ውስጥ ይፈጸማል ተብሎ ከታቀደው 3,000 ሴቶች ለአመራርነት ብቁ ግብ ከማሳካት አንጻር በሶስት አመቱ 4,092 ሴት አመራሮች በአመራር ጥበብ(Transformational leadership) የአቅም ግንባታ ስልጠና ያገኙ ሲሆን በተጨማሪም 205 ሴት አመራሮች እና በ2ኛ ዲግሪ 75 ሴት አመራሮች በመጀመሪያ ዲግሪ በአጠቃላይ 4372 ሴቶች አቅማቸውን የመገንባት ስራ ተሰርቷል፡ ፡ በመሆኑም በ2015 መጨረሻ በየደረጃው 3,097 ሴቶችን ለአመራርነት ብቁ የማድረግ ስራ በመስራት አፈጻጸሙም ከሶስት አመቱም ይሁን ከ10 አመቱ ከ100% በላይ መከናወኑን ያመለክታል፡፡

ሆኖም በአስፈጻሚዉ አካል የአመራር ሰጭነት ቦታ ላይ በክልል በ2012 ከነበረበት 20.2 በመቶ በ2015 ወደ 30 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ 17.67 በመቶ ብቻ ሲከናወን ከመነሻ አመቱም ይሁን ይደረስበታል ተብሎ ከታሰበው አንጻር በእጅጉ ዝቅ ብሎ መከናወኑን ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ የሴቶች የትምህርት ተሳትፎ ማደጉ ሴቶችን ወደ አመራር ሰጭነት ለማምጣት የሚያስችል ሰፊ የአመራር ቋት ለመፍጠር አስችሏል፣ አብዛኛው የክልላችን ሴቶች በመደራጀታቸዉና ወደ ተግባር መግባታቸዉ በክልሉ ለሚካሄደዉ የልማትና የዴሞክራሳዊ ስርዓት ግንባታ የሚያደረጉትን አስተዋፅኦ የጎላ ከመሆኑም በላይ ከጓዳ የመዉጣትና ለመብታቸዉና ጥቅሞቻቸዉ የመታገል ፍላጎታቸዉን አሳድጎታል፡፡ በተለይም በክልሉ ሰላም እንዲሰፈን የሚያደርጉት ሚናም በአርዓያነት የሚጠቀስ ነው፡፡

ይሁን እንጂ የሴቶችን የውሳኔ ሰጪነት ሚና በማሳደግ ከቤተሰብ ጀምሮ በየደረጃው በሚገኙ መንግስታዊ፣ መንግስታዊ ያልሆኑና የግል ተቋማት ወደ አመራርነት እንዲመጡ በማድረግ ረገድ፣ ሴቶች ለራሳቸው የሚሰጡት ግምትና በራስ የመተማመን ብቃታቸው በሚፈለገው ደረጃ አለመድረስ፣ የወንዶች የበላይነት አስተሳሰብ፣ ህብረተሰቡ በሴቶች ላይ ያለው የተዛባ አመለካከት፣ በሴቶች ውሳኔ ሰጭነት ዙሪያ በየደረጃው ያለው አመራር ቁርጠኝነት የሚፈለገውን ያህል አለመሆን እንዲሁም በአመራር ላይ ያሉ ሴቶች ተተኪዎችን በማፍራት ረገድ የሚጠበቅባቸውን ሚና አለመወጣት የተስተዋሉ ዋና ዋና ችግሮች ናቸው፡፡

**የህጻናት** ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ማጠናከርን በሚመለከት መንግስት የህጻናትን ችግሮችን መቅረፍ እንዲቻል የተለያዩ የድጋፍና እንክብካቤ አማራጭ ፕሮግራሞች በማዘጋጀት በህፃናት ድጋፍና እንክብካቤ አማራጮች ላይ በባለፉት ሶስት ዓመታት ለ1,234,042 (ወንድ.626,754 ሴት.607,288) ለሚሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በህፃናት ድጋፍና እንክብካቤ አማራጮች ዙሪያ ግንዛቤ መስጠት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 3,398( ሴት2,238) ቤተሰቦች በፎስተር ወይም በአደራ ቤተሰብ እንዲሰለጥኑ በማድረግ ለሀገር ውስጥ ጉዲፌቻ እና ለአደራ ቤተሰብ ዝግጁ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ከህፃናት ጥበቃና ደህንነት ጋር የተያያዙ 3 የአሰራር ማዕቀፎችን ማለትም የአእምሮአዊና ስነ-ልቦናዊ ድጋፍ አሰጣጥ የማሰልጠኛ ጋይድላይን፣ በህጻናት ጥበቃ ዙሪያ ለማህበረሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ (social mobilization tools) ቡክሌት እንዲሁም የህጻናት መብቶች ኮሚቴ የአሰራር ጋይድ ላይን በአዲስ መልክ በመከለስ ስተዘጋጅቷል፡፡

በአጠቃላይ በባለፉት ሶስት የዕቅድ ዘመን 1,045,372 ህፃናትን በሁሉም አማራጮች ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 555,547 ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 53.14 በመቶ ሲሆን መረጃው እንደሚያመለክተው ለአፈፃፀሙ ዝቅተኛ መሆኑን ያመለክታል፡፡

በሌላ በኩል ሴት የመንግስት ሰራተኞች ህፃናት ልጆቻቸውን በቅርበት እየተከታተሉና እየተንከባከቡ ጊዜያቸውን በአግባቡ ተጠቅመው ውጤታማ ስራ መስራት እንዲችሉ በመንግስት ተቋማት የህጻናት ማቆያዎችን እንዲቋቋሙ አስፈላጊ በመሆኑ በባለፉት ሶስት ዓመታት በ2012 ከነበረበት 29 በ2015 ወደ 50 ለማድረስ ታቅዶ 70 ማድረስ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ በተቋማት ውስጥ የሚሰሩ ሴት የመንግስት ሰራተኞች ከወሊድ በኋላ ወደ ስራ ገበታቸው በሚመለሱበት ወቅት በሚሰሩበት ተቋም ውስጥ ህፃን ልጆቻቸውን በቅርበት እየተከታተሉና እየተንከባከቡ ለመስራት እንዲችሉ እንዲሁም በተመደቡበት የሥራ መስክ ያለምንም ስጋትና ሃሳብ ሙሉ ኃይላቸውን፤ ጉልበታቸውን፤እውቀታቸውንና ጊዜያቸውን ተጠቅመው ውጤታማ ስራ መስራት እንዲችሉ የህጻናት ማቆያ ማዕከላትን ማቋቋም ተችሏል፡፡ ተግባሩ አዲስ ከመሆኑ አንፃር የተጀመረው ስራ አበረታች ቢሆንም ብዙ ርቀት መሄድ የሚጠይቅ በመሆኑ በቀጣይ ያለዉን ችግር በመፍታትና ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ በተሻለ ሁኔታ ሴት መንግስት ሰራተኞች ህፃን ልጆቻቸውን የሚያቆዩበትና በቅርበት የሚንከባከቡበት የህፃናት ማቆያ አገልግሎት መስጫ ማዕከል እንዲቋቋም በየደረጃው ከሚገኙ አስተዳደሮች/የአስተዳደር አካላትና ሌሎች ተቋማት ጋር በመነጋጋርና በመመካከር አስፈላጊውን ግብዓት እንዲሟላ በማድረግ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ከተቋሙ ይጠበቃል፡፡

የህጻናት ድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት በሚመለከት በሌላ በኩል በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ምክንያቶች ለችግር ተጋላጭ የሆኑ 95,327 የህፃናት ቤተሰቦች የኢኮኖሚ ድጋፍ እንዲያገኙ ለማድረግ ታቅዶ 431,106( ሴት 279,014) ድጋፍ እንዲያገኙ ሆኗል፡፡ በተጨማሪም ህጻናት የዴሞክራሲ ስርአት ሂደትን እንዲለማመዱና በዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ተቀርጸዉ እንዲያድጉ ለማድረግ የህጻናት ፓርላማ ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ የህፃናት ፓርላማዎች በ2012 ከነበሩበት 3,592 በ2015 ወደ 3,648 ማድረስ ተችሏል፡፡ ነገር ግን በክልሉ ውስጥ ካሉ የትምህርት ቤት እና የተማሪዎች ቁጥር አንጻር አፈጻጸሙ በጣም ዝቅተኛ ስለሆነ አገር ተረካቢ እና በዴሞክራሲ የሚያምን ትውልድ ለመፍጠር የህጻናት ፓርላማ ማቋቋም አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህ ቢሮው በቀጣይ ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን አፈጻጸሙን ማሻሻል ይጠበቃል፡፡

**የአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን** ከመደገፍ አንጻር ባለፉት ሶስት ዓመታት የመስማት ችግር ያለባቸውን አካል ጉዳተኞች አገልግሎት እንዲያገኙ ለማስቻል በመንግስት ተቋማት የሚሰሩ የመንግስት ሠራተኞች የምልክት ቋንቋ ማስተማር አስፈላጊ በመሆኑ በዕቅድ ዘመኑ 2097 (ወንድ 1039 ሴት 1040) የመንግስት ሰራተኞችን ለማሰልጠን ታቅዶ 685 (ወንድ 314 ሴት 371) ማሰልጠን ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙም 32.66% ነው፡፡በሌላ በኩል የአካል ጉዳተኞች በመንግስት ተቋማት፣ በግል የትምህርት ተቋማት እና በጎንደር የአካል ጉዳተኞች የክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል የቀለምና የሙያ በትምህርታቸው እንዲማሩ በማድረግ ብቁ ዜጋ ሆነው ለሀገራቸው፣ ለቤተሰቦቻቸው እና የራሳቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ በባለፉት ሶስት ዓመታት 9,035 (ወንድ 4,518 ሴት 4,517) አካል ጉዳተኞች እንዲማሩ ታቅዶ 3,720( ወንድ 1,863 ሴት 1,857) የቀለምና የሙያ በትምህርታቸው እንዲማሩ ማድረግ ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙም 41.17% ነው፡፡ እንደዚሁም በዕቅድ ዘመኑ 5,702(ወንድ 2,851 ሴት 2,851) በገቢ ማስገኛ ስራዎች እንዲሰማሩ ታቅዶ 6,650(ወንድ 3,326 ሴት3,324) በገቢ ማስገኛ ስራዎች እንዲሰማሩ ተደርጓል፡፡ አፈፃፀሙም ከዕቅድ በላይ ነው፡፡ በተጨማሪ ባሳለፍናቸው ሶስት የዕቅድ አመታት የህብረተሰቡን አቅም በማስተባበር፣ በየአካባቢው የሚገኝን ሃብት በማስተባበር፣ ሌሎች አጋር አካላትን በማቀናጀት መስራት የሚችሉትን አረጋዊያን ወደ ቋሚ ስራ የማስገባት ጥረት የተደረገ ሲሆን በዚህም ለ19,171(ወንድ 9,585 ሴት9,586) ቋሚ ስራ ለማስገባት ታቅዶ 7,751 (ወንድ 3,587 ሴት 4,164) እንዲሰማሩ ተደርጓል፤ አፈፃፀሙም 40.43% ነው፡፡ ባለፉት ሶስት ዓመታት በደሴ፣ባህርዳር እና ጎንደር ማዕከላት ለ27,758 አካል ጉዳተኞች የአካል ተሃድሶ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ31,048 አካል ጉዳተኞች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ማድረግ ሲቻል አፈጻጸሙም በ3,29 ከፍተኛ ነው፡፡ ከመረጃው እንደተመለከትነው አረጋውያን ወደ ቋሚ ስራ የማስገባት፣አካል ጉዳተኞች የአካል ተሃድሶ አገልግሎት፣አካል ጉዳተኞች እንዲማሩ፣የምልክት ቋንቋ ማስተማር እና በገቢ ማስገኛ ስራዎች እንዲሰማሩ አፈጻጸሙ ከመነሻ አመቱ ሲታይ የተሻለ ቢሆንም የተፈጸመው ተግባር ተደራሽ እና ቀጣይነትን የሚጠይቅ(የማይቋረጥ) ስለሆነ ከቢሮው በቀሪ አመታት በልዩ ትኩረት በማቀድ አፈጻጸሙን ማስቀጥል ይጠበቃል፡፡

### 3.3.4. ወጣቶና ስፖርት ልማት አፈጻጸም

የወጣትና ስፖርት ቢሮ ዓላማው የወጣቶችን ሁለንተናዊ ብቃት በመገንባት በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በማህበራዊ መስኮች እኩል ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፣ በክልሉ ልማት

ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ምቹ ሁኔታዎች በመፍጠር የራሳቸውን ሚና እንዲያበረክቱ ማስቻል ነው፡፡

የወጣቶች የመደራጀት መብትን ማስጠበቅን በሚመለከት በነባርና በአዲስ አደረጃጀቶች እንዲደራጁ በመደራጀት ጥቅምና አስፈላጊነት ዙሪያ ግንዛቤ ያገኙ ወጣቶች ብዛት/ወ 50%፣ ሴ 50%/ ለሶስት ተከታታይ ዓመታት 3,569,400 ለማከናወን ኢላማ ተይዞ 2,378,081 በማከናወን በሶስት ዓመት 66.6 በመቶ ተፈጽሟል፡፡ እንዲሁም በአዲስ አደረጃጀቶች አማካኝነት ወደ አደረጃጀት የገቡ ወጣቶች ብዛት ለሶስት ተከታታይ ዓመታት 1,880,323 ኢላማ በመያዝ 2,127,192 ተከናውኗል፡፡ ለሶስት ዓመት 113.1% ለአስር ዓመት እንዲሁ 113.1 በመቶ ተከናውኗል፡፡በተጨማሪም ለአደረጃጀት አመራሮች የተሰጠ ስልጠና ለሶስት ከታታይ ዓመት 175,014 ኢላማ ተይዞ 65,542 ተከናውኖ ከሶስት ዓመቱ 37.44 በመቶ የተከናወነ ሲሆን ከአስር ዓመት 18.5 በመቶ ደርሷል፡፡ ከሶስት ዓመት ቀሪ ተግባራት በተጨማሪ ሌሎች የኢላማው አካል የሆኑ ተግባራትን ተጠናክሮ ማከናወን ያስፈልጋል፡፡

የወጣቶች ተሳትፎና ውክልና ማረጋገጥን በተለከተ በየደረጃው ባሉ የህዝብ ምክር ቤቶች ወጣቶች ያለ ድምጽ ተሳታፊ የሆኑ ወጣቶ አደረጃጀቶች ብዛት (ወንድ.50% ሴት.50%)/ 174,636 ለሶስት ተከታታይ ዓመታት ለማከናወን ኢላማ ተይዞ 176,499 የተከናወነ ሲሆን ከሶስት ዓመቱ 101 በመቶ ከአስር ዓመቱ ደግሞ 22.2 በመቶ ብቻ ተከናውኗል፡፡

በተፈጥሮ ሃብት ጥበቃና ልማት ስራዎች ላይ ንቅናቄ በመፍጠር የተሳተፉ እና ተጠቃሚ የገጠር ወጣቶች ለሶስት ዓመታት (50% ሴቶች) 1,362,800 ለማድረስ እቅድ ተይዞ 977,574 ተከናውኗል፡፡ ከሶስት ዓመቱ 71.73 በመቶ ከአስር ዓመቱ ደግሞ 30.8 በመቶ ማከናወን ቢቻልም ከአስር ዓመቱ ኢላማ አንጻር 30.8 በመቶ ብቻ በመከናወኑ ተግባሩ በሚፈለገው መልኩ ያልተከናወነ በመሆኑ ለቀሪ ዓመታት የቀሩ ተግባራትን በመጨመር ከኢላማው መድረስ ይጠበቃል፡፡

የወጣቶችን ማህበራዊ ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ አንጻር በበጋ በጎ ፈቃድ በሶስት ዓመት የተሳተፉ 21,727,202 እንዲሳተፉ ኢላማ ተይዞ ክንውናቸው 7,790,592 ደርሷል፡፡ ከሶስት ዓመት 97.82 በመቶ ማከናወን ቢቻልም ከአስር ዓመት የተያዘው ኢላማ ከሁለት ዓመቱ እቅድ ያነሰ በመሆኑ አፈጻጸሙን መግለጽ አልተቻለም፡፡

በህገወጥ የሰዎች ዝውውር ተጋላጭነት ዙሪያ ግንዛቤ ያገኙ ወጣቶችና የህ/ተሰብ ክፍሎች ወጣቶች 1,983,000 ኢላማ ተይዞ 1,568,156 በማከናወን ከሶስት ዓመት 79.08 በመቶ የተፈጸመ መሆኑን ያሳያል፡፡

በሌላ በኩል አዲስ የተገነቡ የወጣት ስብዕና ማዕከላት ለሶስት ዓመት 80 ለማድረስ ኢላማ ተይዞ 60 በማድረስ ኢላማውን 75 በመቶ ማሳካት ቢቻልም ከአስር ዓመቱ ኢላማ አንጻር የተከናወነው 34 በመቶ ብቻ በመሆኑ በቀጣይ ቀሪ ጊዜያት ከሶስት ዓመት የቀሩ ተግባራትን በመጨመር ለቀሪ ዓመታት የታቀደውን እቅድ ማከናወን እንደሚገባ መረጃው ያመላክታል፡፡ እንዲሁም የተጠናከሩ የወጣት ስብዕና ማዕከላት ለሶስት ዓመታት 1,550 እንዲጠናከሩ ግብ ተይዞ 631 የተጠናከሩ ሲሆን ከሶስት ዓመታት 40.71% ማከናወን ቢቻልም ከአስር ዓመቱ ኢላማ አንጻር የተከናወነው 20.3 ብቻ በመቶ የተከናወነ በመሆኑ በቀሪ ዓመታት ከኢላማው ለመድረስ የእቅድ ክለሳ በማድረግ ማከናወን እንደሚያስፈልግ መረጃው ያመላክታል፡፡

የወጣቶች ጉዳይ ተቋማዊነትን ማጎልበትን በተመለከተ የተቋማት አመራሮች ብዛት (ክልል፣ ዞን ወረዳ) 9,763 ለማድረስ ለሶስት ዓመት ኢላማ ተይዞ 3,897 እንዲደርሱ የተደረገ ሲሆን ከሶስት ዓመት 39.92 በመቶ ከአስር ዓመት ኢላማው ደግሞ አፈጻጸሙ 8.8 በመቶ ብቻ በመሆኑ ከሶስት ዓመት ዓፈጻጸም ላይ የቀሩ ተግባራትን ለቅሞ በመያዝ ከአስር ዓመት ኢላማው ጋር ለመድረስ በጥንካሬ መስራት ይጠበቃል፡፡

የስፖርት ማህበራትን ማደራጀትና ከማጠናከር አንጻር መንግስታዊ የስፖርት ማህበራትን ለማደራጀት ለሶስት ዓመት 217 ለማድረስ ኢላማ ተይዞ 216 የተደራጁ ሲሆን ከሶስት ዓመት 99 በመቶ ከአስር ዓመቱ 61.8 በመቶ ላይ በመሆኑ በቀሪ ዓመታት ከሶስት ዓመት ቀሪ ተግባራትን በመጨመር ማከናወን እነደሚገባ መረጃው ያመላክታል፡፡

በየደረጃው የተቋቋሙ የስፖርት ም/ቤቶች ለሶስት ተከታታይ ዓመታት 3,827 የስፖርት ም/ቤቶችን ለማቋቋም ኢላማ ተይዞ 3,697 የተቋቋሙ ሲሆን ለሶስት ዓመት 97 በመቶ የተከናወነ በመሆኑ ከአስር ዓመቱ 96.6 በመቶ ተፈጽሟል፡፡ እንዲሁም የስፖርት ማህበራትን ለማቋቋም የተደረገ መንግስታዊ የፋይናስ ድጋፍ ለሶስት ዓመታት 30,000,000 ሚሊ. ይገኛል በሚል ኢላማ ተይዞ ከተያዘው ኢላማ በላይ 42,229,042 ሚ. የተገኘ ሲሆን የሶስት ዓመቱ 100 በመቶ በላይ የተከናወነ ሲሆን ከአስር ዓመት ኢላማ አንጻር ያለው ክንውን 42.2 በመቶ በመሆኑ የእቅድ ክለሳ በማድረግ በቀሪ ዓመታት ከዚህ በላይ የመንግስት ድጋፍ

ማግኘት እንደሚቻል ፖሊሲ ማትሪክሱ ላይ ያለው መረጃ ያመላክታል፡፡በተጨማሪም ስታንደርዱን አሟልተው የተደራጁ ክልል አቀፍ የስፖርት ማህበራት በተከታታይ ለሶስት ዓመታት 10 ለማደራጀት ታቅዶ 11 የስፖርት ማህበራትን በማቋቋም ከመቶ ፐርሰንት በላይ ማሳካት የተቻለ ቢሆንም ከአስር ዓመት ከተያዘው ኢላማ 73.3 በመቶ ላይ መሆኑን የተላከው መረጃ ያመላክታል፡፡ የስፖርት ሃብትን ከማሳደግ አንጻር የስፖርት ሃብትን ለማሳደግ ለአስር አመታት 279.2ሚ ብር እንዲሁም ለሶስት ዓመት 693,410,036 ለመሰብሰብ ኢላማ ተይዞ 33,0316,921 ተሰብስቧል፡፡ ከሶስት ዓመት 47.63 በመቶ የተከናወነ መሆኑን ያሳያል፡፡

**ሰንጠረዥ 16. የስፖርት ሃብትን ማሳደግ**

| ተግባር | መለኪያ | መነሻ (2013) | የ2 ዓመት ዒላማ | ተቋሙ ያቀደው ዒላማ | የ3 ዓመት ክንዉን | የዕቅድ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ከህ/ሰቡ የተሰበሰበ ብር | በብር | 2.3ሚ | 678,175,018 | 678,175,018 | 298,668,410 | 0 |
| በስፖርት ማህበራት የተሰበሰበ ብር | በብር | 2.5ሚ | 3,500,000 | 3,500,000 | 8,187,087 | 0 |
| ከዲያስፖራ ማህ/ሰብ የተሰበሰበ | በብር | 2,350,00 | 2,000000 | 600,000 | 573,936 | 1,400,000 |
| በስፖርት ተቋማት ከተያዙ ቦታዎች የተሰበሰበ | በብር | 12.6ሚ | 11,135,000 | 11,135,000 | 22,887,488 | 0 |

የመረጃ ምንጭ፡- የ2016 የወጣትና ስፖርት ቢሮ መረጃ

አለም አቀፍ እና ሃገር አቀፍ ስታንደርዱን ያሟሉ የማዘውተሪያ ስፍራዎች በሶስት ተከታታይ ዓመታት 2 ኢላማ ተይዞ 2 በመቶ እንዲከናወን ተደርጓል፡፡ይህም ከሶስት ዓመት 100 በመቶ የተሟሉ ሲሆን ከአስር ዓመት ኢላማ ያልተያዘለት በመሆኑ አፈጻጸሙን ማዬት አልተቻለም ፡፡እንዲሁም በት/ቤቶች እና በተቋማት ያሉ የስፖርት ማዘውተሪያ ለሶስት ዓመታት 1,200 እንዲደርሱ ለማድርግ በተያዘው ኢላማ መሰረት 4,944 ማከናወን የተቻለ ሲሆን ከሶስት ኣመቱም ይሁን ከ10 አመቱ 100 በመቶ በላይ በመሆኑ ከአስር ዓመት ከኢላማው በላይ

ማከናወን የተቻለ በመሆኑ ለቀሪ ዓመታት እቅዱን ሰፋ አድረጎ ተግባራትን ማከናወን እንደሚገባ በፖሊሲ ማትሪክሱ ያለው መረጃ ያመላክታል፡፡ በተጨማሪም ህጋዊ ማረጋገጫ ሰነድ ያላቸው የማዘውተሪያ ስፍራዎች ለይቶ ለመያዝ 1,710 በሶስት ዓመታት ውስጥ ለማድረስ ኢላማ 1,475 ደርሷል፡፡ከሶስት ዓመት 86 በመቶ ማድረስ ቢቻልም ከአስር ዓመቱ አፈጻጸሙ 36.8 በመቶ ብቻ በመሆኑ ከኢላመው ያለው አፈጻጸም ዝቅተኛ እንደሆነ ከፖሊሲ ማትሪክሱ የተያዘው መረጃ ያመላክታል፡፡ የተገነቡ የስፖርት ስልጠና ማዕከላት የተያዘው ለሶስት ተከታታይ ዓመታት አገልግሎት መስጠት የጀመሩ ማዕከላት በሶስት ዓመታት ውስጥ 23 ለመፈፀም ኢላማ ተይዞ 21 ተፈጽሟል ለሶስት ዓመት 91.3 በመቶ በማከናወን ለአስር ዓመት ከመቶ ፐርሰንት በላይ የሆነ ተግባር ማከናወን እንደተቻለ ከመረጃው ለማወቅ ተችሏል፡፡

**ሰንጠረዥ 17. የስፖርት ማዘዉተሪያ ስፍራዎችና ስልጠና ማዕከላት ማስፋፋትና ማሳደግ**

| ተግባር | መለኪያ | መነሻ (2012) | የ2 ዓመት ዒላማ | ተቋሙ ያቀደው ዒላማ | የ3 ዓመት ክንዉን | የዕቅድ ልዩነት በቅናሽ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አለም አቀፍ ስታንደርዱን ያሟሉ የማዘውተሪያ ስፍራዎች ብዛት | ቁጥር | 2 | 2 | 2 | 2 | 0 |
| ሃገር አቀፍ ስታንደርዱን ያሟሉ የማዘውተሪያ ስፍራዎች ብዛት | ቁጥር | 77 | 189 | 189 | 71 | 0 |
| በት/ቤቶች እና በተቋማት ያሉ የስፖረት ማዘውተሪያ ስፍረታዎች ብዛት | ቁጥር | 4000 | 8000 | 1200 | 4944 | -6800 |
| የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ተደራሽነት በመቶኛ | በመቶኛ | 873 | 185 | - | - | -185 |
| ህጋዊ ማረጋገጫ ሰነድ | ቁጥር | 3492 | 1710 | 1710 | | 0 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ያላቸው የማዘውተሪያ ስፍራዎች ብዛት | | | | | | |
| የተገነቡ የስፖርት ስልጠና ማዕከላት | ቁጥር | 3 | 14 | 14 | 16 | 0 |
| አገልግሎት መስጠት የጀመሩ ማዕከላት ብዛት | ቁጥር | 3 | 9 | 9 | 5 | 0 |

የመረጃ ምንጭ:- የ2016 የወጣትና ስፖርት ቢሮ መረጃ

የማህበረሰብ ስፖርትን በማስፋፋት የህ/ሰቡን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ከማሳደግ አንጻር በት/ቤቶች በጤናና አካል ብቃት ተሳታፊ፣በመስሪያ ቤቶች በጤናና አካል ብቃት ተሳታፊ፣በጤና ቡድኖች በአካል ብቃት ተሳታፊ ለሶስት ዓመት 1,166,000 ለማሳተፍ ኢላማ ተይዞ 1,525,834 ተሳትፈውበት ለሶስት ዓመት 130.86 በመቶ ከአስር ዓመት 29.5 በመቶ ማከናወን ተችሏል ።

የታዳጊና የባለሙያ ስልጠና በመስጠት ዉጤታማ ስፖርተኛ ማፍራትን በሚመለከት በግል ባለሃብቶች የተያዙ ስፖርተኞች ለሶስት ዓመት 3 ለማከናወን ኢላማ ተይዞ 4 ማከናወን የተቻለ ሲሆን ከሶስት ዓመት 133 በመቶ ከአስር ዓመት 3.2 በመቶ ላይ በመሆኑ በቀሪ ዓመታት ለተግባሩ ትኩረት ሰጥቶ መስራት እንደሚገባ መረጃው ያመላክታል።በመንግስት ማሰልጠኛ ማዕከላት የተያዙ ስፖርተኞች በሶስት ዓመት 580 ኢላማ ተይዞ 1037 ስፖርተኞችን በመያዝ ከእቅዱ በላይ ማከናወን ሲቻል ከአስር ዓመት 172 በመቶ ተፈጽሟል። በዋና ክለብ ላይ በተከታታይነት መሳተፍ የቻሉ አትሌቶች ለሶስት ተከታታይ ዓመታት 450 ኢላማ ተይዞ 1661 ማሳተፍ የተቻለ ሲሆን ከሶስት ዓመት 100 በመቶ ከአስር ዓመት 332.2 በመቶ ተግባሩ ለመፈጸም ጥረት ተደርጓል በዚህም ኢላማውን ለማሳካት የተደረገው ጥረት ጥሩ እንደነበር መረጃው ያመላክታል።እንዲሁም የሻምፒዎና ወድድሮች በሶስት ተከታታይ ዓመታት 22 ኢላማ ተይዞ 17 ማከናወን ተችሏል። ለሶስት ዓመት እንዲሁም የአስር ዓመታት 77.2 በመቶ በተመሳሳይ ተፈጽሟል።የታዳጊ ወጣቶች ወድድር መካሄድ በሶስት ዓመት ውስጥ 13 ኢላማ ተይዞ 10 ማከናወን ተችሏል።ለሶስት ዓመት 76.9 በመቶ ከአስር ዓመት 76.9 በመቶ ተከናውኗል።

ሰንጠረዥ 18. የታዳጊና የባለሙያ ስልጠና በመስጠት ዉጤታማ ስፖርተኛ ማፍራት

| ተግባር | መለኪያ | መነሻ (2012) | የ2 ዓመት ዒላማ | ተቋሙ ያቀደው ዒላማ | የ3 ዓመት ክንዉን | የዕቅድ ልዩነት በቅናሽ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| በክለቦች መዋቅሮች የተያዙ ሰልጣኞች ብዛት | ቁጥር | | 300 | 300 | 2671 | 0 |
| በመንግስት ድጋፍ የተያዙ ሰልጣኞች ብዛት | ቁጥር | 40 | 7525 | 7525 | 6757 | 0 |
| በፌደራል ድጋፍ | ቁጥር | - | 5750 | 5750 | 4523 | 0 |
| በክልል | ቁጥር | - | 3,550 | 1775 | 2157 | -1775 |
| የስልጠና ጣቢያዎች ቁጥር | ቁጥር | 583 | 602 | 301 | 291 | -301 |
| የስልጠና ጣቢያዎች ቁጥር/በፈደራል/ | ቁጥር | - | 460 | 230 | 160 | -230 |
| የስልጠና ጣቢያዎች ቁጥር/በክልል/ | ቁጥር | - | 142 | 71 | 134 | -71 |
| በዋና ክለብ ላይ በተከታታይነት መሳተፍ የቻሉ ኤሌቶች | ቁጥር | 124 | 450 | 450 | 1661 | 0 |
| የሻምፒዎናወድድሮች | ቁጥር | 22 | 44 | 22 | 17 | -22 |
| የታዳጊወጣቶችወድድር | ቁጥር | 17 | 26 | 13 | 10 | -13 |

የመረጃ ምንጭ:- የ2016 የወጣትና ስፖርት ቢሮ መረጃ

የስፖርታዊ ዉድድር መድረኮችን በማሳደግ የህ/ቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥን በተመለከተ ክልል አቀፍ የውድድር መድረኮችና ውድድር የተካሄደባቸው ስፖርቶች ለሶስት ተከታታይ ዓመታት 10 ሲሆኑ 6 ውድድር የተካሄደባቸው ስፖርቶችን በማከናወን ለሶስት ዓመታት 60 በመቶ መከናወኑን ያሳያል።እንዲሁም በግል ባለሃብቶች የተዘጋጁ የውድድር መድረኮችና የተሳተፉ አትሌቶች ብዛት ለሶስት ኣመት 15 ኢላማ ተይዞ 2 የተከናወነ ሲሆን ለሶስት ዓመታት 13

በመቶ ማከናወን የተቻለ ሲሆን የተሳተፉ አትሌቶች ለሶስት ዓመት 3000 ለማከናወን ኢላማ ተይዞ 1854 በመከናወኑ ለሶስት ዓመት 61.8 በመቶ የአስር ዓመት 20.6 በመቶ ደርሷል፡፡ በተጨማሪም ስታንደርዱን የጠበቀ ውድድር የሚመሩ ፌደሬሽኖች ለሶስት ተከታታይ ዓመታት 15 ኢላማ ተይዞ 10 የተፈፀመ ሲሆን የሶስት ዓመት 67 በመቶ ለአስር ዓመት 45.4 በመቶ መፈፀም ተችሏል፡፡

**ሰንጠረዥ 19 ፡ የስፖርታዊ ዉድድር መድረኮችን በማሳደግ የህ/ቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ**

| ተግባር | መለኪያ | መነሻ (2012) | የ2 ዓመት ዒላማ | ተቋሙ ያቀደው ዒላማ | የ3 ዓመት ክንዉን | የዕቅድ ልዩነት በቅናሽ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ክልልአቀፍ ውድድር መድረኮች | ቁጥ | 4 | 6 | 10 | 6 | 0 |
| ውድድር የተካሄደባቸው ስፖርቶች ብዛት | ቁጥር | 22 | 44 | 22 | 16 | -22 |
| በግል ባለ፤ሃብ/ የተዘጋጁ የውድድር መድረኮች ብዛት | ቁጥር | 1 | 10 | 15 | 2 | 0 |
| የተሳተፉ አትሌቶች ብዛት | ቁጥር | 2000 | 3000 | 3000 | 1854 | 0 |
| ስታንደርዱን የጠበቀ የውድድር የሚመሩ ፌደሬሽኖች ብዛት | ቁጥር | - | 15 | 15 | 10 | 0 |

የመረጃ ምንጭ፡- የ2016 የወጣትና ስፖርት ቢሮ መረጃ

በግል ባለሃብቶች ድርጅቶች የተያዙ ክለቦች ለሶስት ዓመታት 3 ኢላማ ተይዞ 4 በመፈጸም ከሶስት ዓመት ከ100 ፐርሰንት በላይ ከአስር ዓመት 44.4 በመቶ ደርሷል፡፡እንዲሁም ስፖርትን ለማህበራዊ ልማት የሚጠቀሙ ተቋማት ለሶስት ተከታታይ ዓመታት 12 ይደርሳሉ ተብሎ ቢታሰብም 9 ሲደርስ ለሶስት ዓመታት 75 በመቶ ከአስር ዓመቱ 60 በመቶ ተፈጽሟል፡፡

በአጠቃላይ ሶስት አመቱና በአስር አመቱ አንጻር የሚቀሩ ተግባራት በተለያዩ ችግሮች ምክንያት ማለትም ከወቅታዊ ችግሮች አንጻር ተንቀሳቅሶ ድጋፍና ክትትል አለማድረግ ፣ የዞኖች ሪፖርት በሚፈለገው መልኩ እቅዱን ያሳካ አለመሆኑና በሪፖርት መገናኘት አለመቻሉ፣ሌላው መሰረታዊ ችግር በወቅታዊ ችግሩ ምክንያት ውድድሮች መካሄድ አለመቻላቸው ፤ኢላማውና ግቡ ከፖሊሲ ማትሪክሱ ጋር አለመናበብ ፤የሶስት ዓመት እቅድ ከኢላማው በልጦ መታቀድ ወዘተ ኢላማውን ለማሳካት በሶስት ዓመት ውስጥ ያጋጠሙ ችግሮች ነበሩ ሆኖም በአፈጻጸም ደረጃ የተሻሉ አፈጻጸሞችን ለማየት ተችሏል ሌሎች ተግባራቶችንም በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ እንዲከናወኑ ለማድረግ ከአሁኑ ርብርብ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን በየተግባራቶች በተሰጠው ሃሳብ የተገለፀ በመሆኑ በቀጣይ ዓመታት ተግባራትን ለቅሞ ይዞ መተግበር እንደሚገባ መረጃዎች በግልጽ የሚያሣዩ በመሆናቸው ችግሩን አውቆ እልባት ለመስጠት ያስችላል፡፡

### 3.3.5. የሲቪል ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ተግባራት አፈጻጸም

የክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በሶስት ዓመታት የእቅድ ዘመን ዋና አላማ አድርጎ ሲያከናውናቸው የነበሩ የተቋማትን ውጤታማነት በአደረጃጀት ማጎልበት፣የተቋማትን ውጤታማነት በአሰራር ማጎልበት፣የሰው ሃብት ልማት ሥርዓቱን ማሻሻል፣ የሠራተኞችን ዕቅድ አፈፃፀም ሥርዓት ማሻሻል፣የሰው ሃብት ስምሪት ስራዎችን አፈፃፀም ማሻሻል ፣ የክልሉን መንግስት የማስፈጸም አቅም በመገንባት ሀገራችንን መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ እንድትሰለፍ የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ፣ በክልላችን ህዝቡ በየደረጃው በልማቱና በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታው እኩል እንዲሳተፍና እንዲጠቀም ለማስቻል ናቸው፡፡

የተቋማትን ውጤታማነት በአሰራር ከማጎልበት አንጻር ወደ ሥራ እንዲገቡ የተደረጉ መመሪያዎች ጥራት ለሶስት ተከታታይ ዓመታት 100% ኢላማ ተይዞ ለሶስት ዓመት 100% ተፈጽሟል፡፡ አፈፃፀሙ ከፍ ያለበት ምክንያትም በርካታ ተገልጋዮች ጥያቄ የሚያቀርቡባቸው በመሆኑና ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት ባለፉት ሶስት ዓመታት ሁለት ደንቦችና አስራ ስምንት በላይ ልዩ ልዩ የሰው ሃይል አስተዳር መመሪያዎች የማሻሻል ስራ በመከናወኑ ነው፡፡ በክልሉ የሚገኙ የመንግስት ተቋማት የሰው ሃይል ስምሪት አፈፃፀሞች ከግድፈት ነፃ እንዲሆኑ በማድረግ በ3 ዓመታት 0% ለማድረስ ታቅዶ አፈፃፀሙ ሲታይ 2.5 በመቶ መሆኑን ያሳያል፡፡ በመሆኑም አፈፃፀሙ ከመቀነስ ይልቅ መጨመር የሚያሳይ በመሆኑ ኮሚሽኑና በየደረጃው ያሉ ተቋማቱ የድጋፍ ክትትልና ቁጥጥር ስራውን (የኢንስፔክሽን) ስራን በተጠናከረ መልኩ መፈፀም እና ከፍትህ አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት በህግ ጥሰት ምክንያት የሚደርሰዉን

የሀብት ብክነት መቀነስ ይገባል፡፡ በተመሳሳይ የተሰጠ አስተዳደራዊ የዳኝነት ውሳኔ መጠን የመንግስት ሠራተኞች ከስምሪት ሥራዎች አፈፃፀም ጋር በተያያዘ ላቀረቡት የይግባኝ ጥያቄ ለሦስቱ የአስተዳደር ፍ/ቤት ምድብ ችሎቶች የቀረቡ ጉዳዮችን በመመርመር በሶስት አመታት 85% ውሳኔ ለመስጠት ኢላማ ተይዞ 84% ለሶስት ዓመት 98.8 በመቶ ውሳኔዎችን መስጠት ተችሏል፡፡

የሰው ሃብት ልማት ሥርዓቱን ከማሻሻል አኳያ ሥራ ላይ የዋለ የሰው ሃብት ዕቅድ በሶስት ዓመታት ውስጥ አንድ ሰነድ በማዘጋጀት ለሶስት ዓመት 100% ማከናወን ተችሏል፡፡

ባለፉት ተከታታይ ዓመታት በክልሉ መንግሰት ድጋፍ የረጅም ጊዜ ስልጠና በመማር ላይ የሚገኙ የመንግስት ሰራተኞች ብዛት በዲፒሎማ (1,005)፣በመጀመሪያ ዲግሪ (1,207)፣ በ2ኛ ዲግሪ (1,790)፣ እና በ3ኛ ዲግሪ (44) በአጠቃላይ 4,046 (ወ-2,183 ሴ-1,863) ሰራተኞች በመንግስት ድጋፍ አድራጊነት በመማር ላይ የሚገኙ ሲሆን ኮሚሽኑ የሰልጣኞችን የትምህርት ክፍያ ለመፈፀም የሚያስችል የበጀት ዕቅድ በማዘጋጀትና ከክልሉ ገንዘብ ቢሮ በጀቱን በማስፈቀድ ብር 5,988,212.5 ለሚማሩባቸው ዩኒቨርስቲዎች ክፍያ ተፈፅሟል፡፡ለሶስት ዓመትም ሆነ ለአስር ዓመት ተግባሩ አንድ በመሆኑ 100% ተከናውኗል፡፡

የሠራተኞችን ዕቅድ አፈፃፀም ሥርዓት ማሻሻልን በሚመለከት ተሻሽሎ ሥራ ላይ የዋለ የምዘና መመሪያ/ስታንዳርድ በሶስት ዓመታት ውስጥ አንድ መመሪያ በማዘጋጀት ለሶስት ዓመት 100% ተከናውኗል፡፡

የሰው ሃብት ስምሪት ስራዎችን አፈፃፀም ከማሻሻል አንጻር በስምሪት ስራዎች ተጠቃሚ የሆኑ ዜጎች ባለፉት ሶስት ዓመታት 100% ተጠቃሚ ለማድረግ ኢላማ ተይዞ 91% መፈጸም ተችሏል፡፡ እንዲሁም ሌሎች ስምሪቶችን በሚመለከት በምደባ፣ በዝውውር፣ በደረጃ ዕድገት፣ በኬርየር እና በድልድል በድምሩ ለሶስት ዓመት ለ32,583 (17,990 ወንድና 14,593 ሴት) ሠራተኞች በኮሚሽኑና በየደረጃው ባሉ የሲቪል ሰርቪስ ተቋማት አማካኝነት የሰው ሃይል ስምሪቶች መፈፀም ተችሏል፡፡

የለውጥ መሣሪያዎችን ውጤታማነት ማሳደግን በተመለከተ የለውጥ ሥራዎችን ሙሉ በሙሉ የተገበሩ የኮሚሽኑ አደረጃጀቶች በሶስት ዓመታት 216 በእቅድ በማካተት 118 ተከናውኗል፡፡ እንዲሁም ከሶስት ዓመት 55% ከአስር ዓመት 54.6 በመቶ መከናወኑን ያሳያል ፡፡

በአጠቃላይ ተቋሙ ለሶስት ዓመታት ተግባራትን ለማከናወን ኢላማ ቀርጾ በመንቀሳቀስ በርካታ ተግባሮችን አከናውኗል፡፡ ሆኖም ተግባራትን በኢላማው ልክ ለማከናወን በርካታ ችግሮች የነበሩ ቢሆንም ዋና ዋናዎቹን ለመግለጽ ያህል የሰራተኛው የ9 ወር JEG ቀሪ ክፍያ ጥያቄ ምላሽ ማግኘት አለመቻሉ፣የደንብ ልብስ መመሪያ ከወቅቱ የዋጋ ንረት ጋር በተያያዘ አለመሻሻል፣ የመንግስት ሰራተኞች ከወቅቱ የኑሮ ውድነት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ድጎማ አለመፈቀድ፣ እንዲሁም ከወቅታዊ የክልላችን ሁኔታ ጋር ተያይዞ ከዞኖች ጋር ወጥ የሆነ የሪፖርት ልውውጥ አለመኖሩ እና በዚሁ ወቅታዊ ጉዳይ ምክንያት የኢንተርኔት አለመኖር መሰረታዊ ችግሮች ነበሩ ፡፡ ስለሆነም የኮሚሽኑ ዳይሬክቶሬቶች/ቡድኖች እና በተዋረድ የሚገኙ ተቋሞች በቀሪ ዓመታት ታቅደው ያልተከናወኑና ዝቅተኛ አፈፃፀም የተመዘገበባቸውን ተግባራትን በእቅድ በማካተት አቅማቸውን በማቀናጀት ከአሁን ቀደም ከሚያከናውኑት በበለጠ የጋራና የተናጠል ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ በማድረግ በ10 ዓመቱ መሪ እቅድ የተያዙ ግቦች እንዲሳኩ ማድረግ ይጠበቃል፡፡

### 3.3.6. ትራንስፖርትና ሎጂሰቲክ ልማት አፈጻጸም

የትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ዋና ዓላማው ጥራትንና ተደራሽነትን በማረጋገጥ ቀልጣፋ፣ ፍትሃዊና ደህንነቱ የተጠበቀ የትራንስፖርት ስርዓት እንዲስፋፋ ማድረግ፣ የትራንስፖርት አገልግሎት አስተማማኝና በዋጋ ተመጣጣኝ መሆኑን በማረጋገጥ የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማሳደግ፣ የትራንስፖርት አቅርቦትን ከፍላጎት ጋር በማጣጣም ህብረተሰቡ የሚያባክነውን ጉልበት፣ ጊዜና ወጭ በመቀነስ ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት እንዲያውለው ማድረግ፣ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት በማሻሻል የትራንስፖርት አገልግሎት ደህንነቱ የተጠበቀና ምቾት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ፣ አጋር አካላትንና የህዝብ ክንፎችን በማደራጀትና በማሳተፍ ቅንጅታዊ አሰራርን ወደላቀ ደረጃ ማሳደግ፣ በትራንስፖርት ዘርፍ ኢንቨስትመንት ባለሃብቶች ተበረታትው በተደራጀ መንገድ እንዲገቡ ምቹ ሁኔታ መፍጠር ነው፡፡

በትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ዘርፍ ተይዘው የነበሩ እቅዶችን ስንመለከት አንዱና ወሳኝ ስራ ተደርጎ የሚወሰደው የትራንስፖርት መሰረተ ልማቱን የተቀናጀ፣ፍትሃዊ እና ተደራሽ በማድረግ ህብረተሰቡን የዘመናዊ ትራንስፖርት ተጠቃሚ ማድረግ ሲሆን በ2014 ዓ.ም እና በ2015 ዓ.ም በዞን ከተሞችና በሜትሮፖሊታን ከተሞች 3 የህዝብ ትራንስፖርት መናሀሪያዎች መገንባት አሁን ካለበት 231 ወደ 312 ለማሳደግ ኢላማ ተይዞ አፈጻጸሙ 1 ሲሆን ከሁለት ዓመቱ 33 በመቶ እንዲሁም ከዘጠኝ ዓመቱ 5.8 በመቶ መሆኑን ያሳያል ፡፡ በመሆኑም ከዚህ አንጻር

የሁለት ዓመታት ቀሪ ተግባራትን ከቀሪ ዓመታት ተግባር ጋር በማቀድ ማከናወን ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ነባር መናህሪያዎችን ማጠናከር ለሁለት ዓመታት ኢላማ 50 ተይዞ 71 የተከናወነ ሲሆን ከሶስት ዓመቱ 142 በመቶ እንዲሁም ከዘጠኝ ዓመቱ 22.7 በመቶ ማከናወን ተችሏል፡፡ ይህም ከአስር ዓመቱ ኢላማ አንጻር 312 ተይዞ በሁለቱ ዓመታት ከእቅድ በላይ ተከናውኗል ቢባልም የእቅድ ማነስ በመኖሩ እንጅ ሰፋ ብሎ ቢታቀድ ኖሮ በቀሪ ዓመታት ተጨማሪ መናህሪያዎችን ማጠናከር ይቻል ነበር ፡፡ በመሆኑም የህብረተሰቡ ተጠቃሚነት ቁጥር በማሳደግ ብቻ ሳይሆን ለኢኮኖሚ ልማቱ ወሳኝ ድርሻ እንዲያበረክት ለማድረግ ጥረት መደረጉ የሚበረታታ ነው፡፡

**ሠንጠረዥ 20፡ የትራንስፖርት መንኸሪያዎችን ማሳደግ**

| ተግባር | መለኪያ | መነሻ (2013) | የ2 ዓመት ዒላማ | ተቋሙ ያቀደው ዒላማ | የ2 ዓመት ክንዉን | የዕቅድ ልዩነት በቅናሽ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| በዞን ከተሞችና በሜትሮፖሊታንት | በቁጥር | | 17 | 3 | 1 | -14 |
| በአነስተኛ ከተሞች | በቁጥር | 5 | 10 | 10 | 0 | 0 |
| ነባር መነሃሪያዎችን ማጠናከር | በቁጥር | 182 | 50 | 50 | 71 | 0 |

የመረጃ ምንጭ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ባለስልጣን የ2016 መረጃ

የትራንስፖርት አገልግሎቱን የተቀናጀ ፣ ፍትሃዊ እና ተደራሽ ከማድረግ አንጻር የትራንስፖርት አገልግሎቱ ደህንነቱ የተጠበቀ በማድረግ በኩል ለአዲስ የከተማ ትራንስፖርት ማህበራት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስጠት በሁለቱ ዓመታት 16 ፈቃድ ለመስጠት ኢላማ ተይዞ 53 የተከናወነ ሲሆን ከሁለት ዓመቱ 331% ማከናወን የተቻለ ሲሆን ከዘጠኝ ዓመት 56.9% ማከናወን ተችሏልል፡፡ እንዲሁም የነባር ትራንስፖርት ማህበራት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ማደስ በሁለት ዓመቱ 252 ኢላማ ተይዞ 127 የተከናወነ ሲሆን ከሁለት ዓመት 50% ከዘጠኝ ዓመት 68.2% ተከናውኗል ፡፡ ከዚህ ለመረዳት እንደሚቻለው በቀሪ ዓመታት እቅድን በመከለስ ትኩረት ሰጥቶ በመስራት ተግባራትን ማከናወን እንደሚገባ መረጃው ያመላክታል፡፡

በተጨማሪም በከተማ ታክሲ ትራንስፖርት ማህበራት አዲስ አባል ለመቀበል ጥያቄ ሲቀርብ የአባሉን መረጃ በማረጋገጥ አባል እንዲሆን ማድረግ ለሁለት ዓመት 3,068 ለመስራት ኢላማ ተይዞ በሁለት ዓመታት 5,046 የተከናወነ ሲሆን ከሁለት ዓመት 164% ከዘጠኝ ዓመት 30.4% እንደተፈፀመ መረጃዉ ያሳያል፡፡ ለአዲስ የህዝብ ትራንስፖርት ማህበራት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስጠት ለሁለት ዓመት 3 ኢላማ ተይዞ 1 የተከናወነ ሲሆን ከሁለት ዓመት 33% ከዘጠኝ ዓመት 33% እንደተፈፀመ መረጃው ያሳያል፡፡ ከዚህ አንጻር ቀሪው እቅድ በሚታቀድበት ጊዜ ያለፈው አፈጻጸም ዝቅተኛ በመሆኑ ለቀሪ ዓመታት የእቅድ ክለሳ በማድረግ ማከናወን እንደሚገባ ያመለክታል፡፡በተመሳሳይ የነባር የጭነት ትራንስፖርት ማህበር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እድሳት ማድረግ ለሁለት ዓመታት 4 ኢላማ ተይዞ 1 የተከናወነ ሲሆን ከሁለት ዓመት 25 በመቶ ከዘጠኝ ዓመቱ ደግሞ 1.6 በመቶ ላይ እንዳለ ከመረጃዉ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በመሆኑም ተግባሩ በታቀደዉ መሠረት እየተከናወነ ባለመሆኑ በቀሪ ዓመታት 98.3 በመቶ የሚሆነዉን ተግባር በእቅዱ በማካተት በልዩ ትኩረት መሥራት ይጠበቃል፡፡ እንዲሁም አዲስ የተሽከርካሪ የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስጠት በሁለት ዓመታት 3,749 ለመስጠት ግብ ተይዞ ለሁለት ዓመታት 3,821 የተከናወነ ሲሆን የሁለቱ ዓመት 102 በመቶ ከዘጠኝ ዓመት 17.4 በመቶ እንደተፈፀመ መረጃው ያሳያል፡፡ የተሽከርካሪ የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ማደስ ለሁለት ዓመታት 13,413 ለማደስ ኢላማ ተይዞ 8,996 ማደስ የተቻለ ሲሆን ይህም ለሁለት ዓመት 67 በመቶ ከዘጠኝ ዓመቱ ደግሞ 38.6 በመቶ ተፈፅሟል፡፡ ቀሪ ተግባራትን ለማከናወን ጠንክሮ መስራት ካልተቻለ ኢላማውን ማሳካት እንደማይቻል ያሳያል፡፡

የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ተደራሽነትን ከማሳደግ አንጻር በሁለት ዓመታት 17,975,252 የህዝብ ትራንስፖርት ስምሪት ለመስጠት ኢላማ ተይዞ 19,703,503 የተከናወነ ሲሆን ከሁለት ዓመት 110 በመቶ ከዘጠኝ ዓመት ከመረጃዉ ለመረዳት እንደተቻለዉ 18.7 በመቶ ብቻ እንደተፈፀመ ያሳያል፡፡ በተጨማሪም በየዓመቱ ህዝብ ትራንስፖርት የተሸፈነ ኪ.ሜ(በየዓመቱ በ5 በመቶ ማሳደግ) ሲታይ 1,0374,658,42 ኪ.ሜ ለማድረስ ኢላማ ተይዞ 957,675,631 ኪ.ሜ የተሸፈነ ሲሆን ከሁለት ዓመቱ 92.3 በመቶ ከዘጠኝ ዓመት 15.9 በመቶ እንዲያድግ ተደርጓል፡፡ ተግባራትን በቀሪ ዓመታት ማከናወን ይጠበቃል፡፡

**ሠንጠረዥ21 ፡- የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ተደራሽነትን ማሳደግ**

| ተግባር | መለኪያ | መነሻ (2013) | የ2 ዓመት ዒላማ | ተቋሙ ያቀደው ዒላማ | የ2 ዓመት ክንዉን | የዕቅድ ልዩነት በቅናሽ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የአነስተኛ፤መለስተኛና ከፍተኛ የህዝብ ትራንስፖርት ተሽከርካሪዎች ብዛት | በቁጥር | 9621 | 20526 | 20526 | 21993 | 0 |
| ከአጎራባች ክልሎች ጋር የህዝብ ትራንስፖርት ትስስሩን ማጠናከር | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 0 |
| የመናኸሪያ ስታንዳርድ ማስከበር | በመቶኛ | 65 | 95 | 76 | 83 | -19 |

የመረጃ ምንጭ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ባለስልጣን የ2016 መረጃ

የከተማ ትራንስፖርት አገልግሎትን ማሻሻልን በሚመለከት የከተማ ታክሲ መርሃ ግብር በማፀደቅ እንዲሰሩ ማድረግ ለሁለት ዓመት 72,650 ኢላማ ተይዞ 81,651 የተከናወነ ሲሆን ከሁለት ዓመት 112% መሆኑን ያሳያል፡፡ የተሻለ አፈጻጸም ቢያሳይም እቅዱ በጣም አነስተኛ በመሆኑ በቀጣይ ቀሪ ዓመታት እቅዱን በመከለስ ተጨማሪ ተግባራትን ማከናወን ይጠበቃል፡፡ እንዲሁም በከተማ ትራንስፖርት አገልግሎት የተሰጠ ስምሪት በሁለቱ ዓመታት ውስጥ 407,517,068 ለማድረስ በኢላማ ተይዞ ስምሪቱን 680,693,962 በማድረስ የተከናወነ ሲሆን ከሁለት ዓመቱ 167% መፈጸም የተቻለ ሲሆን ከዘጠኝ ዓመቱ ደግሞ 27.8 በመቶ ብቻ መሆኑን መረጃዉ ያሳያል፡፡

ብቃቱ የተረጋገጠ ተሽከርካሪና አሽከርካሪ በማፍራት በክልሉ እየደረሰ ያለዉን የትራፊክ አደጋ በ30% ከመቀነስ አንጻር እጩ አሽከርካሪዎች የፁህፍ /የንድፈ ሀሳብ/ ፈተና መስጠት በሁለቱ ዓመታት 152,722 ለማድረስ ኢላማ ተይዞ 141,043 ማድረስ የተቻለ ሲሆን በሁለት ዓመቱ የኢላማውን 92.3% በመፈፀም ከዘጠኝ ዓመቱ ደግሞ 18.4% ብቻ የተፈፀመ በመሆኑ በቀጣይ ቀሪ ዓመታት ተግባራትን ለቅሞ ይዞ መተግበር እንደሚገባ መረጃው ያሳያል፡፡ በተጨማሪም

ብቁ ለሆኑ አሽከርካሪዎች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስጠት 119,554 ለመስጠት ኢላማ ተይዞ 101,295 ተፈጽሟል፡፡ይህም ከሁለት ዓመቱ 85% ከዘጠኝ ዓመቱ ኢላማ አንፃር 16.8% ብቻ እንተፈፀመ ያሳያል፡፡ በመሆኑም በቀጣይ ቀሪ ዓመታት በፖሊሲ ማትሪክስ መሠረት እቅዱን በመከለስ ተግባራት በትኩረት ሊከናወኑ ይገባል፡፡ በተመሳሳይ በሁለት ዓመታት አዲሱን መንጃ ፈቃድ አሽከርካሪዎች ብቃት ማረጋገጫ ፍቃድ ማደስ፣118,784 ለመስጠት ኢላማ ተይዞ 129,158 ማደስ የተቻለ ሲሆን ከሁለት ዓመቱ 109 በመቶ ከዘጠኝ ዓመቱ ደግሞ 12.5 በመቶ ብቻ መፈፀሙን መረጃዉ ያሳያል፡፡ ነባር መንጃ ፈቃድ አሽከርካሪዎች ብቃት ማረጋገጫ ፍቃድ ማደስ ለሁለት ዓመታት 24,912 ለማደስ ኢላማ ተይዞ 22,674 ማደስ የተቻለ ሲሆን ከሶስት ዓመቱ 91% ከዘጠኝ ዓመቱ ደግሞ 33.3% ብቻ እንደተከናወነ መረጃው ያሳያል፡፡ በመሆኑም የትራፊክ አደጋውን በእቅዱ ልክ ለመቀነስ የተሰሩ ተግባራት በሁለት ዓመታት የተሻሉ ቢመስሉም በ10 ዓመቱ የተቀመጠዉን ግብ ከማሳካት አኳያ በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ በቀሪ ዓመታት አደጋውን በመቀነስ ለህብረተሰቡ ጉዞ የሚጨነቅ ብቃት ያለው አሽከርካሪ እንዲኖር በማድረግ በእቅዱ ልክ ለመተግበር ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በተጨማሪም አመታዊ የተሽከርካሪ ቴክኒክ ምርመራ ማካሄድ ቦሎ መስጠት መነሻውን በየዓመቱ በ10% በማሳደግ በዚህ ተግባር ላይ ርብርብ በማድረግ ተግባሩ ለማከናወን 114,970 የቴክኒክ ምርመራ በማካሄድ 115,612 ለሁለት ዓመት የተከናወነ ሲሆን ከሁለት ዓመቱ 101 በመቶ በማሳካት ተግባሩ የተከናወነ ሲሆን ከዘጠኝ ዓመቱ ደግሞ 73.6% ደርሷል፡፡አሁን ያሉትን የተሽከርካሪ ጥገና ተቋማት 792 ለማድረስ ኢላማ ተይዞ 363 ለማከናወን ተችሏል፡፡ በዚህም ከሁለት ዓመቱ 46% ከዘጠኝ ዓመቱ ደግሞ 77% መፈፀም ተችሏል፡፡ አሁን ያሉትን 15 የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማት ለሁለት ዓመቱ 6 ታቅዶ 5 ሲከናወን ከሁለት ዓመቱ 83% የተከናወነ ሲሆን ከዘጠኝ ዓመቱ ኢላማ አንጻር ሲታይ 21.7% ደርሷል፡፡ በመሆኑም ከዘጠኝ ዓመቱ እቅድ አንጻር በቀሪ ዓመታት ከዚህ በበለጠ ማከናወን ስለሚቻል እቅዱን በመከለስ የተሻለ አፈጻጸም ማሳየት ይገባል፡፡

ለተሽከርካሪ አስመጭወች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስጠትን በሚመለከት የተሽከርካሪ ፍላጎት በክልላችን እያደገ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ የተሽከርካሪ አስመጭወችን የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስጠት ለሁለት ዓመታት 5 ታቅዶ 4 ተፈጽሟል፣ ከሁለት ዓመቱ 80%

የተሰጠ በመሆኑ ከዘጠኝ ዓመቱ ደግሞ 10% ላይ እንደሆነ መረጃዉ ያሳያል፡፡ በመሆኑም በቀሪ ዓመታት ከዚህ በላይ ተግባራትን ቆጥሮ መስራት እንዳለበት ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ ለሁለት ተከታታይ አመታት በርካታ ተግባራትን ለማከናወን ኢላማ ይዞ ሲንቀሳቀስ የቆዬ ሲሆን ኢላማውን ለማሳካት ማነቆ ሆነው ከነበሩ ምክንያቶች መካከል እስከ 2014 ዓ.ም ድረስ ከመንገድ ጋር አብሮ የነበረ በመሆኑና አሁንም ድረስ ወደታች ሲወረድ ወረዳዎች ላይ ከመንገድ ጋር አብሮ ተደርቦ ያለ በመሆኑ ለአፈጻጻም ሰፊ ክፍተት የፈጠረ ከመሆኑ በተጨማሪ በወቅታዊ ችግር ምክንያት ኢንተርኔት መቋረጡና ሪፖርት የማይልኩ ዞኖች መኖራቸው ሰፊ ጉልበትና መሬት በመጠቀም ገበያ ተኮር የግብርና ምርት በስፋት እንዲያመርት የሚታሰበው የገጠሩ ህብረተሰብ ተገቢዉን የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲያገኝ እየተሠራ ያለዉ ተግባር ዉስንነት ያለበት በመሆኑ እና ክልላችንን በገበያ ላይ ተወዳዳሪ ሊያደርግ የሚያስችል ቀልጣፋ፣ ኢኮኖሚያዊ ደህንነቱና ምቾቱም የተጠበቀ የትራንስፖርት አገልግሎት ተደራሽ ማድረግ በቀጣይ ቀሪ ዓመታት ተቋሙ በትኩረት ሊሠራበት የሚገባ ተግባር መሆኑን በመረዳት እቅዱን ከልሶ ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት ይገባል፡፡

## 3.4. የፍትህና አስተዳደር ዘርፍ አፈጻጸም

### 3.4.1.የፍትህ ዘርፍ አፈጻጸም

አስተዳደራዊ ፍትህን ማስፈን፣የዳኝነት አገልግሎት መስጠት፣ የዳኝነት ተደራሽነትን ማስፋፋት፣ የፍርድ ቤት ነፃነትና ተጠያቂነትን ማጎልበት፣ የወንጀል ህግን አፈጻጸም ውጤታማነት ማረጋገጥ፣ የማስፈፀም አቅምን በማሳደግ የመንግስት እና የህዝብን ጥቅም ማስከበር፣ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ውስጥ የልማት ጉዞን በማፋጠን የተጀመረውን የልማት፣ የሰብዓዊ መብት፣ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ግንባታን ማሳደግ፣ የህግ የበላይነትን በማስከበር ህብረተሰቡ ሠላምና ደህንነቱ እንዲሁም ህገ መንግስታዊ መብቱ የተረጋገጠ እንዲሆን ማድረግ፣ የፍትህ ሥርዓቱ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ፍትሐዊ፣ ግልጸኝነትና ተጠያቂነትን ያረጋገጠ እንዲሆን መሥራት የሚሉት የዘርፉ ዋና ዋናዎቹ የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው፡፡በዚህ መሠረት የፍትህ አስተዳደሩ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ለማድረግ የ10 ዓመት መሪ እቅድ ተዘጋጅቶ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም ከ2013 እስከ

2015 በጀት ዓመት በተቋሙ የተከናወኑ የዋና ዋና ተግባራትን አፈፃፀም ትንተና እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

በፍትህ አስተዳደሩ ዉስጥ  የህብረተሰቡን የተደራጀ ተሳትፎና ባለቤትነት ከማሳደግ አንጻር በሦስት ዓመቱ በፍትህ አስተዳደሩ ዉስጥ  የህብረተሰቡን የተደራጀ ተሳትፎና ባለቤትነት ለማሳደግ የንቃተ ህግ ትምህርት በመስጠት በጥቅል 22% ለማድረስ ታቅዶ 8.33% ብቻ መፈፀም የተቻለ መሆኑን መረጃዉ ያሳያል፡፡ በመሆኑም የህብረተሰቡን የንቃተ ህግ ግንዛቤ በማሳደግ ረገድ ተመጣጣኝ የአመለካከት ለውጥ ማምጣት አልተቻለም፡፡ ለዚህም ማሳያ የሚሆነው የወንጀል መዛግብት ሲቀንሱ አለመታየቱ፣ ህብረተሰቡ ለምስክርነት ሲጠራ ፍላጎት ማጣት ችግሮች የሚጠቀሱ ናቸዉ፡፡ በመሆኑም የተቀመጠዉን የአስር ዓመት ኢላማ ለማሳካት በፖሊሲ ማትሪክሱ መሠረት የሚሰጠዉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ህበረተሰቡ በተደራጀ መልኩ የህግ ግንዛቤ ኖሮት ወንጀለኛን በመጠቆም፣ ማስረጃ ሆኖ በመቅረብ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ አስተዋጽኦ እንዲያደርግ፣ እንዲሁም ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲቀንሱ ማህበረሰቡ መብቱን የመጠቀምና ግዴታውን የመወጣት ልምዱን እንዲያዳብር በሚያደርግ መልኩ መሰጠት ይኖርበታል ፡፡

በወንጀል ጉዳይ ከተቋሙ መሠረታዊ ተልዕኮ አኳያ የመዛግብት እንቅስቃሴ ሲታይ በሦስት ዓመቱ በወንጀል ጉዳዮች የማጥራት አቅም 100% ለማድረስ የታቀደ ሲሆን በአማካይ 98.62% መፈፀም ተችሏል፡፡ በሦስት ዓመቱ ከታቀደው አንፃር ሲታይ ግቡን ማሳካት ያልተቻለ መሆኑን መረጃዉ ያሳያል፡፡ ከመረጃዉ መረዳት እንደሚቻለዉ የቀረቡ መዝገቦችን ሙሉ በሙሉ ውሳኔ ከመስጠት አንጻር የሚቀር ተግባር እንዳለ አመላካች ነው፡፡ በመሆኑ በቀጣይ ቀሪ ዓመታት በመዛግብት ማጥራት ላይ ፈጣን ውሳኔ በመስጠት በ10 የተቀመጠዉን ግብ ማሳካት ይገባል፡፡

በሌላ በኩል በፌደራል ዉክልና እና በክልል ጉዳዮች በቀጥታ ክስ በወንጀል መዝገቦች የአቃቢ ህግ ተከራክሮ የማስቀጣት ምጣኔን በሦስት ዓመት በአማካይ 94.93% ለማድረስ ታቅዶ 90.62 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ከመረጃዉ ለመረዳት እንደሞከርነዉ የወንጀል መዝገቦችን የማስቀጣት ምጣኔ አሁንም በርካታ ክፍተት ያለበት መሆኑን ያሣያል፡፡ በመሆኑም ተቋሙ በዚህ ዙሪያ የሚስተዋለዉን የመፈፀም ችግር በቅርብ ተከታትሎ በመፍታት መፍትሄ ማስቀመጥ የሚጠይቅ ሲሆን የ10 ዓመቱን ኢላማ ለማሳካት በቀጣይ ዓመታት የተንከባለሉ ተግባራትን የእቅዱ አካል በማድረግ በትኩረት መስራት ይጠይቃል፡፡ በተመሳሳይ በሦስት ዓመት ዉስጥ የአቃቢ ህግ ይግባኝና ሰበር አቤቱታ መዝገቦችን የክርክር ዉጤታማነት ማሳደግ በአማካይ 82.16 በመቶ

ለማድረስ ታቅዶ 86.5 በመቶ ለመፈፀም ተችሏል፡፡ ተግባሩ በሦስት ዓመቱ የተሻለ አፈፃፀም ቢያሳይም የ10 ዓመቱን ኢላማ ለማሳካት በትኩረት መስራት ይጠይቃል፡፡ በተጨማሪም የፍርደኛ ይግባኝና ሰበር አቤቱታ መዝገቦች የክርክር ዉጤታማነት በአማካይ 86.33 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ በአማካይ 87.77 በመቶ መፈፀም ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል በሦስት ዓመቱ በፌደራል ዉክልና እና በክልል ጉዳዮች በቀጥታ ክስ ተከሳሽ፣ ምስክር ፣ መልስ ሰጭና ተጠሪ አቀራረብን በማጠናከር የመዛግብት መቋረጥ ምጣኔን ከ11.35 በመቶ ወደ 3.5 በመቶ ለመቀነስ የታቀደ ቢሆንም አፈፃፀሙ በአማካይ  ወደ 10.95 በመቶ ከፍ ብሏል፡፡ ከመረጃዉ ለመረዳት እንደተቻለዉ ተቋሙ ከህብረተሰቡ ጋር በቅንጅት በመስራት እና ህብረተሰቡን ከፍትህ ጎን በማሰለፍና ባለቤት በማድረግ በኩል ሰፊ ክፍተት እንዳለ ያሳያል፡፡ በመሆኑም በዚህ በኩል የሚታዩ ክፍተቶችን በመፍታት እና  ከሚመለከታቸው የፖሊስና ሌሎች አጋር አካላት ጋር በትብብር በመስራት ለህብረተሰቡ ፍትህ ከማስገኘትና ደህንነት ከማስጠበቅ አኳያ በቀጣይ ቀሪ ዓመታት በትኩረት መስራት ይጠበቃል፡፡ በተመሳሳይ በሦስት ዓመት የወንጀል አቤቱታ አቀባበል ዉሳኔ አሰጣጥ እና የአቤቱታ ተፈፃሚነት ከ97.06 በመቶ ወደ 100 ከፍ ለማድረግ ታቅዶ በአማካይ 96.84 በመቶ የተፈፀመ ሲሆን ይህ ተግባር በጥቅሉ ሲታይ ኢላማዉን ማሳካት እንዳልቻለ ያመለክታል፡፡ ስለሆነም በቀጣይ ቀሪ አመታት በፖሊሲ ማትሪክሱ መሠረት ተግባሩን በማቀድና በመፈፀም የተቀመጠዉን የ10 ዓመት ኢላማ ማሳካት ይገባል፡፡

በሦስት ዓመቱ በፍትሐብሄር ጉዳዮች ቅድመ-መከላከል ስራን በማጠናከር የመንግስትንና የህዝብን ሀብትና ንብረት 100 በመቶ ከብክነት ለመከላከል የታቀደ ሲሆን በመዝገብ ሆነ በገንዘብ 100 የተፈጸመ መሆን መረጃዉ ያሳያል፡፡ ይሁን እንጅ ይህን ተግባር አፈፃፀሙን በመከታተል ዉሳኔ ያረፈባቸዉን የመንግስት ሀብትና ንብረት በማስመለስና ከብክነት በማዳን በኩል አሁንም ድረስ ተቋሙ ያልተሻገረዉ ችግር በመሆኑ በቀጣይ ቀሪ ዓመታት  ልዩ ትኩረት ሊሰጠዉ ይገባል፡፡

በፍትሃብሄር ጉዳዮች መዛግብትን የማጥራት ምጣኔ በተመለከተ ከ98% ወደ 100% ለማሳደግ ታቅዶ በ3 ዓመቱ በአማካይ ወደ 99% መፈጸም ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል የማሸነፍ ምጣኔ ደግሞ በአማካይ 91% ነው፡፡ በተመሳሳይ በሦስት ዓመቱ በፍትሐብሄር ከሚያዙ ጉዳዮች ዉስጥ 28% በድርድር ለመጨረስ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም በአማካይ 24% መፈፀም ተችሏል፡፡ ይህ

የሚያመለክተዉ በፍትሐብሄር የሚያዙ ጉዳዮችን በድርድር መጨረስ በሶስት ዓመቱ ከተቀመጠዉ ኢላማ አኳያ የ4% ቅናሽ ያሳያል፡፡ በመሆኑም በዘርፉ የሚስተዋለዉን የመፈጸም ብቃት እና የስነ ምግባር ችግር በማስተካከል በቀጣይ ቀሪ ዓመታት የተሻለ ቅንጅታዊ አሰራር በመዘርጋት ተግባሩን በትኩረት መስራት ይጠበቃል፡፡

የክስ አመሠራረትና መልስ አቀራረብ ቅልጥፍናን/ መዝገብ የማጥራት አቅም ከ99.19% ወደ 100% ለማሳደግ ታቅዶ በሦስት ዓመቱ በአማካይ 98% መፈፀም ተችሏል፡፡ መረጃዉ የሚያመለክተዉ መዝገብ የማጥራት ምጣኔ በፍትሐብሄር ጭምር ክፍተት እንዳለበት ያሳያል፡፡

በተመሳሳይ በሦስት ዓመቱ በፍትሐብሄር ጉዳዮች በቀጥታ ክስ እና መልስ  የአቃቢ ህግ ተከራክሮ የማሸነፍ አቅምን በመዝገብ ከ91% ወደ 92 % ለማሳደግ ታቅዶ በአማካይ 88.82% መፈጸም ተችሏል፡፡ ከዚህ በሻገር ይግባኝና ሰበር አቤቱታ መዝገቦች የዓቃቤ ህግ የክርክር ዉጤታማነት በመዝገብ ከ63% ወደ 76% ለማድረስ ታቅዶ 69.5% መፈፀም ተችሏል፡፡ ከመረጃዉ ለመረዳት እንደተቻለዉ በቀጥታ ክስና መልስ የአቃቢ ህግ ተከራክሮ የማሸነፍ አቅም እና ይግባኝና ሰበር አቤቱታ መዝገቦች የአቃቢ ህግ የክርክር ዉጤታማነት 3.18% እና 6.3% በቅደም ተከተል ቅናሽ ያሳያል፡፡ በመሆኑም በዚህ ዙሪያ ያለዉን ችግር በመለየት ተግባሩ ግቡን እንዲያሳካ ለማድረግ ከመሠረተ-ልማት  ግንባታ ፣ ከአዲት ጉድለት ፣ ከህገ-ወጥ የከተማ መሬት ወረራ እና ከግዥ ስርዓቱ ጋር የተያያዙ የፍትሐብሄር ጉዳዮችን በልዩ የአሰራር ስርዓት በማስተናገድ የሦስት ዓመቱን ኢላማ እና የ10 ዓመቱን ግብ ለማሳካት በርካታ ተግባራት የሚጠይቅ በመሆኑ በቀጣይ በልዩ ትኩረት መስራት ይጠይቃል፡፡

በተመሳሳይ ይግባኝ መልስና ሰበር አቤቱታ መልስ መዝገቦች የዓቃቢ ህግ የክርክር ዉጤታማነት በመዝገብ ከ73.8% ወደ 88% ለማሳደግ ታቅዶ በአማካይ 80.4% መፈፀም ተችሏል፡፡ ከመረጃዉ ለመረዳት እንደተቻለዉ ከሦስት ዓመቱ ኢላማ አኳያ 7.6% ተግባራት ያልተፈፀሙ መሆን ያሳያል፡፡ በመሆኑም በቀጣይ ቀሪ ዓመታት በይግባኝ መልስና ሰበር የሚጠየቁ ጉዳዮችን በአግባቡ በመፈተሽ ማቅረብ እና መዝገቦችን ዉጤታማ ማድረግ ይገባል፡፡

በሦስት ዓመቱ ክስ በቀረበባቸዉ ጉዳዮች አስቀድሞ ንብረት አፈላልጎ ማሳገድ ከ63% ወደ 64% ለማሳደግ ታቅዶ በአማካይ 51.95% መፈጸም ተችሏል፡፡ ከመረጃዉ ለመረዳት እንደተቻለዉ አፈፃጸሙ ከተቀመጠዉ ግብ አኳያ ከመጨመር ይልቅ በ12.05% መቀነስ ያሳያል፡፡ በመሆኑም የ10 ዓመቱን ግብ ለማሳካት ትላልቅ የሙስና ወንጀሎችን፣ትላልቅ የመንግስትና የህዝብ ገንዘብ

የተመዘበረባቸዉን ጉዳዮች መርጦ ከፍ/ቤት እና ከፖሊስ ጽ/ቤቶች ጋር በቅንጅት በመስራት በተግባሩ ላይ ያለዉን የአፈፃፀም ችግር መፍታት አጠቃላይ ህግ የማስከበር ስራችንን የሚያጎላ በመሆኑ ልዩ ትኩረት ሊሰጠዉ ይገባል፡፡

በሌላ በኩል በሶስት ዓመቱ የአፈፃፀም ክስ ከቀረበባቸዉ ጉዳዮች ዉስጥ የማስፈፀም አቅም ከ97.71% ወደ 98% ለማሳደግ ታቅዶ በአማካይ 95.76% ተፈፅሟል፡፡ በተመሳሳይ በሦስት ዓመቱ አቤቱታ አቀባበል ውሳኔ አሰጣጥና የአቤቱታ ተፈፃሚነትን በተመለከተ አቤቱታ ለሚያቀርቡ የህብረተሰብ ክፍሎች አቤቱታቸውን ለመፍታት ይቻል ዘንድ አስፈላጊውን ቅፅ እንዲሞሉ በማድረግ ህብረተሰቡ የሚያነሳቸውን ቅሬታዎች ለመፍታት ጥረት ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 98% በ2015 ወደ 100% ለማሳደግ ታቅዶ 99.5% መፈፀም የተቻለ ቢሆንም የሚቀርቡ አቤቱታዎች ላይ ወዲያውኑ ፈጣን ውሳኔ የሚሰጥበት አሰራር በመዘርጋት ተፈፃሚነታቸውን በማረጋገጥ ረገድ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ባለመሆናቸዉ ተፈፃሚነትን ከማረጋገጥ አንፃር የሚስተዋሉ በርካታ ክፍተቶችን ያሉ መሆኑን ያሳያል፡፡ በመሆኑም በቀጣይ ቀሪ ዓመታት በዚህ ዙሪያ ያሉ ችግሮችን ቀርፎ የተሻለ ተግባር በማከናወን የህብረተሰቡን እርካታ ማሳደግ ይገባል፡፡

በአጠቃላይ በወንጀልና ፍትሃብሄር ጉዳዮች የህብረተሰቡን ሰላም ለማስጠበቅና የመንግስትንና የህዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ከፍተኛ ስራዎች የተሰሩ ሲሆን በወንጀልም ሆነ በፍትሃብሄር ጉዳይ ከማጥራትና ከማስቀጣት ውጤት ባለፈም ተገቢውን ፍትህ ከማስገኘትና የህብረተሰቡን ደህንነት ከማስጠበቅ አኳያ ትኩረት መስጠት የሚገባ ነው፡፡ በወንጀል የመዛግብት መቋረጥ ምጣኔ ከተያዘው ዕቅድ አንፃር ዝቅተኛ በመሆኑ በቀጣይ ከሚመለከታቸው የፖሊስና ሌሎች አጋር አካላት ጋር በትብብር መስራት ይጠበቃል፡፡

በቀጥታ ክስና መልስ የአቃቢ ህግ ተከራክሮ የማሸነፍ አቅም እና ይግባኝና ሰበር አቤቱታ መዝገቦች የአቃቢ ህግ የክርክር ዉጤታማነት በ3.18% እና በ6.3% በቅደም ተከተል ቅናሽ ያሳያል፡፡

በፍትሃብሄር ጉዳዮች የመንግስትንና የነፃ ህግ አገልግሎት ተጠቃሚዎች (ልዩ ትኩረት የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎችን ጉዳይ) ትኩረት በመስጠት መስራት ቢቻልም ዕቅድ አኳያ ቀሪ ስራዎች መስራት የሚጠበቅ ሲሆን ተቋማት ለማስረጃነት ሲጠየቁ ያለመቅረብ፣ ተገቢ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ሲጠየቁ ያለማቅረብ እና ውል ሳያስመረምሩ ጉዳዮችን በመፈፀም በፍትህ ዉሳኔ

አሰጣጡ ላይ ተጨማሪ ጫና የሚፈጠርበት ሁኔታ ከፍተኛ መሆኑን ያሳያል ። በመሆኑም በቀጣይ በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን በመፍታትና በቅንጅት በመስራት የመንግስትና የህዝብን ጥቅም ማስጠበቅ ይገባል፡፡

በተጨማሪም ጉዳዮችን በድርድር ከመፍታት አንፃርም በመዝገብ አበረታች ውጤት በመኖሩ በገንዘብ ግን ዝቅተኛ አፈፃፀም ያለው በመሆኑ በመዝገብም ሆነ በገንዘብ ያለዉን አፈፃፀም ከፍ ለማድረግ በትኩረት መስራት ይጠይቃል፡፡ ጉዳዮችን በድርድር መጨረስ ጊዜ፣ ገንዘብና ጉልበትን ለመቆጠብ የሚረዳ በመሆኑ ከክስ በፊት ጉዳዮችን በድርድር የመፈፀም አቅምን በማጎልበት ጉዳዮች ለዐ/ህግ እንደቀረቡ በድርድር የመፍታት አማራጭን መጠቀም በትኩረት ሊሠራበት ይገባል፡፡

### 3.4.2. የሥነ-ምግባር እና ጸረ-ሙስና አፈጻጸም

የሥነ-ምግባር ግንባታ እና ሙስናን መከላከል ተልዕኮ ለመወጣት የአሠራር ሥርዓት፣ስትራቴጂ እና አደረጃጀት በተከታታይ ማሻሻልና በብቃት ማረጋገጥ፣ የሥነ-ምግባር ግንባታ፡ በሥነ-ምግባር የታነጹ፣ ሙስናን የሚጠየፉና በጽናት የሚታገሉ አመራሮች፣ ሠራተኞች እና ዜጎች እንዲበራከቱ በትብብር መሥራት፣በመንግሥት ተቋማት ሙስናና ብልሹ አሠራር በዘላቂነት እንዲቀንስ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት፣የሙስና እና ብልሹ አሠራር ችግሮች መረጃ እና ማስረጃ በማደራጀት፣ የሕዝብ እና የመንግሥት ሀብት ከብክነት ለማዳን ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር እና በቅንጅት መሥራት የሚሉት ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው፡፡በዚህ መሠረት ኮሚሽኑ ሙስናን በመከላከል ዙሪያ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ለማድረግ የ10 ዓመት መሪ እቅድ ተዘጋጅቶ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት በተቋሙ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትን አፈፃፀም ትንተና እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡
በክልሉ ውስጥ በአስር አመቱ እቅድ በልማትና በመልካም አስተዳደር ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትሉ የሙስና ወንጀሎችን፣ብልሹ አሠራሮችን ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት ለመዘርጋትና ተፈጽመው ሲገኙም አስተማሪ የሆነ እርምጃ መውሰድ የሚቻልበት ደረጃ ላይ ለመድረስ የመንግሥትና የሕዝብን መብትና ጥቅም ለማስከበር ትብብርና አጋርነትን ከህብረተሰቡ እና ከሚመለከታቸው አካላት በየደረጃው ለማረጋገጥ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡

በሥነ ምግባር እና ፀረ ሙስና ዙሪያ ሕብረተሰቡ የአመለካከት ለውጥ እንዲያመጣና ሙስናን የሚጠየፍ ማህበረሰብ ለመፍጠር፣ በፊት ለፊት ትምህርት በሦስት ዓመቱ በጥቅል 1,452,775

የሕብረተሰብ ክፍል ሥልጠና መስጠት ታቅዶ ለ1,980,656 /100%/ የህብረተሰብ ክፍሎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ለመስጠት ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ የተቋሙን ዋና ተልዕኮ ከማሳካት አንፃር የተገልጋዮችን እርካታ 75% ለማድረስ ታቀዶ ማከናወን አልተቻለም፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ሰዓት በህብረተሰቡ ዘንድ ሙስናን የማይሸከምና የሚጠየፍ ማህበረሰብ ከመፍጠር አኳያ የሚፈለገዉ የግንዛቤና የአመለካካት ለዉጥ የታየበት አይደለም፡፡ ስለሆነም በቀጣይ ቀሪ ዓመታት የህብረተሰቡን የአመለካከት አድማስ ሊያሰፉ የሚችሉ የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮችን በማዘጋጀት እና ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በቅንጅትና በትብብር መስራት ይጠበቃል፡፡

በሦስት ዓመቱ ሙስናን ለመከላከል 30 የአሰራር ጥናቶችን በተቋማት በማካሔድ ለሙስና ተጋላጭነታቸዉን ለማስተካከል ታቅዶ 17 (56.6%) የአሰራር ጥናቶችን ማካሄድ ተችሏል፡፡ ይሁን እንጅ የተጠኑ ጥናቶችን ወደ ተግባር በማሸጋገር በኩል ዉስንነት የታየበት በመሆኑ በቀጣይ ከተቋማት ጋር በጥናቶቹ ዙሪያ ተጨማሪ ዉይይቶችን በማሄድና በማዳበር ወደ ተግባር ማሸጋገር ይገባል፡፡

የመንግስት ባለስልጣናትን ሀብትና ንብረት በመመዝገብ ለሙስና ተጋላጭነትን ለመቀነስና የመንግስትን ሃብት ከዘረፋ ለማደን በሦስት ዓመቱ 80,731 ሃብት አስመዝጋቢዎችን የሃብት ምዝገባና የ450 ሃብት አስመዝጋቢዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ታቅዶ 68,654 /85%/ ሃብት ምዝገባና የ383 /85%/ ሃብት አስመዝጋቢዎችን ሃብት ትክክለኛነት ማረጋገጥ (ቬርፊኬሽን) ስራ ለመስራት ተችሏል፡፡ ከመረጃዉ መረዳት እንደተቻለዉ ተቋሙ የመንግስት ባለስልጣናትን ሀብትና ንብረት በመመዝገብ የሙስና ተጋላጭነታቸዉን መቀነስ ተግባሩ ግቡን ያላሳካ መሆኑን ያሳያል፡፡ በመሆኑም የመንግስት ባለስልጣናትን ሀብትና ንብረት ከመመዝገብ ባለፈ የሙስና ተጋላጭነታቸዉን በመቀነስ ረገድ ያመጣዉን ፋይዳ ስለማያሳይ በቀጣይ በመጣዉ ለዉጥ ዙሪያ በጥናት መለየት ይኖርበታል፡፡

የሙስና መንስኤዎችንና መከላከያ ስልቶችን መቀየስ በተመለከተ ባለፉት ሦስት ዓመታት 12 ከፍተኛ በጀት የሚመደብባቸውን እና የአሰራር ክፍተት የሚታይባቸውን ተቋማት በመለየት የአሰራር ሥርዓታቸውን በጥናት በማረጋገጥ የመፍትሄ ሀሳብ ለማቅረብ ታቅዶ በ4 (33%) ተቋማት ጥናቱን ማከናወን ተችሏል፡፡ ከመረጃዉ ለመረዳት እንደተቻለዉ አፈፃፀሙ በጣም ዝቅተኛ ከመሆኑም በላይ በፀጥታ ችግር ምክንያት ወደ ጥናቱ ወደ ተግባር ያልተሸጋገረ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም በዚህ ዙሪያ ያለዉን ችግር በመፍታት በቀጣይ ቀሪ ዓመታት

የተጠኑ ጥናቶች ላይ ተጨማሪ ዉይይቶችን ከተቋማቱ ጋር ማካሄድ ዉጤታማ በሆነ መልኩ ወደ ተግባር በማስገባት የሙስና መንስኤዎችን ማድረቅ ይገባል፡፡

በአጠቃላይ በኮሚሽኑ ከታቀዱ ተግባራት አንፃር ሙስናን ከመከላከልና ዉጤታማነትን በማሻሻል በኩል በተግባር ዝቅተኛ አፈጻፀም ላይ የሚገኝ ከመሆኑም በተጨማሪ በሂደት ላይ ያለና ዉጤቱን የማያሳይ ነዉ፡፡ በተመሳሳይ  የሀብት ምዝገባና ማሣወቅን እንዲሁም ሌሎችም ጥናቶች በዕቅዳቸዉ መሠረት ያልተሳኩ መሆናቸዉን መረጃዉ ያመለክታል፡፡ ከዚህ ባሻገር የኮሚሽኑ ስልጣን የነበረዉ የሙስና ወንጀሎች ምርመራና ክስ ተነስቶ ወደ ፖሊስና ፍትህ በመሄዱ በህበረተሰቡ ዘንድ የኮሚሽኑን ሚና አሳንሶ ማየት፣ ወቅታዊ የፀጥታ ችግሮችና ሌሎችም ለዕቅዱ አለመሳካት ምክንያቶች ናቸዉ፡፡ በመሆኑም በቀጣይ የተቋሙን ተልኮ ከማሳካት አንፃር ሙስናን በተግባር ታግሎ ለልማትና መልካም አስተዳደር እንቅፋት እንዳይሆን ከማድረግና በተግባር የሚታይ ዉጤት ለማምጣት ሰፊ ግንዛቤ የማሳደግ ስራ መስራት፣ ሙስና መከላከልንና የተጠያቂነት አሰራሮችን እና የተቋማትን ቅንጅታዊ አሰራር የሚመልስ ህጋዊ የአሰራር ማዕቀፍ  በማዘጋጀት በኩል በቀጣይ ትኩረት ሊሰጠዉ ይገባል፡፡

### 3.5. የመንግስት ኮሙኒኬሽን ዘርፍ አፈጻጸም

የኮሚኒኬሽን ሥራ ዓላማ ዘላቂነት ባለው በዋና ዋና ሀገራዊ ክልላዊ ጉዳዬች ላይ መግባባት ፈጥሮ በሠላም፣በልማትና በመልካም አስተዳዳር ፕሮግራሞች ውስጥ የራሱ ሚና የሚጫወት ለሀገሩና በብሄራዊ ጥቅሞቹ ላይ በምክንያታዊነት ብያኔ የሚሰጥና በመረጃ የረካ ማሕበረሰብ መፍጠር የሚችል አቅም መገንባት ነው፡፡የትኩረት አቅጣጫው ደግሞ በዋና ዋና ሃገራዊና ክልላዊ ጉዳዮች ላይ መግባባት መፍጠር ፣የክልሉን ታሪክ፣ባህልና አሴቶች እንዲታወቁና ለብልጽግና ጉዞ መሰረት ሆነው እንዲያገለግሉ የሚያስችል ሁኔታ በመፍጠር የተነደፉ የልማት ፣የሰላም ፣የመልካም አስተዳደርና የዲሞክራሲ ግንባታ ስርዓት ውስጥ አጠቃላይ መግባባት ተፈጥሮ እንቅስቃሴ እንዲደረግ ማስቻል በመሆኑ በአስር ዓመቱ ዕቅድ ዘመን የተነደፉ ፕሮግራሞችንና የተቀመጡ ግቦች እንዲሳኩ የለውጥ መሣሪያ ሆኖ እንዲያገለግል ማድረግ ነው፡

በክልል ደረጃ የሚዲያና ኮሙዩኒኬሽን አመራር ፎረም (በወር አንድ ጊዜ) እና የኮሙዩኒኬሽንና የህዝብ ግንኙነት የሚዲያ ፎረም (በሩብ ዓመት 1 ጊዜ ) እንዲሁም  በዞኖችና በወረዳዎች የአማተር የኪነ-ጥበባት ዘርፍ ሙያተኞችን ፎረም (በወር 1 ጊዜ) ማካሄድኝ በተመለከተ የተካሄደ የሚዲያና የኮሙዩኒኬሽን አመራር ፎረም በሶስቱ ዓመታት 36 ለማከናወን ኢላማ

ተይዞ 31 ተከናውኗል፡፡ ይህም ከሶስት ዓመቱ 86.11 በመቶ የተከናወነ ሲሆን ከአስር ዓመቱ 23.4 በመቶ ተፈጽሟል፡፡ እንዲሁም የተካሄደ የኮሚዩኒኬሽን የሕዝብ ግንኙነትና ሚዲያ ፎረም በሶስት ዓመታት ውስጥ 12 ታቅዶ 12ቱን ተከናውኗል፡፡ በሶስት ዓመት 100% በአስር ዓመት 10 በመቶ ብቻ ማከናወን መከን መቻሉ መረጃው ያሳያል፡፡

በዋና ዋና ክልላዊና ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ መግባባት በመፍጠር የክልሉን ልማታዊ አስተሳሰብ ከማጎልበት አንጻር በክልል ቢሮ ፣ በዞኖችና በከተሞች በሩብ ዓመት 1 ጊዜ በወሣኝ ጉዳዮች ላይ የክልሉን መንግስት አቋም የሚያንፀባርቁ (የአቋም መግለጫ) ጽሁፎችን በማዘጋጀትና በሚዲያዎች በማቅረብ ግንዛቤ መፍጠርና የሕብረተሰቡን ተሣትፎ ማሣደግን በተመለከተ በክልል እና በዞን ደረጃ ተዘጋጅተው በሚዲያ የቀረቡ ጹሁፎች ብዛት በቁጥር (የአቋም መግለጫ) ለሶስት ዓመታት 13 ታቅዶ 16 ተከናውኗል ለሶስት ዓመት 123 በመቶ ከአስር ዓመት 40 በመቶማከናወን ተችሏል ይህም ከአስር ዓመቱ ኢላማ አንጻር በቀሪ ዓመታት ከዚህ በበለጠ ተጠናክሮ መስራት ይጠበቃል፡፡በተጨማሪም በዞንና በከተማ ተዘጋጅተው በሚዲያ የቀረቡ ጹሁፎች ለሶስት ዓመታት 459 ለማከናወን ታቅዶ 509 በማከናወን የእቅዱን 110.89 በመቶ ማከናወን ሲቻልለአስር ዓመት 28.2 በመቶ ብቻ ተከናውኗል፡፡

በክልል ቢሮ ፣ በዞኖችና በከተሞች በሩብ ዓመት 1 ጊዜ በወሣኝ ጉዳዮች ላይ የክልሉን መንግስት አቋም የሚያንፀባርቁ (የአቋም መግለጫ) ጽሁፎችን በማዘጋጀትና በሚዲያዎች በማቅረብ ግንዛቤ መፍጠርና የሕብረተሰቡን ተሣትፎ ማሣደግን በተመለከተ በክልል ደረጃ የተፈጠረ የፓናል ውይይት መደረክ ለሶስት ዓመታት 12 ኢላማ ተይዞ 6 የተከናወነ ሲሆን ከሶስት ዓመቱ 50 በመቶ ከአስር ዓመት 15 በመቶ ብቻ እንደተከናወነ መረጃው ያሳያል፡፡ በተጨማሪም በዞን ደረጃ የተፈጠረ የፓናል ውይይት መደረክ ላለፉት ሶስት ዓመታት 2,211 ታቅዶ 2,101 ተከናውኗል፡፡ ከሶስት ዓመት 95 በመቶ ከአስር ዓመት 28.3 በመቶ ብቻ ለማከናወን ተችሏል፡፡

በተመረጡ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የፕሬስ ኮንፈረንስ /የሚዲያ መግለጫ / በማካሄድ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ ላይ በክልል ደረጃ የተፈጠረ የፕሬስ ኮንፈረንስ ለሶስት ዓመታት 37 ታቅዶ 109 ማከናወን ተችሏል በዚህም በሶስት ዓመት 294.5 በመቶ ከአስር ዓመት 90.8 በመቶ ተፈጽሟል፡፡ የተፈጠረ የፕሬስ ኮንፈረንስ (ሚዲያ መግለጫ) 6,671 ለሶስት ዓመታት ኢላማ በመያዝ 5,572 ሲከናወን በሶስት ዓመት 83.5 በመቶ ለአስር ዓመት 29.8 በመቶ ብቻ ተከናውኗል፡፡

የመንግስት ኮሚዩኒኬሽንና የሚዲያ አሰራሮችን ብቃት ከማጎልበት አኳያ በዚህም መሰረት ክልላዊ የሚዲያ አውታር በመዘርጋት የሚዲያ ተደራሽነትንና ተጠቃሚነትን ከማሳደግ አንጻር ህብረተሰቡ ለመረጃ ቅርበት ኖሮት በልማት፣ በመልካም አስተዳደርና በዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ንቁ ተሳታፊ መሆን እንዲችል የአካባቢ ሚዲያዎችን ማቋቋም እና ለማጠናከር ለሶስት ዓመት 226 አዲስ ሚኒ ሚዲያ ማስፋፋትና 2,718 አዲስና ነባር ሚኒ ሚዲያዎችን ክትትል እና ድጋፍ ለማድረግ ኢላማ ተይዞ ለ226 አዲስ ሚዲያዎች 2,718 አዲስና ነባር ሚኒ ሚዲያዎችን ክትትል እና ድጋፍ ተደርጓል፡፡ ከዚህ ለማየት እንደሚቻል የአስር ዓመት ኢላማ የሌለውና ያልተከናወነ በመሆኑ ተግባሩን በውል መግለጽ አልተቻለም፡፡48 አዲስ ማስታወቂያ ሰሌዳ ማስፋፋት 9,439 በሶስት ዓመታት ኢላማ ተይዞ 8497 ተከናውኗል በሶስት ዓመት የእቅዱን 90 በመቶ በአስር ዓመት 24.7 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡እንዲሁም 3,315 ለአዲሶችና ለነባር ማስታወቂያ ሰሌዳ ክትትል እና ድጋፍ የተደረገላቸው ነባር ማስታወቂያ ሰሌዳ 13,588 ለሶስት ዓመታት ኢላማ በመያዝ 10,765 የተከናወነ ሲሆን ለሶስት ዓመት 79.2 በመቶ ለአስር ዓመት 79.2 በመቶ ተከናውኗል፡፡በተጨማሪም 36 አዳዲስ የመረጃ ማእከላትን ማቋቋም እና 2,406 ለነባር የሚዲያ ማዕከላት ክትትልና ድጋፍ ማድረግ በአዲስ የተቋቋሙ የመረጃ ማእከላት ለሶስት ዓመታት 178 ኢላማ ተይዞ 157 የተፈፀመ ሲሆን ለሶስት ዓመት 88.2 በመቶ ለአስር ዓመት 61.3 በመቶ ማናወን ተችሏል፡፡እንዲሁም 19 አዳዲስ የቲቪ ፓርክ ማቋቋም እና 437 ለነባር ቲቪ ፓርኮች ክትትልና ድጋፍ ማድረግ 118 ኢላማ ተይዞ ለሶስት ዓመታት 65 ለማከናወን ታቅዶ 60 የተከናወነ ሲሆን ለሶስት ዓመት 60 በመቶ ከአስር ዓመት 50.8 በመቶ ማከናወን ተችሏል፡፡በክልሉ ተቋቁመው ለሚገኙ የማህበረሰብ ሬዴዮ በየዓመቱ በወር 1 ጊዜ ድጋፍ ማድረግ ለሶስት ዓመታት 24 በማቀድ 23 የተከናወነ ሲሆን ለሶስት ዓመት 95.8 በመቶ ከአስር ዓመት 287.5 ከመቶ ፐርሰንት በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡ ስለሆነም የእቅድ ችግር ያለበት መሆኑን ያመላክታል፡፡

ከአጎራብች ክልሎች፣ ዩኒቨርስቲዎች ማዕከላት እንዲሁም ተቋማት ጋር ቅንጅታዊ አሰራርን/ ትስስርን ማሳደግ በሚመለከት ህዝቡ በልማትና መልካም አስተዳደር ሥራዎቻችን ላይ ከሚያነሳው የህዝብ አስተያየት በመነሳት ልማታዊ አስተሳሰቡና ተሳታፊነቱ እንዲያድግ የተለያዩ የህዛብ መድረኮች በማዘጋጀት ግልጽነት መፍጠር ለሶስት ዓመታት 3 ለማከናወን ኢላማ ተይዞ 3 ተከናውኗል፡፡ ከሶስት ዓመቱ 100% ከአስር ዓመቱ 30 በመቶ ብቻ ማከናወን ተችሏል፡፡እንዲሁም ከአጎራባች ክልሎች እና ከተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ጋር በተለያዩ የጋራ

ጉዳዮች ላይ የጋራ ውይይት፣ የልምድ ልውውጥ ጉብኝት በማዘጋጀት የመደጋገፍ ስራ መስራት ከክልሎች ጋር የተፈጠረ የልምድ ልውውጥ መድረክ ለሶስት ዓመት 6 ታቅዶ 3 በማከናወን የእቀዱን 50 በመቶ የተከናወነ ሲሆን ከአስር ዓመቱ 15 በመቶ ብቻ ማከናወን ተችሏል፡፡ የክልሉ መንግሥትና ህዝብ ከሌሎች አጎራባች ክልሎችና ህዝቦች ጋር ያለው ግንኙነት ጤናማና በመደጋገፍ ላይ የተመሰረተ መሆኑን የሚያሣዩና የሚያስገነዝቡ ትንታኔዎችን ማዘጋጀት 12 ለሶስት ዓመት እቅድ ተይዞ 12 በማከናወን ለሶስት ዓመት 100 በመቶ ከአስር ዓመት 30 በመቶ ብቻ ማከናወን ተችሏል፡፡

ስለ ክልላችን ሁለንተናዊ የገጽታ ግንባታና የጋራ መግባባት ዙሪያ የመረጃ አቅርቦትና ጥራትን ከማሻሻል አንጻር ሁነቶችን በመፍጠር በሚገኘው አጋጣሚ ሁሉ ለህዝቡ አስተማሪ የሆኑ መልዕክት/ በወር 1/፣ ፎቶ ኤግዚብሽን /በሩብ ዓመት 1/፣ አዘጋጅቶ ለህብረተሰቡ መረጃዎችን ማስተላለፍን በተመለከተ በዞን ደረጃ የተዘጋጀ መልእክት (ሞቶ) ለሶስት ዓመታት 6,649 ኢላማ በመያዝ 7,939 የተከናወነ ሲሆን ከሶስት ዓመት 119 በመቶ ከአስር ዓመት 35.7 በመቶ ብቻ ማከናወን ተችሏል፡፡ይህም ከአስር ዓመት ኢላማው በቀሪ ዓመታት ቀሪ ተግባራትን ማከናወን እንደሚቻል ያሳያል፡፡እንዲሁም በክልል ደረጃ የተዘጋጀ የፎቶ ኤግዚብሽን በኢላማ ደረጃ መያዝ ባይቻልም ለሶስት ዓመታት 42 የፎቶ ግራፍ ኤግዚቢሽን ለማከናወን ኢላማ ተይዞ 35 ተከናውኗል፡፤ከሶስት ዓመት 83.3 በመቶ ከአስር ዓመት 0% ማከናወን ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በዞን ደረጃ የተዘጋጀ የፎቶ ኤግዚብሽን ለሶስት ዓመታት 6,159 ኢላማ በመያዝ 7,424 ተከናውኗል፡፡ ከሶስት ዓመት 120 በመቶ ከአስር ዓመት 99.2 በመቶ ማከናወን የተቻለ በመሆኑ ኢላማውን ለማሳካት ተግባራት መከናዎናቸውን ያሳያል፡፡

የሚዲያ ሽፋን ለሚያስፈልጋቸው ዋና ዋና ክልላዊና መንግስታዊ ጉዳዮች ለሚዲያ አካላት በተደራጀ ሁኔታ የሚዲያ ዘገባ ጥቆማ የመስጠት ስራ መስራት፡-በክልል ደረጃ በጹሁፍ የተዘጋጀ የሚዲያ ዘገባ ጥቆማ ለሶስት ዓመታት 80 ኢላማ በመያዝ 314 የተከናወነ ሲሆን ለሶስት ዓመት 392 በመቶ ከአስር ዓመት 130.8 በመቶ ተፈጽሟል፡፡ እንዲሁም በዞን ደረጃ በጹሁፍ የተዘጋጀ የሚዲያ ዘገባ ጥቆማ ለሶስት ተከታታይ ዓመታት 6,626 ለማከናወን በእቅድ ተይዞ 9,533 የተከናወነ ሲሆን ከሶስት ዓመቱ 143.8 በመቶ ከአስር ዓመት 42.7 በመቶ እቅዱን ማከናወን ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በሳምንት 1 ጊዜ በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ሣምንታዊ መረጃዎችን መቀበልና ለውሣኔ ሰጪ አካላት ማቅረብና ተሰብስበው ለውሳኔ ሰጭ አካላት የቀረቡ ሳምንታዊ መረጃዎች ለሶስት ዓመታት 1,084 በማቀድ 604 የተከናወነ

ሲሆን ለሶስት ዓመታ 55.72 በመቶ ከአስር ዓመት 116.1 በመቶ ማከናወን ተችሏል፡፡በእቅድ ዘመኑ የመንግስትና የግል ሚዲያዎችን ሚዲያ ዳሰሳ በማድረግ በየወሩ የተዳሰሱ ሚዲያዎችን የአዝማሚያ ትንተና ወይም ጭማቂ ሰነድ በአወንታና በአሉታ ለይቶ በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካላት መስጠትን በሚመለከት ለሶስት ዓመታት 36 የአዝማሚያ ትንተና ለማከናወን ታቅዶ 36 የተከናወነ ሲሆን ከሶስት ዓመት 100 በመቶ ከአስር ዓመት 21.1 በመቶ ማከናወን መቻሉን ማዬት ተችሏል፡፡

በቢሮ ደረጃ በዘርፉ /በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በመልካም አስተዳደር /ዙሪያ በየወሩ የተነተነ መረጃ ለአስር ዓመት 30 ኢላማ ተይዞለት በተከታታይ ሶሶት ዓመታት 9 ለማከናወን ኢላማ ተይዞ 9 ተከናውኗል ለሶስት ዓመት 100 በመቶ ከአስር ዓመት 30 በመቶ ብቻ ተከናውኗል ፡፡ እንዲሁም በዞኖች በወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ የተነተነ መረጃ 2,183 ለሶስት ዓመታት ለማከናወን ኢላማ ተይዞ 2,186 ፈጽሚል፡፡ ከሶስት ዓመት 101በመቶ ከአስር ዓመት 28.1በመቶ ማከናወን መቻሉን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የተዘጋጀ አመታዊ መጽሀፍ ብዛት በዕትም በኢላማ ደረጃ ተይዞ 13 ተይዞ ለሶስት ዓመታት 3 ታቅዶ 3 ከሶስት ዓመት 100 % ከአስር ዓመት 23 በመቶ ተከናውኗል፡፡

ህብረተሰቡን ለልማት የሚያነሳሱ የሚዲያ ውጤቶችን ተደራሽነት ከማሳደግ አኳያ በክልል ደረጃ ደረጃውን የጠበቀ ሀዲስ መጽሄት ዝግጅት የክልሉን ኢኮኖሚያዊ፣ማበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን ለህብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ የተዘጋጀ መጽሄት በእትም ለሶስት ዓመት 12 ለማድረስ ኢላማ ተይዞ 10 የተከናወነ ሲሆን ከሶስት ዓመቱ 83.3 በመቶ ከአስር ዓመቱ 25 በመቶ ብቻ ማከናወን ተችሏል፡፡በተጨማሪም የተዘጋጀ ሀዲስ መጽሄት ብዛት በቅጅ(የተጫነ መጽሄት ብዛት ) ለሶስት ዓመታት 8,215 እቅድ ተይዞ 8,524 ተከናውኗል፡፡ከሶስት ዓመቱ 103 በመቶ ከአስር ዓመቱ 31.3 በመቶ ብቻ ማከናወን የተቻለ በመሆኑ በተያዘለት የጊዜ ገደብ እቅዱን ማሳካት እንደማይቻል ያመላክታል፡፡ የተዘጋጀ በራሪ ወረቀት በቅጅ በተከታታይ ሶስት ዓመታት 3,410,009 በማቀድ 3,343,238 የተከናወነ ሲሆን ከሶስት ዓመት 55 በመቶ ከአስር ዓመት 24.6 ብቻ ማከናወን እንደተቻለ ያሳያል፡፡ እንዲሁም የተሰራጨ በራሪ ወረቀት ለአስር ዓመቱ ኢላማ 13,570,000 ሲሆን ለሶስት ዓመታት 3,410,000 በማቀድ 3,343,224 ተፈጽሟል ለሶስት ዓመት 98.04 በመቶ ለአስር ዓመት 24.6 በመቶ ብቻ እንደሆነ ያሳያል፡፡ በተጨማሪም የተዘጋጀ ፖስተር ብዛት በዕትም የተያዘው ኢላማ 40 ሲሆን ለሶስት ተከታታይ ዓመታት 12 በእቅድ ተይዞ 10 ተከናውኗል፡፡ ከሶስት ዓመት 83.3 በመቶ ከአስር ዓመት 25

በመቶ ብቻ ተፈጽሟል ። በሌላ በኩል የተዘጋጀ ፖስተር ብዛት 120,000 ኢላማ የተያዘ ሲሆን ለሶስቱ ዓመታት 24,000 ለማከናወን ኢላማ ተይዞ 12000 የተከናወነ ሲሆን ከሶስት ዓመት 50 በመቶ ከአስር ዓመት 10 በመቶ ብቻ እንደተፈጸመ ያሳያል።

በዞን ደረጃ ለአካባቢ ማስተማሪያ የሚውል የአካባቢ ማስተማሪያ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት በቲቪ ፓርክ ማስተላለፍ  ለሶስት ዓመት 7,164 ኢላማ ተይዞ 7,048 የተከናወነ ሲሆን ከሶስት ዓመት 98.3 በመቶ ከአስር ዓመት 29.5 በመቶ ብቻ  ማካናወን እንደተቻለ መረጃው ያመላክታል።

በልዩ ልዩ የኮሙዩኒኬሽንና የመረጃ አቅርቦቶች ተፈላጊነት ላይ የሚደረጉ ጥናቶችን ማጎልበትን በሚመለከት ህብረተሰቡ የሚያነሳቸውን የተለያዩ ጥያቄዎች በተደራጀ ሁኔታ መረጃዎችን በመሰብሰብ መደበኛ የሆነ የህዛብ አስተያየት ጥናት የማካሄድ ስራ ተከናውኗል። በዚህም በክልል ደረጃ  የተጠና መደበኛ የህዝብ አስተያየት ጥናት በሰነድ ለሶስት ተከታታይ ዓመታት 6 ታቅዶ 3 ተከናውኗል። ለሶስት ዓመታት 50 በመቶ ከአስር ዓመታት 50 በመቶ% እንደተፈጸመ መረጃው ያሳያል።

በአጠቃላይ የኮሙኒኬሽን ቢሮ በአስር ዓመታት ውስጥ አከናውናለሁ ብሎ የያዛቸውን ኢላማዎች በሶስት ዓመት ውስጥ ለማከናወን ጥረት የተደረገ ሲሆን ቀሪ ያልተከናወኑ ከሶስት ዓመት ኢላማ የቀሩ ተግባራት በቀሪ ዓመታት የሚከናወኑ ሲሆን በክንውን ወቅት አፈጻጸማቸው የተሻሉ ተግባራት ውጤታማ የሆኑት ሁሉንም ተግባራት በተያዘላቸው  የጊዜ ገደብ ትኩረት ሰጥቶ በመስራት ጥሩ ውጤት እንደተገኘ ተመላክቷል።ቢሆንም ከእቅድ በታች የተከናወኑ በርካታ ተግባራትን ለማከናወን  ከአደረጃጀት  አኳያ የማህበራዊ ሚዲያው ክልል ላይ በስድስት ባለሙያዎች ብቻ ተንጠልጥሎ ወደታች ዞንና ወረዳ ድረስ ባለመውረዱ ሁሉንም ተግባራት በሃላፊነት ወስዶ ለማከናወን ችግር የፈጠረ ከመሆኑ በተጨማሪ የበጀት ችግር መድረኮችን በየአካባቢውና ከአጎራባች ክልሎች ጋር የምክክር መድረክ ማደረግ አለመቻል እና ድጋፍና ክትትል ለማድረግ የተሸከርካሪ ችግር የአስር ዓመት ኢላማውን በተያዘለት የጊዚ ገደብ ለማከናወን ሰፊ ክፍተት የነበረው በመሆኑ ፣እንዲሁም ወቅታዊ ችግሩ እስከታች ድረስ በሪፖርትም ይሁን በአንዳንድ ስራዎች ለመገናኘት እንዲሁም የኢንተርኔት ችግሩ አለመቀረፍ መረጃዎችን በወቅቱ ለማቅረብ የነበሩ ችግሮች መሆኑን ለማመላከት ተችሏል። በመሆኑም በቀሪ ጊዜያት ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይገባል።

### 3.6. ዘላቂ የልማት ፋይናንስ ማረጋገጥ

በክልሉ የልማት ፋይናንስ ማመንጨትና ዘላቂነቱን ማረጋገጥ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ በአለፉት ዓመታት የክልሉን ገቢ በማሳደግ ረገድ አበረታች ሥራዎች የተከናወኑ ቢሆንም ክልሉ ለልማት ከሚያስፈልገው ወጪ እንዲሁም ከሚያመነጨው ሀብት አንፃር ሲመዘን የገቢ አሰባሰቡ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ስለሆነም በቀጣይ የዕቅዱ ዓመታት በክልሉ የሚሰበሰብ ገቢን በእጅጉ የማሳደግ እና በራስ ገቢ ወጪን የመሸፈን አቅምን ማጎልበት ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ፡፡

## ክፍል አራት፡- የእቅድ አፈጻጸሙ ጠንካራ ጎኖችና ክፍተቶች

### 4.1. የእቅድ አፈጻጸሙ ጠንካራ ጎኖችና እና ክፍተቶች ማጠቃለያ

የአስር  ዓመቱን መሪ ዕቅድ በመፈጸም ህብረተሰቡን ወደ ተሻለ የኑሮ ደረጃ ለማሸጋገርና ሁለንተናዊ ዕድገት ለማረጋገጥ እንዲቻል ባለፉት ሶስት የበጀት ዓመታት የታቀዱ ተግባሮቻችንን ለመፈጸም ሰፊ ርብርብ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ በመሆኑም የተቀረጹት ግቦች መሳካታቸውን ለመለካት የተጠቀምንባቸውን  የየዘርፎች የተለያዩ አመልካቾችን መሰረት በማድረግ የክልሉን የልማትና መልካም አስተዳደር እቅዶች አፈጻጸምን ስንወስድ በተደረገው ጥረት ቀላል የማይባሉ አፈጻጸሞቻችን አበረታች መሆናቸውን ያሳያል።ከዚህ አንጻር የግብርና ምርትና ምርማነትን በማሳደግ በክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገት ውስጥ ትልቅ ድርሻ እንዲኖረው ለማስቻል ምንም እንኳን እጥረት ቢታይበትም የቴክኖሎጂና የግብዓት አቅርቦት ተግባር ሲሰራ ቆይቷል። በመሆኑም የግብርናው ዘርፍ የክልሉን ኢኮኖሚ ከመደግፍ አንጻር እስካሁን ድረስ ትልቁን ድርሻ ይዞ መቀጠሉን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ ካስቀመጥነው ትልቅ ግብ አንጻር  ሁሉንም ሳይንጠባጠቡ ውጠታማ ከማድረግ አንጻር ሰፊ ክፍተቶች በመሆናቸው ከግብርና ልማቱ ማግኘት የሚገባን ምርት በታሰበው መንገድ አለመገኘቱን መረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም በቀጣይ የአምስት አመት ዕቅድ ዘመን እምርታዊ የግብርና ምርት ዕድገት ለማምጣት የተጀመሩ ጥረቶችን አጠናክሮ መቀጠል ይገባል።በተለይም የህዝብ ንቅናቄን ማዕከል በማድረግ የተጀመሩትን የመስኖ፣ የመካናይዜሽን እና የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ስራዎች ዘላቂነት ላለው የግብርና ምርት ዕድገት ወሳኝ በመሆናቸው አጠናክሮ መቀጠል ተገቢ ይሆናል።

በሌላ በኩል የገጠሩንና የከተማውን መሰረተ ልማት አቅርቦት ለማሳደግ በሚደረግ ጥረት ውስጥ የገጠር እና ከተማ መንገድ ግንባታ በስፋት ተከናውኗል። በዚህም የተነሳ ቀደም ሲል የገጠሩና ከተማው ህብረተሰብ የነበረውን የመንገድ ተደራሽነት ችግር ለማቃለል የተደረገው ጥረት ወሳኝ ድርሻ ነበረው። በተለይም የገጠር ቀበሌ ማዕከሎችን ከዋና መንገድ ለማስተሳሰር እንዲቻል በመካሄድ ላይ ያለው የገጠር መንገድ ተደራሽነት ፕሮግራም ለልማታችን መሳለጥ የሚኖረው ፋይዳ በቀላሉ የሚገመት አይደለም።በገጠርም ሆነ በከተማ ያለውን ህብረተሰብ የንጹህ ውሃ ተጠቃሚነት ለማሻሻል ሰፊ የመሰረተ ልማት ተቋማት ተገንብተው አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ።

ይሁን እንጂ ተጀምረው ያላለቁ እና አገልግሎት መስጠት ጀምረው የተበላሹና አገልግሎት ያቋረጡ የልማት ተቋማት በመኖራቸው የመስጠት ሽፋኑን ዝቅተኛ እንዲሆን አድርጎታል እንዲሁም እና በከተማ የመጠጥ ውሀ ብክነት ከመቀነስ ይልቅ እየጨመረ መምጣቱን ያሳያል፡፡ በመሆኑም በቀጣይ ፕሮጀክቶችን አስጀምሮ በማጠናቀቅ እና የተሰሩትን በመንከባከብና በመጠገን በኩል ያሉ ክፍተቶችን ሊያስተካክሉ የሚችሉ ስትራቴጂዎችን በመንደፍ መንቀሳቀስ ይገባል፡፡

በከተሞች አካባቢ የሚታየውን ድህነት ለመቅረፍ ብሎም ለኢንዱስትሪው መሰረት የሚሆኑ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ተቋማትን ለማስፋት የሚያስችሉ ልዩ ልዩ ድጋፎችን በማሟላት በርካታ ተቋማት እንዲቋቋሙ በማድረግ በርካታ ዜጎች የስራ እድል ያገኙ ቢሆንም አብዛኛዎቹ የተቋቋሙት ኢንተርፕራይዞች በሚፈለገው መልኩ የተደገፉ ባለመሆናቸው የሚፈለገውን ውጤት ማስመዝገብ አለመቻላቸውን እንዲሁም ለበርካታ ዜጎች የተፈጠሩት የስራ እድሎች ጊዜያዊ በመሆናቸው የዜጎችን ችግሮች በዘላቂነት እየፈቱ አለመሆናቸው በጉልህ የሚታይ ጉድለት በመሆናቸው በተሻለ እቅድና በተናበበ የእቅድ ትግበራ የድጋፍና ቁጥጥር ስራዎች አጠናክሮ መስራት ይጠይቃል፡፡

በማህበራዊ ልማቶቻችንም የየደረጃውን ትምህርት ከማስፋት ጎን ለጎን ጥራቱን ለማስጠበቅ በሚደረጉ ጥረቶች በርካታ ግብዓቶች እንዲቀርቡ በመደረግ ላይ ነው። ከአስር አመቱ እቅድ በፊት የየደረጃው የትምህርት ሽፋን በከፍተኛ ደረጃ እያደጉ እንደነበር ቢታወቅም በእነዚህ የሶስት አመታት እቅድ ዘመናት የትምህርት ሽፋኑ እያሽቆለቆለ መምጣቱን ያሳያል።ከዚህ በተጨማሪም በየደረጃው በመማር ላይ የሚገኙ ተማሪዎች የትምህርት ውጤት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ በመምጣቱ ለትምህርት ስርዓቱ ቀጣይነት ትልቅ ችግር

እየፈጠረ መምጣቱን ማየት ይቻላል፡፡ይህ የትምህርት ውጤት ማሽቆልቆል የተማሪዎችንና ወላጆቻቸውን እምነት እየሸረሸረ ተማሪዎች በሙሉ ፍላጎት ወደ ትምህርት ቤት እንዳይመጡ እያደረገ መሆኑን በመገንዘብ የትምህርት ፖሊሲውን ፈትሾ ችግሩን መፍታት ይጠበቅብናል፡፡ ከመደበኛው ትምህርት ስርዓት ባሻገር የጎልማሶች ትምህርት በመስጠት ላይ ቢሆንም ከሚጠበቀው ውጤት አንጻር ሲታይ እጅግ ዝቅተኛ መሆኑን በግልጽ ማየት ይቻላል፡፡በሌላ በኩል ክልሉ የሚፈልገውን በመካከለኛ ደረጃ ያሉ ሙያተኛ በማፍራት ሂደት የቴክኒክና ሙያ ተቋሞቻችን ተደራሽነታቸውን በማስፋት በርካታ ሙያተኞች በማሰልጠን ላይ ይገኛሉ።በዚህ ደረጃ ሰልጥነው የሚወጡ ሙያተኞች የራሳቸውን የስራ ዕድል መፍጠር የሚያስችላቸውን የተለያዩ ምቹ ሁኔታዎች መፍጠር ጉዳይ በስፋት ሊሰራበት ይገባል።

መሰረታዊ የሆነውን የጤና አገልግሎት ለዜጎች እንዲዳደረስ በማድረግ ሂደት ከአስር አመቱ እቅድ በፊት በርካታ የጤና ተቋማት ግንባታ የተካሄደ እና በእነዚህ የእቅድ ዘመናት በየአካባቢው ግንባታቸው የተጀመሩ የጤና ተቋማት ግንባታዎች ቢኖሩም ግንባታቸው በተለያዩ ምክንያቶች በመቋረጡ ለህብረተሰቡ መስጠት ያለባቸውን አገልግሎት እየሰጡ አይደሉም። በተጨማሪም ህብረተሰቡ ከጤና ተቋማት ማግኘት ያለበትን የህክምና አገልግሎትና የመድሃኒት አቅርቦት በበቂ ሁኔታ እያገኘ ባለመሆኑ በጤናው ላይ ከፍተኛ ችግሮች እየተፈጠሩበት በመሆኑ በትኩረት ሊሰራበት ይገባል፡፡

ክልሉ በአስር አመት በልማት እና መልካም አስተዳደር ውጤት ለማስመዝገብ አቅዶ እየሰራ በቆየባቸው ባለፉት ሶስት አመታት የክልሉን መልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት እየሰሩ የሚገኙ የፍትህና ጸጥታ ተቋማት የራሳቸውን ጥረት በማድረግ ላይ ቢገኙም በተለያየ መንገድ የተፈጠሩ የመልካም አስተዳደር ችግሮች በክልሉ ሰፍነው በመቆየታቸውና ተገቢ የሆኑ እርምጃ መውሰድ ባለመቻሉ ህብረተሰቡ በተደጋጋሚ የሚያነሳው መሆኑና በሂደትም ህብረተሰቡን ያስመረረው ጉዳይ መልኩን ቀይሮ ላልተጠበቀ ግጭት መንስኤ መሆኑን በተለያዩ ተጨባጭ መረጃዎች ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ በመሆኑም ችግሩን ለመቅረፍ የተዘጋጁ የለውጥ ፕሮግራሞችን በየደረጃው ለመፈጸም ትኩረት መስጠትና ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ ይገባል። በተጨማሪም የሲቪል ሰርቫንቱን የአገልጋይነት ስሜት አለማደግ፣ የግልጽነትና ተጠያቂነት ስርዓት አለመስፈን፣አሁን የተመጀረውን በውጤት የመለካት ስርዓት ተቆራርጦ አለመተግበር እና ሌሎች አጋዥ

የሆኑ የማሻሻያ ፕሮግራሞችን በተሟላ ደረጃ አለመፈጸም በእነዚህ የእቅድ ዘመናት በሰፊው ያጋጠሙን ተግዳሮቶች በመሆናቸው እንዚህን ፈጥኖ በመፍታት ችግር ውስጥ ያሉትን የልማት ውጤቶቻንን በላቀና ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ማረጋገጥ ይገባል።

በሌላ በኩል ክልሉ ለተለያዩ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳዮች ማስፈጸሚያ የሚሆን በጀት በመመደብ የህብረተሰቡን የልማት ፍላጎት ለመመለስ ጥረት በማድረግ ላይ ነው። የክልሉ የልማት ማስፈጸሚያ ሀብት ከተለያየ የበጀት ምንጭ የሚገኝ ሲሆን ከዚህ ውስጥ የክልሉ ገቢ አንዱ ነው።ይህ ገቢ በየዓመቱ እያደገ የመጣ መሆኑ በግልጽ የሚታይ ቢሆንም ከኢኮኖሚ ዕድገታችን አንጻር ተመጣጣኝ አይደለም።ስለዚህም የገቢ መሰረታችንን በማስፋት ገቢ የመሰብሰብ አቅማችንን ማሳደግ ትኩረት ልንሰጠው ይገባል።ከዚሁ ጎን ለጎን የህብረተሰቡን ልዩ ልዩ አቅም ውሱን ከሆነው የመንግስት ሀብት ጋር በማቀናጀት የተጀመረውን ሁለንተናዊ የልማት ጥረታችንን ማጠናከር ይገባል።

በአጠቃላይ ባለፉት ሶስት ዓመታት የአስር አመቱ ዕቅድ የትግበራ ዓመታት የታዩ አበረታች ውጤቶችን የበለጠ በማጠናከርና በክፍተት የታዩትን ችግሮች በየደረጃው በተሟላ ሁኔታ በትክክል በመረዳት እና ወደ መልካም አጋጣሚዎች በመቀየር በሁሉም የልማት ዘርፎች ቅልጥፍናን፣ ምርታማነትንና ጥራትን በማረጋገጥ ተወዳዳሪነትን ትርጉም ባለው ሁኔታ ማሳደግ እና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በተደራጀና በተቀናጀ አግባብ መፍታት በቀጣይ የእቅድ ዓመታት የትኩረት መስኮች መሆን ያለባቸው እርምጃዎች ናቸው፡፡ ለእቅዶቻችን አለመሳካትና የሚፈለገውን ውጤት አለማስመዝገብ የሚነሱ ምክንያቶች በርካታ ቢሆኑም የመልካም አስተዳደርና ቅሬታ አፈታት ደረጃችን ዝቅተኛ መሆኑ፣ክልሉን በመውረር የህዝባችንን እልቂት እና የኢኮኖሚ ውድመት የፈጠረው የሰሜኑ ጦርነት ያደረሰብን ጠባሳ፣ ክልሉ ከዚህ የወረራ ጦርነት ሳያገግም በክልሉ ውስጥ ያሉ የታጠቁ አካላት የፈጠሩት ግጭት እየቀጠለ መሆኑ፣ በየደረጃው የተመደቡ አመራሮችና የመንግስት ሰራተኞች በሙሉ ሃላፊነትና ቁርጠኝነት የተሰጣቸውን ተልእኮ በሚፈለገው መንገድ ማከናውን አለመቻላቸው ወዘተ...የመሳሰሉት አንኳር የሚባሉ ተግዳሮቶቻንን በአዲስ መንፈስ በቁርጠኝነትና በተናበበና በተደራጀ መንገድ መፍትሄ ልንሰጣቸው ይገባል፡፡ በዚህም ረገድ መላውን ህዝብ ያሳተፈ ንቅናቄ ውስጥ መግባት ይጠበቅብናል፡፡

## ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎች

ክልላችን በሁሉም አካባቢዎች በተደራጀና በተቀናጀ የህዝብ ተሳትፎ የአስር አመቱን ዕቅድ ለባለፉት ሶስት አመታት በመተግበር ላይ የቆየና በዚህም አንዳንድ መልካም ውጤቶች የተመዘገቡ ቢሆንም በዕቅዱ የአፈፃፀም ሂደት ወሳኝና አደገኛ ፈታኝ ሁኔታዎች አጋጥመዋል፡፡

ከእቅድ ዘመኑ በፊት ተከስቶ የነበረውና አሉታዊ ተጽእኖው እስካሁን ድረስ የቀጠለው አለም አቀፍ ይዘት ያለው ኮቪድ-19 ወረርሽኝ በሽታ በመኖሩ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገታችን ላይ ማነቆ ሆኖ መቆየቱ መነሳት ያበት ፈታኝ ጉዳይ ነው፡፡

በሌላ በኩል ህወሀት ወረራ ምክንያት የክልሉ ህዝብ ለእልቂት መዳረጉና በኢኪኖሚው ላይ ያደረሰው ውድመትናበህዝባችን ላይ የተከሰተው ተከታታይ መፈናቀል ከፍተኛ ፈተና ሆኖ መዝለቁ፣ ክልሉ ከዚህ የወረራ ጦርነት ጉዳት ሳያገግም በክልሉ ውስጥ ያሉ የታጠቁ አካላት የፈጠሩት ግጭት በአሰቃቂ ሁኔታ እየቀጠለ በመሆኑ አርሶ አደሩ በየቀዬው እየኖረ ምርቱን እንዳያመርት አሉታዊ ተጽእኖ መፍጠሩና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች እንዳይደረጉ መንገዶችን በመዝጋት የህዝብን እንቅስቃሴ በማገድ ክልሉን ማጎሳቀሉ ሌላው ፈታኝ ገጠመኝ ነው፡፡ በክልሉ በተለያዩ አካባቢዎች እና ከክልሉ ውጭ በነበሩ ግጭቶች እና መፈናቀሎች ህዝቡ ለስደትና ለሰላም እጦት በጋለጡ እንዲሁም በክልላችን የተከሰተው ድርቅ በርካታ ወገኖችን ለአደጋ ያጋለጠ መሆኑ ሌላው ፈታኝ ሁኔታ ነው፡፡

ሌላው የተከሰተው የዋጋ ንረት በህብረተሰቡ የመግዛት አቅም ላይ ጫና በማሳደርና ገቢያው እንዳይረጋጋ በሚሰሩ ህገወጦች ምክንያት የፍጆታ ምርቶች ዋጋን በማናር ህዝቡ ለስቃይ እንዲዳረግ እንዲሁም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች በእጅጉ እንዲጎዱ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተጽእኖ ያለው በመሆኑ ባለፉት ሶስት ዓመታት የኢኮኖሚው ተቋማዊና መዋቅራዊ ማነቆዎች በዕቅዱ የአፈፃፀም ሂደት ትልቅ ፈተናዎች የነበሩ ናቸው፡፡ ከዚሁ ጋር በተገናኘ **በሶስት አመታት** የትግበራ ዘመን በተለያዩ ዘርፎች የተቀመጡትን ግቦች ከማሳካት አንፃር በተለያዩ ደረጃዎች የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም ውስንነቶች ፈተናዎች ነበሩ፡፡ በተለይ በፕሮጀክት ማኔጅመንት (በማቀድ፣ በመተግበር፣ በመከታተል፣ ኮንትራት በማስተዳደር) የታዩ የአቅም ውስንነቶችና የቅንጅት ችግሮች፣የግብርናን ምርታማነት በተጠበቀውና በታቀደው መሠረት ከመፈፀም አንፃር የፈፃሚ አካላትን አስተሳሳብ ቀይሮ ከማነሳሳት፣ ከማደራጀት፣ አሰልጥኖም ከማስማራት አንፃር የታዩ ጉድለቶች፣ ወዘተ ዋና ዋና ፈተናዎች ነበሩ፡፡ከወጪ ንግዳችን ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ያለው

የሎጂስቲክስ አገልግሎትና የጉምሩክ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚታዩ ችግሮች በኢንቨስትመንትና በንግድ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድረዋል፡፡በሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም ብዙ ኢንቨስትመንት ቢፈስም በየተቋማቱ ያለው አቅም ውስንነት አሁንም የተፈታ ጉዳይ አይደለም፡፡በመሆኑም በሲቪል ሰርቪሱ ብቁ፣ተነሳሽነት ያለው፣ በክህሎት የዳበረና ቀልጣፋ አገልግሎት አሰጣጥ የተላበሰ የሰው ኃይል ለማደራጀት እየተደረገ ያለው ጥረት ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል፡፡

ሌላው ፈታኝ ጉዳይ የአላግባብ በአቋራጭ የመክበር እና ህገወጥነት (በአመለካከትም ሆነ በተግባር) እና የመልካም አስተዳደር ችግሮች የኢኮኖሚና ማህበራዊ አገልግሎቶች በታቀደውና በተጠበቀው ደረጃ እንዳይሳለጡ በመግታት፣በዚያው ልክ በተለያዩ ዘርፎች የተቀመጡ የኢኮኖሚና ማህበራዊ የልማት ግቦች በተጠበቀው ደረጃ እንዳይፈፀሙ ከፍተኛ ጫና በማሳደር አሉታዊ ተፅዕኖ ፈጥረዋል፡፡ግልፅነትንና ተወዳደሪነትን ለማስፈን የተዘረጋው የንግድ ሥርዓትና የንግድ ሥርዓት ሪፎርም በክልላችን ብሎም በሀገራችን በተሟላ ሁኔታ ተፈፃሚ አልሆነም፡፡ከዚህ አንፃር የወጪ ንግዳችንን እና የሀገር ውስጥ ገበያችንን ግልፅነት የሰፈነበትና ተወዳዳሪ በማድረግ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ከሚገኘው ሀብት ፍትሀዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡

በተመሳሳይ የመሠረተ ልማት የኢኮኖሚ ዕድገቱ እንዲፋጠን የሚያስፈልጉ የትራንስፖርት፣ የኮሙኒኬሽን እና ኃይል አቅርቦትን በጥራትና በተወዳዳሪ ዋጋ ለማቅረብ ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ ከዚህ አንፃር በዕቅዱ ትግበራ ወቅት የመሠረተ ልማት አቅርቦትን አስተማማኝ ለማድረግ የሚያስችሉ በርካታ የልማት ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ ሆኖም አሁንም እየታዩ ያሉ በኢነርጂ መሠረተ ልማት የኃይል አቅርቦት ሥርጭት ችግርና የኃይል ብክነት፣ የሎጂስቲክስ አገልግሎት...ወዘተ ችግሮች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እነዚህን ችግሮች መፍታት ዘርፉ ያሉበትን ማነቆዎች በቅርብ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የተያዘውን ልማታዊ አቅም ያለተጨማሪ ኢንቨስትመንት ጥቅም ላይ ለማዋል ያስችላል፡፡

በመጨረሻም ዕቅዱ የትግበራ ወቅት የታክስ ሪፎርሙንና የታክስ አስተዳደር ሥርዓቱን ተፈፃሚ በማድረግ የሀገር ውስጥ ገቢን ለማሳደግ እና የውጭ የልማት ፋይናንስ ለማሳባሰብ ከፍተኛ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ በዚህም መልካም ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡ ሆኖም የሚፈለገውን የልማት ፋይናንስ በጊዜ ከማግኘትና የልማት ፕሮጀክቶችን የግንባታ ሂደት

ከማፋጠን አንፃር ከፍተኛ ተፅዕኖ እንደነበረው ታይቷል፡፡በቀጣይ የገቢ አቅማችንን በላቀ ደረጃ በማሳደግ እና የልማት ፋይናንስ ፍሰትን ትርጉም ባለው ደረጃ በማሻሻል በሚፈለገው ጊዜ የፋይናንስ አቅርቦት እንዲኖር ማድረግ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ይሆናል፡፡ከፍ ብሎ በዝርዝር የቀረቡና በአፈፃፀም ሂደት ያጋጠሙ ፈተናዎችን ለማቃለል በየደረጃው እርምጃዎች ተወስደዋል፡፡እነዚህ እርምጃዎች የኢኮኖሚ ዕድገቱ ፈጣንና ቀጣይ እንዲሆን ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡